# "My Bride I am on My way get ready" - Book 1 - Amharic

## ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! ፩ኛ መፅሐፍ



# መግቢያ

ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! በሚለው ርዕስ ውስጥ የተካተቱ እነዚህ መልዕክቶች ከኢየሱስ የተላኩ የፍቅር ደብዳቤዎች በሚል ርዕስ በሲስተር ክሌር ዴቡስ ከቀረቡ መልዕክቶች ተመርጠው የተተረጎሙ ናቸው፡፡ ይህንንም ርዕስ የመረጥንበት ምክንያት በእርግጥም ሙሽራው ሊመጣ በደጅ ስለሆነና ሙሽሪት ይህንን በመገንዘብ መዘጋጀት እንዳለባት አፅንዎት ለመስጠት ነው፡፡ ተርጉመን ያቀረብናቸው እነዚህ መልዕክቶች ከአንዱ በስተቀር ሲስተር ክሌር ዴቡስ የምትባል የ74 ዓመት አሜሪካዊት ሴት ከጌታ ተቀብላ በመፅሐፍ መልክ ያዘጋጀችውን መልእክቶች ነው፡፡ አንዱ መልዕክት በካሮል ጂንጊዝ የተላለፈ ነው፡፡ የሲስተር ክሌር መልእክቶች እጅግ ብዙ በመሆናቸው ለእናንተ ለአንባቢዮቻችን የበለጠ ይጠቅመናል ብለን የመረጥነውን ብቻ ተርጉመን በመፅሐፍ መልክ በማጠናቀር አቅርበናል፡፡

ዘ ኤንድ ዴይስ ሚኒስትሪስ/ The End Days ministries / ዋና ዓላማው በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡና ህዝባችን ሊሰማቸው የሚገቡ አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች በመተርጎም ለህዝባችን ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ እነዚህንና ሌሎች መልዕክቶችን በንባብ መልክ በድምፅ ተቀርፆ በዩ ቱዩብ ቻናላችን ላይ ታገኙታላችሁ፡፡

በሲስተር ክሌር የሚተላለፉ መልዕክቶች አጠቃላይ ይዘታቸውን ስንመለከት ሙሽራው በቅርብ ሊመጣ እንደሆነ፣ ሙሽሪት ከጌታዋ ጋር ለመሄድ /ለንጥቀት/ መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዴት መዘጋጀት እንዳለባት፣ እንዲሁም የማይነጠቁ ሰዎች በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ታላቁ መከራ ተብሎ የተጠቀሰውን ዘመናት በምድር እንደሚያልፉና በዚህም የመከራ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክቱ ወሳኝ መልዕክቶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ጠቅላላውን መልዕክት በሚከተሉት ቻናሎችና ዌብሳቶች ልታገኙ ትችላላችሁ፡፡

(1) በአማረኛ የተተረጎሙ መልዕክቶችን ለማግኘት/ translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) በአማረኛ ዘ ኤንድ ዴይስ የተተረጎሙ ትንቢታዊ መልዕክቶችንና መፅሐፎችን ለማግኘት - heartdwellers.org – Book በሚለው ውስጥ ገብታችሁ እነዚህን ርዕሶች ታገኛላችሁ;-

- The Rapture was real Book Amharic pdf - ንጥቀቱ እውን ነበር በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- Tethered Book Amharic pdf - ቴተርድ በሚል የተተረጎመ መፅሐፍ
- My Bride get ready Book one – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ አንድ
- My Bride get ready Book two – Amharic pdf / ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሁለት
- My Bride get ready Book three – Amharic pdf/ ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ መፅሐፍ ሦስት
- Events after the rapture Amharic pdf/ በቅርብ ስለሚሆኑ ክስተቶችና ስለ ታላቁ የመከራ ዘመን

(3) በኢንጊሊዘኛ ቋንቋ መልዕክቶቹን ለማግኘት/ Messages in Engilish

- heartdwellers.org
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## ጌታ ዘመናችሁን ይባርክ

# Introduction

The title of this book, in Amharic "ሙሽራዬ ልመጣ በደጅ ነኝና ተዘጋጂ!!! " translated to Engilish "My bride get ready I am on my way ", was given to show that the Groom is truly on His way and to alert the bride. All the messages in the three books (book 1, book 2 and book 3) except same messages (Calor jenngs' messages) were taken and translated from Sister Clare. Sister Clare is a 74 years old American prophetess who hears and transmites messages from God to the world through different Medias since 2014. Her messages are so many and we have tried to translate very few of them.

We are doing this since one of our ministries goals is to acceses prophetice messages spoken in Engilish and which are relevant to our people. For this purpose we have translated and recorded same messages and uploaded them on you tube.

When we look to the content of Sister Clars' messages, they talk about the coming of Jesus sooner than expected, intiate brides to be ready for the rapture and explaine how to be ready. In addition, they reveal what is to come after the rapture, what will the left behind face in the period called great tribulation, which is written in the Bible, and the messages also give same hints how to persevere in the tribulation. Therfore if you want to get the whole messages in English and the translated messages in Amharic you can find them as follows:-

(1) Translated to Amharic messages audio – Youtube, - The End Days ministries channel

(2) Translated messages compiled in book pdf - go to - heartdwellers.org to Book folder then search for these titles;-

- The Rapture was real Book Amharic pdf
- Tethered Book Amharic pdf
- My Bride get ready Book one – Amharic pdf
- My Bride get ready Book two – Amharic pdf
- My Bride get ready Book three – Amharic pdf
- Events after the rapture Amharic pdf

(3) The whole Messages in Engilish

- heartdwellers.org
- Youtube – libesbriefe von Jesus –Loveletters from Jesus

## God bless you

| ተራ ቁ. No | የመልዕክቱ ዝርዝር ርዕሶች / Messages titles | ገፅ page |
|---|---|---|
| 1 | አንድ ነፍስ ለመንግስት ሰማይ/ Another Soul for Heaven, another Jewel in Your Crown | 5 |
| 2 | ሙሽራዬ ምላሽ እየሰጠች አይደለም/My Bride is Not Responding | 9 |
| 3 | ገሃነም በምድር ላይ / Hell on Earth | 11 |
| 4 | ሙሽሮቼ አሁን የመመለሻችሁ ጊዜ ነው/ /My Bride, Now or Never | 13 |
| 5 | የነውጡን ትዕይንት ወደ ሰላም መቀየር / Turning Drama into Peace | 15 |
| 6 | በአለም ያላችሁን ተሳትፎ ገደብ አብጁለት/ Draw the line on your involvement With the World | 18 |
| 7 | በእምነት ላይ ተቃውሞ እየጣ ነው/ Attacks against the faith are on the way | 22 |
| 8 | እምነታችሁ ያለገደብ በእኔ ላይ አድርጉ / Unconditional Trust in Me | 27 |
| 9 | ከእኔ ጋር የቅርብ ወዳጅነትስትመሰርቱ ዋጋችሁን ተምኑ/ Count the Cost of an intimate relationship with Jesus | 30 |
| 10 | በእግዚአብሔር መስታወት ራሳችሁን በሃቅ ተመልከቱ / Honesty, Looking At Yourself in God's Mirror | 39 |
| 11 | ፍቅር ከሌላችሁ የንጥቀቱ ተካፋይ አትሆኑም / Without Love You Will Not Be Taken in the Rapture | 43 |
| 12 | ስፍራን ላዘጋጅላችሁ ሄጀለሁ/ I have gone to prepare a place for you | 46 |
| 13 | ቸርነት ማድረግ የኃጥያትን ብዛት ይሸፍናል / Charity covers a multitude of sins | 50 |
| 14 | አለም ፍርክስክሱ ሲወጣ እናንተስ ትቆሙ ይሆን? / Will You Stand When The World Crumbles? | 52 |
| 15 | ለእኔ ማን እንደሆንሽ / Who you are to me. | 53 |
| 16 | እግዚአብሔር ስቃይን ለምን ይፈቅዳል? / Why Does God Allow Suffering? | 55 |
| 17 | አስተዳደሬን አልተቀበላችሁምና ሙሽራዬን መጥቼ ልወስድ ነው/ You Have Rejected My Rule I am coming to take my bride | 61 |
| 18 | ቀላል የስጋ ወደሙ አወሳሰድ/ A Simple Communion Service | 63 |
| 19 | የመጨረሻው መጨረሻ ከፋች ክስተት/ Turning key event | 67 |
| 20 | "ለመነጠቅ ዝግጁ ናችሁ?" / "Are You Ready for The Rapture?" | 69 |
| 21 | መልካም ዛፍ መጥፎ ፍሬ አያፈራም/ A good tree cannot bear bad fruit | 72 |
| 22 | "ኑ ወደ ዕረፍቴ ግቡ" / "Enter Into My Rest" | 76 |
| 23 | "ጊዜው አጭር ቢሆንም የተዘጋጃጅሁ ግን አንዳንዶች ናችሁ"/ "Time is short, some of you are ready" | 80 |
| 24 | ኢየሱስ ኑ ወደእኔ እያለ ይጣራል / Why temptations & hope for you who are lost | 81 |
| 25 | ያሳለፋችሁት ህይወት አልባከነም / Your Lives Have Not Been Wasted | 83 |
| 26 | የክስተቶች ቅደም ተከተል / War Comet Rapture Treaty- Order of Events | 86 |
| 27 | ለመንገዳችሁ ተዘጋጁ/ Get ready for your journey | 91 |
| 28 | የቅድስና ጣፋጭ መዓዛና የጠላት ማዘናጋት / Sweet Aroma of Holiness | 95 |
| 29 | ሙሽሮች ንጥቀት ለሁሉም የሚታይ ይሆናል / "The Rapture Event Will Be Visible" | 97 |
| 30 | እግዚአብሔርን መፍራት የቅድስና መንገድ መሆኑ / The Journey of Holiness | 100 |
| 31 | ለእናንተ ያቀድኩት አስደሳች ነገር አለኝ / Ask Me For Supernatural Gifts | 102 |
| 32 | የእግዚአብሔርን የጦር መሳሪያ በፀሎት መልበስ / The Armor of God--A Prayer | 104 |
| 33 | ብዙዎቻችሁ ስለ ንጥቀት እያሰባችሁ / Clare Has Not Abandoned You & New Onslaught of Demons) | 106 |
| 34 | ለመነጠቅ የመጨረሻ ማጣሪያ / Final Exams for the Rapture in Progress | 107 |

## አንድ ነፍስ ለመንግስተ ሰማይ - ተጨማሪ ፈርጥ በአክሊላችሁ ላይ / ማርች 25 ቀን 2014 ዓ.ም

## Another Soul for Heaven, another Jewel in Your Crown / March 25, 2014

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "የኔ ውድ የእስራኤልን መንግስት እንደተቋቋምኩት ሁሉ ይህንንም ከፉ አለም እቋቋመዋለሁ፡፡ እንዲህም ቢሆን ቅሬታዎች እንደነበሩኝ አንብበሻል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በዚህም ዘመን ለእኔ የማድናቸው ይኖሩኛል፡፡ እነዚህም በእሳት ውስጥ የሚያልፉ ሲሆኑ እኔ በሁሉም መንግስታትና ህዝቦች ላይ ከማፈሰው ቁጣ ለማምለጥ የሚገባቸው ናቸው፡፡

"የአንቺ ልጆችም ከእነዚህ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በእምነትሽ ምክንያት ከእነሱ እስከ መለየት ስደረስሽ ይህንን ለአንቺ ቃል ገብቼልሻለሁ፡፡ አሁንም ቢሆን ብዙ መንፈሳዊነት እየታየባቸው ነው፡፡ ይህንንም የበለጠ አደርገዋለሁ፡፡ በተጨማሪም ዘረመላቸው(DNA) እንኳን ሳይቀር ከእኔ ጋር እንዲመሳሰል እቀይረዋለሁ፡፡ የኔንም ክብር በእነርሱ ላይ ታያለሽ፡፡ ቀሪ ዘመናቸውን ሁሉ እኔ ባዘጋጀሁላቸው መንገድ ይሄዳሉ፡፡ እናም በእነርሱ የበለጠ ደስ ይልሻል፡፡ የተሰበረውን ልብሽን እኔ ራሴ እጠግነዋለሁ፣ እቀባዋለሁ ደግሞም ወደ ቅድስና ውበት አመጣዋለሁ፡፡

"ለሙሽራዬ ልጆች ምህረት ማድረግ አይገባኝምን? በእርግጥ እነርሱም በእሳት ውስጥ እንደነጠረ ብር ያበራሉ፡፡ ተስፋ የሌላቸው የሚመስሉ ብዙዎች ከሚያነጥረው እሳት ውስጥ በመውጣት በፊታቸው ላይ የኔን ክብር ያንፀባርቃሉ፡፡ ስለዚህም ይህንን በልብሽ ውስጥ በመያዝ ብርታት ይኑርሽ፡፡ ክሪስቶፈርና ብሬንዳንም ከሞታን ይነሳሉ፡፡"

(ክሌር) ይህ ቃል ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለሁላችሁም እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ጌታ ከራሳችን ቤተሰቦች ተቀባይነት በማጣት እንዴት እንደተሰቃየን ያውቃል፡፡ እናም መልሶ ወደእኛ ሊያመጣቸው ታማኝ ነው፡፡

(ኢየሱስ) "ብዙዎች ቀድሜ የተናገርኩትን ቃሌን ስለተቀበሉትና ወደ ልባቸው ስላስገቡት መናገሬን እቀጥላለሁ፡፡ ቃሌን በማመን ወደልባቸው ባስገቡት ታማኝ በሆኑት በትናንሾቼ እንዴት እኮራለሁ፡፡ መባረኬንና መመሪያ መስጠቴን እስከዚያን ቀንና ሰዓት ድረስ እቀጥላለሁ፡፡"

(ክሌር) አያችሁ ቀኑና ሰዓቱ መቼ መሆኑን አልጠይቅም፡፡

(ኢየሱስ) "እኔም ብሆን መቼ እንደሆነ አልናገርም . . . አንዳንድ ነገሮች ሳይባሉ እንዲሁ ቢቀሩ ይሻላል፡፡"

(ክሌር) ለምሳሌ በቅርብ?

(ኢየሱስ) "ትክክል፡፡ እኔ ዝም ብዬ ከአንቺ ጋር እየተጫወትኩ ነው፡፡ ነገር ግን እዚህጋ ማለት የምፈልገው ቢኖር ነገሮች መጨረሻ ሲደርሱ ያን ጊዜ በምድር የምትኖሩበት ጊዜ ያበቃል፣ ነገሮችም የበለጠ እየጠነከሩና የበለጠ ኃይለኛ እየሆኑ

ይሄዳሉ፡፡ ቢሆንም እኔ እናንተን ለመጠበቅ፣ለመመገብና ለማጠንከር ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ አንድ ላይ ሆነን የጣር ምጥ መጀመሪያን እየቀረብን እንሄዳለን፡፡ ክሌር ጠብቂ በዚያ ውስጥ እናልፋለን፡፡

"የጦር መሳሪያችን ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው፡፡ እናም ነገሮች እየተጋጋሉ ሲሄዱ ክርስቲያኖች በእምነታቸው የበለጠ ችግር እየገጠማቸው ይሄዳል፡፡ በእምነትና በተስፋ ላይ ጥቃት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ አንገታችሁን ቀና አድርጉ! ምን እንደነገርኳችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሜ ደጋግሜ አረጋግጬላችኋለሁ፡፡ ያንን ለውድ ህይወታችሁ ስትሉ አጥብቃችሁ እንድትይዙት፡፡ እናም በአካባቢያችሁ ምንም ነገር ቢከናወን ምንም ጥያቄ አይኑራችሁ፡፡

"በአክሊላችሁ ላይ ፈርጦች የሚጨመሩት በየቀኑ እንደሆነ ይህንን ልብ በሉ፡፡"

(ክሌር) አ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አውቀዋለሁ፡፡ አክሊል ማለት ስቃይ መቀበልና ያንንም ስቃይ አልፎ መሄድ ማለት ነው፡፡

(ኢየሱስ) "ስለ ንቀትና ስለ መዋረድ ስጋት አይግባሽ፡፡ ከእነዚህ ጋር አብረሽ ሥሪ፡፡ አንዳንዶች በግልፅ ያላወጡትና ቀነስ አድርገው የያዙት ለትህትና ብለው ነው፡፡ ነገር ግን ሰብሮ ወደ ውጪ ሲወጣ የግል ጉዳይ አድርገሽ አትውሰጂው፡፡ ደካሞች ስለሆኑና ጠላት አንቺን ለመሸርሸርና ግራ እንዲገባሽ ለማድረግ እየተጠቀመባቸው ስለሆነ ነው፡፡ የኔ ዕርግብ ይህንን አትፍቀጂ፡፡ ወደ እኔ ቅረቢና ጠንካራ ሁኚ፡፡ እነርሱን ግን በተረጋጋ ሁኔታ ትክክለኛውን መንገድ አሳያቸው፡፡

"በተለይም ወደ እኔ ልወስዳችሁ በተቃረበ በዚህ ጊዜ ለሁላችሁም የከበሩ የድንጋይ ፈርጦችን በአክሊላችሁ ላይ እጨምራለሁ፡፡ ከክብር ወደ ክብር ትሄዳላችሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ ስቃያችሁንና የሚገጥማችሁን ችግር እንደ ፈጣን ስጦታ በመውሰድ ብዙ ነፍሳት እንዲለወጡበት እጠቀምበታለሁ፡፡

"ታማኝ ክርስቲያኖቼ ሁሉ መናቅ፣ውርደትና ጥቃት ገና ይጠብቃቸዋል፡፡ ፈተናውን በሚገባ ካላለፉ እንዴት አድርጌ ነው የምሸልማቸው? እናም እስከዚያው ድረስ ከንጥቀት የሚቀሩትን ሊረዳቸው የሚችል ትምህርቶች ይቀርባሉ፡፡ እያንዳንዱ ነገር ትንሽም ሆነ ትልቅ ለዓላማ የሚውል ነው፡፡ ይህንን የባህርይ ፈተና፣ እንዲሁም አመለካከታችሁን ንፁህና አመስጋኝ የሚያደርግ ሌላ ፈጣን ስጦታ አድርጋችሁ ልትወስዱት ትችላላችሁ፡፡

"በዚህ አገር ውስጥ በስተ ጀርባ እየተሰራ ያለው ነገር በእውነት ሲታይ አስቃቂ ነው፡፡ የዚህን ብልጭታውን በዚህም በዚም አይታችሁታል፡፡ ለምሳሌ በ1996 በጆርጂያ ጭንቅላት መቅላትን ህጋዊ የተደረገበት!! ነገር ግን ትልቅ ጥቃት ለማድረግ መሰረቱ መጣሉን ቀጥሏል፡፡ ራስሽን አረጋጊ ለዚህኛው ጥቃት እናንተ በዚህ አትሆኑም፡፡ በአድማስ ባሻገር እየመጣ እንደሆነ በግልፅ ታዩዋለሽ ነገር ግን እንድትፈሪ አልፈልግም፡፡

(ክሌር) አዎ ፍርሃት ነው የተሰማኝ፡፡

(ኢየሱስ) "ይህንን እንደገና መናገር እፈልጋለሁ፡፡ በዛን ጊዜ አንቺ እዚህ ስላይደለሽ ጭንቅላትሽን አትቀይም፡፡ አንቺ እዚህ አይደለሽም፡፡ ይህንን እንደገና ደግሜ ለመናገር ፍፁም አያስፈልገኝም፡፡ በዚህ ነገር ላይ እንድታርፊ እፈልጋለሁ፡፡

"ነገር ግን በዚያን ጊዜ እዚህ ለሚሆኑ ለሌሎች እንዲህ እላለሁ ከእነርሱ ጋር እሆናለሁ፡፡ ለጥቂት ጊዜ በፍርሃት ሊሰቃዩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ቃል የምገባላቸው በቅፅበት ዓይን እነርሱ በመንግስተ ሰማያት ከእኔ ጋር ይሆናሉ፡፡ በሰማያት ባሉ ምክር ቤቶች እንኳን ደህና መጣችሁ! በማለት አቀባበል ይደረግላቸዋል፡፡ ብዙ መስዋዕት የሚሆኑ ሰዎች ምንም ህመም ሳይሰማቸው ያልፋሉ፡፡ ምክንያቱም ህመማቸውን እኔ በመስቀሉ ላይ ስለወሰድኩት ነው፡፡ በጣም በሚያስፈራ ሁኔታ እንኳን መስዋዕት ለሚሆኑት በጣም ደካማ ለሆኑት ህመማቸው እንዳይሰማቸው እኔ እወስድላቸዋለሁ፡፡ ምህረት ማድረግ ተፈጥሮዬ ነው፡፡ ስለዚህም ለእያንዳንዳቸው የሚያስፈልጋቸውን ብርታት እሰጣቸዋለሁ፡፡ ሞትን የሚጋፈጡት ብቻቸውን አይደለም፡፡ እኔ ከእነርሱ ጋር ነኝ፡፡"

(ክሌር) ጌታ ሳስበው እኔ የማልረባ ነኝ፡፡

(ኢየሱስ) "እኔ እንደማስበው ደግሞ አንቺ ቆንጆ ነሽ፡፡ ራስሽን አታታልዪ፡፡ አንቺ የተለያዩ ዓይነት መስዋዕቶችን በመክፈል ብዙ ተሰቃይተሻል፡፡ አንቺ ለእኔ የተሰቃየሽው ከዚህ ጋር እኩል ዋጋ የሚሰጠው ነው፡፡ በተለይም ጥቃት ያደረሱብሽን ስታገኛቸው ያደረግሽው ቸርነትና ይቅርታ ተጠቃሽ ነው፡፡

"ከእኔ ጋር የቀረበ ግንኙነት ማድረግ ለአይምሮ ቁልፍ ነገር ነው፡፡ ከአለም ጋር መስማማት ግን ለሰይጣንና ለአጋንቶች በሮችን ይከፍታል፡፡ በጣም ትንሿን ኃጢያት ስትፈፅሙ እንኳን ትናንሽ ቀበሮዎች ወይኑን እንደሚያበላሹት ሁሉ በሩ በግድ በመጫን ይከፈትና አንድ ቀጫጫ አጋንንት እንዲገባ ምክንያት ይሆናል፡፡ ከዚያም በሩ ይሰፋና በኃጢያት ላይ ኃጢያት በመጨመር በሩ በትልቁ ወለል ብሎ ይከፈታል፡፡ ለዚህ ነው ገና በመጀመሪያው ወቅት መደራደር የሌለባችሁና መቃወም ያለባችሁ፡፡ ነገሮች እየጨመሩ እንዲሄዱ ካደረጋችሁ ወይም በወቅቱ ካላከማችሁት ነገሮች እያደጉና እየተለቁ በመሄድ እጅግ የሚያም ትልቅ ጣልቃ ገብነት የሚያስፈልግበት ደረጃ በመድረስ መርዙ ሰውነትን ሁሉ የሚመርዝ ይሆናል፡፡ ልጆቼ ለዚህ ነው ገና በመጀመሪያው ጠላትን መቃወም ያለባችሁ፡፡

"የከረሩ አለመጋባባቶችን ከወንድሞች ጋር መጠንቀቅ አለባችሁ፡፡ ሃሜት፣ ሰውን ማዋረድ፣ ትዕግስት ማጣት፣ አመለካከቶችን ወንድሞችን በሚጎዳ መልኩ መተርጐም፣ ዝቅ አድርጎ መመለከትና የመሳሰሉት እርስ በርስ በማለያየት አንዱ ከሌላው እንዲለይ ያደርጋል፡፡ እንደምታውቁት በጫካ ውስጥ ከመንጋው የተለየ በግ የሞተ ነው፡፡ ስለዚህም ያለመግባባትን ገና በእንጭጩ ለመቅጨት ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ ንቁ ሁኑ፡፡ የበለጠ ትዕግስት፣ የበለጠ ፍቅርና የበለጠ ትሁት መሆን የተበላሹትን ለማስተካከል መሳሪያዎች ስለሆኑ ለዚህ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን አለባችሁ፡፡"

(ክሴር)፡- በዚህ ጊዜ ዝም ብዬ ወደ ሬማ ሳጥኔ ሄድኩ፡፡ ይህም ሳጥን የተለያዩ መንፈሳዊ ጥቅሶችን በካርድ መልክ ተዘጋጅተው የሚገኙበት ሳጥን ነው፡፡ ያነሳሁትም ካርድ እንዲህ ይላል. . . ' ማንኛውም ትንሽ ስቃይ ምንም እንኳን ትንሽ ቢሆን ያደረጋችሁት ለእግዚአብሔር ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ሳይሰጠው የሚያልፍ የለም፡፡ ለማሸነፍ ከፈለጋችሁ ግን ለመታገል ተዘጋጁ፡፡ ሳትታገሉ የትዕግስትን አክሊል መቀዳጀት አትችሉም፡፡'

(ኢየሱስ) "በጉዟችሁ ላይ ቸርነትንና ይቅርታን በማድረግ ትፈተናላችሁ፡፡ ስለዚህም ለኃጢያተኞች ልባችሁን በደንብ ከፈት አድርጉት፡፡ በተለይም እኔ ወደ እናንተ የላኳቸውን በፍቅርና በይቅርታ እቀፏቸው፡፡ ለመዳናቸውም ፀልዩ፡፡ በእውነት በጣም የሚያሳዝኑ ናቸው፡፡ ወደ እናንተ የላኳቸው አብዛኛዎቹ በዚህ ምድር ላይ የሚፀልይላቸው የላቸውም፡፡ ነገር ግን እናንተ እንደምትፀልዩላቸው አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም በመንገዳችሁ ላይ መጥተዋል፡፡ የኔ ውዶች አታሳፍሩኝ፡፡ በህይወታችሁ ውስጥ ለሚገኙ አስቸጋሪ ሰዎች እንድትፀልዩ እፈልጋለሁ፡፡

"ተስፋ እንዳትቆርጡ በማለት በህይወታችሁ ብዙ ደስ የማይሉ ነገሮችን እየከለከልኩ ነው፡፡ ነገር ግን ከእኔ ጋር የቅርብ ግንኙነታችሁ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ብዙ የባህርይ ፈተናዎችን እፈቅዳለሁ፡፡ ቢሆንም ግን ከምትችሉት በላይ በፍፁም አይሆንም፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ውጥረቶች እየጨመሩ እንደሚሄዱ በማወቅ ራሳችሁን ቀና እንድታደርጉ፡፡ ትግሎች ይቋቋማችኋል፡፡ ነገር ግን አትፍሩ፡፡ በሙሉ ልባችሁ በእኔ ታመኑ፡፡ በራሳችሁ መረዳት ላይ አትደገፉ፡፡ እንዲህም  ሲሆን እኔ በምትሄዱበት መንገድ እመራችኋለሁ ደግሞም ነፃ አወጣችኋለሁ፡፡

"እያንዳንዳችሁን እወዳችኋለሁ፡፡ እናንተ የኔ ቆንጆ ሙሽሮች ናችሁ፡፡ እጃችሁን ይገፎ ለዘላለም የኔ ላደርጋችሁ እንዴት እንደምናፍቅ!

“እነዚህ መመሪያዎችን የሰጧችሁ እዚህ ብዙ ስለምትቆዩ እንደሆነ ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዳታስቡ፡፡ በፍፁም ብዙ ጊዜ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ግን እናንተ ብዙ ነፍሳት ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገቡ እየፀለያችሁ እያለ እኔ ደግሞ ብዙ ፈርጦችን በአክሊላችሁ ላይ ለመጨመር ነው፡፡ ፀሎቶቻችሁን ደግሞ እመልሳለሁ፡፡ እኛ በአንድ ቡድን ውስጥ ያለን ሰራተኞች ነን፡፡ የሚገኙት ፍሬዎች ደግሞ ከምትገምቱት በላይ ነው፡፡ ብዙውን ከእናንተ የምደብቀው ትህትናን ለመጠበቅ ነው፡፡

## ሙሽራዬ ምላሽ እየሰጠች አይደልም / ሰብቴምበር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

## My Bride is Not Responding / September 28, 2014

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ካንቺ ጋር መሆን እንዴት መልካም ነው፡፡ የእኔ ታማኞች ጥሪዬንና የዘላለም ደስታዬን አስተውለው ከእኔ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ቢጥሩና በንስሐ ህይወት ውስጥ መሆን ቢችሉ ስለ እነርሱ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር፡፡"

(ክሌር)፡- ራሴን ባየሁት ቁጥር እንዴት ወደ ልብህ እንዳቀረብከኝ እና ካንተ ጋር ጊዜ ማሳለፍ እንደፈለክ ግራ ይገባኛል፡፡ለብዙ ቀናት ስለ ኩራቴና ስለመዳፈሬ ንስሐ በመግባት ብቆይም አሁንም ተስፋዬ የአንተ ፀጋ ብቻ ነው፡፡

ኢየሱስም . . . ይህ ተጨማሪ ነጥብ ነው፡፡ አንድ ፈቃደኛ ከሆነ ሰው ጋር፣ ከአንድ ፈቃደኛ ሰው ብቻ ምንም ነገር ማድረግ እችላለሁ፡፡ እዚህ ደግሞ ሁለት ፈቃደኞችን አግኝቻለሁ፡፡ ይህ ለእኔ እንዴት የሚያስገርም ነው? ብዙ የማታዩትና የማይገባችሁ ነገሮች አሉ፡፡ እንዲሁም ብዙ ነገሮች አሉ ከተዘጋጁ ሙሽሮቼ የምደብቃቸው፡፡ እንዲህ ካላደረግሁ ግን በእርግጥ ይበላሹብኛል፡፡ ነገር ግን ከአለም የሚያገኙት ምላሽ ትንሽ ቢሆንም እንኳን ያላቸውን ሁሉ ስለሰጡኝ፣ እኔን ለማስደሰት በጣም ጉጉት ስላላቸውና ለእኔ ፈቃደኛ ስለሆኑ እጅግ ደስተኛ ነኝ ማለት ብቻ በቂ ነው፡፡ ምንም ምላሽ ሳያገኙ መስጠት መቻል፤ ምንም ፍሬ ሳያገኙ መስጠት መስጠት መስጠት ይህ የማይገኝ ጥራት ያለው ማንነት ነው"

(ክሌር)፡- ጌታ አንተ ሽልማቴ ነህ፡፡
(ኢየሱስ)፡- "መሆንም ያለበት እንዲህ ነው፡፡ በቃ ታማኝ የማረሻ በሬዎቼ ሁኑ፡፡ መንተት፣ መንተት፣ መንተት፡፡ ቢደክማችሁና ብትንዱም እንኳን ያላችሁት እየንተታችሁ ነው ፡፡ ለእኔ ታማኝ የሆኖ ሁሉ ለእኔ ክብር ሲሉ እነዚህን ጥቂት ነገሮች ይታዘዛሉ፡፡

"ሆኖም እውነቱን ልንገራችሁ ድካም በሌለው መታዘዛቸው ብቻ ለመንግስቴ ብዙ ፍሬዎችን ሰብስበዋል፡፡ ብዙ ፍሬዎች፡፡ ስለዚህም ሌሎች ፍሬ ቢስ ለሚሉት ነገር ጆሮአችሁን አትስጡ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ለማይረቡ ነገሮች ራሳችሁን አታስጨንቁ፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ደረጃ የማይታይ ቢሆንም የታዘዙኝ ብዙ ፍሬዎችን አምጥተዋል፡፡

ለሙሽራዬቱ የተነገረ፡-

"አስደስተሽኛል፡፡ የሚፈለገው ደግሞ ይህንን ነው፡፡ የቅርብ በምትያቸው ሰዎች ታምተሻል፡፡ ነገር ግን ሌሎች ደግሞ አንቺን የሚያዩት ለመንግስቴ እንቁ እንደሆንሽ ነው፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ማንም ይህንን ማየት ባይችል እንኳን ከአለም ከምታገኘው ነገር በመለየትሽና እኔን በመታዘዝሽ ብዙ ፍሬዎችን አፍርተሻል፡፡ እንዲሁም ሁልጊዜ የራስሽን ከመፈለግ ይልቅ እኔንና የእኔን ፈቃድ ብቻ ፈልገሻል፡፡ እያልኩ ያለሁት ለዚህ ነገር ሽልማትሽ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ትንሽና የተጠበቅሽ ትሆኛለሽ፡፡ በልቤ ውስጥ ተደብቀሽ በፍቅሬና በፀጋዬ ለክብሬ ተትረፍርፈሽ ትኖሪያለሽ፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ሙሽራዬ ራሷን ዝቅ እያደረገች በሄደች ቁጥር ብዙ የሚያስደንቁ ነገሮች አሉኝ፡፡ ብዙ ስጦታዎችን በመቀበል በሥራዋ ትበለፅጋለች፡፡"

ጌታ ይህንን ያህል ልትቆይ ነው ማለት ነው?

"በጣም ብልህ ነሽ! እኔን ልታወጣጪ? እሺ መልካም ትንሽ ሚስጥር ልንገርሽ . . . አንቺ ከምታቂው የበለጠ ብዙም አላውቅም»

ይህማ በፍፁም የማይሆን ነው!

"አታልዬሽ አውቃለሁ?"
አይ በፍፁም፡፡

"መልካም እንዲህ ከሆነ እንግዲያውስ የተናገርኩሽን እንዳለ ተቀበዪው፡፡ እኔም እየጠበኩ ነው፡፡በእውነት ከሆነ እኔም እየጠበቅሁ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኔን ሁኔታ እያየሁ ነው፡፡ አብ መቼ በቃ እንደሚል ግን አላውቅም፡፡ እኔ የማውቀው ሁላችንም በር ላይ እንዳለንና ቃሉን እየጠበቅን መሆናችንን ነው፡፡ በእውነትም እየጠበቅን ነው፡፡"

"ሙሽራዬ እስካሁን እንዳልተዘጋጀች ነግሬሻለሁ፡፡ ይህ ማለት ግን ለመነጠቅ ዝግጁ ለመሆን የማይጥሩትን በትዕግስት ይጠብቃቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ፍላጎት ማጣት እየቀጠለ ከመጣ ምን እንደሚሆን ልትገምቺ ትችያለሽ፡፡"

ጌታ እኔ በእውነት ምንም አልገባኝም፡፡ አንተ እግዚአብሔር ሆነህ ሳለ እንዴት ምንም አለማወቅ ትችላለህ? ይህ በእውነት ግራ የሚያጋባኝና የተናገርከውንም እንዳለ መውሰድ የሚያስቸግረኝ ለዚህ ነው፡፡

‹‹አውቃለሁ፣ይገባኛል፡፡ ላለማወቅ መርጬ ነው ልበል?››

"ይህ ለእኔ ምን ያህል ህመም እንደሆነ ታውቂያለሽ? እርግጥ ነው ከሙሽራዬ ጋር ቅርበት አለኝ ደግሞም ከእርሷ ብዙ እጠብቃለሁ፡፡ ነገር ግን እርሷ እንደዛ እየኖረች አይደለም፡፡ ወደ ህይወቷ ገፍቶ እየመጣ ላለው ነገር ምላሽ እየሰጠች አይደለም፡፡ ይህንን በዩቲብ ላይ በሚሰጠው ምላሽ ማየት ትችያለሽ፡፡ በዚህ በጨለማ ጊዜ እርሷን ለመመገብ አንቺና ሌሎች ያደረጋችሁት ነገር ከሚገመተው በላይ ነው፡፡ ነገር ግን እርሷ የሰጠችው ምላሽ በጣም ጥቂት ወይም ምንም ነው፡፡ ለዚህ ነው እርሷ ባትዘጋጅም የንጥቀቱ ምልክቶች ይጀምራሉ ብዬ የምጠረጥረው፡፡

"ምን ያህል እንደምወዳት ይገባችኋል? ምን ያህል በእኔ ውስጥ ፍፁም ሆና ማየት እንደምጓጓ? እንዴት እጓጓለሁ! እኔ ብዙ የምሰጣት አለኝ፡፡ ክሌር እርሷ  ግን ምላሽ እየሰጠች አይደለም፡፡ ምላሽ እንድትሰጥ ፀልይ፡፡"

ጌታ አንተ እኮ ምላሽ እንድትሰጥህ ማድረግ እንዴት እንደምትችል ታውቃለህ፡፡ በራሳችን ህይወት ከጊዜ ወደ ጊዜ አይቸዋለሁ፡፡ በጣም የምትደንቅ ነህ፡፡

"በእርግጥ እችላለሁ፡፡ ነገር ግን ነፃ ምርጫ እጇን ያስረዋል፡፡ ሁሉንም መናገር ካለብኝ ትኩረት በመስጠት ራሳቸውን ያዘጋጁና እየተሰቃዩ ያሉትን ማየት ደክሞኛል፡፡ ይህ ማለት ለእነርሱ የበለጠ ስቃይ ነው፡፡ ግልፅ ለማድረግ የሰጠሁት ስጦታ መናቁና ሙሽራዬ ደግሞ የመምጣቴን ምልክቶች ችላ ብላ በነፃነትና በደስታ እየተጓዘች ማየት ደክሞኛል፡፡ የሰጠኋት ንፁህ ህይወት ለዓለም ባላት ነገር ተውጧል፡፡"

ጌታ አንተ ግን ለዚህ ማርከሻ አለህ፡፡

"አዎ ይህ ደግሞ ታምነው ለሚጠብቁት የበለጠ ስቃይ ያመጣል፡፡"

አንተ ለእኛ ከተሰቃየኸው ስቃይ ጋር ሲወዳደር፣ ለአንድ ተጨማሪ ነፍስ በትዕግስት ትንሽ መሰቃየት እንችላለን፡፡

"መልካም ምንም ተስፋ የሌለው ነገር አይደለም፡፡ ነገር ግን ወደዛ እየተጠጋን ነው፡፡ በአጠቃላይ ማለት የምችለው ተዘጋጁ ነው፡፡ ክሌር በማንኛውም ሰዓት፣ በማንኛውም ጊዜ አባቴ ይህንን ህይወት በቃ ሊል ይችላል፡፡"

በእውነት?

"በእውነት፡፡ አሁን ለምን ላለማወቅ እንደመረጥኩ አስረዳሁሽ፡፡ እባክሽ ባለማመንሽ አትጉጂኝ፡፡"

## ገሃነም በምድር ላይ / ዲሴምበር 13 ቀን 2014 ዓ.ም

## Hell on Earth/ December 13, 2014

ጌታ መልዕክቱን እንዲህ በማለት ጀመረ... "ገሃነም በምድር ላይ፣ በትክክል አነጋገር ገሃነም በምድር ላይ፡፡ በምድር ላይ ሊከሰት ያለው ነገር ሆሊውድ ሊያልመውና ሊፈጥረው ከሚችለው አሰቃቂ ፊልም በላይ እንዲሁም ማንም ሊያምነው ከሚችለው በላይ ሊሆን ያለ ነገር ነው፡፡ ስለሚመጣው ነገር ከባድነት ማንም ሰው ሊያውቀው ከሚችለው በላይ ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎች በዚህ ውስጥ ሊያልፉ ነው፡፡"

"በጣም በዙ የዋሆች፣ አይነስውሮች፣ ምንም የማያውቁና ደካማዎች ስለዚህ ጉዳይ ምንም ፍንጭ የላቸውም፡፡ የታወቁ የትምህርት ተቋማትም ስለዚህ ነገር ምንም የነገሯቸው ነገር የለም፡፡ እኔ ግን ለልጆቼ ስፈልገው የነበረው አሁን በምድር ላይ እየተደረጉ እንዳሉት ዲዳና ምንም የማያውቁ ሆነው እንዲኖሩ አልነበረም፡፡ ይህም በፍፁም እኔ የፈለግሁትና ያቀድኩት አልነበረም፡፡ እኔ ለህዝቤና ለልጆቼ ያቀድኩት ምድረ ገነትን እንጂ ይህንን አይደለም፡፡ እኔ የፈለኩት ልክ እንደ ገነት የሆነችን ምድር ነበር፡፡ እኔ ሰው በራሱ ፈቃድ እንዲገዛ ነፃነትን መስጠት ነበረብኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ነፃ ፈቃድ የሚያስከትለው ውጤት አለ፡፡ ስለዚህም ሰው በራሱ ፈቃድ ከትምህርት ተቋማትም ይሁን ከዘመኑ የሙዚቃ ባህል /Pop culture/ በላይ እኔን መምረጥና መጥራት መማር አለበት፡፡"

"ወደ ውስጥ ህሊናቸው በጥልቀት ማድመጥ አለባቸው፡፡ እኔ በጥልቅ ማንነታቸው ብዙ ጊዜ ተጣርቻለሁ፤ ቃሌን አስቀምጫለሁ፡፡ በጥልቁ ህሊናቸው ብዙ የጥሪ ካርዶችን፣ ፍቅሬንና ማስጠንቀቂያዎችን አስቀምጫለሁ፡፡ ነገር ግን በአንፀባራቂው ባህላችሁ የተነሳ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በህይወት ያሉት ለመሞት ቢሞኙም በሰውነታቸው የሚቀበር ቺብስ (RFID) ሞትን እንዳይቀምሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ቴክኖሎጂው ሰዎች በቺብሱ አማካኝነት በህይወት እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች በሚደርስባቸው ስቃይ ለመሞት ቢፈልጉም በውስጣቸው የሚቀበረው ቺብስ ግን እንዳይሞቱ ይከለክላቸዋል፡፡

(ክሌር) በዚህ ወቅት ጌታን አቋረጥኩትና ገብቶኛል ነገር ግን ከድልድይ እራሳቸውን መጣል አይችሉም ? አልኩት፡፡

"አይምሮን የሚቆጣጠረው በውስጣቸው እስካለ ድረስ አይችሉም፡፡ ወደፊት የሚሆነውንና ለመግለፅ የሚያዳግተውን ስቃይ በራሴ አምሳል ለፈጠርኳቸው፣ ህይወቴን አሳልፌ እስከ መስጠት ለወደድኳቸው ለሰው ልጆች በሰይጣን አማካኝነት እንዴት

እንደተቀነባበረ ምንም አልገባሽም፡፡ እኔን ለማጥፋት አይችልም፡፡ ነገር ግን ሰዎች እንዲሰቃዩ በማድረግ ሊጎዳኝ ይችላል፡፡ ክሌር፣ በማይነገር ስቃይ … ነገር ግን እንዲህም ሆኖ ምህረቴ ድል ያደርጋል፡፡ ወደ እኔ የሚጮሁትን በምህረቴ ነፍሳቸውን ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡

(ክሌር)፡- ነገር ግን ጌታ ሆይ አንዴ በሰውነት ውስጥ ቺፑ ከተቀበረ መዳን የሌለ መስሎኝ ነበር፡፡

"አዎ እንደዛ ነው የተፃፈው፡፡ ነገር ግን እኔ ምህረት የማላደርግ ነኝ? እነርሱ በጣም ዘግይተዋል፡፡ በጣም ዘግይተዋል፣ ነገር ግን እነርሱን ከዚህ ስቃይ የሚገላግላቸው ሞት ነው፡፡ ስለዚህም ነፍሳቸውን ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡ ከዚህ ክፉና ሰይጣንን ከሚያመልክ ትውልድ በምህረቴ የእነሱን ነፍስ፣ መንፈስ ከሥጋቸው እለያለሁ፡፡"

(ክሌር) ጌታዬ ይህ መልዕክት ከተለመደው የወጣ ስለሆነ ምንድነው የማደርገው?

"ይህንን በአንክሮ ውሰጂው፡፡ በጣም፣ በጣም፣ በጣም በአንክሮ ውሰጂው፡፡ በህይወት ያሉት በሞቱት ይቀናሉ፡፡ ይህ ክፉና ጨካኝ ትውልድ ያመጣው ነገር በፍፁም ውሸት የተሞላበት ነው፡፡ እነርሱ ቺብሱን ያቀረቡት ሰው ለሚገዛው ነገር እንደ ደረሰኝ አድርጎ እንዲቆጥረው ነው፡፡ይህ የሚደረገው ነገር ሊሆን ካለው ነገር ጋር ሲወዳደር ምንም አይመሳሰልም፡፡ ሰይጣን የእነርሱን ስስታምነት ተጠቅሞ ለራሳቸው መጥፊያ የሚሆነውን እንዳዘጋጀ አልገባቸውም፡፡ በዚህም ሥራቸው ወረርሽኝና ቸነፈር በምድር እንዲመጣ ምክንያት ስለሆኑ እነርሱም በዛው ወረርሽኝና ቸነፈር ይጠፋሉ፡፡ እንዲሁም በምድር ውስጥ ብዙ ገንዘባቸውን አፍስሰው አሳምረው በገነቧቸው ከተሞቻቸው በእሳት ባህር ውስጥ መዋጣቸው ተስማሚ ነው፡፡ እጅግ ተስማሚ ነው፡፡"

"ይሁን እንጂ እኔ ሰውን ወደ ምድር ያመጣሁት ለዚህ አይደለም፡፡ በፍፁም፣ በፍፁም ይህ የኔ እቅድ አይደለም፡፡ ነገር ግን የእነርሱ /ከዲያቢሎስ ጋር የተባበሩ ሰዎች/ ትዕቢትና አመፀኝነት ለእውሸት አባት አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ እናም እርሱ ሥራውን በሚገባ ተወጥቷል፡፡"

"እነርሱ የሚጠብቁት በአስተሳሰብ የላቀና ያሸበረቀ ህይወት የሚኖርበት ቆራጥ አዲስ ዓለምን ነው፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው ከብዙ አታላዮች ጋር በመሆን በእሳት መቃብሮቻቸው ውስጥ ይሞታሉ፡፡ ይገባችኋል? እኔ ስመለስ ፍፁም ድብልቅልቅ ይሆናል፡፡ ምድርን ለማዳን ሲባል በምድር የሚገኙ ግዙፍና አስቀያሚ ፍጥረታት ሁሉ ሊገደሉ ይገባል፡፡"

(ክሌር) ነገር ግን ጌታ ሆይ ከመከራው በኋላ በምድር ላይ ለሶስት ቀናት ጨለማ የሚሆነው እና ምድርን የሚያነፃውስ እሳት?

"አዎ በትክክል ምድርን በእሳት አነፃታለሁ፡፡ ነገር ግን በእሳቱ ሁሉም አይሞቱም፡፡ ከጉድጓድ የሚወጡ ሌሎች መንፈስ የሌላቸው ፍጥረታት አሉ፡፡ እነርሱ ሊገደሉ ይገባቸዋል፡፡ አጋንንቶች ይታሰራሉ፡፡ ነገር ግን በአርቲፊሻል መንገድ፣ እንዲሁም ሰውና እንሰሳትን በማደባለቀ የተፈጠሩ ፍጥረታት በምድሪቱ ላይ ስላሉ እነዚህ ከምድረ ገፅ ሊወገዱ ይገባቸዋል፡፡ በትክክል ለመናገር ዓለም እጅግ ትቆሸሻለች፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳን ሥራው ብዙ ቢሆንም ምድርን እንደገና አድሳታለሁ፡፡"

"እኔ የማለቅሰው አልስማ ብለውኝ ለስቃይ ለሚዳረጉ ለብዙ ህዝብ ነው፡፡ የሚነገረው መልዕክት ለእነርሱ የማይመች ስለሆነ አልሰማ ብለው ጀርባቸውን አዙረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ህይወታቸውን የሚያድነውን መልዕክት በመስማት ራሳቸውን እንዳያስተካክሉና እንዳይድኑ ሆነዋል፡፡"

"እነዚህ እልቂቱ ወይም መቅሰፍቱ ከመምጣቱ በፊት ወደ እኔ አይመለሱም፡፡ በዚያ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱት ለቅድስና ሳይሆን ራሳቸውን በመውደድና ከጥፋቱ ለማምለጥ ነው፡፡ ይህም ቢሆን ከእሳቱና ከአባቴ ቁጣ ለማምለጥ ጊዜው ስለሚያልፍባቸው ከጥፋት አያመልጡም፡፡"

"ይህንን አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ይህ እኔ ለሰው ልጆች በፍፁም ያቀድኩት አይደለም፡፡ እኔ ለወንድና ለሴት ልጆቼ የፈጠርኩት የአትክልቱን ሥፍራ ነው፡፡ ወደፊት ሊሆን ያለው ነገር እንዲሆን በሐሳቤም የሌለ ነው፡፡ ይህ የሆነው ሁሉ በሰይጣንና በተከታዮቹ አቀናባሪነት ነው፡፡ ልትረዱኝ ሞክሩ ይህ እቅድ በፍፁም የኔ አይደለም፡፡

"አያችሁ ብዙ ክፋዎች በእኔ ላይ ያሳብባሉ፡፡ ምክንያቱም ራሳቸው ለተሸነፉበት ሥራ ኃላፊነቱን መውሰድ አይፈልጉም፡፡ እነርሱ የሚፈልጉት በተቻለ መጠን ፍጥረታት ሁሉ በእኔ ላይ እንዲሳ ማድረግ ነው፡፡ ይህ አሁን ያለ ትውልድ ሊያውቀው የሚገባው ነገር ይህ ሊሆን ያለ ነገር የኔ እቅድ ሳይሆን የሰይጣን መሆኑን ነው፡፡ በእኔ ላይ በማመካኘት ልትወቅሱኝ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን እውነቱን ስታውቁ እኔ በፍፁም እንዳላቀድኩት ትረዳላችሁ፡፡

"ከሰይጣን ጋር የወገናችሁ እናንተ የሰው ልጆች፣ ይህንን ያመጣችሁት እናንተ እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ ምድርን ያጠፋችሁ እናንተ ስትሆኑ ሰዎች ግን ክንዳቸውን ወደ ሰማይ እያነሱ እኔን ይሳደባሉ፡፡ ነገር ግን ምድርን ያጠፉሁት እኔ ሳልሆን እናንተ የሰው ልጆች መሆናችሁን የሚያመለክት ተፅፎ ይቀመጥ፡፡

(ክሌር) ነገር ግን አንተ እኮ ነህ የቁጣውን ፅዋ የደፋኸው፡፡ እናም ሰይጣን ባያቀነባብረው ኖሮ ከፅዋው ውስጥ ምንም የሚደፋ ነገር አይኖርም ነበር፡፡ አንተ ሰይጣን በመሬትን እንዲገዛ ስላደረከው ይኸው እንዲህ ሆነ፡፡

## ሙሽሮቼ አሁን የመመለሻችሁ ጊዜ ነው! / ዲሴምበር 13 ቀን 2014 ዓ.ም

## My Bride, Now or Never/ December 13, 2014

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ . . . "በማብቂያው ሰአት የጸሎት ክፍልሽ ውስጥ ገብተሽ እኔን ማፅናናት ትፈልጊያለሽ ወይስ ሁሉ ነገር በሚወድም ወቅት ከአለም ጋር ሆነሽ እቃ በመግዛት፣ በመሸጥና በደስታ ላይ ትገኛለሽ ? የት ነው የምትሆኚው? የኖህ መርከብ ላይ ወይንስ በከፍታ ሥፍራ ላይ ሆነሽ ለአለም አድናቆትን በመስጠት ላይ?"

ታምኝነትሽ ለማን ነው? ለእኔ ነው? ለራስሽ? ወይንስ ለአለምና ለሰይጣን? ለአንቺ ክብደት ያላቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ባንክ ? ቤተሰቦችሽ ? ጓደኞችሽ? ወይስ እኔ ? ሙሽራዬ ታማኝነትሽ የት ነው? የጎርፉ ውኃ ሊያጥለቀልቅ ድንገት ሲመጣ የት ነው የምትሆኚው?""

"አሁን እየጠራኋችሁ ያለሁት ይህንን እንድትወስኑ ነው፡፡ ሙሽራዬ በእምባ ተሞልቼ እባክሽ ከእኔ ጋር ሆነሽ በፍቅሬ መርከብ ውስጥ ግቢ እያልኩ እጠራሻለሁ፡፡ እዛ እኔን ስሰቃይ ታገኚኛለሽ በእዛም የእኔን ጥበቃ ታገኛለሽ፡፡አዎ ክፉ እስኪጠፋ ድረስ እኔ እየተሰቃየሁ ነው፡፡ እናም ክፉ ካልጠፋ በቀር መሰቃየት አላቆምም፡፡ አዎ እኔን ትታ ለአለም ብልጭልጭ ነገር እራሷን እንደገና ለመሸጥ ወደ ንግድ ቦታ ለምትሄደው ሙሽራዬ አነባለሁ፡፡"

“ይህ ቀላል መልዕክት ነው፡፡ ምንም የተመሰቃቀለ ነገር የለውም፡፡ በዚህ ወቅት የሙሽራዬን አብሮነት፣ ማፅናናት እፈልጋለሁ፡፡ ለመታቀፍና ለመወደድ እጓጓለሁ፡፡ ቁስሌን የሚያክመውን ጣፋጭ የሆነውን ሰላምታዋን እንዲሁም በየቀኑ የማየውን እንዳላይ የሚያስረሳኝን  ንፁህ የሆነውን ድምጿን መስማት እፈልጋለሁ፡፡

"ሙሽራዬ እባክሽ በዚህ በተቀደሰ ወቅት ከአለም ጋር ያላችሁን መንገድ ነገር ትታችሁ ወደ እኔ የሚስጥር ቦታ ማለትም የፍቅር መርከቤ ውስጥ ግቡ፡፡ቁስሎቼን ተንከባከቡ፣በበራድ ልብ ስለእኔ አስቸጋሪ ሁኔታ ሳይጨነቁ ከእኔ የራቁትን አስረሱኝ፡፡”

"የሙሽራዬ አንድ ዕይታ ለእኔ ምን ያህል ትርጉም እንዳለው አታውቁም፡፡ የንጉሱን ልደት ልታከብሩ በሰዎች የተሞላ አዳራሽ ውስጥ እንደተገኛችሁ አድርጋችሁ ራሳችሁን አስቡት፡፡ እያንዳንዱ ሰው ውበቱን ለማሳየትና ለማስጎምጀት ከበሩ እስከ መደነሻ ቦታው ድረስ ትዕይንት ያሳያል፡፡ እያንዳንዱ ሰው በማያልቀው በስልጣን፣በኃያልነት ፣በሃብትና በዝና ጨዋታ ተወጥሯል፡፡ ፡፡”

“ከዛም በመቅጽበት የሚቀጠለው አጭር የሙዚቃ ትርዒት ሲጀምር ሁሉም ወደ በሩ አቅጣጫ ዞሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሱ ገባ፡፡ንጉሱም ሲገባ የእያንዳንዱን ሰው ጭንቅላት እያነበበ ነበር፡፡ አጭሩ የሙዚቃ ትርዒት በሚከናወንበት ሰዓት በመምጣቱና እርሱ ሲገባም ቆም ብለው እውቅና መስጠት ስለሚገባቸው ይህንን ማድረግ ቁጣን ፈጠሮባቸዋል፡፡ በሰዓቱ ከገቡበት ከፍተኛ ጉጉት መውጣትም አበሳጭቷቸዋል፡፡ እናም በአለም ሁሉ ላይ ሉአላዊው የሆነው ንጉሥ ያሸበረቀ ልብሱን ለብሶ በፊታቸው ቆሟል፡፡ የተሰበሰበውን ህዝብ አያውቁትም፡፡ እርሱም በክፍሉ ውስጥ ያለውን የእያንዳንዱን ሃሳብና ስሜት እያነበበ ነበር፡፡”

“ጥጉ ላይ የተቀመጠች አንድ ትንሽ አበባ ነበረች፡፡ እሷ ለደማቁ፣ ውብ ለሆነው በአልና በልጦ ለመታየት ለሚደረገው ጨዋታ ምንም ፍላጎት የሌላት ናት፡፡ እርሷ የተማረከችው በንጉሱ  ውበት ብቻ ነው፡፡ በነፍሷ ውበት ተማርኮና ከሌሎቹ ሁሉ የተለየች መሆኗን አይቶ በትህትና ተሞልቶ ወደ እሷ ተራመደ፡፡ ከተቀመጠችበት አስነሳትና እጆችዋን በእጁ ይዞ 'የእኔ ንግስት ለመሆን ብቁ የሆነችውን አግኝቻለሁ አለ'፡፡"

“ሌሎቹ ሁሉ በመደንገጥና በመጠራጠር አፋቸው በመገረም ተከፍቷል፡፡ እርሷ ማንም  አይደለችም!! የለበሰችው  ልብስ መናኛ ነው፣ ቤተሰቦችዋ እንኳን ከንጉሳዊ ዘር አይደሉም በማለት ፀጥ ብሎ የነበረው ቤት በጫጫታ ተሞላ፡፡”

“ሙሽሮቼ ወደ እናንተ ስመለከት ምን ለማየት ነው የምገደደው? በልባችሁ፣በሃሳባችሁ ውስጥ የሚኖረው ምን ይሆን? መግዛት ያለባችሁ እቃ ዝርዝር ብዙ ስለሆነና ስለረፈደባችሁ ወደ ገበያ ለመሄድ ስለቸኮላችሁ ለእኔ ትዕግስት በማጣት ይሆን? ወይንስ ንጉሳችሁ በመካከላችሁ ስለሆነ ትልቅ ስሜት ውስጥ ትገባላችሁ? ይህቺ ነች እኔ የምፈልጋት ሙሽራ፡፡ ከእኔ ጋር ከባድ ፍቅር ውስጥ ስለሆነች ከእኔ ጋር ለመሆን እንጂ ለመሸመት ጊዜ የላትም፡፡ ከጓደኞቿ ጋር ስሜት በማይሰጥ መልኩ ከምትመገብ ከእኔ መራራ ጽዋ ብትጠጣ ትመርጣለች፡፡”

“በአለማችሁ አስቸጋሪ ሁኔታ በሃዘን ተሸፍኛለሁ. . . አዎ የእናንተ አለም የምለው  የእኔን አለም ምንም ምንም ስለማይመስል ነው፡፡ በድንገት ስለሚመጣባችሁና ልታመልጡት ስለማትችሉት ነገር ትልቅ ሃዘን ላይ ነኝ፡፡”

“ሙሽራዬን በንግድ ቦታ፣በምግብ ቤቶች፣ በበአላት ላይ በየቦታው ፍልጌያታለሁ፡፡ እናም ከሌሎች ወንዶች ጋር ሃፍረተ ቢስ በሆነ ወሲባዊ ባህርይ ተጠምዳ፣ ሰይጣን እንድትጠመድ በሰጣት አፀያፊ ባህሪ ውስጥ ስትፈነጥዝ አገኘኋት፡፡ አሁን ግን መፈለግ፣ መጣራትና መለመን እጅግ አድክሞኛል፡፡ ምንም ያህል ጊዜ ስለሌላችሁ የምትመለሱ ከሆነ በፍጥነት አሁኑኑ አድርጉት፡፡ ሙሽራዬ አሁን ካልሆነ መቼም አይሆንም፡፡ አሁን ካልሆነ መቼም አይሆንም፡፡ አሁን ካልሆነ መቼም አይሆንም፡፡

## የነውጡን ትዕይንት ወደ ሰላም መቀየር/ ማርች 16 ቀን 2015ዓ.ም/
## Turning drama into peace/ March 16, 2015

ህይወታችሁ ቋሚ ትዕይንት የሚታይበት ነው? ወይስ መጣ ሄደት የሚሉ ትናንሽ ትዕይንቶችን ታስተናግዳላችሁ?

አንድ ሰሞን  ህይወቴ ወደ አንድ "ትዕይንት" ተስቦ እንደነበር ተገንዝቤያለሁ፡፡ ይህም "ትዕይንት" ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሸጋገርና እንደ ኃይለኛ ሞገድ ዙሪያዬ ያለውን ነገር ሁሉ በመሰባበር ሰላም፣ ዕረፍትና ደህንነት እንዳይሰማኝ አድርጎኝ ነበር፡፡

ጠላት ይህንን ተግባርያዊ ለማድረግ ሌሎችን ስንት ጊዜ ይጠቀማል? በፎኒክስ አራት ልጆቼን ብቻዬን ሳሳድግ በነበረ ወቅት ምንም የገቢ ምንጭ ሳይኖረኝ ሁሉንም ነገር ከአምላኬ እጅ እጠብቅ ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ቋሚ የሆነ የጠላት አሰራርን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ይህም ከታመምኩ ወይም በወር አበባዬ ምክንያት ድካም በሚሰማኝ በዛው ወቅት አንድ ኃይል መጥቶ ይመታኝና ሁሉ ነገር ድብልቅልቅ ይልብኝ ነበር፡፡

በዚህም መገንዘብ የቻልኩት ጠላት ደካማና ለጥቃት ተጋላጭ በምሆንበት በወር አበባዬ ወቅት ከሁለት በላይ በሆኑ ስጋቶች ጥቃት በመፈፀም ያስደንቀኝ ነበር፡፡ በዚህም ጊዜ ታዲያ ሌሎችን ሰዎችን ይጠቀማል፡፡ ይህንን ስላችሁ ደህና የሚባሉትን የቤተ ክርስቲያን ሰዎችን እንኳን ማለቴ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ቧንቧ ይበላሻል፣ ቤት አከራዮቻችን ያስፈራሩናል፣ ቤት ኪራይ ቶሎ መክፈል አንችልም፣ መኪና ይበላሻል፣ ልጆቹ ጉንፋን ይይዛቸዋል፡፡ ምን ልበላችሁ ሁሉም በአንድ ላይ ይደራረብና አንዳንድ ጊዜ ችግሮቹን በአንድ ላይ ለመፍታት የማልችልበት፣ ከአቅሜ በላይ በመሆን ተስፋ ልቆርጥ የደረስኩበት ወቅት ነበር፡፡

ነገር ግን ጌታ ወዲያው ይህ ነገር እኔን ሳይሆን እርሱን እንደሆነ ያስተምረኝ ጀመር፡፡ "አንቺ የእኔ አገልጋይ ነሽ፡፡ እናም እነርሱ ማለትም አጋንንቶቹ ችሎታሽን ለማገድና ተስፋ ቆርጠሽ ተሸንፌያለሁ በማለት እጅሽን አጣጥፈሽ እንድትቀመጪ ለማድረግ ነው፡፡ ይህ እነርሱ የሚወዱት ግብ ነው፡፡ በመጨረሻውም ሰላምሽን ለመስረቅ ነው" አለኝ፡፡

ጌታ በዮሐንስ 14፡27 እንዲህ በማለት ቃል ገብቶልናል፡፡ "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።" በሌላ ትርጉም ደግሞ  " የአይምሮና የልብ ሰላም

እሰጣችኋለሁ፡፡ የምሰጣችሁም ሰላም አለም እንደሚሰጣችሁ አይነት ሰላም  አይደለም፡፡ ስለዚህም አትጨነቁ ደግሞም አትፍሩ" ይላል፡፡

አያችሁ ጠላት ግርግርንና ጥፋትን ለመፈፀም ሲከታተላችሁ አይምሮአችሁን የተናወጠ ባህር እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ስለዚህም ከደህንነት ይልቅ አደጋ ውስጥ እንዳላችሁ ይሰማችኋል፡፡ እርሱን የምታገለግሉት ከሆነ ደግሞ መናወጡ ይቀጥልና ውጤት አልባ ትሆናላችሁ፡፡ ምክንያቱም ነገሩን ሁሉ በራሳችሁ ዙሪያ ማጠንጠን ትጀምሩና ከራሳችሁ ውጪ የሆኑ ችግሮችን መቋቋም አትችሉም፡፡

በዚህ ጊዜ ታዲይ ሰዎች ሰላም ለመፈለግ ወደ እናንተ ሲመጡ የኢየሱስ አምባሳደር በመሆን ፈወስ ማስተላለፍ ሲገባችሁ ነውጥን ለሌላ ሰው ታስተላልፋላችሁ፡፡ እነርሱም ለሌላ ሰው እንዲሁ ይቀጥላሉ፡፡ ስለዚህም አለም በረብሻ ዙሪያ መሽከርከሯን ትቀጥላለች፡፡

ከዚህም ልንወጣ የምንችልበትን መንገድ አለ፡፡ ኢየሱስ ራሱ በጳውሎስ በኩል በዕብራውያን መፅሐፍ ላይ አስተላልፎልናል፡፡ ክፍሉም "ወደ ዕረፍቴ ግቡ" ይላል፡፡

ቃሉ ምን እንደሚል በአዲሱ ትርጉም እንመልከት፡፡ዕብራውያን 4፡1 "እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፥ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።"

እንደ እውነቱ ከሆነ ሰላም በሌለበት ሥፍራ የሚገኘው ፍርሃት ነው፡፡

"2 ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምስራች ተሰብኮልናልና፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።3 ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም። እንዲህ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ፥ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን።4 ስለ ሰባተኛው ቀን በአንድ ስፍራ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ብሎአልና፤ 5 በዚህ ስፍራም ደግሞ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም።6 እንግዲህ አንዳንዶች በዚያ እንዲገቡ ስለ ቀሩ፥ ቀድሞም የምስራች የተሰበከላቸው ባለመታዘዝ ጠንቅ ስላልገቡ፤ 7 ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ በፊት እንደ ተባለ፥ ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር፤ ዛሬ ብሎ አንድ ቀን እንደ ገና ይቀጥራል። 8 ኢያሱ አሳርፎአቸው ኖሮ ቢሆንስ፥ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር። 9 እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል። 10 ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና። 11 እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።"

እርግጥ ነው አሁንም አሁንም በተደጋጋሚ እንወድቃለን፡፡ ከዚህም የተነሳ ህይወታችን በማያቋርጥ ውጥረቶች፣ በድንገተኛ አደጋዎች፣ በከፍተኛ ጭንቀቶች፣ በማይቻሉ ሁኔታዎች የመናወጥ ዑደት ውስጥ የሚሽከረከር ይመስላል፡፡ በዚህም ምክንያት በማያቋርጥ ረብሻና ዕረፍት ማጣት ውስጥ እንወድቃለን፡፡ ይህንንም ትዕይንት ለሌሎች እናስተላልፋለን፡፡ ምክንያቱም እኛ

ያለንበት አካባቢ ሁሉ በነውጥ የተሞላ ስለሆነ ከእኛ ጋር የተገናኘ ማንኛውም ሰው በነውጡ፣ በተስፋ ቢስነትና ደህንነት በማጣት ስሜት ተነክቶ ይሄዳል፡፡

ወንድሞቼና እህቶቼ ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ጊዜ ራሳችንን ያዝ በማድረግ እኛ እግዚአብሔር እንዳልሆንንና ወደ እኛ የሚወረወሩትን ነገሮች እርሱ መፍትሔ እንደሚሰጥባቸው በግልፅ ማየትና መረዳት አለብን፡፡ ይህም በመሆኑ ወደ እርሱ ፊታችንን በፍጥነት በመለስንና ነገሮችን በተውናቸው ፍጥነት መጠን ሌሎችንም እንዲሁ እንዲያደርጉ ማበረታታት እንችላለን፡፡ ጌታ በነገሮቻችን ላይ ጣልቃ እንዲገባ ተንበርክከን በጠየቅነው ፍጥነት መጠን መፍትሔዎቻችን እንዲፈጥኑ እናደርጋለን፡፡ ነገር ግን እኛ በራሳችን ልናደርገው አንችልም፡፡

ዘለፋ በበዛበት በሚያድጉ ወይም በሚኖሩ ቤተሰብ መካከል ነገሮችን ለማብረድ፣ ሰላም ለመፍጠር፣ ስርዓትን ለማስከበርና ነገሮችን 'ትክክል እንዲሆኑ ለማድረግ' የሚሞክሩ አንድ ወይም ሁለት ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል፡፡ እነዚህ ሰዎች ታዲያ ሰዎችን እጅግ በቁጥጥር ሥር የሚያደርጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ የሆነው ግን ከተንኮል የተነሳ ሳይሆን ነገሮችን ትክክል ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ነገር ግን እውነትን ተመርኩዞ ነገሮችን ትክክል ሊያደርግ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እርግጥ ነው ሰላምን የሚፈጥሩ የተባረኩ ናቸው፡፡ ቢሆንም ግን ሰዎችን ሰላም ፈጣሪ የሚያደርጋቸው ያሳለፉት ወከባ የበዛበት ትዕይንት ኃይል ስለሰጣቸው ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነው ሰላም ፈጣሪ የሚያደርጋቸው፡፡

እንዴት ነው ሰላም ፈጣሪ የምትሆኑት? በመጀመሪያ እናንተ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መፍጠር አለባችሁ፡፡ በውስጥ ማንነታችሁ ለሁሉ ነገር ምላሽ ሰጪው እርሱ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ ይህም እምነትን ይመለከታል፡፡ ከራሳችሁ ውጪ በሆነ በእግዚአብሔር እምነት ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ በዚያን ጊዜ ነው ሁሉን በመተው ለእርሱ አሳልፋችሁ ለመስጠት የምትችሉት፡፡

በቀደመው ጊዜ ውጥረትን ለማርገብ በሥራ ላይ ውላችሁ ይሆናል፡፡ አላደረጋችሁትምም ይሆናል፡፡ ነገር ግን በእርሱ ላይ ያላችሁ እምነትና ጥሩ ግንኙነት ነው ወደ ትክክለኛውን ሚና እንዲመራችሁ የሚያደርገው፡፡ እንደገና ወደኋላ ቁሙና እግዚአብሔር ራሱ ያድርገው . . . ወይም ለጊዜው የሚሆን ቃል ይስጣችሁ፡፡ ስልክ ደውሉ . . . ወይም በመስቀሉ እግር ሥር አስቀምጡት፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንዴት የሚደንቅ ነው እግዚአብሔርን በመተካት የተበላሹትን ለመጠገን የምናደርገውን ጥረት በመጨረሻው ስናቆም፡፡ በዚያን ጊዜ መልሱ ይመጣና እንደገና ፀጥ እርጭ ይላል፡፡

እርሱ የሚፈልገው መልሳችንን ከእርሱን እንድንጠብቅ ነው፡፡ ስለዚህም ችግሮቻችንን በእጁ ላይ ካስቀመጥን በኋላ ከእርሱ መመሪያን እንጠብቅ፡፡ በችግሮቻቸው ጊዜ ሌሎችንም ማበረታታት ያለብን ወደ ጓደኞቻቸው ስልክ በመደወል ራሳቸውን ሥራ እንዲያበዙ ሳይሆን በጉልበታቸው እንዲበረከኩና እንዲፀልዩ ነው፡፡ ነገሮችን የሚያቃልል ኃይል ያለው እዚህጋ ነው፡፡ በእናንተ እጅ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር እጅ ላይ ነው ያለው፡፡

ደስታና ሰላም ባላቸው ሰዎች ዙሪያ መሆን እንዴት ደስ ይላል፡፡ እነርሱ በመካከላችን ሲገኙ እንዴት ደስ ይላል፡፡ ነገር ግን ልብ ብላችኋል? የሚያሳዩት ትዕይንት የለም፡፡ እነርሱ የሚያደርጉት ነገር ቢኖር መፀለይና ለፀሎቶቻቸው መልስን መጠበቅ ነው፡፡ እነዚህም ሰዎች በኢየሱስ ጥልቅ የሆነና የሚያንፀባርቅ እንዲሁም ሌሎችን ወደ እርሱ በመመለስ እንዲፈወሱ የሚያደርግ ሰላም አላቸው፡፡ እነርሱ የእውነትን ቃል፣ የመፍትሄ ቃል እንዲሁም በአለም አጣብቂኝ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ መልስ ተሸካሚዎች ናቸው፡፡

ይህንንም መፅሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን መፅሐፍ ላይ ክርስቶስ የእኛ ታላቅ ሊቀካህን እንደሆነ በመግለፅ ያስተምረናል፡፡ ዕብራውያን 14-16 "እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።"

አጋንንቶች ሊፈጥሩ ያሉትን በመቃውምና በራሳቸው ላይ ግርግር እንዲፈጥሩ በማድረግ እኛ በፀጥታ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ የሚቻል የማይመስለንን ነገር እርሱ ሲጨርሰው እንመልከተው፡፡ ሰዎች እምነት ይኑራችሁ!!! እምነታችሁም እናንተ መስራት በምትችሉት ላይ ሳይሆን እምነታችሁ በእግዚአብሔር ችሎታ ላይ ይሁን፡፡ ምክንያቱም እርሱ ይሰራል ብላችሁ ፀልያችሁ እየጠበቃችሁ ስለሆነ ነው፡፡

**በአለም ያላችሁን ተሳትፎ ገደብ አብጁለት/ ማርች 24 ቀን 2015 ዓ.ም**
**Draw the line on your involvement with the world/ March 24, 2015**

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . "ሙሽራዬ ሰላም ለአንቺ ይሁን፡፡ ለአንቺ ሰላምን አውጃለሁ፡፡ በፍርሃትና በመጠባበቅ ልብሽ ተሞልቷአል፡፡ በዚህም በዚያም ብዙ ቋጠሮዎች አሉ፡፡ በእኔ ላይ አርፈሽ በሰላሜ እንድትጠበቂ እንዴት እመኛለሁ፡፡ የዚህን ዓይነት ስጋት በልጆቼ ላይ እንዲያልፍ አልፈልግም፡፡ በአንፃሩ ግን ለእነርሱ የምፈልገው ሰላም፣ ዕረፍትና መረጋጋትን ነው፡፡"

ክሌር፡- ጌታ ሆይ ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምችል አላውቅም፡፡

"በክንዶቼ ደግፌ ስይዝሽ ከውስጥ በኃይል ተንፍሺና ሰላሜ ከእኔ እንደ ወንዝ ወደ አንቺ በመፍሰስ በአንቺ ውስጥ ቦታን ያገኛል፡፡ ያንንም ሰላም ለልጆቼ ታመጫለሽ፡፡ ለዚህ ነው መልዕክቱን ከመፃፍሽ በፊት ይህ ጊዜ ለእኔ፣ ለእኛ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው፡፡ አሁን ምን እየተሰማሽ ነው?"

ሰላም፡፡

"ይህ በእውነት ትክክል ነው፡፡ ይህ ሰላምና መረጋጋት ከእኔ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቀን በዚህ ዓይነት እየጨመርሽ መስራት

አለብሽ፡፡ ምክንያቱም የሰላም አገልጋይ አድርጌ እጠቀምብሻለሁ፡፡ ይህ ለእኔ አስፈላጊ ነው፡፡ የጠላትን ኃይል አጣጥለሽ አትመልከቺ፡፡ ምክንያቱም ብዙዎች የተሞሉት አለም በሚያጓጓቸው ነገር ስለሆነ እምነታቸውን ሊያስጥላቸው ይችላል፡፡

"በድህረ-ገፆች ላይ በጣም ብዙ ሰዎች በአለም ላይ ሊመጣ ያለውን የሚያስፈራ ነገር በተለይም በክርስቲያኖች ላይ ሊሆን ያለውን እያወሩ ይገኛሉ፡፡ ህዝቦቼ እኔን በማግኘት ሰላሜን መቀበል አለባቸው፡፡ የዚህም ቻናል ሥራ መሆን ያለበት በእኔ ሰላምን እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ እኔ የእናንተ መጠለያ ነኝ፡፡ ወደ እኔ ኑና በእኔ ተሸፍናችሁ ዕረፍትን አግኙ፡፡

"ክሌር እነርሱ ውሳኔዎችን ለመስጠት፣ በፍርሃት፣ ሰቃይ ይደርስብኝ ይሆን? ብሎ በመስጋት በብዙ ተቸግረዋል፡፡ እያንዳንዱ ቀን የራሱ የሆነ ችግር ስላለው ወቅቱ ከስቃይ ሁሉ ነፃ ይሆናል ብዬ ቃል መግባት አልችልም፡፡ ቃል ልገባ የምችለው ቁጣዬን እንደማያዩት ነው፡፡ ቁጣዬ ከመምጣቱ በፊት ከዚህ ትወሰዳላችሁ ፡፡ ነገር ግን ይህንን፣ ያንን በማድረግ እንዴት ልትተሳሰሩ እንደምትችሉና በዛም ነገሮች እንዴት እንደሚደበላለቁ ታውቃላችሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከእኔ ጋር ለመሆን ብቻ በአለም ያለውን ትስስር ለመበጣጠስ በራሳችሁ መንገድ መታገል ሊኖርባችሁ ይችላል፡፡

"ብዙ፣ እጅግ ብዙ፣ ሙሽሮቼ ህይወታቸውን ቀለል አድርገው ስላልያዙት ጊዜያቸውን ከሚወስድ ነገር መላቀቅ አልቻሉም፡፡ ይህ ግን እንዲቀየር እፈልጋለሁ፡፡ በመንግስተ ሰማያት ሊኖሩ ያሉትን ዓይነት ኑሮ አሁኑኑ መኖር እንዲጀምሩ እፈልጋለሁ፡፡ አዎ በምድር መሥራት ያለባቸው ስራዎች አሉ ፡፡ ነገር ግን በድጋሚ ቢያስቡበት አለም ጊዜያቸውን ከሚወስደው ቢያንስ በግማሽ መቀነስ ይችላሉ፡፡

"ብዙ ነገሮችን እንግዲህ ምን ማድረግ ይቻላል? በሚል ተቀብላችሁ እየኖራችሁ ነው፡፡ ለምሳሌ ወደ ገበያ አዳራሾች መሄድ፡፡ እዛ ምን እንደተለማመዳችሁ ታውቃላችሁ፡፡ ያንን መለካት፣ ያንን ማውለቅ፣ ያንን መለካት ያንን መጣል! ይህንን እስከ መጨረሻው ድረስ ታደርጋላችሁ፡፡ ይህ ጥሩ ነው? እነዚህ የገበያ ማዕከላት የሚያደክሙና ሰላምን የሚያውኩ እንደሆኑ ከእኔ ጋር በፀጥታ በቆዩ ጊዜያት ለእያንዳንዳቸው አካፍያቸዋለሁ፡፡ በአለም ነገር ላይ በሚሳተፉበት ጊዜ ግልፅና የማይጎዳ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቢሆን እንኳን እንዲሁም ወደ ገበያ አዳራሾች መሄድና መፅሔቶችን ማንበብ የመሳሰሉት ሁሉ አይምሮን በማይፈለጉ ነገሮችን በመሙላት ሰላማቸውን ይሰርቃሉ፡፡ ንፁህ ልብና ንፁህ አይምሮ መኖሩ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ አይምሮአቸው ሊይዝ የሚችለው የተወሰነ ነገር በመሆኑ ለአይምሮአቸው የሰጡት ምድራዊ ነገር ከሆነ ያልተፈለገ ቆሻሻን ሁሉ ስለሚሰበስብ እኔ ከእነርሱ ጋር በመሆኔ ያካፈልኳቸውን ሁሉ ይጠርገዋል፡፡ ስለዚህም ለእኔ ቦታ አይኖራቸውም፡፡

ክሌር፡- ጌታ ነገር ግን አልፎ አልፎ አመለካከታችንን ለመጠበቅ ዕረፍት አያስፈልገንም?"

"አዎ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ዕረፍቱን ቀላልና ንፁህ አድርጉት፡፡ ለምሳሌ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ የዛፍ እምቡጦችን መመልከት፣ ሳር ማጨድ፣ ከድመትና ከውሻ ጋር መጫወት የመሳሰሉትን፡፡ ነገር ግን የሩቅ የእግር ጉዞ በማቀድ ራሳችሁን ችግር ውስጥ እንዳትከቱ፡፡ እንዲሁም ይህንን ማስተካከል አለብኝ፣ ያንን ማስተካከል አለብኝ በሚል ሐሳብ በሥራ እንዳትጠመዱ፡፡ ይህ እናንተን በሥራ ለማጥመድ፣ ለማድከምና መንፈሳዊ ሰላማችሁን ለመንጠቅ የሚደረጉ የሰይጣን ድለላዎች ናቸው፡፡

"ብዙ ጊዜ ወደ ገበያ ሥፍራዎች መሄድ ወይም በድህረ ገፆች አማካኝነት ግብይት ለመፈፀም ትፈልጋላችሁ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለመንፈሳዊ ሰው ጥንቃቄ መደረግ ያለባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ነገሮች ማድረግ ጀመሩ ማለት ነገሩ አለቀ

ማለት ነው፣ ከዚያ በኋላ መላቀቅ ያስቸግራችኋል፡፡ ይህንን ስታደርጉ ግን መደረግ ያለበትና ምንም ችግር የሌለው አድርጋችሁ ነው የምትቆጥሩት፡፡ ነገር ግን ሰይጣን በተሻለ ያውቃል፡፡ እናንተ እነዚህን ሥራዎች ከፈፀማችሁ በኋላ ሰይጣን ጭፍሮቹን በማዘዝ 'ኃላፊነት የማትወስድ፣' 'ያንን ባለፈው ዓመት ማድረግ ነበረብህ'፣ እንዲህና እንደዚያ እያለ መክሰስ ይጀምራል፡፡"

"አይምሮአቸው በእነዚህ ነገሮች እንዲያዝ አልፈልግም፡፡ የአንቺም አይምሮ በእነዚህ ነገሮች እንዲያዝ አልፈልግም፡፡ እያንዳንዱ ትኩረቱን እንዲያደርግ የምፈልገው በመንግሰተ ሰማያት ላይና እኔ መጥቼ እንደምወስዳችሁ ብቻ መሆን አለበት፡፡ የአምስቱ ቆነጃጅት አንዱ ችግራቸው በአለም ነገር ተተብትበው ዘይት ሳይዙ መቅረታቸው ነበር፡፡ እነሱ የመሰላቸው እኔ ትንሽ ቆይቼ እነሱም ወደ ሥራቸው የሚመለሱ ነበር ፡፡ ልክ እንደ ማርታ አይምሮአቸው እኔ ላይና የእኔ አጀንዳ ላይ ሳይሆን ቤት ሄደው የሚሰሩት ነገር ላይ ነበር፡፡ ነገር ግን ልክ እንደ ማሪያም አስተዋይ የሆኑት ቆነጃጅቶች መጠበቅ እንችላለን በማለት እኔን ይጠብቃሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ይጠብቃሉ፡፡ ይህ ለእነርሱ ጊዜ ማባከን ሳይሆን ፍፁም ደስታ ነው፡፡ ምክያቱም በአይምሮአቸው ሁሉ ያለሁት እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው፡፡ ሌላው ነገር ሁሉ ለእነሱ ሸክም ስለሆነ 'ሊዘገይ ይችላል፣ ግን ፀጥ ብለን እንጠብቀዋለን' ብለው ማሰብ እንኳን ለእነሱ ደስታ ነው፡፡ ውዶቼ! ይህንን ሐሳብ እንድትረዱኝ ስለምፈልግ የምናገረው እርግጡን ነው፡፡  ሞኞቹ ቆነጃጅት አስተሳሰባቸው ሥጋዊ ነው፡፡ የተያዙት በአለም ነገር ነው፡፡ ስለዚህም እኔን መጠበቅ ጊዜ እንደማባከን አድርገው ነው የሚቆጥሩት፡፡

"አንቺም በእንደዚህ አመለካከት ውስጥ ስለነበርሽ ምን እንደማወራ ይገባሻል፡፡ ዘመንሽን ሁሉ ይህንን ስትታገይ ኖረሻል፡፡ በቅርቡ ነው ራስሽን አሸንፈሽ ከዚያ የወጣሽው፡፡"

ይህ በጣም በጣም እውነት ነው፡፡ በበልግ ወራት አትክልቶችን በመትከል፣ በመኮትኮትና ነገሮችን በማሰዋብ ነበር ጊዜዬን የማሳልፈው፡፡ አሁን ግን ሁሉን ትቻለሁ፡፡ ምክንያቱም አንተን በማገልገል ስለተጠመድኩ ስለዚያ ብቻ ነው ግድ የሚለኝ፡፡ ወደ ገበያ ማዕከልም መሄድ አስጠልቶኛል፡፡

“አየሽ ምን ያህል እንደተለወጥሽ? “

አዎ ጌታዬ አንተ ነህ በእኔ ውስጥ ይህንን የሰራኸው፡፡

“አንቺ ደግሞ ለዚህ ተባበርሽ፡፡“

በዚህ ጊዜ አንድ ነገር ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ጠላቴ በበልግ ወራት ትኩረቴን በፅዳት ሥራ ላይ በማድረግ በፅዳት ሥራው ጠልቄ በመግባት ጊዜዬን ሁሉ በዛ እንዳጠፋ ለማድረግ እየፈለገ ነበር፡፡ ነገር ግን ያንን የሚያስቸኩል ሐሳብ ተቋቁሜ ሐሳቡን ሳልፈፅም ቀረሁ፡፡

“እኔ በዛ ወቅት እየተመለከትኩሽና ወጥመዱን እንድታስተውይ እየረዳሁሽ ነበር፡፡“

አዎ በርግጥም ወጥመድ ነበሩ፡፡

“ለሁላችሁም እንዲህ ልበላችሁ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ነገር ጊዜ የላችሁም፡፡ የአይምሮአችሁ ትኩረት ሁሉ በመንግስተ ሰማያት ላይ፣ በእኔ መምጣት ላይ፣ በመንፈሳዊ ወንድማማች ፍቅር ላይና ለጎረቤቶቻችሁ ልታደርጉ በምትችሉት ቀላል ነገር

ብቻ ይሁን፡፡ ሙሽሮቼ በመምጣት ላይ ስለሆንኩ ለሁሉ ነገር ገደብ አብጁለት፡፡ ከእኔ ትኩረታችሁን ሊወስድ በሚፈልግ በማንኛውም የአለም ጉዳይ አትወሰዱ፡፡ ብድራታችሁን ትኩር ብላችሁ ተመልከቱ፡፡ ወታደሮች በአለም ነገር አይጠመዱም፡፡ ለመስራት ግዴታ የሆነባችሁን ሥራ ብቻ ሥሩ፡፡ አስፈላጊ ስል 'አስፈላጊ ማለቴ' ነው፡፡ ትኩረትን የሚወስድ፣ ጉልበትን የሚበላና ጊዜን በማባከን የሚያደክም ሥራ ውስጥ አትዘፈቁ፡፡

"በሳምንቱ የዕረፍት ቀናቶቻችሁ ላይ ስትሆኑ ልክ ተኩላዎች የትኞቹ መንጋዎች ለመጠመድ ምቹ እንደሆኑ እንሚያጠኑ ዓይነት ጠላቶቻችሁ በቅርብ እንደሆነ ተገንዘቡ፡፡ ኢጋንንቶችም እናንተን በማጥናት እስከትወድቁ ይጠብቃሉ፡፡ እናንተም ከልክ በላይ ሰርታችሁ፣ ደክሟችሁና ዝላችሁ እያለ በጥርጣሬ፣ በፍርሀት፣ ደህንነትና እምነት በማሳጣት ዘሎ ይከመርባችኋል፡፡ ራሳችሁን እዚህ ውስጥ እንዳትከቱ፡፡ ሁልጊዜ ንቁ፣ ዝግጁ እና ትኩረታችሁን በእኔ ላይ አድርጉ፡፡ አይኖቻችሁን ሁልጊዜ ክፍት በማድረግ በተዘጋጀላችሁ በየትኛውም ወጥመድ ለመግባት አትሂዱ፡፡ ወጥመድ ስል ለምሳሌ የእናንተን እርዳታ የሚፈልግ አስቸኳይ የስልክ ጥሪ ሆኖ የእናንተን ጉልበት እንደሚጨርስ የምትገነዘቡት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ከእኔ የተላከ የእርዳታ ጥሪ አይደለም፡፡ ይህ የወንድማማች ፍቅር አይደለም፡፡ ይህ የሰይጣን ወጥመድና በዕረፍት ጊዜያችሁ በድካም ወድቃችሁ ኃጢያት እንድትሰሩ ወደ ፈተና የሚጋብዝ ነው፡፡"

"ሌላኛው ወጥመድ ደግሞ ትታችሁት የነበረን ነገር “ ይህን ነገር ማድረግ አለብኝ!' ብሎ በመነሳት የሚመጣ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ተረጋጉና ችግሩን አጢኑት፡፡ ራሳችሁን በዚያ ነገር ውስጥ ከማስገባታችሁ በፊት በሌላ መንገድ ያንን ችግር ማቃለል አይቻልም? በማለት መጀመሪያ በደንብ አስቡበት፡፡ ክሌር ለዚህ ነው በፊት ለፊት ካለው ቤት እንዳትሄጂ የከለከልኩሽ፡፡ ያ ትልቅ ፈተና ነበር፡፡ ምክንያቱም በትልቅ ድካም ሊጥልሽ ነበር፡፡ እስካሁን ከዛ እየራቅሽና በማስተዋል አካባቢሽን እየቃኘሽ ነው፡፡

"እንዲሁም የኢ-ሜሉ ጉዳይ እንደ ትሮጃኑ ፈረስ ሁሉንም ዓይነት “ማድረግ አለብኝ“ የሚል ሐሳብን የሚያስጀምር ነበር፡፡ ነገር ግን ያንንም ለመለየት ስለ ሰለጠንሽ በፈተናው አልወደቅሽም፡፡ ያ አንቺን ከእኔና ከአገልግሎትሽ የሚነጥል ትልቅ ፈተና ነበር፡፡ አንቺ ግን ተረጋግተሽ ሁኔታውን በጥሞና በማጤን ፍፁም አስፈላጊ የሆነውን መረጥሽ፡፡ ይህንን ነው ለመናገር የፈለግሁት፡፡ ሙሽሮቼ ተረጋግታችሁ በማወቅ ሁኔታውን አጥኑና ፍፁም አስፈላጊ የሆነውን ብቻ አድርጉ፡፡ ወጥመድ አለመሆኑንና ከውስጣችሁ ህይወታችሁን ሁሉ አሟጦ እናንተን ከፀሎት ለማራቅ እንዳልሆነ እርግጠኞች ሁኑ፡፡

“አሁን ማናችሁም ብትሆኑ አቅጣጫ መቀየር አትችሉም፡፡ ሙሉ ትኩረታችውን በእኔ ላይ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ፡፡ለዚህም ብቻችሁን አይደላችውም እኔ እረዳችኋለሁ ፡፡ መንፈሴ ለጆሮአችሁ “አታድርጉት“ በማለት ያንሾካሽክላችኋል፡፡ በተጨማሪም በመንፈሳችሁ ማረጋገጫ ታገኛላችሁ፡፡ የመጣላችሁን ያንን ሐሳብ ታዘዙት እንጂ በቀልድ አትመልከቱት፡፡ የኔ መንገድ መሆኑን ያወቃችሁትን ያንን ተከተሉ፡፡

“ይህ ነገር መሰራት አለበት . . . ያ ነገር መሰራት አለበት . . . የሚል የማያቆርጥ ግብግብ ከአለም ይመጣል፡፡ ነገር ግን ሞኞች አትሁኑ፡፡ አለም አለሙን ይቅበር እናንተ ግን እኔን ተከተሉ፡፡“

“ሙሽሮቼ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ ፡፡ ጊዜው እያለቀ ነው፣ እኔ ልመጣ ነው፡፡ በአለም ነገር እራሳችሁን አታድክሙ፡፡ ነቅታችሁ በመጠበቅ ጊዜያችሁንና ጉልበታችሁን ለእኔና ለእኔ ብቻ ቆጥቡ፡፡ በዚህ በፍፁም አትፀፀቱም፡፡

**በእምነት ላይ ተቃውሞ እየመጣ ነው / ማርች 30 ቀን 2015 ዓ.ም/**

**Attacks against the faith are on the way/ March 30, 2015**

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . ዛሬ ምሽት በፀሎት ጊዜ ጌታ በመስቀሉ ላይ ነበር፡፡ ሰውነቱ ሁሉ በደም ተጨማልቋል፡፡ እኔም ከእርሱ ጎን በግራው በኩል በመስቀል ላይ ተሰቅዬ ነበር፡፡ እርሱ ሁልጊዜ ያለው በቀኘ በኩል ነው፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ መሬቱ ላይ ቆሞ አየሁት፡፡ እኔንም በእጆቹ ይዞኝ ነበር፡፡ ሁለታችንም የሾህ አክሊል ደፍተን ነበር፡፡ እርሱም እጅግ እያለቀሰ ነበር፡፡

ኢሱስ እንዲህ አለ . . . "መራራ፣ መራራ፣ ማድረግ ያለብኝ ነገር እጅግ መራራ ነው ፡፡ ክሌር አፅናኘኝ፡፡ ዛሬ በእውነት ከእኔ ጋር እንድትቆዪ እፈልጋለሁ፡፡"

ጌታ እጅግ በጣም አዝኛለሁ፡፡ የበለጠ ታዛዥ እንደሆን እባክህ እርዳኝ፡፡

"አሁን እዚህ ከእኔ ጋር ነሽ፡፡ እናም ደስ ብሎኛል ከእኔ ጋር ቆዪ፡፡"

ጌታ ነገ እችላለሁ? እንዴት ከባድ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡

"ከእኔ አትራቂ በተለይም አሁን፡፡"

ጌታ መልዕክቱን እንዲህ በማለት ማስተላለፍ ጀመረ . . . ጊዜው እየቀረበ ሲሄድ በእምነትና በተስፋ ላይ ያለው ተቃውሞ እየበረታና እየተያያዘ ይሄዳል፡፡ በልሳን ስለመናገር እስካሁን የተነገረው ውሸት ሰይጣን አመንጭቶ ከለቀቀው ጋር ሲወዳደር ትንሽ ጉርምርምታ ብቻ ነው፡፡ በእምነት ላይ የሚነሳው ተቃውሞ አስፈሪ ነው የሚሆነው፡፡ ሁላችሁም ተዘጋጅታችሁ እንድትቆሙ እፈልጋለሁ፡፡ አምላካችሁ ትክክል እንደሆነ ሙጭጭ ያለ አቋም ያዙ፡፡ አምላካችሁ ትክክል መሆኑን አምናችሁ ችክ በማለት ከእኔ ጋር ቁሙ፡፡

"ይህንን ስል ምን ማለቴ መሰላችሁ፣ የሚመጣውን ተቃውሞ ሁሉ ሰብስባችሁ በውሸት ግድግዳ ላይ በምስማር አጣብቁት፡፡ ወደ አይምሯችሁ አስገብታችሁ አታስላስሉት፡፡ የሚወረወሩትን ሐሳቦች ሁሉ አታስተናግዱ፡፡ ነገር ግን ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር አመሳክሩት፡፡

በእናንተ ላይ የሚወረወር የትኛውም መሳሪያ አይከናወንም፡፡ ለሚከሳችሁ ሁሉ መልስ ይኖራችኋል፡፡ ይህ ለጌታ አገልጋዮች ሁሉ የተሰጠ ውርስ ነው፡፡ ማሸነፋቸው ከእኔ የተነሳ ነው፡፡ ጌታ እንዲህ ብሎ አወጀ "ከእኔ የተነሳ አሸናፊዎች ይሆናሉ፡፡ 54፡17 ኢሳያስ የጌታ ቃል ትርጉም "

"በአንቺ ላይ የተሠራ ማንኛውም መሣሪያ አይከናወንም በፍርድም በሚነሣብሽ ምላስ ሁሉ ትፈርጂበታለሽ። የእግዚአብሔር ባሪያዎች ርስታችሁ ይህ ነው፥ ጽድቃቸውም ከእኔ ዘንድ ነው፥ ይላል እግዚአብሔር፡-"

የኔ ሙሽሮች ክብሬን አስከብሩ፡፡ በከሳሼ ፊት ተከላከሉ፡፡ ምን ሊሆን እንዳለ ይህም ወደ እኔ እንደምወስዳችሁ ነግሬያችኋለሁ፡፡ ጠላት በእኔ ላይ ያላችሁን እምነት ለማስጣልና ነፍሳችሁን ከእኔ ለመንጠቅ ተስፋ በማድረግ የመጨረሻ አንድ ተከታታይ ሙከራ ያደርጋል፡፡

ስለ እኔና ስለ ክብሬ የቆማችሁ አገልጋዮቼ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ሐሜት የሚፍጥር ነገር መስማት የለባችሁም፡፡ በትልቅ ፍርሃትና ግራ መጋባት ወቅት ነው ጠላት መንገድ በማግኘት እምነታችሁን ለማጥፋት የሚሞከረው፡፡ እነዚህ ነገሮች እየተሰማችሁ ከሆነ ከአጋንንት ጋር ተጋጥማችኋል ማለት ነው፡፡ ከዚህ ስሜት ውስጥ ወጥታችሁ የሚጨቁናችሁን ለመጣል እንዴት ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ለዚህ ነው እኔን ለእርዳታ ጥሩ እያልኩ የማስጠነቅቃችሁ፡፡ ይህንን ሁኔታ ለብቻችሁ ለመጋፈጥ እንዳትሞክሩ፡፡ እነርሱ በኃይል በርትተው ሊያሸንፏችሁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም እኔን መጥራት አለባችሁ፡፡

"ክብሬን አስከብሩ፡፡ የተገለጠላችሁን እውነት አጥብቃችሁ ያዙ፡፡ እውነት ሆኖ ያወቃችሁትን ሊያስጥላችሁ የሚያሳድዳችሁን ጠላት አትፍቀዱለት፡፡ የብልጦችን ክርክርና ምክንያት አትስሙ፡፡ እኔ የሰጠኋችሁ እውነታ ጥቃት እንደተቃጣበት ሲሰማችሁ ተነስታችሁ ተሟገቱ እንጂ ወደ አይምሮአችሁና ወደ ልባችሁ እንዲገባ አትፍቀዱ፡፡

"ያለነው በጦርነት ላይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ጠላት እስረኛ አድርጎ ለመውሰድ ያለው የመጨረሻ እድሉ ነው፡፡ ቀድሞ ያወቀ ቀድሞ ይዘጋጃል፡፡ ሁልጊዜ 'ጌታ ከክፉ አድነን' እያላችሁ ፀልዩ፡፡ በዚህ ጊዜ ህዝቄኤል አንድ ነገር ለመጨመር ፈለገ፡፡ ጌታም "ትክክል ነው አለኝ"፡፡

"ሰላምንና ደስታን የሚረብሽ የትኛውም ነገር የአጋንንት ሥራ ነው፡፡ ፍርሃት ሲሰማችሁ አቁሙ፡፡ ቃሌን ተጠቅማችሁ ያንን ውሸት አጥፉት፡፡ ፍርሃት፣ ስጋት፣ ደህንነት ያለመሰማት፣ ጥርጣሬና መርበትበት፣ እነዚህ ሁሉ እናንተን ሽባ አድርጎ ለማጥፋት ጠላት የሚጠቀምባቸው የጦር መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ጥርጣሬ፣ ፍርሃትና ግራ መጋባት የአጋንንትን ጣልቃ ገብነት የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው፡፡ ለእግራቸው ጠንካራ መርገጫ ሥፍራ ከማግኘታቸው በፊት ሰይፋችሁን ያዙና አጥፏቸው፡፡

"ወደ እናንተ ለመምጣት ይሞክራሉ፣ ነገር ግን በአንድ አቅጣጫ ሲመጡባችሁ በሰባት አቅጣጫ እመልሳቸዋለሁ፡፡ ተዋግታችሁ በሰባት መንገድ እንዲመለሱ ለማድረግ እረዳችኋለሁ፡፡ እንዲሮጡና እንዲበተኑ አደርጋቸዋለሁ፡፡ ነገር ግን የእናንተን ትብብር እፈልጋለሁ፡፡

ከሌር በእኔ ላይ ለማረፍ ሞክሪ፡፡ የምናገረው ነገር በእርግጥ ለአንቺ እንደሆነ እውቅና ለመስጠት ሞክሪ፡፡ እባክሽ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አይምሮሽን ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዲዋልል አትፍቀጅለት፡፡ እሺ?

አዎን ጌታ የሚናገረውን እየሰማሁ እያለ መንቀጥቀጥ ጀመርኩ፡፡ እንዲህም አልኩ "ጌታ እርዳኝ፡፡"

"እረዳሻለሁ፣ እየረዳሁሽም ነው፡፡ ይህ መልዕክት ሰላምን ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ብሎ አንድ ላይ ሆነን የሰራነውን መልካም ነገር ጠላት እንዴት አድርጎ ሊመልሰው እንደሞከረ ተመልክተሻል፡፡ የአንቺንና በዚህ ጊዜ ጥበብ የሰጠኋችሁን የነቢያቶቼን ደስታ ሊሰርቅ፣ የውሸት ወሬ ሊነዛና ስም ሊያጠፋ እንደነበረ ተመልክተሻል፡፡ ውጤታማ እንዲሆኑ አትፍቀጅላቸው፡፡ ታማኝ መሆኔንና ሙሽራዬን በሐሴት ፣ በሙላትና በደስታ ወደ መንግስቴ ላስገባት የገባሁትን ቃል እንደምፈፅም ተሟገቺ፡፡ ክብሬንም አስከብሪ፡፡

እንደማስበው ከሆነ "ኢየሱስ በአንተ እታመናለሁ" ብለን በኃይል መጮህ አለብን፡፡

"እነዚህ ነገሮች የመጨረሻውን መልዕክቴን አስቀድመው አጉድፈውታል፡፡ የኔ ሙሽሮች  በእናንተ ላይ ያመጣውን ውጤት በማየት በጥቃት ላይ እንደሆናችሁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመንፈሳችሁ ዕረፍት የሚነሳ ምንም ነገር ሲገጥማችሁ በጥቃት ላይ ናችሁ፡፡ ጠላት ደስታችሁንና ሰላማችሁን ሰርቋችሁ እንዲሄድ አትፍቀዱለት፡፡ ሰይፋችሁን አንሱና ተዋጉ፡፡ ይህ ጊዜ ብዙ አይቆይም ነገር ግን ከባድ ይሆናል፡፡ ቀድሞ ያወቀ ቀድሞ ይዘጋጃል፡፡"

ጌታ . . .? (ጥያቄውን ገና ሳልጠይቀው መለሰልኝ)

"የመገናኛ አውታሮችን እጠብቃቸዋለሁ ብዬ አልነገርኩሽም?"

ነገር ግን እነርሱ ከሁሉ እንቅስቃሴ በፊት የመገናኛ አውታሮችን እናጠቃለን ብለው የለም? (በኤሌክትሪክ የሚደረጉ ማንኛውንም የመገናኛ ዘዴዎችን እንደ ኢንተርኔት፣ ኮምፒተሮችንና የመሳሰሉትን በኤልክትሮ ማግኔቲክ ፐልስ ማጥቃት)፡፡

"የኔ ውድ እነሱ እናደርጋለን የሚሉትና የኔ ችሎታ ለውድድር አይቀርብም፡፡ እኔ ከእነርሱ መንገድ በላይ ነኝ፡፡ እናም እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ልጆቼን በኢንተርኔት መገናኘት አስባለሁ፡፡ አዎ ለጥቂት ጊዜ መገናኘትን የሚያቃውስ የኃይል መቋረጥ ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ ሊያጠፉ የሚችለውን አልፈቅድም፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ክሌር አታምኚኝም? አየሽ እንደገና ኩራትሽ መጣ፡፡ ልትሟገቺለት ስለማትችይ አትቀበዪውም፡፡ ታሳፍሪያለሽ፡፡"

አዝናሁ፡፡ ጠላት እዚህ ደርሶ እንዳልሆነ እርግጠኛ ለመሆን ብቻ ነው፡፡

"ለዛ ደግሞ ትዕዛዝ ሰጥቼሽ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚያ የበለጠ ነው እያየሁ ያለሁት፡፡ በእውነቱ ከሆነ አንዳንዱ ሰዋዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ስለምወድሽ አምላክሽን እንኳን ጥያቄ ውስጥ ብታስገቢም አልተውሽም፡፡ እያልሽ ያለሽው እኮ 'ጌታ እርግጠኛ ነህ? እነርሱ በመጀመሪያ የሚያጠፉት ያንን ነው፡፡ ስለዚህም ያንን አያደርጉም ብሎ ለማመን ያስቸግራል፣ እርግጠኛ ነህ?' እያልሽ እኮ ነው ያለሽው? ምክንያቶችሽ ምን ያህል መሳለቂያ እንደሆኑ ታያለሽ?

አዎ ጌታዬ ፍርድ የሚገባኝ ጥፋተኛ ነኝ፡፡ በጣም አዝናለሁ፡፡ እባክህ እርዳኝ፡፡

"አሁን እያደረግሁ ያለሁት ያንን አይደለም?"

አዎ ማለቴ ገና ይህ ነገር መታየት ሲጀምር እባክህ ኩራቴን አስታውሰኝ፡፡ እባክህ?

"አዎ አደርጋለሁ፡፡ ነገር ግን ኩራትሽ ሁልጊዜ የሚመጣ ከሆነ መቼ ነው የማስታውስሽ? እንዲህ ከሆነ ነገሮችን መስራት እጅግ ያስቸግረናል፡፡ እንችላለን?

ኢየሱስ አንተ ካልክ . . .

"አዎ ብያለሁ፡፡ በይ አሁን ትንሽ የሳቅ ጊዜ ይኑረን፡፡ ከአንቺ ጋር መጫወትና የማይጠበቀውን ነገር መናገር ደስ  ይለኛል፡፡ በአይምሮሽ ስታመላልሽው ማየት ለእኔ ዝም ብሎ ጨዋታ ነው፡፡ በተጨማሪም በአንቺ አይምሮ ውስጥ የምሰራው ይህ ሥራ

በሌሎችም በሚያዳምጡሽ ውስጥ በምንም መልኩ ይኖራል፡፡ እናም እምነታቸውን የሚሸረሽረው ምን እንደሆነ እነርሱም ያያሉ፡፡"

ይህንን ስትል በዚህ ጉዳይ ብቻዬን አይደለሁም ማለት ነው?

"ዝንጀሮዎች በዛፎች ላይ ይጠላጠላሉ?"

እንደሚመስለኝ ሥራቸው ሁልጊዜ መንጠላጠል ነው፡፡

"ትክክል፡፡ ከእስራኤል ጋር ስንት መቶ ዓመታት ተቋቋምኳቸው? እናም እስካሁን እነርሱ ችክ ያሉ  የማያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስለ ሰው ፍጥረት አንድ ነገር ወይም ሁለት ነገር አውቃለሁ፡፡ አንቺስ ስለዚህ የምትይው የለሽም?

ያለኝ ይመስለኛል!

"በጣም ጥሩ አሁን እንቀጥል፡፡"

ጌታ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ትንሽ የሚያሳፍር ነበር፡፡

"የኔ ውድ የአንቺ ስህተት የሰው ልጆች ሁሉ ስህተት ነው፡፡ ይህንን ቀድሜ አልነገርኩሽም? እኔ እንዲያገለግለኝ ስፈልግ የነበረው የመጨረሻ ትንሽ ብቃት ያለውን ሰው ነበር፡፡ በዚህም ደረጃ አንቺን አግኝቻለሁ፡፡ ታዲያ አሁን ምኑ ነው የሚያሳፍረው? አንቺ ብቸኛዋ ልዩ ሰው እንደሆንሽ ይታይሻል?

ሳቅ፣ ጌታ አመሰግንሃለሁ፡፡ አዎ በእውነትም በራሴ ልዩ ነገር ተባርኬያለሁ፡፡

"በዚህ ምክንያት ለአንቺ ያለኝ ፍቅር ያነሰ እንደሆነ ለአንድ ደቂቃ እንኳን እንዳታስቢ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አንቺና እንደ አንቺ ያሉት ሙሽሮቼ ሁሉ ታናሽነታችሁ በእኔ ተወዳጅ አድርጓችኋል፡፡ ይህ ሪክ ጆይነር የትህትና ካባ ብሎ የተናገረው ነው፡፡ እንዲሁም ጳውሎስ በድካሜ እመካለሁ ያለው ነው፡፡ ይህም ገና ሳትወለዱ ጀምሮ ባዶ፣ ደሃና ደካማ ሆናችሁ እንድትወለዱ የተወሰነና ውጤታማ ለመሆንም የኔን ቅባት እንደሚያስፈልጋችሁ ምልክት ነው፡፡ በመንግስተ ሰማይ ይህ እጅግ ክብር ያለውና ምርጥ ነገር ነው፡፡ ሁሉም ሙሽሮቼ ነገሮችን በዛ መንገድ ቢመለከቷቸው እመኛለሁ፡፡

"ይህ መሆኑ በእናንተ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሚያስችለውን ዋነኛውን በር እንዲዘጋ ያደርጋል፡፡ አየሽ ጠላት ሁልጊዜ 'አንቺ ደደብ ነሽ፣ ምን ታውቂያለሽ፤ ማን የሆንሽ መሰለሽ? እግዚአብሔር ለአንቺ ይናገራል? ያስቃል፣ እየቀለድሽ መሆን አለበት፣ አንቺ እኮ የማትረቢ ነሽ፣ ለምንም ነገር የማትበጂ ነሽ' እያለ ያንኳስሳል ደግሞም ይዋሻል፡፡ እጅግ የሚወደው ነገር ደግሞ 'እንትናንና እንትናን አየሻቸው? እነርሱ አሁን አንድ ነገር ላይ ደርሰዋል፡፡ ብልሆችና ችሎታ ያላቸው ናቸው፡፡ አንቺ ግን ? ያስቃል ለምንም የምትበጂ አይደለሽም፡፡ የሆነ ሆኖ ያመንሽው ሁሉ ውሸት ነው! ታያለሽ' በማለት ነገሮችን በመበጥበጥ ቀንተሽ ኃጢያት እንድትሰሪ ማድረግ ነው፡፡"

"ስለዚህ ሙሽሮቼ ደህንነት እንዳይሰማችሁ የሚያደርገው ይህ በር እንዴት በሰፊው እንደተከፈተ ታያላችሁ? ልትዘጉት ትፈልጋላችሁ? እንዲህ በሉ 'አዎ ይህ ሁሉ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን በሚያበረታኝ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን እችላለሁ፡፡' ይህ

ክርክሩን ሁሉ የሚዘጋ ቃል ስለሆነ የሚጮሁትን ድምፆች ሁሉ በዚህ ዝጉ! እናም 'አምላኬ እኔን ሊጠብቀኝና መመሪያ ሊሰጠኝ የታመነ ነው' በሉ፡፡

"የኔ ውዶች አሁን የሆነ ድምፅ ስለ እኔ ባህርይ ሥም ለማጥፋት ቢሞክር ትክክለኛውን መልስ ትሰጡታላችሁ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ተነሱና ክብሬን አስከብሩ፡፡ እንደዛ አድርጋችሁ አፋቸውን ስትዘጉ እንዴት ተባርኬያለሁ! አያችሁ ጨዋኙ እናንተን ሊያጠቃ እያቀደ ያለውን እንዴት መመከት እንዳለባችሁ ጥቂት ትምህርቶች እየሰጠኋችሁ ነው፡፡ እባካችሁ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

"ሙሽራዬ (ህዝቄል) አንድ ነገር ሊነግርሽ እየፈለገ ነበር ፡፡ ክሌር አይደለም እንዴ?"

እምም?

ምንድነው ቅድም የነገርከኝ?

ረሳሁት፡፡

"ስለ ብዙ አስተማሪዎችና ስለ ብዙ ድምፆች?"

ትክክል በዚህ ጉዳይ ላይ ቀደም ብዬ አንድ ቪዲዮ ሰርተን ነበር፡፡ እናም ይህንን ቪዲዮ እንድትመለከቱት የዩቲዩብ አድራሻውን በስተመጨረሻ እፅፍላችኋለሁ፡፡ ይህም በውሸት መልዕክቶች በመናወጥና አንነጠቅ ይሆን ? ብለው በመስጋት ከጌታ ሙሽሮች ብዙ ደብዳቤዎች ደርሰውናል፡፡ እኔ ለማለት የምፈልገው ተጠነቀቁ ነው፡፡ አንድን ነገር ለማወቅ መጓጓት እንዴት ኃይል እንዳለሁ አውቃለሁ፡፡ እናም እየሰማችሁት ያለው ነገሮችን የመቆፈር መጥፎ ምግባር ያለውን ሰው ነው፡፡ ጌታ ግን ነገሩን በቁጥጥር ሥር ያደርገዋል፡፡ ሁላችንም ብንሆን ጌታ መልካም እንደሆነና የንጥቀቱ ተካፋይ እንደሚያደርገን ማረጋገጫ እንፈልጋለን፡፡ ሁላችንም ብንሆን አሁን በዚህ ሰዓት እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ ሁላችንም ስለ ንጥቀት ብዙ ነገሮችን ማረጋገጫ እንፈልጋለን፡፡ ነገር ግን ይህ ደግሞ መንፈሳዊ አለመብሰላትንና ግራ መጋባትን ይፈጥራል፡፡ ብዙ ሰዎችን በምትሰሙበት ጊዜ እነርሱ ያሉትን ሁሉ በየመልኩ ማስቀመጥ አለባችሁ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ነገሮችን ለማግኘት ብዙ የምንፈልገው ከደህንነት እጦት የተነሳ ነው፡፡ ጌታ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲህ ብሎኛል፡፡ "ስለ አንድ ነገር እውነት እንደተሰጠሽና ቅባት እንዳለው መንፈስሽ ከመሰከረልሽ በመፈለግ ዝም ብለሽ አትባክኚ፡፡" ይህ የሚያሳየው ደካማ እምነትንና አለማመንን ነው፡፡ ይልቁንም የተሰጣችሁን አሰላስሉት፣ አጥብቃችሁ ያዙት እንጂ የማወቅ ጉጉት ወጥመድ ውስጥ አያስገባችሁ፡፡ በእርግጥም ደግሞ ወጥመድ ውስጥ ያስገባችኋል፡፡

ጠላት እንድትፈፅሙ ለሚፈልገው ለእያንዳንዱ ኃጢያት ሁሉ የማወቅ ጉጉትን ይጠቀማል፡፡ መልካም ሰዎች ክፉ ነገሮችን እንደማይሰሙ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ለማወቅ ትልቅ ጉጉት እንዲኖራችሁ ካደረገ ብዙ ምንጮችን እንድትፈትሹና ግራ እንድትጋቡ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ያለማመንን በመፍጠር በእምነታችሁ ላይ ቀውስን ይፈጥራል፡፡ በተለይም ጠላት የእምነታችንን አቅጣጫ ሊያስቀይር እቅድ እንዳደረገ ጌታ እያስጠነቀቀን ባለንበት በዚህ ጊዜ መጠንቀቅ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም ማንን እንደምንሰማ ትልቅ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡

ካገኘናቸው ምንጮች ሁሉ አንዱ ለእኛ ተስማሚ ነው ብለን ካሰብንና ለመረዳታችንም አስተዋፅዎ ካደረገ በጥያቄ ውስጥ ከሚገቡ ከሌሎች ምንጮች ላለመጠጣት መጠንቀቅ አለብን፡፡ ለማወቅ በመጓጓት ያለማቋረጥ አንድን ነገር ስፈልግ ጌታ ከዚህ ድርጊቴ ሊያስጠነቅቀኝ በተደጋጋሚ ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚሰጠኝ ክፍል አለ፡፡

"ከጉድጓድህ ውኃ፥ ከምንጭህም የሚፈልቀውን ውኃ ጠጣ" ምሳሌ 5፡15፡፡ ይህ ክፍል ምንም እንኳን የሚያወራው ስለ ሞራል ውድቀት ቢሆንም ለአስተማሪዎችና ግንዛቤ ለማግኘት ለምንጠቀምባቸው ምንጮችም የሚሰራ ነው፡፡ በተለይም ባለ ድርሻ አካላት በበዙበት በዚህ ዘመን በትል የተበከለ ውኃን ከመጠጣት መጠንቀቅ አለብን፡፡

እኔ እንደማስበው ዕረፍት የሚያሳጣችሁ ነገር ካለ የተቀደሰ ጥሩ ፊልም እዩ፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር አልሞትም የሚለውን ፊልም፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ ወይም ስለ ኢየሱስ የተዘጋጀውን የምትወዱትን የትኛውንም ፊልም፣ ወይም የልዕልቷ ማስታወሻ 2 የሚለውን ዓይነት እንኳን ማየት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ፊልም የሚያሳየው አንዲት ተራ ሴት እንዴት ልዕልት ከዚያም ንግስት ልትሆን እንደቻለች የሚያሳይ ነው፡፡ ታዲያ እኛስ ብንሆን በመጨረሻው እንደዛ ለመሆን አይደለም እየሰራን ያለነው? ይህ አሁን የተነጋገርነው ትንሽ እንድናስብ የሚያደርገን ይመስለኛል፡፡

(ኢየሱስ) "የኔ ሙሽሮች በዚህ ላይ ልጨምር የምፈልገው አንድ ነገር ይህንን የሰጧችሁን ቃል በልባችሁ ብትይዙትና ለመታዘዝም ታማኝ ብትሆኑ እኔም ጠላት እንድትፈሩ ከሚያደርጋችሁን ወጥመድ ለመጠበቅ ታማኝ እሆናለሁ፡፡"

"ምንም የሚያስፈራችሁና የሚረብሻችሁ ነገር እንዳይኖር አሁን በረከቴን በእናንተ ላይ አደረግሁ፡፡  እኔ አምላካችሁ ነኝ እናንተም ሙሽሮቼ ናችሁ፡፡

https://youtu.be/Cj-7MR2BruA Confusion-Listening To Too Many Prophets on the Rapture

## እምነታችሁን ያለገደብ በእኔ ላይ ጣሉ / ኤፕሪል 8 ቀን 2015 ዓ.ም
## Unconditional Trust in Me/ April 8, 2015

(ክሌር)፡-  ጌታዬ ዛሬ ስለልፍለፋዬ ይቅር በለኝ፡፡

(ኢየሱስ)፡- "ደክሞሻል"

(ክሌር)፡- ደግሞም በጣም አዝናለሁ

ኢየሱስም . . . "ክሌር ይቅር ብዬሻለሁ፡፡ ብቻ አንቺ ሁልጊዜ ማስታወስ ያለብሽ እውነትን ተመርኩዘሽ ከእነዚህ ጥቂቱን ስታደርጊ ለእኔ እንዳደረግሽው ቁጠሪ፡፡ ይህም አመለካከትሽንና ቸርነት ማድረግን ቀላል ያደርግልሻል፡፡

(ክሌር)፡- አመሰግናለሁ፣ እባክህ ይህንን ሁልጊዜ እንዳስታውስ እርዳኝ፡፡

(ኢየሱስ)"ዛሬ ብዙ ጊዜ እንዳደረኩት?"

(ክሌር) አንተ ነበርክ ያደረከው?

(ኢየሱስ) ፡-"አዎ እኔ ነበርኩ፡፡ ደግሞም ረድቶሻል አይደለም?"

(ክሌር) በጣም ረድቶኛል፣ አመሰግናለሁ፡፡ እኔ በራሴ አፍሬያለሁ፡፡

(ኢየሱስ)፡- "ሰው ስለሆንሽ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ዛሬ ምሽት ልትናገረን በልብህ ያለው ምንድነው?

(ኢየሱስ)፡- "ስለ ንጥቀቱ ማስተማመኛ ያጣሽ አንቺ ብቻ ሳትሆኚ ብዙዎች ናችሁ፡፡"

(ክሌር)፡- ምን እናድርግ?

(ኢየሱስ)፡- "በፀሎት ቆዩ፡፡ በእያንዳንዱ ቀን የምልክልሽን ምልክቶች ተመልከቺ፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስሽ ውስጥ የሬማ ቃል አግኚ፣ የኔ ውድ እኔን አነጋግሪኝ፡፡ የልብሽን ጥያቄ አጫውቺኝ፡፡ አንቺን ለማዳመጥ በአጠገብሽ ነኝ፡፡ ደግሞም ለራስሽ አሳልፌ እንደማልሰጥሽ ቃል ገብቼልሻለሁ፡፡  እኔን መስማት በአስተማማኝ እስከትችዪ ድረስ አንቺን ለመርዳት ተስፋ አልቆርጥም፡፡ በልብሽ የመተማመን ማጣት ጥላ እየታየኝ ነው፡፡ ጎበዝ ሆኖ ግንባር ቀደም የሆነ እያንዳንዱ በተመሳሳይ መልኩ አይጨነቅም ብለሽ አታስቢ፡፡

"የክርስቲያኑ ማህበረሰብ ድክመትን፣ ውድቀትን፣ ፍርሃትንና ለእያንዳንዱ በግል እውነት የሆነውን  የኢጋንንቶች ትግል አይቀበልም፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ መሸፈኛ የሚሆናቸውን ቃል ማጣቀስ ተለማምደዋል፡፡ በዚህም በፊታቸው ላይ የውስጥ ስሜታቸው እንዳይንፀባረቅ መሸፋፈንን ተምረዋል፡፡ ይህ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ ይህም አንዳንዶችን ትልቅ ሲያስመስል ሌሎችን ደግሞ ፈሪ አድርጓቸዋል፡፡ በእኔ አመለካከት ግን ሁላችሁም ፈሪዎች ናችሁ፡፡ ስለዚህም ይህንን መሸፋፈን ትታችሁ አንዳችሁ ለአንዳችሁ እውነተኛ ሁኑ፡፡

"ሊደረስባችሁ እንደሚቻል ፣ ቅኖች፣ ልትጎዱ የምትችሉና እውነተኞች ሁኑ፡፡ በዚህ ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ስትሆኑ ነው ቅባቱ የሚንቀሳቀሰው፡፡ በእነዚህ ዝቅተኛ ሥፍራዎች፣ በታናናሾችና ከሁሉም ታናሽና ደካማ በሆኑት ላይ፣ ከህይወት ይልቅ እኔ እንደማስፈልጋቸው በሚናገሩት ላይ የሚያነፃውና የሚያደምቀው ቅባቴ ይፈሳል፡፡ ለእነዚህ ነው እኔ ከፍተኛ ዋጋ የምሰጠው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ በእኔ ፊት ራሳቸውን የሚመለከቱት በእውነት እንደሆኑት ነው፡፡

"ከነዚህም ውስጥ አንዱ ዳዊት ነው። እርሱ ከጎኑ እንደሆንኩ ያውቅ ነበር። ነገር ግን በእኔ ፊት ታናሽ እንደሆነ ስለሚያውቅ ታላቅነቱን ሌሎች እንዲያደንቁለት ጊዜ አላጠፋም። በአንፃሩ ግን በእያንዳንዱ እርምጃው ከአንበሳ ጀምሮ እስከ ግዙፉ ድረስ እኔን ይፈልግ ነበር። በእኔ ላይ መተማመን ባቆመ ጊዜ ግን ወድቀት ደርሶበታል። ይህም ቢሆን እንኳን በወደቀ ጊዜ በእኔ ፍቅርና ይቅርባይነት በመተማመን ወደ እኔ መጥቶ ነበር። እርሱ ምህረቴንና ይቅርባይነቴን በህይወቱ ስለተለማመደ ባህርዬን ያውቅ ነበር።

"በእኔ ጥበብ መደገፍ ስታቆሙ ትወድቃላችሁ።"

(ክሌር)፡- ጌታ ታውቃለህ ዛሬ ምሽት እንደገና እየታገልኩ ነው ያለሁት። እንዴት ነው የምታስተካክለኝ?

(ኢየሱስ) "ይህ ቀላል ነው። ምክንያቱም እንደምትወጂኝ ስለማውቅ በመጨረሻ ፍቅሬ ያሸንፍሻል። ምን እንደሚሰማሽ እያየሁ ነው። ጥበብሽ በአንቺ ላይ ሊሰለጥን እየፈለገ ነው። ጠላት ሥራውን እየሰራ ስለሆነ እዚህጋ ቦታ አንስጠው። ክሌር ውጊያ ላይ ነሽ። ስለዚህም ብቸኛው ተስፋሽ በእኔ ላይ ፍፁም በመታመን ራስሽን ለእኔ አሳልፈሽ መስጠት ነው።

"ፈተናዎቹና ግፊቱ እየጠነከረ ስለሚሄድ ብዙ መዳዝ አያስፈልግሽም። እኔንና የነገርኩሽን አጥብቀሽ እስኪያዝሽ ድረስ ልትወጪው ትችያለሽ።"

(ክሌር)፡- ጌታ አንተ የምትመጣው የቁጥቋጦው አበባ ገና እየፈካ እያለ ነው በሚለው ሐሳብ ላይ ጭራሽ ደህንነት እየተሰማኝ አይደለም። ስሜቶቼና ምክንያቶቼ ይህንን ሐሳብ ለመቀበል አሻፈረኝ ብለዋል። በተጨማሪም ስለ ፈውስ አገልግሎት የተነገሩኝ ትንቢቶችና የሰጠኸኝ ራዕዮች ብዙ ነፍሳትን እንደሚሰቡ ሁሉ ከንጥቀት በፊት የሚከናወኑ ይመስለኛል።

(ኢየሱስ)፡- "ከኩራትሽና ከማሰብ ችሎታሽ የተነሳ ስለዚህ ጉዳይ እንደገና ምክኒያታዊ እየሆንሽ ነው። ክሌር እነዚህ ጠንካራ ኃይል ናቸው። ይህ ደግሞ ምንም ሳትጠራጠር በአባቷ የምትተማመነውን የህፃን ልጅ ቅንነት የሚቃረን ነው።

"ነገር ግን በልብሽ 'ቢገለኝም እንኳን፣ ለስህተት ቢጥለኝም እንኳን፣ ለመጨፍለቅና ለመቃጠል እንኳን አሳልፎ ቢሰጠኝም አፈቅረዋለሁ' ብለሽ ማሰብ ብልህነት ነው። ይህ ከሁኔታ ውጪ የሆነ ፍቅርና መተማመን ነው። አንድ ሰው እንዳለ 'እኔ የጌታዬ ትንሽ ኳስ ነኝ። በአልጋ ሥር ሊወረውረኝና እዛው ሊተወኝ ይችላል። የእጅ ውርወራ ሊጫወትብኝ ይችላል። ከግድግዳው ጋር ሊያላትመኝ ይችላል። በመደርደሪያው ላይ አስቀምጦኝ ሊረሳኝ ይችላል። ዋናው ቁም ነገር እኔን ምን እንደሚያደርገኝ ሳይሆን ሁሉ ነገሬ የእርሱ መሆኑ ነው።'

"የኔን ሰላም ሰጥቼሻለሁ፡፡ ስለዚህ ሁሉን ምክንያትሽን ወደ ጎን ትተሽ በሙሉ ልብሽ ከእኔ ጋር ተጣበቂ፡፡ የአንቺን አስተያየት ተዪው፡፡

(ክሌር)፡- ጌታ ሆይ ትረዳኛለህ?

(ኢየሱስ)፡- "አዎ የእኔ ውድ በእርግጠኝነት እረዳሻለሁ፡፡ እናም ለሁላችሁም ሙሽሮቼም የምለው ይህንን ነው፡፡ አሁን በውጊያ ላይ ናችሁ፡፡ የጦፈ የፍርሃት፣ ደህንነት የማጣት፣የጥርጣሬ ጦርነት ላይ ናችሁ፡፡ ባለፈው ሳምንት ይህ እንደሚመጣ አላስጠነቀኳችሁም?"

ያዕቆብ 1፡2-3 <u>ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፡፡4ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም። 12 በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።</u>

## ከእኔ ጋር የቅርብ ወዳጅነት ስትመሰርቱ የምትከፍሉትን ዋጋ ተምኑ/ ኤፕሪል 13 ቀን 2015 ዓ.ም

## Count the Cost of an intimate relationship with Jesus / April 13, 2015

በትላንት ምሽት ያስተዋልኩት አንድ ነገር ቢኖር ከጌታ ጋር የነበረኝን ልምምድ ለእናንተ ማካፈል ስጨርስ እርሱ መልዕክቱን መናገር መጀመሩን ነው፡፡ ስለዚህም ከአሁን ወዲያ እንደዚህ ማድረግን እሞክራለሁ፡፡

ዛሬ ምሽት ከጌታ ጋር የነበረኝ ቅርበት እንቅፋት እንደገጠመው ሆኖ እንደገና ተሰማኝ ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ጌታን በማምለክ እያንዳንዳችሁን በዙፋኑ ፊት በማቅረብ በሚያስፈልጋችሁ እንድትባረኩ እየፀለይኩ ነበር፡፡ በመጨረሻም በቴሪ ማልኮም ሙዚቃ ከኢየሱስ ጋር ተረጋግቼ ዘና ማለት ስጀምር ከአምስት መቋረጦች በኋላ ከእርሱ ጋር መገናኘት ቻልኩ፡፡

በርህራሄ አይኖቹም ሲመለከተኝ ምንም ማረግ አልቻልኩም የቀለጥኩ ያህል ተሰማኝ። ከዛም በፍፁም ፍቅሩ ተማርኩ፣ በፍቅሩ ሰከርኩኝ ማለት እችላለሁ፡፡ የነበረኝን ዕድል ተጠቅሜ ሙሉ በሙሉ ዘና ብዬ፣ ለረጅም ጊዜ ዓይኖቹ ውስጥ ተመለከትኩ፡፡ ይህም ፍፁም በቤቱ ውስጥ እንዳለሁ እየተሰማኝ ነበር። እንደዚህ ከዚህ በፊት ሆኖ አያውቅም፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት ሁልጊዜ ትንሽ ፍርሃት ነበረብኝ፡፡ ዛሬ ምሽት ግን ያንን ፍርሃቴን ችላ በማለት ዝም ብዬ እንድመለከተው ራሴን አስገደድሁት።

እኔና ሕዝቅኤልን እግዚአብሔር አንድ ላይ እንዳመጣን ስንገነዘብ ከጭነት መኪና ጀርባ ተቀምጠን በሮችን ከፍተን ህፃናቶቹ ያለማቋረጥ ሲጫወቱ እንመለከት ነበር፡፡ በዛን ጊዜ በመካከላችን የነበረው ኃይል በጣም ጣፋጭና ጥልቀት ያለው ነበር፡፡ ታዲያ ያን ጊዜ ምንም ቃል ሳንናገርና ምንም እንቅስቃሴ ሳናደርግ በእንደዚያ ሁኔታ በትንሹ ለአንድ ሰዓት ያህል እንቆይ

ነበር፡፡ አብረን በመሆናችን ብቻ እንዲሁ እንደሰት ነበር፡፡ አሁንም እንኳን በጭነት መኪና ጀርባ ላይ ተቀምጠን የነበርንበትን ጊዜ እንጠቅሰዋለን፡፡ ዛሬ ከኢየሱስም ጋር የነበረኝ ልምምድ ይህንን ይመስል ነበር ፡፡ በማንነቴ ላይ በእርሱ ፊት እምነት ነበረኝ፡፡ በትንሽነቴ ምክንያት አላፍርም ወይም ለመደበቅ አልሞከርኩም፡፡ በዚሁ ማንነቴ እንዲሁ እንዲወደኝ ፈቀድኩለት፡፡

ኢየሱስን እንዲህ አልኩት 'ውስጤንና ውጪዬን፣ ጀርባዬን፣ ስህተቶቼን ሁሉ፣ የማስበውን፣ ጉድለቶቼንና የመሳሰሉትን ሁሉ ታውቃለህ፡፡ ስለዚህ ዓይኖችህን ለመመልከት የማፍርበት ምንም ምክንያት የለኝም፡፡'

እነዚያ አፍቃሪ አይኖቹን መመልከት በቀጠልኩ ጊዜ በእጆቹ ውስጥ በመሆኔ ቤቴ እንዳለሁ ተሰማኝ፡፡ ይህም ደግሞ በጣም ትክክል፣ ተፈጥሮአዊ ፣ ሙሉ በሙሉ ዘና የሚያደርግና ዋስትና ያለው ሆኖ ተሰማኝ። ከቅዱሱ መደበቅ አያስፈልገኝም፡፡ ማንነቴና ሥራዬ ለእርሱ ግልፅ ነው፡፡ እርሱም ደግሞ ተመችቶታል፣ ዘና ብሏል፣ ደህንነትም ተሰምቶት ነበር፡፡

ይህ ለእኔ የሚገርም አዲስ ምዕራፍ ነበር ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ በፍርሃት መሮጥ ፣ መደበቅ ወይም መደናገጥ አይኖርም፡፡ ከአሁን ወዲያ የምፅናናው በሚያውቀኝና ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በሚወደኝ ነው፡፡ ፍርፋሪ ብስኩቶቼን የማካፍለው፣ ስለ ልጆቼ ጭቃ ጂንስ የማዋየው፣ የልጆቼ ልብስ ጭቃ ሳይነካው እንዴት አድርገን ወደ ጭነት መኪናው እንደምንመልሳቸው የማዋራው! ይህ በጣም የሚገርምና ለእኔ ምን ዓይነት ግንኙነትና አዲስ ምዕራፍ እንደሆነ!

ኢየሱስም እንዲህ አለኝ "ይህን ለብዙ ጊዜ ስጠብቀው የነበረ ነገር ነው፡፡ ያለቅድመ ሁኔታ እንደ ግማሽ አካልሽ በእውነትም እንደ ባለቤትሽ እንድትቀበይኝ ስጠብቅ ነበር፡፡ "እኔም 'ይህ ሕዝቅኤልን አያስቀናም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡' በማለት አሰብኩ፡፡

ነገር ግን በኋላ ዕረፍት ለማድረግ በሄድኩ ጊዜ 'የኔ ማር ከኢየሱስና ከእኔ ጋር አብረህ ና ተኛ፣ ከመኪናው ጀርባ እንዳለ ይሰማኛል' አልኩት ፡፡ እርሱም ከጌታ ጋር በዚያ አስደሳች ሥፍራ እንድቆይ ነገረኝ፡፡ ያለን አንድ መኪና ብቻ ስለ ነበር ያንን አንዱን መጋራት ስለነበረብን ነው፡፡ ታዲያ ህዝቄኤል ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማኝ አውቋል፡፡ ምክንያቱም እርሱም ያንን የተረጋጋ፣ ተወዳጅ የሆነውንና የተለመደውን የኢየሱስን ፍቅር አልፎበት ስለነበረ ነው፡፡

አንድ የተገነዘብኩት ነገር በእኛ ላይ ብዙ ትችት እየቀረበብን ያለው እኛ በምናካፍላችሁ ነገሮች ነው፡፡ አንድ ሰው አንድ ቀን አንቺ የሁሉንም ሰው ትኩረት በመሳብ ብዙ አድናቂዎችን ለማግኘት የምትጫወቺ ከፉ ሴት ነሽ አለኝ፡፡ በዚህ ጊዜ መሳቅ ነበረብኝ፡፡ ደግሞም እንዲህ ብዬ ማሰብ ነበረብኝ፡፡ ነገሩ አልገባችሁም አይደል? ይህ ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ ነው፡፡ የእኛን ቻናል የምተከታተሉ ሰዎች ኢየሱስ ምን ያህል እውነት መሆኑንና እናንተም ከእርሱ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ቅርበትና ግንኙነት እንደሚኖራችሁ የሚያሳይ ነው፡፡ እኛ እዚህ ያለነው ሙሉ ልባችሁን ለጌታ ለመስጠት ፈቃደኞች ከሆናችሁና የማይረባውንና ባዶ የሆነውን ሁሉ ከህይወታችሁ ካስወገዳችሁ ከእርሱ ጋር ህብረት መፍጠር ምን ያህል ቀላል እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡ ስለዚህ ማናችሁም ሰውን ለማድነቅ ከሆነ ያላችሁት ትኩረት ወደሚገባው ነገር ተመለሱ፡፡ እኔ ምን ያህል መጥፎ እንደነበርኩ ስንት ጊዜ ልንገራችሁ?

አሁን የገባኝን ታውቃላችሁ?... ነቢያት የእውቀት ቃል ይቀበላሉ፡፡ ጌታን ይሰሙታል ደግሞም ያዩታል ፡፡ ነገር ግን እንደ ሙሽራና እንደ ሙሽሪት ባለ ግንኙነት ለምንድነው ጌታን መስማትና ማየት ማንችለው? የተወደደው ዮሐንስ ራሱን በኢየሱስ ደረት ላይ አደርጓል፡፡ ታዲያ እኛስ ለምን አንችልም??? እናም ይህንን ተገነዘብኩ ጌታ ቃል መስጠት ቢወድም እርሱ የእድል ኩኪሶችን እንደሚረጭ ማሽን ሆኖ ብቻ መታየት አይፈልግም፡፡ ቃል ለመስጠት ብቻ ሳይሆን እርሱ ለእኛ በሆነው ማንነቱ

ከእርሱ ጋር ህብረት እንድናደርግና ከእርሱ ጋር እንድናሳልፍ እጅግ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ ዮሐንስ ማድረግ ከቻለ እኛም ማድረግ እንችላለን !!! አሜን....

ኢየሱስም በእርጋታ እንዲህ አለኝ . . . "አሁን እንድናገር ትፈልጊያለሽ?" እኔም አዎን ጌታ ሆይ እባክህ አልኩት፡፡

"ዛሬ ማታ ያገኘሽው የደስታን እውነተኛ ምስጢር ነው፡፡" ወደ ልቡ እየጠቆመ "ሁሉም መንገዶች ወደ ቤት ይወስዳሉ፡፡"

"ይህ ሁላችሁም ያጋጠማችሁ ባዶነትና ለንጥቀቱ ያላችሁ ጥልቅ ፍላጎት እንዲሁም ሁላችሁም የምትጓጉት ይህንን አንድ ለአንድ የሆነውን ፍቅር ፍለጋ ነው፡፡ ሁላችንም በሞት እንኳን ቢሆን(ለሚሞቱት) ከዚያም በበለጠ ቢሆን እስከመጨረሻው አብረን ነን፡፡ ስለሆነም ከአሁን ወዲያ በጭራሽ አንለያይም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ልትጎዱኝና እኔም እጅግ ዝም ልል እችላለሁ፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን እኔ ከእናንተ ጋር መሆን ያስፈልገኛል ደግሞም እፈልጋለሁ፡፡ እኔ የምፈልገው እንደ ታማኝ የህይወት ፍቅረኛ፣ ፈታ ብሎ አብሮ እንደሚኖርና እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ እንድትቀበሉኝ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እኔን መስማትና ማየት የማትችሉበት መሰዋዕትን መክፈል ያስፈልግ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ይህንን የእናንተን ስቃይ ሌሎችን ነፍሶች እየረዳሁበት ስለሚሆን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ግንኙነት በውስጣችሁ ያለ የእግዚአብሔር ቅርፅ ያለበት ሥፍራ ነው፡፡ ይህ በልባችሁ የሚገኘው ባዶ ሥፍራ ሌላ ሰው ፣ ሌላ ነገር፣ ምንም ነገር በጭራሽ ሊያረካው የሚችል አይደለም፡፡

"ለዚህ ነው የእኔና የክሌርን አይነት ግንኙነት ከእኔ ጋር እንዲኖራችሁ የምትጓጉት፡፡ ምክንያቱም እኔ እንድትፈልጉ ስላደረግኋችሁ ነው፡፡ እናም አሁን ሃይማኖት ይህን እጅግ ውድ የሆነ እውቀት እንደወሰደባችሁ እየተረዳችሁ ነው፡፡ እውነት ነው ይህ ጊዜ ሙሽራይቱ ወደ ሙሽራው መጥታ ቅዱስ ጋብቻ አንድ ላይ የምንፈፅምበት ስለሆነ ማንም ሰው በእኔና በእናንተ መካከል የማይገኝበት ነው፡፡ ይህ ሥፍራ ለእኔና ለእናንተ ብቻ ተቀድሶ የተከለለ ሥፍራ ነው፡፡

"ብዙዎቻችሁ ቀደም ብላችሁ በዚህ መንገድ ቀርባችሁኛል፡፡ ነገር ግን አሁንም በፍርሃት ወደኋላ ታፈገፍጋላችሁ፡፡ ይህም እኔን በመፍራት፣ ፈራጅ የሆነውን ኃያሉን አምላክ በመፍራት፣ ወደ እኔ ከመቅረባችሁ በፊት ፍፅምናን የሚፈልገውን እኔን በመፍራት ነው፡፡

"ይህ ከእውነት የራቀ እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከእኔ ውጪ ወደ ፍፅምና ልትደርሱ በፍፁም አትችሉምና ነው፡፡ ይህ ለእናንተ ፍፁም የማይቻል ነገር ነው፡፡ ከሰይጣን ውሸት በተገኘ ሃማኖታዊ አመለካከት የተነሳ ህይወታችሁን ሁሉ ከእኔ በመራቅና እኔን በመሸሽ ትፈጃላችሁ፡፡ እኔ አሁን ለእናንተ ለእያንዳንዳችሁ የምላችሁ ይህ ነው ከእኔ ርቀታችሁን የምትጠብቁት እኔን ስለፈራችሁ ነው፡፡ ስለዚህም እኔ ሳልሆን የራቅኋችሁ እናንተ ናችሁ በመካከላችን ግንብን ሰርታችሁ የራቃችሁኝ፡፡

"ይህ ምን ያህል ትርጉም የለሽ እንደሆነ ታያላችሁ? እኔን መፍራት እንደማያስፈልግ ታያላችሁ? የበለጠ በተጎዳችሁ ቁጥር የበለጠ እኔን እየፈራችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ፍቅር በጭራሽ አታውቁም፡፡ ቅርብ ከመሆናችሁ በፊት ከቅድመ ሁኔታዎች ውጪ የወደድኳችሁን ፍቅር ልታውቁ አትችሉም፡፡ እስካሁን የምታውቁት እያንዳንዱ ሰው ስለ እናንተ አንድ የሚጠብቀው ነገር እንደሚኖር ነው፡፡ እናም ወዲያው ይሁን ቆይቶ ያንን ሰው አሳዝናችሁት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ጥሩ ስሜት ተሰምቷችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህም አይነት ጠላት በተደጋጋሚ መቀራረብን እንድትፈሩ አስተምሯችኋል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁልጊዜ ህመምን ይዞ ስለሚመጣ ነው፡፡ ህመም፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ውድቀትና እኔ በአስፈላጊው መጠን ጥሩ አይደለሁም ወደሚል አመለካከት እንደገና ይመልሳችኋል፡፡

"እኔ ሰው ስላልሆንኩ ከእኔ አንዳች ነገር መደበቅ አትችሉም፡፡ እኔ ወደ እናንተ ስመጣ እናንተ ስለራሳችሁ የማታውቁትን ነገሮች እንኳን አውቃለሁ፡፡ ስለራሳችሁ ያንን ብታውቁ ኖሮ  እጅግ ከማፈራችሁ የተነሳ ደንግጣችሁ ለእኔ ግልፅ አትሆኑም ነበር፡፡

"ስለዚህ የራሳችሁን ሐሳብ ትታችሁና እናንተ ብቁ አይደላችሁም እያለ ጣቱን የሚጠቁምባችሁን የሃይማኖት አስተሳሰብ ትታችሁ ወደ እኔ ኑ፡፡ 'አንተ ራስህን ማን እንደሆንክ ነው የምታስበው? አንተ እኮ ኃጢያተኛ ነህ ! እስቲ ከአስር ደቂቃ በፊት ምን እያሰብክ እንደነበር ተመልከት! እርሱ እኮ አምላክ ነው፣ እንደ አንተ ዓይነት ሰዎችን ለማናገር አይፈልግም፡፡ አንተ ተሞኝተሃል ደግሞም ተታለሃል!' ይላችኋል፡፡ ይህ ነው ከእኔ የሚያርቃችሁ፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጠኝነት የሃይማኖት መንፈስ ነው፡፡

ከሌር) ጌታ ...እንትናስ . . .?

(ጌታ) ጃይደንን ነው?

(ከሌር) አዎ

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ጃይደን እኔ እወድሻለሁ ነገር ግን አንቺ እውነተኛ ፍቅር በጭራሽ ስለማታውቂ ይህ ፍርሃት አለብሽ ፡፡ ሰዎች በተደጋጋሚ ሳይቀበሉሽ በመቅረት ያንን ፍርሃት በአንቺ ላይ አስቀምጠዋል፡፡ እኔ ግን ማን እንደሆንሽ አውቃለሁ፣ የቱጋ ጠንካራ እንደሆንሽ፣ የቱጋ ደካማ እንደሆንሽ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እኔ ወደ አንቺ የመጣሁት አሁን ባለሽበት ማንነትሽ ላፈቅርሽና የተሰበረ ልብሽን ለመጠገን ነው፡፡ ለእኔ በመልካምነት ብቁ ልትሆኚ አይገባሽም፡፡ እኔ ለአንቺ ጥሩ ነኝ? እኔን ልታምኚኝ ትቺያለሽ ? ለመሆኑ ስሜ ፍቅር፣ ደስ የሚል፣ አስደናቂ፣ የሚያጽናና፣በምንም ሁኔታና ሁል ጊዜ ከአንቺ ጋር የሚገኝ መሆኑን ታውቂያለሽ?

"ሃይማኖት ከእኔ ጋር እውነተኛ ግንኙነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙን አበላሽቶታል፡፡ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን በጠራኋቸው ጊዜ እነርሱ ረዳቶቼና ወዳጆቼ ነበሩ ፡፡ ከእነርሱ ጋር አውርቻለሁ፣ ተጉዣለሁ፣ ተመግቤያለሁ፣ ከዋክብቶች በሚገኙበት ምሽት አብረን ሜዳ ላይ ተኝተናል ። እኔ ለእነርሱ እውነት ነበርኩ፡፡ ከሁላችሁም ጋር መሆን የምፈልገው እንደዚህ ነው። ሃይማኖት ግድግዳዎችን፣ መሰናክሎችንና ሁኔታዎችን በመካከላችን አስቀምጧል፡፡ እኔ ግን ይህ እንዲሆን አልፈልግም ነበር፡፡ እኔ ሁልጊዜ እንዲሆን የምፈልገው ከአዳምና ከሔዋን ጋር እንደነበረኝ ዓይነት ግንኙነት እንዲኖረን ነው፡፡ በምድር ላይ ከኖሩ ሰዎች ሁሉ ሰው ሊረዳኝ ያልቻለ ሰው ቢኖር እኔ ነኝ፡፡ ሰው የኔን ማንነት ወስዶ ከእኔ ውስጥ አንድ ጭራቅ ፈጥሯል፡፡

"ሰዎች ናቸው ጭራቆቹ፡፡ እነርሱ በጥላቻ ፣ በምሬትና በቁጣ የተሞሉ ሆነው ሳለ እኔን ግን እንደዛ አድርገው ስለውኛል፡፡ የእኔ ባህርይ ለስላሳ፣ ደግ ፣ተራና አብሮ ለመሆን የቀለለ ነው፡፡ በቀደመው ዘመን አባቴ በዚያ መንገድ የተገለጠበት ብቸኛው ምክንያት ሰዎች ኃጢያተኞች ስለሆኑ ንፁሆችን ሲያጠፉ፣ ልጆችን ሲገድሉ፣ ቤተሰብን ሲያጠፉ፣ ሲሰርቁ፣ ሲዋሹና ሲያጭበረብሩ ስለነበረ ነው፡፡ ይህም ንፁሆችን ስለጎዱ ነው፡፡ እኔ እንዳቀድኩላቸው ቢኖሩ ኖሮ ከምድረ ገፅ በጭራሽ እንዲጠፉ አላደርጋቸውም ነበር፡፡

"ነገር ግን እኛ እጅግ እውነተኛ የሆነ ጠላት አለን፡፡ እነዚህም የወደቁ መላእክቶች ሲሆኑ እነርሱም በሽታ አምጪዎች፣ አሰቃያሚዎች፣ ከፋዎች፣ አሰቃቂዎች፣ ሰዎችን ለመጉዳትና ምድርን ለማጥፋት ቆርጠው የተነሱ ናቸው፡፡ እናም ሰዎች በእነሱ ዕድል ፋንታ ውስጥ ሲጣሉ፣ አባቴ አንድ እርምጃ በመሄድ ትክክለኛ ፍርድን በማምጣት  ፍትህን ማስፈን ነበረበት፡፡ አሁን ምድር እየተጋፈጠች ያለችው ነገር ይህንን ነው፡፡ ይህም ፍርድ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የአባቴም ይሁን የእኔ ባህርይ አይደለም፡፡ እኛ ለስላሳ፣ የዋህና ደግ ነን፡፡ ነገር ግን ኃጢያትንና ክፋትን ካልቀጣን ሰዎች ያንን አጋጣሚ ይጠቀሙበታል፡፡

"አያችሁ እኔ በአብዛኛው ጊዜ ጠላት እንደሚያስቀምጠኝ አይነት አይደለሁም፡፡ ስለዚህ ወደ እኔ ኑ ፡፡ እኔ በልቤ የዋህና ትሁት ስለሆንኩ ለነፍሳችሁ ዕረፍት እሰጣችኋለሁ፡፡ በመካከላችን መጋረጃና መሰናክሎችን ማስቀመጥ አቁም፡፡ ያለምንም ህፍረት ወደ ዓይኖቼ በመመልከት ለእናንተ ብቻ የሚያንፀባርቀውን ፍቅሬን ተመልከቱ። በእምነት አንድ እርምጃ ተራመዱና እኔ ነኝ ያልኩትን እኔ እንደሆንኩ እመኑ ፡፡

"ክሌር መተኛት ትፈልጊያለሽ ?"

አዎን ጌታዬ እንቅልፍ ሊጥለኝ ነው፡፡

"ከእኔ ጋር እረፊ ፣ ይህንን እንመለስበታለን፡፡"

ጌታ አመሰግናሉ፡፡ ስለተረዳኸኝ አመሰግናለሁ ፡፡

"አንቺ ሚስቴ ነሽ ፣ ለፍላጎትሽ ክብካቤ ማድረግ አይገባኝምን?

(ክሌር)፤- ከአንድ ሰዓት በኋላ ከእንቅልፌ ስነቃ በጣም የሚገርም ነው ጥሩ ስሜት ተሰምቶኝ ነቃሁ፡፡ ከትንሽ የእንቅልፍ ዕረፍት በኋላ አሁን መቀመጥ እችላለሁ፡፡ እናም ይኸው እንደገና ከእኔ ጋር ነህ! ለምንድነው በማንኛውም ጊዜ ከአንተ ጋር እንደዚህ ቁጭ ብዬ ማውራት የማልችለው?

(ኢየሱስ)፡-  "እኔ አትችይም አላልኩም፡፡ እነዚህን ገደቦች በእኔና በአንቺ መካከል ያስቀመጥሽው አንቺ እንጂ እኔ አይደለሁም፡፡ እኔ በመጀመሪያ የአምልኮን ጊዜ አብረን ብናሳልፍ በጣም ነው የምወደው ፡፡

(ክሌር)፡-  ጌታ ዛሬ ማታ ከእዚህ መውጣት እንደማልፈልግ ታውቃለህ፡፡

(ኢየሱስ)፡-  እኔ የማውቀው በአንቺ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ቅርፅ ያለውን ሥፍራ ለመሙላትና እያንኮራፋሽም ቢሆን ጉዞሽን ለመቀጠል ሁልቀን እንዲሁም ሁልጊዜ እንደማስፈልግሽ ነው፡፡

(ክሌር)፡-  ጌታ እንዲህ ማለትህን አላምንም።

(ኢየሱስ)፡- "ደህና ይህ ትክክለኛ ቃል አይደለም?"

(ኢየሱስ)፡- "ይህ የማይሆን ነው፡፡ አሁን ገና ሞኝ እየሆንሽ ነው! ሰዎች እየተናገርኩሽ ያለሁት በእውነት  እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆንኩ በጭራሽ ሊያምኑሽ አይችሉም፡፡

(ኢየሱስ)፡- "አንቺ ግን እኔን ማን ትይኛለሽ?"

(ክሌር) ፡- አንተ እስካሁን ገጥሞኝ የማያውቅ እጅግ አስደናቂ፣ ጨዋ፣ ደግና ጥሩ ጓደኛ ነህ፡፡ እና ደግሞ ... እግዚአብሔር ነህ።

(ኢየሱስ)፡- "ይህንን ሙሽራዬ እንደሳመችኝ አድርጌ እቆጥረዋለሁ፡፡"

(ክሌር) ጌታ ሌላ መናገር የምትፈልገው ነገር አለ?

"በእርግጥም የምናገረው ነገር አለ፡፡ እኔ በዚህ አይነት ግንኙነት አንድ ላይ አብረን እንድንሆን ዕድሜሽን ሁሉ ጠብቄአለሁ፡፡ ይህን ግብዣ ቆይታ ከመቀበል ይልቅ ወዲያው የተቀበለች ነፍስ ብፅዕት ናት፡፡ ካለማወቅ በብቸኝነት ብዙ ተሰቃይተሻል፡፡ ገና ከልጅነትሽ ጀምሮ እንደዚህ አብረን መሆን እንችል ነበር፡፡

(ክሌር) አዎ ጌታ ሆይ ቢሆን....(በትልቁ መተንፈስ)

"ለዚህ ነው ለውድ ሙሽሮቼ እንደ ስጦታ አድርጌ ያመጣሁሽ፡፡ እነርሱ አሁን መግባት እንጂ መጠበቅ የለባቸውም፡፡ ከአሁን ወዲያ በህይወታችሁ ብቸኛ መሆንና በራሳችሁ መወሰን አያስፈልጋችሁም፡፡ እኔ በቀኝ እጃችሁ በኩል ከእናንተው ጋር ነኝ፡፡ በጠየቃችሁኝ ጊዜ ደግሞ ለመምራት ሁልጊዜ ከጎናችሁ ነኝ፡፡

"ለግንኙነታችን ትልቁ አደጋ ትኩረትን የሚስብ ጉዳና ሥራ ነው ፡፡ እነዚህን ነገሮች ሰይጣን ቀስ በቀስ እናንተን ከእኔ ፍፁም ለመለየት የሚጠቀምባቸው የረቀቁ መሣሪያዎቹ ናቸው፡፡ እሱ እየተከናወነ ያለውን ነገር እንዳታስተውሉ ለማድረግ ነገሮችን የሚፈፅመው ቀስ በቀስና እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው አንቺ ባለፈው እንዳሊጋጠመሽ ዓይነት ፕሮጀክትን በማቅረብ ነው፡፡

(ክሌር)፡- እህ! ያን ጊዜ በአራት ውሾች የምትመራውን የ83 ዓመት ሴት ፊት ለፊት ካለው ቤት ማዘዋወርና በዚህ ርስት ላይ ልሰራው የነበረውን አንዳንድ ሥራዎች ነው?

(ኢየሱስ)፡- "አዎን ይህንን እንደ ማስጠንቀቂያ ልትወስጂ ይገባል፡፡ ነገር ግን አሁን አዲስ ኃላፊነት አለብሽ፡፡ ይህም ወደ እኔ ለመቅረብ የሚፈልጉ ነፍሳትን ወደ እኔ እንዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት ነው፡፡ የእናትነት ባህርይ አሁን ያለሽን ነገር እንዳታጪ ያደርግሻል፡፡ በቀደመው ጊዜ ግን ከእኔ እንዲህ አድርጎ ነበር የሰረቀሽ፡፡ እናም በዚህ ምክንያት አጥቼሽ ስለ ነበር ክሌር ብዬ አብዝቼ ጮሁኩ፡፡ እጅግ አዝኜ ስለነበር በወቅቱ እንባዬ ከአይኖቼ ይፈስ ነበር፡፡

(ክሌር)፡- ኦ ! እግዚአብሔር እንዲሁም እጅግ ምርጡ ጓደኛዬ...እኔ እጅግ ከልብ አዝናለሁ፡፡

(ኢየሱስ)፡- "አዎን ሙሽሮቼ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ህይወታችሁ በጣም አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ብቻ ይወሰናል፡፡ ደግሞም ከውጪ የምታገኙት ደስታ እጅግ ጥቂት እየሆነ ይሄዳል፡፡ ይህንን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ይገባችኋል፡፡ እኔ አጠገባችሁ ሆኜ እየጠበኳችሁ እያለ እናንተ ግን ጉጉታችሁን ለማሟላት ኢንተርኔት ከፍታችሁ ከአንዱ ወደ ሌላው በመሸጋገር ጊዜያችሁን ስታጠፉ እወቅሳችኋለሁ፡፡ እንደገናም ራሳችሁን ለማቆንጀት በመስታወት ፊትለፊትና በገበያ ሥፍራ ጊዜያችሁን ስታጠፉ እወቅሳችኋለሁ፡፡ በተጨማሪም በሳሎን ወይም ከጓደኞቻችሁ ጋር ምግብ በመብላት በምታጠፉት ጊዜ፣ ይኸውም ከሁለት ለአንዳችሁ መንፈሳዊ እድገት የማይጠቅም ከሆነ እወቅሳችኋለሁ፡፡ በኩሽና ውስጥ፣ በአትክልት ሥፍራ እና ከባድ በሆነ የቤት ፅዳት ሥራ ላይ በምትወስዱት ያለአስፈላጊ ጊዜ እወቅሳችኋለሁ።"

(ክሌር)፡- ኢየሱስ አሁን እያወራ ያለው ስለእኔ ነው ፡፡

"ከእኔ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌለውን ማንኛውንም ሥራ ስትሰሩ ሰላምና ደስታ የሚሰማችሁ ከሆነ በዚያ እንቅስቃሴ ውስጥ እኔ ከእናንተ ጋር እንደሆንኩ እወቁ፡፡ ይህ መመሪያችሁ ይሁን፡፡ ነገር ግን በጎናችሁ የሚጎነትልና የሚጎትት ነገር ካለ ለምሳሌ 'ይህንን ማድረግ እንደሌለብኝ አውቃለሁ . . . ነገር ግን. . . ' የሚል ነገር ከተሰማችሁ ሙሽሮቼ እኔ በጎናችሁ ለብቻዬ ሆኜ የእናንተን አብሮነት በመጠበቅ ላይ ነኝ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ዝም ብላችሁ በዛው ከቀጠላችሁ እያለቀስኩ እንደሆነ እወቁ፡፡ ዕንባዬን ላታዩት ትችላላችሁ ነገር ግን በውስጣችሁ ትክክል ያልሆነና መጥፎ የሆነ ስሜት ይሰማችኋል፡፡ ስለዚህም ትክክል ያልሆነና መጥፎ ስሜት በጥልቅ ልባችሁ ሲሰማችሁ ያ የአምላካችሁ ቅሬታና ሃዘን እንደሆነ እወቁ፡፡

"አያችሁ እኔ በቀላሉ የምገኝ አይደለሁም፡፡ ደግሞም ከእኔ መለየት ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ስለዚህ 'ከኢየሱስ ጋር እንደዚህ ዓይነት ግንኙነት እፈልጋለሁ' በእውነት የምትሉ ከሆነ ብዙ መስዋዕቶችን መክፈልና ጊዜያችሁን ከኔ ጋር ለማሳለፍ መዘጋጀት አለባችሁ። እስቲ ጊዜሽን እንዴት እንደምታሳልፊ አካፍያቸው፡፡"

(ክሌር)፡- በየቀኑ የተለመደው ሥራዬ ምግብ ወደ ምግብ ማከማቻው መውሰድ፣ ምናልባት ደግሞ በትንሽ ርቀት ወደሚገኝ የመድሐኒት መሸጫ ሱቅ በመሄድ የታዘዙ መድኃኒቶችን መግዛት፣ ውሻና ድመቶችን በጀርባችን ወደሚገኝ ሜዳ በእግራቸው ይዤ መሄድ ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም መሰረታዊ የሆኑ የቤት ሥራዎችን ለምሳሌ ዕራት መሥራት፣ ዕቃና ቤት ማፅዳት የመሳሰሉት ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም ከባለቤቴ ጋር ምግብ አብሮ በመመገብና መንፈሳዊ ነገሮችን በመለዋወጥ እናሳልፋለን፡፡ ይህ ሁሉ በአጠቃላይ አራት ሰአት ያህል ይፈጃል ፡፡ ከዚያም በምሽት ከ4-6 ሰአት ያህል ከእናንተ ጋርና ከረዳቶቻችን ጋር የምፃፃፍበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚያም አምልኮና መልዕክቶችን ከጌታ የምሰማበትና ቀድቼ የማስቀምጥበት ጊዜ ሲሆን ይህም ተጨማሪ ከ4 እስከ 5 ሰአት ያህል ይወስዳል፡፡ በእነዚህም ሰዓታት ውስጥ ፋይብሮማልጂያ ስላለብኝ ሰውነቴን ለማሳረፍ ሁለት ጊዜ የ45 ደቂቃ የዕንቅልፍ ዕረፍት(naps) አደርጋለሁ፡፡ የንጥቀቱ ጉዳይ ከሰማሁ በኋላ ድሮ ሳደርጋቸው የነበሩትን ስራዎች ለምሳሌ አልባሳትን በስፌት መኪና መጠገን፣ ልብሶችን መግዛት ፣ ከባለቤቴ ጋር ፊልም ማየት፣ ተጨማሪ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ እና የምወዳቸውን ምግቦች ማብሰል (መጋገር እወዳለሁ) እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ።

(ኢየሱስ)፡- "ስለዚህ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ኑሮሽ በከፍተኛ ሁኔታ ተቀይሯል ማለት ነው?"

(ክሌር)፡- በጣም ተቀይሯል እንጂ! ጌታ ሆይ አመስግንሃለሁ፡፡ እኔ በዚህ መርሐ ግብር እጅግ ደስተኛ ነኝ። ብዙ መስዋዕቶችን መክፈል ቢኖርብኝም እንኳን የኔ ውድ ኢየሱስ ካንተ ጋር ከመሆን አንዱም ሊወዳደር አይችልም፡፡

(ኢየሱስ)፡- ስለዚህ አያችሁ ውድ ሙሽሮቼ እስካሁን ህይወታችሁን ካላስተካከላችሁ ብዙ መስዋዕት የምታደርጉት ነገር አላችሁ፡፡ እናም ይህንን መመሪያ የምሰጣችሁ ለእናንተ ብቻ ሳይሆን ከንጥቀት ለሚቀሩትም ነው፡፡ ምክንያቱም ከእኔ ጋር ህብረት ለመፍጠር ምን እንደሚያስፈልግ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ እነዚህን ነገሮች ወደኋላ መተዋችሁ ለአንድ ደቂቃ ያህል እንኳ በጭራሽ አይቆጫችሁም፡፡

"ነገር ግን ክሌር ቀደም ሲል እንደገለፀችውና እኔም እንዳስጠነቀቅኋችሁ 'ግዙፍ' ጊዜን የሚወስድ ፕሮጀክት ሰይጣን ተግባራትን በማብዛት ቀስ በቀስ ከእኔ እየራቃችሁ ህይወታችሁን ከውስጣችሁ ሙጥጥ ለማድረግ ያዘጋጀው የጥፋት ዕቅዱን የሚያስፈፅምበት እንደሆነ እወቁ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ፕሮጀክቶች በፊታችሁ ሲቀርቡ ምን ታደርጋላችሁ? ይህ ቀላል ነው፡፡ እጅግ አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ተግባርያዊ አታድርጓቸው፡፡ እናም መፈፀም ያለባችሁ ዕለት ተዕለት እናንተን

የሚጠግናችሁን ብቻ ነው፡፡ብታምኑም ባታምኑም አንድ ቀን ፀሎት ማቋረጥ እጅግ ከባድ ጉዳይ ነው፡፡ ትናንሽ ቀበሮዎች ናቸው የወይኑን ቦታ የሚያጠፉት፡፡ እናም ይህ የሚጀምረው በአንድ ቀን ነው። የሚቀጥለው ቀን ሌላ ነገር ይመጣና የፀሎት ጊዜያችሁን ይሰርቃል። በሚቀጥለው ቀን ተጨማሪ ነገሮች ይመጡና ከዚያም እኔን ወደ መርሳት ትመጣላችሁ። በዚህ ጊዜ ከባድ እርምጃ ካልወሰዳችሁ በስተቀር ወደ እኔ ለመመለስ አዳጋች ይሆንባችኋል፡፡ ይህ ልክ ከማዕበል እንደ መውጣት ዓይነት ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት ከቤታችሁ ይኸውም እኔ ከምኖርበት ከልባችሁ በጣም ርቃችኋል ትሄዳላችሁ፡፡

"ስለዚህ የምትከፍሉት ዋጋ ይህንን ይመስላል፡፡ ምንም አድርጋችሁ ካልቆጠራችሁትና ህይወታችሁን በእግዚአብሔር ስርዓት ካስያዛችሁት ደስተኞች ትሆናላችሁ፡፡ ይህ በአንድ ሌሊት ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በየእለቱ ይህንን ከሰራችሁ ትክክለኛ ምርጫ እንድትመርጡ በማድረግ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ እንደ ክሌር በማይገመት ሁኔታ ወደ ኋላ ስትሸራተቱ ደግሞ ክሌርን "ነገ የተሻለ ምርጫ እንድትመርጪ እረዳሻለሁ" እንደምላት ሁሉ ለእናንም እንዲሁ እላችኋለሁ፡፡ ከዚያም ወደ ትክክለኛው መንገድ አብረን እንመለሳለን፡፡"

(ክሌር)፡- ጌታ ሥራ የሚሰሩ ወይም ትምህርት ቤት የሚሄዱ ሰዎችስ?

"ለዚህ ቀላል መልስ የለኝም፡፡ እንደገና ልናገርና "እንደዚህ ዓይነቱን ግንኙነት ምን ያህል ነው የምፈልገው?" ይህንን ግንኙነት የምፈልገው የህይወት ዘይቤያችሁን መቀየር እስኪችል ድረስ ነው፡፡ ስለሆነም ጥቂት የምትከፍሉት ወይስ በአንፃሩ ምንም ክፍያ የሌለው ነው የምትፈልጉት? የተማራችሁት ትምህርት እኔ በእናንተ ላይ ያቀድኩትን ፍፁም ፈቃዴን ለመፈፀም የሚያስችል ነው? ወይስ በአፍሪካ ጫካዎች ውስጥ ነፍሶችን ወደ እኔ ለማምጣት የበለጠ ደስታን ይሰጣችኋል? የምትሰሩት ሥራ ሙሉ በሙሉ ለእኔ ያላችሁን ፍቅርና መሰጠት የሚያንፀባርቅ ነው? ወይስ ለመኖር የሚያስችላችሁን የገንዘብ ዋስትና ለመጠበቅ ነው?

"አያችሁ ለዚህ ቀላል መልስ የለም፡፡ ከዓለም ብትወጡ ዓለም የሚያቀርብላችሁ እንዲላገጥባችሁና እንድትናቁ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ መልስ ለመስጠት ዝግጁ ናችሁ? ወይስ በወሰናችሁት ውሳኔ ኃላፊነት የማይሰማውና ተሸናፊ አድርገው ለሚቆጥሯችሁ ቤተሰቦቻችሁና ወዳጆቻችሁ መልስ ሳትሰጡ ዝም ብላችሁ ትሄዳላችሁ? ወይስ በእኔ ፍቅር ከመያዛችሁ የተነሳ ምንም ግድ አይሰጣችሁም? ወይስ "ሞኝ" የሆነ ውሳኔ በመምረጣችሁ በውስጣችሁ ለመጎዳት፣የወላጆቻችሁንና የጓደኞቻችሁን ድጋፍ ለማጣት ፈቃደኞች ትሆናላችሁ? ስለዚህም ለዚህ ቀላል መልስ የለም፡፡"

(ክሌር)፡- 'ይህንን አሁን ነው የሰማሁት ነገር ግን አግብቻለሁ' ለሚሉስ ?

(ኢየሱስ)፡- "በእኩልነት ከተጣመራችሁ ይህ ምንም እንቅፋት ሊሆን አይችልም፡፡"

(ክሌር)፡- '... ጥሩ ሥራና ጥሩ ገቢ አለኝ፡፡ አሁን ባለሁበት ኃላፊነት ለብዙ ዓመታት ሰርቻለሁ፡፡ የጡረታ ዋስትናዬ የተጠበቀ ነው ወዘተ. . .ወዘተ' ለሚሉስ ?

"እንኳን የዛሬ አሥር አመትና በሚቀጥለው ሳምንት እንኳን በሕይወት ላትኖሩ ትችላላችሁ። እስካሁን ባጎለበታችሁት ክህሎት መንግስቴን ለመገንባት ምን መስራት ትችላላችሁ? ምናልባት ደግሞ እናንተን የምፈልጋችሁ ባላችሁ ክህሎት ሳይሆን እናንተ ፍፁም ባልተዘጋጃችሁበት አቅጣጫ ቢሆንና ለሥራውም ፍፁም በእኔ ላይ መመርኮዝ ቢኖርባችሁስ?"

(ክሌር)፡- አዎ ከልምዴ እንዳየሁት ከ30 ዓመታት በፊት የተፈጥሮ ፎቶ አንሺ ባለሞያ ነበርኩ፡፡ ታዲያ ህይወቴን ለአንተ ለመስጠት በወሰንኩ ጊዜ ወደ ካሜራ እንድቀርብ እንኳን አልፈቀድክልኝም ነበር፡፡

(ኢየሱስ)፡- "አዎን ካሜራሽን ባነሳሽ ቁጥር አለም አለምን ስለምትሸቺ ክርፋቱን መቋቋም አልቻልኩም ነበር፡፡"

(ክሌር)፡- ከፍ ባለ ሳቅ! አዎ ገብቶኝ ነበር።

(ኢየሱስ)፡- "በዛ ምትክ የሙዚቃና የማስተማር ስጦታ ሰጠሁሽ፡፡"

(ክሌር )፡- ጌታ የሰጠኸኝን ስጦታዎች ወድጄያቸዋለው ፡፡

(ኢየሱስ)፡- እኔ ለእኔ ፍቅር ለምን እንደፈጠርኩሽ አወቃለሁ፡፡ እናም ይህንን ሥራ እንደምትወጂውና በፊት ለነበረው ነገር ሙሉ በሙሉ ለመሞት ፈቃደኛ እንደምትሆኚ አውቅ ነበር፡፡ ስለዚህም ወደ እኔ ባዶሽን መጣሽ እኔም በፈቃዴ ሞላሁሽ፡፡

(ኢየሱስ)፡- "ስንቶቻችሁ ናችሁ ሁሉንም ለመተው ፈቃደኞች የሆናችሁ??? የሚያስከፍላችሁን ዋጋ ተምኑ፡፡ እኔ በቀላሉ የምያዝ አይደለሁም፡፡ ደግሞም እኔን ማጣት ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ነገር ግን ጥቅሞቹ ከዚህ ዓለም ውጪ ናቸው፡፡ ሙሽሮቼን ሁሉ እወዳቸዋለው፡፡ እናም ራሳችሁን ከራሳችሁ ባዶ ስታደርጉ እኔ እራሴን እሞላባችዋለሁ፡፡ ህይወቱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል፡፡ ህይወቱን ለእኔ የሚያጣ ሁሉ ግን በእርግጥ ያድናታል፡፡

"አሁን ሂዱና በጥልቀት ዋጋውን ተምኑ። እኔ የምትወስኑትን ውሳኔ ለመስማት ከጎናችሁ እጠብቅችኋለሁ። እናንተ ማድረግ ያለባችሁ መጠየቅ ብቻ ነው እኔም እረዳችኋለሁ፡፡"

"ልቤን ሰጥቻችኋለሁ፣ መንፈሴንም ሰጥቻችኋለሁ፡፡ እናንተ ለእኔ ምን ልትሰጡኝ ትሻላችሁ?"

(ክሌር)፡- እዚህጋ አንድ ለመናገር የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ ጌታ በንጥቀት እስኪወስደን ድረስ እርሱን በሕይወታችሁ ማገልገል የምትፈልጉ ከሆነ እጅግ በጣም የምመክራችሁ እንደ አይሪስ ሚኒስትሪስ ያሉ (Iris Ministeries) በተልዕኮ የሚንቀሳቀሱ የወጣት ህብረቶችን ተቀላቅላችሁ ስልጠና እንድትወስዱ ነው፡፡ በራሳችሁ ጥሩ በሆነ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ብቸኛው አማራጭ በጌታ በትክክል አጥብቃችሁ የምትመሩ ከሆነና ምን እንደምትሰሩ በግልፅ የምታውቁ ከሆነ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ይህም ማንም ቀልበቢስ እንዳይሆን ነው፡፡ ይህ መልእክት የሚተላለፈው በዚህ ጊዜ ለምንገኝ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለውም ትውልድ ነው፡፡ በሺህ ዓመቱ ንግስና እንኳን ቢሆን ይህ መልዕክት የብዙዎችን ልብ ሊነካ የሚችል ነው፡፡ ስለዚህም እኔ መናገር የያስኩት ከመነጠቅ በፊት ባሉ ዓመታት ውስጥ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ለአንድ አፍታ እንኳን አታስቡ፡፡ ይህንን እኔ አላምንም፡፡ የዚህ መልዕክት ጭብጥ ሐሳቡ "እኔን ማደብዘዝ ኢየሱስን ማድመቅ" የሚል ነው፡፡ ይህም ለራሴ ነገር መሞትና ለኢየሱስ ብቻ መኖር የሚለውን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ አሁን ሁላችሁንም እባርካችኋለሁ፡፡ እናም ጌታ ሰላሙንና ጥበቡን እንዲያፐለቀልቃችሁ እፀልያለሁ፡፡ አሜን

## በእግዚአብሔር መስታወት ራሳችሁን በሃቅ ተመልከቱ / ኤፕሪል 18 ቀን 2015 ዓ.ም

## Honesty, Looking At Yourself in God's Mirror / April 18, 2015

"በዛሬው ምሽት ለመናገር የፈለግሁት ስለ ሐቀኝነት ነው፡፡ ይኸውም ለራሳችሁና ለሌሎች ሐቀኛ ስለመሆን ነው፡፡ ሁላችሁም ብትሆኑ ራሳችሁን በደንብ ማየት ያለባችሁ ነገር ይኖራል፡፡ የማልወዳችሁ ቢሆን ኖሮ ይህንን ርዕስ ለውይይት ፍፁም አላቀርበውም ነበር፡፡ ነገር ግን ሙሽሮቼ የቀረው ጊዜ አጅግ ጥቂት በመሆኑና ለእኔ ንስሐ ያልገባችሁባቸው ኃጢያቶች ገና ስላሉ እንደገና ራሳችሁን በደንብ እንድታዩ እጠይቃችኋለሁ፡፡

"እስካሁን ባሉት ዘመናት ለመኖር ብላችሁ አንዳንድ ነገሮችን ከራሳችሁ ደብቃችሁ ትኖሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም ዞር ብላችሁ ስትመለከቱት እንኳን ህመም ይፈጥርባችሁ ስለነበር ነው፡፡ ነገር ግን ከእኔ ምንም ነገር መደበቅ አያስፈልጋችሁም፡፡ ውዶቼ የሰራችሁትን ኃጢያት ሁሉ እኔ አውቀዋለሁ፡፡ ከእናንተ ጋር በመሆን በውስጣችሁ የደበቃችሁትን የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሁም ሸክም የሆነባችሁንና ስለነገሩ እንኳን ለመነጋገር ህመምና ጭንቀት የሆነባችሁን ጉዳይ ላነሳላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

"እናንተን ለመውደድ ምንም የሚከለክለኝ ነገር የለም፡፡ በፍፁም ምንም ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ግንኙነታችን በሃቅ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ እናንተ ለማየት ያልፈለጋችሁትን ነገር እኔ ፍፁም ላደርገው አልችልም፡፡ ወደ ፍፅምና እንዳመጣችሁ ስለራሳችሁ ያላችሁ ዕይታ እውነትን የተመረኮዘ መሆን አለበት፡፡ እናንተ ከሚገመተው በላይ ውብ መሆናችሁንና ይህንንም ስለእናንተ ያለኝን አመለካከት ሊቀይረው የሚችል ምንም ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በውስጣችሁ የተቀበረውና ያልተናዘዛችሁት ኃጢያት ያመጣው የጥፋተኝነትና የሃፍረትን ሽታ ይሰናበት፡፡"

"ይህም ደግሞ ከእኔ እንድትርቁ ያደረጋችሁ ምክንያት ነው፡፡ ታውቃላችሁ ምንም እንኳን የምትጋፈጧቸው ብዙ ጨለማ ነገሮች ቢኖሩም እኔ በምገኝበት ግን ሁሉ ነገር ግልፅ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ከመከሰታቸው በፊት እኔ አይቻቸዋለሁ ልበላችሁ? ማንም ቢሆን ራሱን ክፉ አድርጎ ሊመለከት የሚፈልግ የለም፡፡ በዚህም ምክንያት የሚያስበውን ይሁን የሚፈፅመውን ክፉ ነገር ከራሱ እንኳን በመደበቅ ወይም ደግሞ ሌላ ታሪክ በመፍጠር ለራሱ ይቅርታ ለማድረግ ይሞክራል፡፡

"የኔ ውዶች ወደ እኔ ቅረቡና ከእነዚህ ኃጢያቶች እንድትገላገሉ ጠይቁኝ፡፡ የኔ ፀጋ ሥጋችሁን ገርዞ ወደ ፊት እንድትራመዱና ከዚህ ሸክም እንድትላቀቁ ጠይቁኝ፡፡

"ለምሳሌ ብዙ ሰዎች መፀለይ እንዳለባቸው ነገር ግን መፀለይ የማይችሉት ጊዜ እንደሌላቸው ለራሳቸው ምክንያትን ያቀርባሉ፡፡ እስቲ ይህንን እንመርምረው፡፡ ነገሮችን ለመግዛት፣ ራትን ለማዘጋጀት፣ ቴሌቪዥን ለማየት ከጓደኞቻችሁ ጋር ለ45 ደቂቃ ለመጫወት፣ ፀጉር ቤት ሄዳችሁ ፀጉራችሁን ለመሰራት ወይም ለመቆረጥ፣ ከጓደኞቻችሁ ጋር ጉዞ ለማድረግ፣ በምሽት በረንዳ ላይ ቁጭ ብላችሁ ንፋስ ለመቀበል ጊዜ የላችሁም?

"እስቲ ይህንን እንመዝነው፡፡ ሰውነታችሁን ለመመገብና ለሰውነታችሁ የሚያስፈልገውን ለማድረግ ጊዜ ነበራችሁ፡፡ ለመዝናናትና ለመደሰት ጊዜ መድባችኋል፡፡ ለስሜታችሁ ዕረፍት ለመስጠት፣ ያሳለፋችሁትን ስኬትና ወድቀት

ለጓደኞቻችሁ ለማካፍል ጊዜ ነበራችሁ፡፡ በሰው ፊት ቆንጆ ሆኖ ለመታየት ጊዜ ሰጥታችኋል፡፡ እናም ከተደጋገመ ህይወት ወጣ ብላችሁ ለመዝናናት በማሰብ የሸርሽር ጉዞ ከጓደኞቻችሁ ጋር አድርጋችኋል፡፡

"ታዲያ የዚህ እውነታ ምንድነው? ከዚህስ ምሳሌ ድምዳሜው ምንድነው? ይህ የሚያሳየው የእነዚህን ነገሮች ያህል እኔ አስፈላጊ አለመሆኔን ነው፡፡ ለእኔ የሚታየኝ እውነተኛው ሃቅ ይህ ነው፡፡ ለህይወታችሁ አስፈላጊ ናቸው ለምትሏቸው ነገሮች ሁሉ ጊዜ አላችሁ፡፡ ገንዘብን ለማግኘት ጊዜያችሁን ትሰጣላችሁ፡፡ ከዚያም ባገኛችሁት ገንዘብ ትገዛላችሁ፣ ራሳችሁን ታዝናናላችሁ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ እንኳን ጊዜ አላችሁ፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለእናንተ አስፈላጊ ሲሆኑ ከእኔ ጋር ግን ግንኙነት ማድረግ ግን ለእናንተ አስፈላጊ ነገር አይደለም፡፡

ጌታዬ . . .

"እሺ ቀጥዪ፡፡"

"ጌታ አንድ ነገር ለመናገር ፈልጌ ነው፡፡ በቀደመው ህይወቴ በእያንዳንዱ ቀን ምን መስራት እንዳለብኝ ዝርዝር አወጣ ነበር፡፡ ይህም ዝርዝር ደግሞ እጅግ ብዙ ነበር፡፡ ታዲያ በዝርዝር ያሰፈርኩትን ተግባራት ካላጠናቀቅሁ ወይም አብዛኛውን ካልጨረስኩ ተስፋ እቆርጥ ነበር፡፡ በዚህም ደስታዬ ሁሉ ተወስዶ ብስጩ እሆን ነበር፡፡ አንድ ቀን ታዲያ ጌታ በልቤ "የምኞት መንፈስ አለብሽ" ብሎ ተናገረኝ፡፡ ይህም መንፈስ አንድ ነገር እንድጠብቅ ሃሳብ ይሰጠኝ ስለነበር በዚህም ዝርዝሮቹን እፅፍና በአንድ ቀን ተሰርተው እንዲያልቁ አደርግ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ነገር ከአቅሜ በላይና ካለኝ ጊዜ በላይ ሆነብኝ፡፡ ስለዚህም ዝርዝሩን ሁሉ አከናውኖ ለመጨረስ በጣም እጨናነቅ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ከፃፍኩት ዝርዝር ሌላ ጊዜ የሚወስድብኝን ምንም ነገር አልሰራም ደግሞም ማንንም አልቀበልም ነበር፡፡

እንዲህም ሆኖ ግን ከዝርዝሩ ውስጥ ሳላጠናቅቅው የሚቀር ነገር ነበር፡፡ ነገር ግን በዛ ዝርዝር ውስጥ የነበረ ነገር ሁሉ ከአለም ወይም ለአለም የሚሆን ነበር፡፡ በእርግጥም በኩሽና ከመሆንና ኬኮችን ከመጋገር ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ሌሎች ነገሮች ነበሩ፡፡ እቤት ከመጋገር ይልቅ ያንን ሊተካ የሚችል ከውጪ መግዛት እችል ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንን የማላደርገው በጣም ምርጥ ባይሆን እንኳን እጅግ ጥሩ መሆን አለበት ብዬ ስለማስብ ነው ራሴ መስራት ያለብኝ፡፡

ነገሮችን ለመሥራት ሁለት ዘዴዎች አሉ፡፡ ይህም በቀላል የመስራት ዘዴ ወይም የበላይ ለመሆን ከባድ የሆኑ ዘዴዎችን መጠቀም ናቸው፡፡ የበላይ ለመሆን ደግሞ የእናንተን ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ በአንፃሩ የእናንተን የበለጠ ጊዜ ይፈልጋል፡፡ እኔ ሁልጊዜ ስመርጥ የነበረው የኔን ጊዜ በብዛት የሚወስደውን ዘዴ ነበር፡፡ ምናልባትም የዚህ ኃጢያት ሥር መሰረቱ ኩራት ነው፡፡ አንድ ነገር ከሆነ ምርጥ መሆን አለበት የሚል ኩራት፡፡

እናም ለእግዚአብሔር በፍፁም በቂ ጊዜ አልነበረኝም፡፡ ሳይደከመኝም ሆነ ነገሮችን ቶሎ ወጥቼ ለመስራት ስጣደፍ ምንም ጊዜያቶች አልነበረኝም፡፡ ገና በጠዋቱ ተዘጋጅቼ መውጣት ስላለብኝ ሥራ ይበዛብኛል፡፡ በምሽት ደግሞ ኃይሌ ሁሉ ተሟጦ አልቋል፡፡ ጌታ ለበለጠ ፀሎት እንደጠራኝ አውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔ በአለም ደስታና አጀንዳዎች ታስሬ ስለነበር ጊዜ የለኝም ነበር፡፡ እውነቴን ነው የምላችሁ ከጌታ ጋር ብዙ ጊዜ አልነበረኝም፡፡

አንድ ቀን ታዲያ ጌታ ችግሬ ምን እንደሆ ነገረኝ፡፡ "ክሌር ለእኔ ጊዜ የለሽም" አለኝ፡፡ በዛ ንግግር ወደ መሬት ወረድኩ፡፡ . . . ለእግዚአብሔር ጊዜ . . . የለኝም? ይህ ለምን ሆነ? እርሱ በህይወቴ እጅግ አስፈላጊው አይደለም እንዴ?

መልሱ ቀላል ነው፡፡ "አይደለም" የሚል ነው፡፡

አዎን እርሱ በህይወቴ እጅግ አስፈላጊው ነገር አልነበረም፡፡ በጣም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዝርዝር የአለም ነገሮች ከጌታ ይልቅ ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነበሩ፡፡ የሰውነት እንቅስቃሴ ማድረግ፣ ትክክለኛውን ልብስ ለመልበስ መፈለግ፣ ፀጉሬን መሰራት፣ የተለያዩ የውበት መጠበቂያ ዘዴዎችን መፈለግና አዲስ ዘዴዎችን መሞከር፣ በጣም ቆንጆ የሆነ ጥቁር ቸኮሌት ኬክ በልዩ መልክ መጋገር፣ መኪና ማጠብና አንፀባራቂና አብለጭላጭ ማድረግ፣ በዕቃ የሚተከሉ አበባዎችን እንደገና መትከልና ማሳመር፣ ስለከብካቢያቸው ማጥናት፣ ስለ ጤንነት ጉዳዩችና ቫይታሚኖች ለምን እንደሚጠቅሙ ማጥናት፣ እንደዚህ እያልኩ ብዙ መዘርዘር እችላለሁ፡፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ከኢየሱስ ይልቅ ለእኔ በጣም አስፈላጊዎች ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ የማይካድ እውነት ነበር፡፡ ጌታን እወደው ስለነበር ህይወቴን ሰጥቼዋለሁ እናም ለእርሱ እየኖርኩ ነው ብዬ አስብ ነበር፡፡ ነገር ግን ወደኋላ መለስ ብዬ ስመለከት እኖር የነበረው ለእራሴ ነበር፡፡

በእርግጥ ነው የፀሎት ጊዜ ነበረኝ፡፡ ነገር ግን ጌታ ከእኔ እንደሚፈልገው አልነበረም፡፡ እንደዚህም ሆኖ ግን ሌሎች ያላቸውን የፀጋ ስጦታዎችና የአገልግሎት ዓይነት እንዲኖረኝ እጠማ ነበር፡፡ ውጤታማ በሆኑ በሌሎች የቅናት ስሜት ይሰማኝ ነበር፡፡ እናም ለምንድነው እኔ እንደዛ ውጤታማ የማልሆነው እያልኩ ራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ እንዳውም ጌታን ወደ አገልግሎት ብታስገባኝ ሌሎች ነገሮች ሁሉ እየከሰሙ እንደሚሄዱ አውቃለሁ እለው ነበር፡፡

ጌታ ግን እንደዛ አላደረገም፡፡ እርሱ ከእኔ ሲፈልግ የነበረው የለመድኩትን እነዚህን የአለም ነገሮች ከአገልግሎት በፊት እንድተዋቸው ነበር፡፡ እነዚህም ነገሮች እኔ አስፈላጊ ብዬ ያሰብኳቸው ነገር ግን ከንቱና የማይረቡ ነገሮች ናቸው፡፡ ጌታ በእኔ ህይወት ውስጥ ማየት የሚፈልገው የነበረው እርሱ ለእኔ ሁሉ ነገሬ መሆኑንና በህይወቴ ከእርሱ በላይ ምንም ነገር አስፈላጊና የበለጠ አለመሆኑን ነበር፡፡

በአገልግሎት ስኬታማ በሆኑት የምቀናው መሰረቱ ስንፍና እንደሆነ እየተረዳሁ መጣሁ፡፡ ውጤታማ ለመሆን የሚበቃውን ያህል ሙከራ ማድረግ ያልቻልኩት ህይወቴ በአስቸጋሪ ነገሮች እጅግ ተወስዶ ስለነበር ነው፡፡ እነዚህም ነገሮች በእሳት ውስጥ ማለፍ የማይችሉና የሚቃጠሉ ነገሮች ናቸው፡፡ አንድ ጊዜ በአይምሮዬ ውስጥ ተቀርቅሮ የቀረ አባባል ሰምቻለሁ፡፡ "በአንድ ሰው የምትቀና ከሆነ ምክንያቱ እነርሱ እየሰሩ ያሉት ነገር አንተ መድረስ ያለብህ ነገር ግን ያንን ለማግኘት በተፈለገው መጠን ያልሰራህበት መሆኑን ስላወቅህ ነው፡፡" ይህ አረፍተ ነገር ከሃሳቤ አልጠፋ አለ፡፡ ስለዚህም መድረስ ያለብኝ ቦታ መድረስ ያልቻልኩበት ምክንያት በህይወቴ ዘመን ሁሉ ጊዜዬን ያጠፋሁት በአስቸጋሪ ነገሮች ላይ ስለነበረ ነው፡፡

ከዚያም አንድ ቀን ከንጥቀት ጉዳይ ጋር ተፋጠጥኩ፡፡ እናም ከሞኞቹ ልጃገረዶች አንዷ እንደሆንኩ ተነገረኝ፡፡ ይህንን እንዴት አወቅሁ? በውስጥ አንጀቴ፣ በውስጠኛው ማንኔቴ በጣም ውድ የሆነውን ጊዜዬን በማይጠቅም ነገር ላይ እያዋልኩት እንደሆነ የሚከነክን ስሜት ተሰማኝ፡፡ ነገር ግን 'መሰራት የያስኩት እኮ መሰራት ያለበትን ጉዳይ ነው ፣ መሰራቱ አስፈላጊ ነው' እያልኩ ለራሴ ብዙ ምክንያቶችን አቀረብኩ፡፡ በውስጤ የሚከነክነው ስሜት ግን ለቆ ለመሄድ አሻፈረኝ አለ፡፡ እናም ጌታ ለእኔ ጊዜ የለሽም ሲለኝና የንጥቀቱን እውነታ ስረዳ ያን ጊዜ ነበር የኔ የማንቂያ ደውል የተደወለው፡፡ በዚያን ጊዜ መንገዴን ካልቀየርኩና ካላስተካከልኩ ዘይቴ እንደሚያልቅ ተረዳሁ (እስከዚያም ካላለቀ ማለቴ ነው)፡፡ በዚን ጊዜ ነው የተቀየርኩት፡፡ እግዚአብሔር ህይወቴን እንዲቆጣጠር በአለም ላይ ለመሆን የምጠብቀውንና የኑሮ ከፍታዬን ቀነስኩ፡፡

ጌታ እንዲህ በማለት ቀጠለ... " የኔ ሙሽሮች ላገኛችሁና ልወስዳችሁ የምፈልገው ከዛ ቦታ ላይ ነው፡፡ ጊዜያችሁን እንዴት እየተጠቀማችሁበት እንደሆነ በምንም ሳትበገሩ ለራሳችሁ ታማኝ እንድትሆኑ ነው፡፡ በህይወታችሁ በእርግጥ አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንደገና መርምሩ፡፡ በህይወታችሁ እንዲሆን የምትጠብቁትን ነገር አሳንሱ፡፡ ይህ በሚሆን ጊዜ አስቸጋሪና የማይጠቅሙ ነገሮች ከእኔ አይሰርቋችሁም፡፡ አንድ እርምጃ በስህተት መራመድ የሚያዳልጠው መንገድ ላይ ይጥላችኋል፡፡ ከዚያ በኋላ ሁሉም የስህተት ነገሮች ከፊት መጥተው ይደቀናሉ፡፡"

(ክሌር) ጌታ ከአመታት በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ በምዘጋጅ ጊዜ የነበረውን ሁኔታ ሁሉ አስታውሳለሁ፡፡ መልበስ የምፈልገው ከላይ እስከ ታች የተቀናጀ አለባበስን ነበር፡፡ ትክክለኛ ልብስ፣ ከልብሱ ጋር የሚሄዱ ተጨማሪ አልባሳቶችን፣ ትክክለኛ ቦርሳ፣ ትክክለኛ ጫማና አስቶኪንግ፣ እናም ትክክለኛ የፊት ማስዋቢያዎችን ነበር ማድረግ የምፈልገው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እንኳን ከጎደለ ሌላው ሁሉ በአግባቡ ይቀየራል፡፡

በአንፃሩ ግን ለውጫዊ  ውበቴ ትኩረት ባልሰጥ ኖሮ ቀለል ያለ አንድ ልብስ በየሳምንቱ መልበስ እችል ነበር፡፡ በዚህም ደግሞ የውስጥ ማንነቴ እውነተኛ አምልኮ ለማድረግ ዝግጁ በመሆን ለውጫዊ ውበት ግድየለሽ በሆንኩ ነበር፡፡ ወንዶች ለእናንተም በተመሳሳይ መልኩ ትክክለኛ ክራቫት ከትክክለኛው ሸሚዝ ጋር፣ ትክክለኛው ኮትና ሱሪ፣ ትክክለኛ ጫማ፣ እንዲሁም የሚያንፀባርቅ፣ አዲስ ንፁህ የሆነ መኪና በመያዝ ወደ ቤተክርስቲን የሚመጡትን ቤተሰቦች ሁሉ ማስደነቅ ነው፡፡ ሰዎች ወዴት እየሄድን ነው ያለነው?

(ኢየሱስ) "ሙሽራዬ ከዚህም በበለጠ የሚያሳዝነው ክፍል ደግሞ እናንተ ማፍራት ለባችሁ ፍሬ በፈፀማችሁት በዚህ ድርጊት ምክንያት መታነቁን ያለማየታችሁ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ አገር ከቤተክርስቲያን በላይ የእሾህ ቁጥቋጦ አድጎ እኔ እንዳልንቀሳቀስ አድርጎኛል፡፡ ደግሞም አብዛኛውን እንዳልቀሳቀስ ያሰረኝ  በህብረተሰቡ ተቀባይነት ማግኘት የሚለው ነገር ነው፡፡ ነገሮች ሁሉ ስህተት ሆነው እያለ ትክክለ መልበስ፣ ትክክል ማየት፣ ትክክል ማድረግ የሚለው ሐሳብ ይንፀባረቃል፡፡ ስለዚህም እኔ የምተነፍስበት ምንም መንገድ የለም፡፡

"ለዚህ ነው ስለ ሃቅ ጉዳይ እየተጣራሁ ያለሁት፡፡ አዲስ እርከን ያለው ሃቅ፡፡ ይህ አገር በጦርነት ላይ በሚሆን ጊዜ ያን ጊዜ ሃቁ ይወጣል፡፡ ምክንያቱም ብልጭልጭ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ሊኖሩ የማይቻሉ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህም ተመልሰን ወደ ይዘት እንመለሳለን፡፡ ይህም ወደ ግል ቅድስናና በእውነትም ወደሚያስፈልጉ ነገሮች እንመለሳለን፡፡  አሁን ግን ቤተክርስቲያኔ በህብረተሰብ ባላት ትልቅ ሥፍራና በሰዎች ፊት በምታገኘው ተቀባይነት ታስራለች፡፡

"የኔ ሙሽሮች፣ የኔ ቆንጆ ሙሽሮች እለምናችኋለሁ፣ የውስጥ ፍላጎታችሁን መርምሩ፡፡ ሊኖራችሁ የሚገባው አንድ ውስጥ ፍላጎት ብቻ ነው፡፡ ይህም እኔን መውደድና ጎረቤታችሁን መውደድ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነ ማንኛውም የውስጥ ፍላጎት ንፁህ ያልሆነ ነው፡፡ እኔን አጥርቶ ለመስማትና ለማየት የሚያስፈልገው ደግሞ ንፅህና ነው፡፡ ስለዚህም ሁላችሁም ወንዶችም ሆናችሁ ሴቶች በሚቀጥለው ዓይነት የውስጥ ፍላጎታችሁን በደንብ ፈትሹ፡፡ 'ያንን ያልኩት ጎበዝ መሆኔን ለማሳየትና እነሱን ለማስደመም ነው? ይህንን አለባበስ የለበስኩት ከእነ እከሌ ከፍ ብሎ ለመታየት ነው? የሰውነት እንቅስቃሴ የማደርገው በቤተ ክርስቲያን የወንዶችን ዓይን ለመሳብና ባል ለማግኘት ነው?' እዚህጋ እንዲህ ልበል፣ ባልን ለመሳብ የምትጠቀሙት የሥጋ ልኬት ከሆነ የምታገኙት ሥጋዊ ባልና ጋብቻችሁም የሥጋ ትዳር ነው፡፡"

"እንዲሁም 'እከሌና እከሌጋ የደወልኩት ስለምጠላው አንድ ሰው መጥፎ ነገር ንግሬያቸው እንዲጠሉት ለማድረግ ነው? በቤተክርስቲያን ለማገልገል የፈረምኩት ተፅዕኖ ለመፍጠርና ደረጃዬን ከፍ ለማድረግ ነው? ለቤተክርስቲያን ስጦታ የምሰጠው ሰዎች መልካም ነው ብለው እንዲያስቡኝ ነው? አዲሱን መኪና የገዛሁት ሳቆም ሰዎች አንገታቸውን ቆልምመው እንዲያዩኝ ነው? እያንዳንዱን ነገር ስታደርጉ ያደረጋችሁት እኔን ከመውደድ እንጂ ከሌላ ከምንም ነገር እንዳልሆነ በደንብ ፈትሹ፡፡ የምታደርጉት ነገር ሁሉ በሌሎች የሚታይና መልካም መስሎ እየታየ ካለ ይህንን ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ዘይታችሁ ከመብራታችሁ ውስጥ እየተጠባጠበ ነው፡፡ ስለዚህም ከውስጡ ፈሶ ለማለቅ አደጋ ላይ ነው፡፡

"በዚህ በሚመጣው ሳምንት የውስጥ ፍላጎታችሁ ላይ ልፈርድ ነው፡፡ እናንተ በእርግጥ በእኔ ማን መሆናችሁን እንዳታዩ ያደረጓችሁንና የከለከሏችሁን ዝንባሌዎችንና ልማዶችን አጋልጣቸዋለሁ፡፡ አንዳንዶቹ ለምን እንደምታደርጓቸው በእውነት ሲገባችሁ ሊያስደነግጧችሁ ይችሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ለራሳችሁ መልካም እንዲሆን ነው፡፡ ይህ ከሠርግ ልብሳችሁ ላይ ብዙ የቆሻሻ ጠብታዎችን ለማንሳት ነው፡፡ ይህ ለንስሐ የሚጋብዛችሁ ነው፡፡ እናም ማንም ራሱን ከሌላው ከፍ የሚያደርግ ቢኖር እናንተ ደግሞ ምን ያህል ዝቅ እንዳላችሁ ራሳችሁን ታገኙታላችሁ፡፡ እናም ይህ ጥሩ ነገር ነው፡፡ በእርግጥም እኔ ከፍ ያሉትን ዝቅ አደርጋለሁ፣ ትሁቶችን ደግሞ ከፍ አደርጋለሁ፡፡

"የኔ ወንድና ሴት ሙሽሮች እባካችሁ ለራሳችሁ ሐቀኛ ሁኑ፡፡ እናም ለምታደርጉት ነገር ሁሉ ለምን እንደምታደርጉት ምክንያት ከመስጠት ወይም ከእውነቱ ከማፈንገጥ ተቆጠቡ፡፡ በእያንዳንዱ ድርጊታችሁ ንስሐ በመግባት ከእነዚህ አለማዊ ዝንባሌዎችና አቋሞች እንድትወጡ እኔን እርዳታ ጠይቁ፡፡ እኔ እንደተፈተነ ወርቅ እያነፃኋችሁ ነው፡፡ እኔ ስለምወዳችሁና ለእናንተ በልቤ ያለው የዘላለም ሐሳብ ምርጥ ስለሆነ ከእኔ ጋር ተባበሩ፡፡"

"ለሠርጋችን ቀን ዝግጁ እንዳደርጋችሁ ከእኔ ጋር ለመተባበር በሚያስችላችሁ ጉብዝና አሁን ባረኳችሁ፡፡"

## ፍቅር ከሌላችሁ የንጥቀ ተካፋይ አትሆኑም / ኤፕሪል 20 ቀን 2015 ዓ.ም

## Without Love You Will Not Be Taken in the Rapture/ April 20, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . ."ብዙዎች በእኔ ፊት ለመቆም እርገጠኞች ሆነዋል፡፡ ነገር ግን ውስጣቸውን በሚገባ አልፈተሹም ወይም በእኔ መስታወት ውስጣቸውን አልመረመሩም፡፡ ክሌር እኔን እያሳሰበኝ ያለው ነገር ይህንን ሳያደርጉ እኔን ለመገናኘት እርግጠኞች መሆናቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም እርስ በርስ እየተጣሉና እየተነካከሱነው፡፡ እስካሁንም አንዱ ሌላውን ያማል ደግሞም እርስ በርስ ውሸትን ይነጋገራሉ፡፡ እስካሁንም ራሳቸውን ፃድቅና ስህተት የለሾች በማድረግ ሌሎችን ይኮንናሉ፡፡

"ነገር ግን እንዲህ እያደረጉ በፊቴ ለመቆም ዝግጁ እንዳይደሉ ይህንን ልናገር፡፡ በራሳቸው ፅድቅ ዓይናቸው ታውሯል፡፡ አለምን ትክክል ለማድረግና ለማስተካከል ትግል ላይ ናቸው፡፡ ነገር ግን ንፁሑህ የሆነውን ነጩን የሠርግ ልብስ ለመልበስ ብቁ አይደሉም፡፡ በምላሳቸው ሰዎችን የሚያጠፉትን እነዚህን ቀናተኞች ይህንን የሰርግ ልብስ ማልበስ አልፈልግም፡፡ እኔን እንደሚወዱኝ ወንድሞቻቸውን ለማይወዱ ለየትኛቸውም ይህንን የሠርግ ልብስ ማልበስ አልፈልግም፡፡"

ኢየሱስ  በዚህ ደረጃ ይህንን ማሟላት የምችል አይደለሁም፡፡

"የአንቺንም ሆነ የሌሎችን የውስጥ ፈቃዳችሁን እመለከታለሁ፡፡ ያለመውደድን፣ ቂምን፣ ቅሬታን፣ ቅናትን፣ ሌሎችን መጥላትን በራሳችሁ ፍላጎት መተው ከፈለጋችሁ እኔ እረዳችኋለሁ፡፡ የሚያስፈልገውን ሌላውን ሁሉ እኔ አስተካክላለሁ፡፡ ሁሉ ነገር ያለው በፈቃድ ላይ ነው፡፡ በራሳችሁ ፈቃድ ቅናትን፣ ሃሜትን፣ ጥላቻን፣ ኩራትንና የራሳችሁን ፅድቅ ለማስተናገድ ከፈለጋችሁ ትልቅ ችግር ላይ ናችሁ፡፡

"አንድ የምጠይቃችሁ ነገር ቢኖር ለዚያን ቀን የተዘጋጀላችሁን የሠርግ ልብስ ለመልበስ ብቁ ሆናችሁ እንድትቆዩ ነው፡፡ ስለዚህም እነዚህን ነገሮች በመተዋችሁ የተገባችሁ እንደሆናችሁ ራሳችሁን በሃቅ ለመቁጠር እንድትችሉ ሁልጊዜ ራሳችሁን ጠብቁ ደግሞም ሁልጊዜ ፀልዩ፡፡ ይህ ሳይሆን ግን እያወቃችሁ በፈቃዳችሁ ንቀትን ካስተናገዳችሁና ሌሎችን በበታችነት የምትመለከቱ ከሆነ ከሚመጣው አምልጣችሁ በፊቴ ልትቆሙ አትችሉም፡፡(ሉቃስ 21፡36)

"እኔ ወድጄያችሁ እያለ እናንተ ግን ሌሎችን ለመውደድ ራሳችሁን ካልሰጣችሁ በምድር ከሚመጣው ነገር ለማምለጥ የሚገባችሁ አይደላችሁም፡፡ ለዚህ ነገር ብቁ መሆናችሁን የመፈተሻው መሣሪያ ፍቅር እንጂ የሚያልፈው ስለ እምነት የሆነው አመለካከት አይደለም፡፡ እንዲሁም ትንቢት ኃላፊ ስለሆነ መፈተሻ መሣሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ 'በጌታ ቃል' የተሞላችሁ ነቢያት ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ፍቅር ግን ከሌላችሁ በፊቴ ልትቆሙ አትችሉም፡፡"

(ክሌር) ጌታ ሆይ ይህ በእውነት እጅግ ከባድ ይመስለኛል፡፡

ልክ እዚህጋ አቁሜ ወደ ባለቤቴ በመሄድ ጌታ መሆኑን ማረጋገጥ ነበረብኝ፡፡ ምክንያቱም መልዕክቱ እጅግ ጠንካራ ስለሆነብኝ ለመቀጠል ከብዶኝ ነበር፡፡ ደግሞም ይህኛው መልዕክት ጌታ እስካሁን ከሰጠኝ ከሌሎቹ መልዕክቶች በባህርዩ የተለየ ሆኖብኝ ነበር፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ማንም ፍፁም ስለሌለ በሐሳብ፣ በቃልና በድርጊት ፍፁም መሆን አለባችሁ አላልኩም፡፡ ነገር ግን ፍፁም በሆነ ፍቅር ለመውደድ፣ ደግ ለመሆን፣ ይቅርታ ለማድረግ፤ በሌሎች ላይ ምንም የተንኮል ሐሳብ እንዲኖራችሁ ካልፈቀዳችሁ በእኔ ፊት መቆም ትችላላችሁ፡፡

"ይህ ሳይሆን ግን ራሳችሁን ፃድቅ በማድረግ እጃችሁን በሰው ላይ በመቀሰር ከተጣላችሁ፣ ከፈረዳችሁ፣ በእኔ ቦታ ቆማችሁ ፈራጅ ከሆናችሁ እነዚህ ነገሮች ናቸው የመከራውን ዘመን በዚሁ እንድትቆዩ የሚያደርጓችሁ፡፡ ክሌር ለመሆኑ ለምን ይመስልሻል እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንድታሰላስዬ የሰጠሁሽ?"

ልታዘጋጀን?

"በትክክል፣ እኔ ማንንም ሰው ወደ ኋላ ለመተው አልፈልግም፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቻችሁ ልባችሁን በሌላው ላይ አጠንክራችኋል፡፡ በዚህም ምንም የማያውቀውንና አይነስውሩን ረጋግጣችኋል፡፡ አብዛኛዎቻችሁ በኢንተርኔት በኩል አንዱ ሌላውን ተኩሶ ገድሏል፡፡ ብዙዎች ቆስለዋል፣ አካለ ስንኩል በመሆን ለሞት ታልፈው ተሰጥተዋል፡፡ ከሌሎች ተገልለውና

ተንቀው የለፉበትን ፍሬ ሳያገኙ ቀርተዋል፡፡ እናንተም ንስሐ ገብታችሁ ነቀፋችሁን ካላስወገዳችሁ በስተቀር ከእኔ ጋር ስለማትሄዱ የመከራውን ዘመን እዚህ ለመቆየት እቅድ አውጡ፡፡

"የኔ የከፍታ መለኪያ ፍቅር ነው፡፡ የሙሽራዬ መገለጫ ትዕግስት፣ ስቃይን መቋቋም፣ ደግነት፣ ይቅርታ፣ የዋህነትና ብፅዕናዎች ናቸው (ማቴዎስ 5)፡፡ በፈቃዳችሁ ከብፅዕናዎቹ ውጪ ከሆናችሁ እስካሁንም ልቤን አላገኛችሁትም፡፡ ደግሞም እስካሁንም እኔን አልመሰላችሁም፡፡ ሙሽራዬ ደግሞ እኔን መምሰል አለባት!

"አንዳንዶቻችሁ ይህ በጣም ከባድ ነው! ልትሉ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ለእናንተ እንዲህ እላለሁ፡፡ እነዚህን ኃጢያቶች ስላልተናዘዛችሁ ጥላቻን እየደበቃችሁ ነው፡፡ ለመሆኑ እኔ በምሬት፣ በቅናት፣ በጥላቻ የተሞላች ሙሽራ የማገባ ይመስላችኋል? እነዚህን ኃጢያቶች ሁሉ ከተናዘዛችሁ ብቻ ልወስዳችሁ እችላለሁ፡፡

(ክሌር) አሁንም ማቅማማት ጀመርኩ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . "ክሌር እባክሽ አታሳዝኚኝ እኔው ራሴ ነኝ፡፡ በእኔ ፊት ሊቆሙ እንደማይገባቸው አሁን ሳልነግራቸው ቀርቼ ከንጥቀት በኋላ ልንገራቸው? ለመሆኑ ለምን ይመስልሻል ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ዝንባሌ ስታሳዪ ጠንካራ በመሆን የቀጣሁሽ? እነዚህ ባህርያት እንዴት ከባድ እንደሆነ ተገነዘብሽ? ሰውነቱ ምንም ያልተበላሸውን ነፍስ እየሸለምኩ በአንፃሩ ደግሞ እኔ የተሰቃየሁለትንና የሞትኩለትን ወንድሙን ወይም እህቱን የሚጠላውን በሰማያት ሥፍራ ልስጠው?

"ሌላው ሰው እናንተን ምን እንዳደረጋችሁ አይገደኝም፡፡ የእኔ ሙሽራ ከሆናችሁ ለእኔ ስትሉ ያንን ሰው ይቅር ለማለትና ለመውደድ ፈቃደኛ የምትሆኑበትን ፀጋ ሰጥቼያችኋለሁ፡፡ ይህንን ፀጋ ለእያንዳንዳችሁ ሰጥቼያለሁ፡፡ ነገር ግን ካልተለማመዳችሁት ምን ማሰብ አለብኝ? ሚስቴ ብትሆንም እኔ የሞትኩለትን ያንን ነፍስ ግን ትጠላዋለች ብዬ ላስብ? ይህ እኩል ሸክም መሸከም ነው? አያችሁ ድካማችሁን በይቅርታ ማለፍ እችላለሁ ነገር ግን ፈቃዳችሁን ማለፍ አልችልም፡፡

"ከእናንተ ውስጥ አንዳንዶች ምናልባት በጣም ደካሞች፣ የበሰለ አመለካከት የሌላችሁና ያልኩት ነገር ገብቷችሁ መፈፀም የማትችሉ አላችሁ፡፡ ለእናንተ ይቅርታ አለ፡፡ ነገር ግን ራሳችሁን የኔ ደቀመዝሙር አድርጋችሁ የምትቆጥሩ እንዲሁም አስተማሪዎችና ነቢያቶች በእኔ መንገድ መሄድ አለባችሁ፡፡

እንዲህ ተብሎ አልተፃፈም? : <u>"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።</u>"(ማቴዎስ 7፡21-23)

<u>"ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።</u> (1ኛ ቆሮንቶስ 13፡2)

"አሁን ወደእኔ የምትጠጉበት ጊዜ ነው፡፡ ኃጢያታችሁ እንደ አለላ ቢቀላ እንደ በረዶ አነፃችኋለሁ፡፡ አሁን በፊታችሁ የቆምኩት ንስሐ እንድትገቡና ከክፉ ሥራችሁ ተመልሳችሁ ትክክለኛውን ነገር እንድታደርጉ ነው፡፡ እኔ የመጣሁት በቅጣቴ

አድምቻችሁ ትቻችሁ ልሄድ አይደለም፡፡ የመጣሁት ቁስላችሁን ለማከምና መንግስቴን ለመገንባት የሚያስፈልገውን እጅግ የበለጠውን ቅባት ልሰጣችሁ ነው፡፡

"በረጋውና ፀጥ ባለው ማለዳ ፈልጉኝ፡፡ ያን ጊዜ ለእኔ የማያስደስቱኝን ነገሮች በልባችሁ ለመግለጥ እንቀሳቀሳለሁ፡፡ አዝንላችኋለሁ ደግሞም እራራላችኋለሁ፡፡ ወደ እኔ በማስጠጋት እንደገና እሰራችኋለሁ፡፡ ደግሞም እየቀረበ ከመጣው ከዚያ ቀን እንድታመልጡ በእርግጠኝነት ወደ ራሴ እወስዳችኋለሁ፡፡

"እወዳችኋለሁ ደግሞም የምወዳቸውን እገስፃለሁ፡፡ ሰዎች እንዳያዩ የጋረዳቸውን ነገር ከንጥቀት በኋላ እንዲነሳላቸው እንደ ማድረግ ሌላ የሚያሳዝነኝ ነገር የለም፡፡ ለዚህ ነው ይህንን ጉዳይ አሁን ያመጣሁት፡፡ እባካችሁ ያልኩትን በጥሞና ውሰዱት፡፡ ሄዳችሁ በልባችሁ የተቀበረውን ጨለማ በትኩረት ለመመርመር ሞክሩ፡፡ ደግሞም በመረቀዙት ቁስሎቻችሁ ላይ ፈውስ የሚሰጣችሁን ቅባት እንዳፈስላችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ በውስጣችሁ ያለውን ሁሉ ለእኔ አሳልፋችሁ ብትሰጡኝ ምንም የምትጎዱት ነገር የለም፡፡ ሙሽሮቼ እጅግ አድርጌ እወዳችኋለሁ ከእኔ አትለዩ፡፡"

## ስፍራን ላዘጋጅላችሁ ሄጀለሁ / ኤፕሪል 26 ቀን 2015 ዓ.ም

## I've gone to prepare a place for you / April 26, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ. . . " በመንግስተ ሰማይ ለሙሽሮቼ ለእያንዳንዳችሁ  የተሰራላችሁ ቤት በፍላጎታችሁ መሰረት ፍፁም የተለየ ተደርጎ ነው የተሰራው ፡፡ የእያንዳንዱ ቤት ቀለም፤ የአሰራር ህብር፣ የስነ ህንፃ፤ የአትክልት ቦታ፣ የእንስሳት መገኛትና የተፈጥሮ አካባቢዎች ሁሉ የእያንዳንዱን ፍላጎትና ምርጫ ያካተተ ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ የምትመርጡት የጋራ መኖሪያዎችን ነው፡፡ እናም ለእናንተ ያዘጋጀሁላችሁን መኖሪያዎችን ትወዷቸዋላችሁ፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ በረሃ ትወዳላችሁ፡፡ ለእናንተ ያሳደኩትን ቁልቋል እስከታዩ ጠብቁ፡፡ ደግሞም የምትወዱት ቀለም ያለውና ሁልጊዜ እምቡጥ የማይጠፋውን አበባ ትመለከታላችሁ፡፡ የውኃ ጅረትና ገደላማ ሸለቆ፤ ከሰማይ በላይ ሰማያዊ ቀለም ያለው ውሃ፣ በአረንጓዴ የተሸፈነና  በውኃ ላይ  የመንቀሳቀስ ትዕይንት ያለው ተደርጎ የተዘጋጀላችሁን ቤተ መንግስት ትወዱታላችሁ፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ ደግሞ የባህር ዳርቻን ትወዳላችሁ፡፡ ለእናንተ የምትወዱትን የቀንድ አውጣ ሼል፤ በቅርጽ፤ በቀለም እና በአንፀባራቂነቱ በተለያየ መልኩ መርጬላችኋለሁ፡፡ በጣም ረጃጅምና ቀጫጭን ቅጠል ያላቸው ተክሎች፤ ሰፋፊ ቅጠል ያላቸው ተክሎች፣ እንዲሁም የከበሩ የቴምር ዛፎችና ትኩስ ኮኮናት አዘጋጅቼላችኋለሁ፡፡ ከመጠን በላይ የተዘጋጀውን መኖሪያችሁን  አይታችሁ አትጠግቡትም፡፡"

«ተራራና ጫካ ለምትወዱ ደግሞ ከሌርን መጠየቅ ወይም የፃፉትን መፅሐፍ ማንበብ ይጠቅማችኋል፡፡ እጅግ ትገረማላችሁ፡፡ ልብ ቅርፅ ያላቸው ኃይቆች፤ አብሮነትን የሚፈልጉ ብዙ ቀለማት ያላቸው አሣዎች፣ በጀርባቸው በማዘል የውኃውን ጥልቀት የሚያስጎበኟችሁ የውኃ ውስጥ ኤሊዎች፣  በሞገስ ከጎናችሁ የሚራመዱ የዱር እንስሳቶች ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ሁሉም

የምትወዷቸው እንስሳቶች እየጠበቋችሁ ነው፡፡ እነርሱም እንዴት እየጠበቁ እንዳሉ ልትረዱ አትችሉም፡፡ አመናችሁም አላመናችሁም ቃሉ እንደሚል እንስሳቶቹም የእናንተን ጓደኝነት በናፍቆት እየጠበቁ ነው፡፡"

ሮሜ 8-19-21 "<u>የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና።ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው።"</u>

«ስማቸውንና ማን መሆናችሁን ያውቃሉ፡፡ ከእናንተ ጋር መግባባትን በመፍጠር ልክ እንደተፃፈው እንደዛው የፍጥረትን አንድነት ለማምጣትና ንፁህ የሆነ ብፅዕናን ለመፍጠር ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን ያስረዳሉ ፡፡ ሁሉም ነገር የተሞላው በፍቅር እንደሆነ ሁሉ ሁሉም ያንኑ የተሞላውን ፍቅር ያፈሳል፡፡"

«ሙሽሮቼ ለእናንተ አዘጋጅቼ የምጠብቃችሁ ነገር ከመደነቃችሁ ብዛት ትወድቃላችሁ፡፡ እያንዳንዱን ለእናንተ የፈጠርኩትን ነገር ቀን በቀን ማየት ስትጀምሩ ለብዙ ቀናት ያህል(ምንም እንኳን ጊዜ ከምድር የተለየ አግባብ ቢኖረውም) ከመደነቃችሁ ብዛት ግራ ይገባችኋል፡፡ ቢራቢሮዎች በምትወዱት ቀለማት፤ የምትወዷቸው ወፎች፤ የሚዘምሩና ማራቸውን በለጋስነት የሚያካፍሉ፣ በእኔ ፍቅር መሞላታቸውን ለመግለፅ ልብ ቅርፅ ሰርተው የሚበሩ ንቦችን ታያላችሁ፡፡"

«ሰዎች የክፉ ምሳሌ አድርገው የተጠቀሙባቸው እንሰሳት እንደ በረዶ ጉጉት፣ ጭልፊትና የመሳሰሉት እንስሳት እኔ በፈጠርኳቸው በቀደመው ማንነታቸው የፍጥረታቱ አባልና ስብስብ በመሆን ይገለጣሉ፡፡

«በመንግስተ ሰማያት ሞት የለም ውልደት ግን አለ፡፡»

ጌታ ሆይ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

«ይህ ሚስጥር ነው፡፡ አሁን ለአንቺ የምገልጥልሽ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንን ጉዳይ ወደፊት አንቺን ላስደንቅበት አስቀምጬዋለሁ፡፡ እሺ ምክንያታዊ ላድርገውና ለምሳሌ ቅሪት የሆነች አንድ እንስሳ ሞተች እንበል፡፡ በእርግጥም ይህች እንሰሳ ከህፃን ልጇ ጋ እንደገና እንድትኖር ትደረጋለች፡፡

«ይህ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎችም መንገዶች አሉ፡፡ መጓጓቷን ከማታቋርጥ ሙሽራዬ ጋር ነው እየተጓዝኩ ያለሁት . . .»

"በምድር የምትወዱትን ምግብ የሚተካ የምግብ ዓይነት ነገር ግን ከሥጋ ውጪ የሆነ በመንግስተ ሰማይ አዘጋጅቼላችኋለሁ፡፡ በመንግስተ ሰማይ እንሰሳትን አሣዎችን ቢሆን ወፎችን ወይም ጡት አጥቢዎችንም ቢሆን መግደል የለም፡፡ እንደምትገምቱት መንግስተ ሰማይ በጣም ሰፊ ነው! በአንድ ሜዳ ውስጥ ሜዳ እንደገና በዛ ሜዳ ውስጥ ሌላ ሜዳ ይገኛል፡፡ ህዝቅኤል በትልቅ ዛጎላማ ሼል ውስጥ እንዳየው ዓይነት በአንድ ወርድና ስፋት /Dimensions/ ውስጥ ሌላ ወርድና ስፋት ይገኛል፡፡ »

አዎ ህዝቅኤል ከጌታ ጋር እየዋኘ እያለ በሐይቁ ታችኛው ክፍል በአሻዋው ላይ በጣም ትልቅ የሆነ የዛጎል ሼል ያያል፡፡ እየዋኘና ወደ ሼሉ እየቀረበ ሲመጣ ህፃናትና የእንስሳት ልጆች እየተጫወቱበት ወደአለ ወደ ትልቅ አረንጎዴ ሜዳ ውስጥ ይገባል፡፡ በጣም ደስታ የተሞላበት ቦታ ነበር ይህም ለህፃናት የተሰራ ቦታ ነበር፡፡ በቃላት ሊገለጥ የማይችል ደስታን ለህፃናቶች ተብሎ የተዘጋጀ ሥፍራ ነው፡፡

«በመንግስ ሰማያት ውስጥ በአቫተር ፊልም ላይ እንዳያችሁት ዓይነት መጎነኘ መኪናዎች፣ ፈረሶችና ትላልቅ ወፎች አሉ፡፡ በአየር ላይም በነፃነት መንቀሳቀስ ብትችሉም በምታራመዱ ጊዜ እንኳን ሽክም የሚሆንባችው ነገር አይኖርም፡፡ ሁሉም ነገር የእናንተን ጥረት የማይጠይቅ ወይም ህመም የሌለው ነው፡፡ ይህ ለአንዳንዶቻችሁ መገለጥ ይሆናል፡፡ ምክንያቱ አሁን በዚህ ምድር ላይ ህይወት ሁሉ ለእናንተ ህመም ስለሆነ ነው፡፡

ጌታ ጥያቄ አለኝ፡፡ ኪቦርድስ . . . ይኖራል? ታውቃለህ እኔ ምን ያህል ኪቦርዴን እንደምወድ፡፡

ጌታም እንዲህ አለ . . . «በመንግስተ ሰማያት ውስጥ የሚኖረው መሳሪያ እንደ ላባ በጣም የቀለሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ልክ አሁን እንዳለሽ ዓይነት ብዙ ስራዎች ይኖሩሻል፡፡ ቢሆንም ከመሳሪያዎቹ ጋር መላክቶች ይመደቡልሻል፡፡ እናም ማንኛውንም የወደድሽውን ዓይነት የሙዚቃ ድምጽ ወዲያው በቅፅበት ያወጡልሻል፡፡ በአይምሮሽ ያለውን ማድመጥና ያለ ምንም ስህተት ተግባርያዊ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ተግባቦት ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ነው የሚከናወነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ከተፈጥሮ በላይ ነው የሚከናወነው፡፡»

አ! በጣም የሚደንቅ ነው! ይህ የምድርን ሁለት ሶስተኛውን ጭንቀት ይቀንሳል፡፡

«እንደ እውነቱ ከሆነ በመንንግስተ ሰማያት ውስጥ ሁሉ ነገር ያለ ልፋት የሚገኘው ነው፡፡»

ጌታ ታዲያ ይህንን ኑሮ ለምደነው ወደ መሰልቸት እንመጣ ይሆን?

«ኦ በፍፁም! በጣም ብዙ ብዙ ስጦታዎችን መለዋወጥ፣ ተግባቦቶች፣ መዝሙሮችና ፊልሞች ይኖራሉ ......»

ቆይ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ፊልም መሥራት አለ?

«አዎ ብዙ የሚነገሩ የታሪክ ትርክታዎችና የፈጠራ ስራዎች ከምድር ካሉት ሙሉ ለሙሉ የሚሻል ነገር ይኖራል፡፡ ቀላሉ ነገር ደግሞ እነዚህ ስራዎች በመንግስተ ሰማያት በቴፕ ተቀርፀው ለዘላለም መቀመጣቸው ነው፡፡»

በመንግስተ ሰማያት ውስጥ መቅረጫ አለ?

«አዎ የመቅረፅ መሳሪያዎች አሉ፡፡ ልክ በመንግስተ ሰማያት መፅሐፍት ቤት ውስጥ መፅሐፍት እንዳለ ሁሉ ምስልና ድምፅ መቅረጫም አለ፡፡ ነገር ግን በመላዕክቶች ቀጥታ የሚቀርቡ ብዙ ፕሮግራሞችም ይኖራሉ፡፡ እነርሱም በአጠቃላይ ሂደቱ ውስጥ በተዋናይነትና በረዳትነት ያገለግላሉ፡፡ ክሌር እኔ ለናንተ ያዘጋጀውትን ነገር ለማሰብ መጀመር እንኳን አትችሉም፡፡»

ኦ! ይህን ስሰማ ብዙ ለመስማት እጓጓለሁ፡፡ በጣም የሚደንቅ ነው፡፡ ሁልግዜ ፊልም መስራት እፈልግ ነበር፡፡ ህዝቅኤልም እንደዛው፡፡

«እድል ታገኛላችሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን ልናገር፣ አምልኮውን ፍፁም ስለምትወጂው ወደዛ ትሳቢና የዛ አካል ትሆኛለሽ፡፡ ከዚያ በኋላ ከአምልኮ ላይ አንቺን ማስነሳት ከባድ ነው የሚሆነው፡፡»

ኦ ጌታ! ይህ ልቤን በበረከት ይሞላዋል፡፡ በምድር ላይ በጣም የምንፈልገውን አምልኮ የመምራት እድል አግኝተን እንደማናውቅ ታውቃለህ፡፡ ደግሞ የኔ ችሎታ መሻሻል ያስፈልገዋል፡፡

«ይህ ነገር ከአሁን በኋላ ምንም ችግር ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በአይምሮአችሁ የሆነ ነገር ትሰማላችሁ፣ ከዚያም ወዲያውኑ ፍፁም በሆነ መልኩ ትጫወቱታላችሁ፡፡»

"ኦ ጌታ ሆይ ይህ ለእኛ እጅግ ብዙ ነው፡፡

«አውቃለሁ የእኔ ፍቅር፡፡ ነገር ግን ለሙሽሮቼ ሁሉ በቅርብ የት እንደምወስዳቸው ትንሽ ሐሳቡ እንዲኖራቸው ፈልጌ ነው፡፡ ይህም ለጉዞዋቸው የመጨረሻ እርምጃ ብርታት እንዲሆናቸው ነው፡፡የአሁኑ ስቃይ ከሚጠብቃቸው ክብር አንፃር ምንም ሊወዳደር የማይችል እንደሆነ እንዲያዩ ነው ፡፡ በእርግጥም ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል ይፈፀማል፡፡

«እንግዲህ ተስፋ አደርጋለሁ ሁላችሁም ቃሌን ጠጥታችሁ የሚጠብቃችሁን መንግስተ ሰማያት አትኩራችሁ እንደምታዩ፡፡ ከሌር ደግሞ ማታ ስለነበረን የፀሎት ጊዜ ንገሪያቸው፡፡»

እና በሚወዛወዘው ወንበር ላይ በገነት አትክልት ሥፍራ ውስጥ የነገረኝን ይህንን ነው የማካፍላችሁ ፡፡ በጣም በሚያምርና የተለያዩ ቀለማት ያላቸው የተዋቡና ሽታቸው የሚያውድ ዕፅዋዕት ያሉበት፣ ደግሞም እፅዋት የሚያዜሙ የሚመስልበት ሥፍራ፣ ፍፁም ሰላምና ደስታ ያለበት ቦታ፡፡ ብቻ ምን ልበላችሁ በቃ በጣም የሚያምር አካባቢ ነው፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የምወዳቸውን አንዳንድ ክርስቲያኖች ማየት ጀመርኩ፡፡ ሐዋሪያቶች፣ ነብያቶች፣ታማኝ ሰዎችና የእግዚአብሔር ሴቶችን፡፡ በተጨማሪም ታማኝና እጅግ ውብ የሆኑ የዩቲዩብ ቤተሰቦችንም በዛ ለማየት ጓጉቼ ነበር፡፡ እንዲህም እያልኩ አሰብኩ ምነው እነሱም ነፍሳቸው እንደዚ ባማረ ቦታና በክርስቶስ ልብ ውስጥ እንዳለ ማየት ቢችሉ፡፡

እናም ጌታ እንዲህ አለኝ. . . «አንድ ቀን ይህ ራዕይ እነሱንም ያጠቃልልና ሁላችንም አብረን እንደሰታለን፡፡ ነገር ግን ለአሁን የእኔ ጣፋጭ ወንድና ሴት ሙሽሮቼ ሁላችሁም እውነተኛውን ፍፁም ህይወት አንዳንችን ከአንዳችን ጋር በህብረት የምንኖርበት ሥፍራ ለእናንተ እያዘጋጀሁላችሁ ስለሆነ ተፅናኑ፡፡ ተበረታቱ እናም ጠንክሩ በቅርብ እመጣለሁ፡፡»

## ቸርነት ማድረግ የኃጥያትን ብዛት ይሸፍናልአ.አ. /ሜይ 5 ቀን 2015 ዓ.ም

## Charity Covers a Multitude of Sins/ May 5, 2015

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . «የኔ ሙሽሮች በአጠገባችሁ ያለውን አስተውሉ፡፡ እናም የቱጋ ፍትህ እንደሚያስፈልግ ተመልከቱ፡፡ በአካባቢያችሁ ምግብ ፣ መድኃኒት፣ እዳቸውን የሚከፍልላቸው፣ መኪናቸውን የሚያድስላቸው፣ የህክምን ወጪ የሚሸፍንላቸው ያጡትን ተመልከቱ፡፡ ፡፡ ዕርዳታ የሚሹ ብዙ ሽግሌዎችና ቤተሰብ ያላቸው ወጣቶች አሉ፡፡ አከባቢያችሁን በመመልከት ዕርዳታ ለሚያስፈልገው ዕርዳታ አድርጉ፡፡ የማትፈልጉት መኪና አላችሁ? ሌሎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉት ለእናንተ ግን የማያስፈልጉ ልብሶች፣ የቤት ዕቃዎችና የኩሽና ዕቃዎች አላችሁ? ለሚያስፈልጋቸው ስጡ፡፡

«ብዙ የተቸገሩ በአካባቢያችው አሉ ፡፡ በሰማይ እንዳለው አባቴ በመሆን በተቸገሩ ላይ መልካም ነገርን አፍስሱ፡፡ ለሌሎች መልካም ለማድረግ የምትችሉበት ብዙ ጊዜ የላችሁም፡፡ ስለዚህ በተቻላችሁ አቅም በቀረው ጊዜያችሁ መልካም ነገር አድርጉ፡፡ በምድር ሆናችሁ መልካም ነገር እንዴት እንዳደረጋችሁ የምታስመዘግቡበት ጊዜ ለዘላለም እየተዘጋ ነው፡፡ በምድር የምትኖሩበትን የመጨረሻ ሰዓታት መልካም ነገር አድርጉበት፡፡ በዙሪያችሁ ሆነው የሚስፈልጋቸውን ለማግኘት ለሚጠባበቁ ድሆችና እንዲሁም ለሚጠይቋችሁ ስጡ፡፡ በጭውውቶች መካከል ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሲናገሩ ለመስማትና ለመርዳት ጆሮቻችሁን ክፍት አድርጉ፡፡ በዚህ ምድር የምትቆዩት ለጥቂት ጊዜ በመሆኑ ለመስጠት ሁኔታዎችን ሁሉ ተጠቀሙ፡፡

«ይህ ለእኔ ያላችሁን ፍቅር የምታሳዩበት ጥሩ አጋጣሚ ነው ፡፡ ተርቤ ሳለ አብልታችሁኛል፤ በብቸኝነቴ ሰዓት ጎብኝታችሁኛል፤ መጓጓዣ ባጣሁ ጊዜ አጓጉዛችሁኛል፣ መድኃኒት ባጣው ጊዜ ገዝታችሁልኛል፡፡ አይታያችሁም? እነዚህን ሁሉ ሰዎች ከፊታችው ያስቀመጥኩት ያላችሁን ቸርነትና ለእኔ ያላችውን ፍቅር ለመፈተን ነው፡፡ እኔ የማደርገውን ታደርጉ እንደሆነ ማየት እፈልጋለሁ፡፡ የተወሰነ ኃብት አላችሁ ፤ ከዚህ ሌላ የሚጠይቀው ነገር የሌሎችን ችግር በማስተዋልና በፍቅር ልብ ወደሚያስፈልጋቸው ሰዎች መድረስ ነው፡፡

«ቸርነት የኃጢያትን ብዛት ይሸፍናል፡፡ በዚህ ህይወት ሳላችሁ ስለ ራሳችሁ ከእናንተ በጥልቅ የሰወርኳቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ ነገር ግን እናንተ በምታደርጉት ቸርነት ለዘላለም ከእናንተ ይወገዳሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ለፅድቅ የሚሰራ ሥራ አይደለም፡፡ ይህ የወንጌል ፍቅር ነው፡፡ ይህ ቸርነት በማድረግ ማጣትን መሸፈን ነው፡፡ ይህ የእኔ ልብ በሥራ ላይ ሲወል ነው፡፡ ራሳችሁን ለማስደሰት ከምታደርጉ ይልቅ በአካባቢያችሁ ለሚገኙ በጣም ለሚያስፈልጋችሁ ሰዎች ገንዘባችሁን ብታውሉ እኔ የማደርገውን ማድረጋችሁ ስለሆነ እንዴት ያለ ታላቅ ሽልማት ይጠብቃችኋል!

«ይህ የምትኖሩት ህይወት ሁሉ የእኔ መሆናችሁንና ለመንግስተ ሰማያት የምትገቡ መሆናችሁን መመዘኛ ነው፡፡ ብዙዋቻችሁ የሚጠበቅባችሁን ማሟላት አልቻላችሁም፡፡ ነገር ግን መውደቃችሁን በማወቅ ለመስተካል እየሞከራችሁ ነው፡፡ ንስሐ ገብታችሁ ራሳችሁን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ በመመለስ ከመጀመሪያው ይጠበቅባችሁ የነበረውን እያደረጋችሁ ነው፡፡ ከአሁን ወዲያ ውድቀታችሁ አይታሰብም፡፡

«አንዳንዶቻችው ከሌላችሁ ነገር ላይ ማድረግ የምችሉትን ሁሉ አድርጋችኋል፡፡ የእናንተም ሽልማት ከጉድለቷ እንደ ሰጠችው እንደ ድኃዋ መበለት ነው፡፡ ሌሎቻችሁ የሰጣችሁት ከተትረፈረፈ ነገራችሁ ስለሆነ በሰማይ የተመዘገበው ጥቂትና የጎደለ ነው፡፡ ለአንዳንዶቻችሁ መስጠት ያለባችሁ ገንዘብ ሳይሆን ያላችሁን ጊዜ ከመንገዳችሁ ወጣ በማለት ለሚያስፈልጋቸው ማዋል ነው፡፡ ይህም የራሱ ሽልማት ያለው ነው፡፡

«ነገር ግን አሁን እያልኩ ያለውት ከራስ ወዳድነትና ትኩረት ካለመስጠት እንድትነቁ እድል እየሰጠኋችሁ ነው፡፡ይህን እድል ተጠቀሙበት፡፡ ይህ ለሙሽራዬ  ያቀረብኩት ምህረት ነው፡፡

«የእኔ ሙሽሮች በጥንቃቄ ስሙ፡፡ እኔ የምፈርደው በሌላችሁ ነገር ላይ ሳይሆን ኖሯችሁ ከሰዎች ጋር እንዴት ተካፍላችሁ በምትኖሩት ላይ ነው፡፡ በቀላሉ ለማየት የጋገራችሁትን ትንሽ ዳቦ ለአንድ ለተራበ ደሃ ሰው ማካፈል በእኔ ዘንድ ትልቅ ቦታ አለው፡፡ አንድ መኪናው ነዳጅ ያለቀበት መንገደኛ ነደጅ ማደያ ድረስ ማድረስ ለእኔ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ እንዲሁም ብዙ ልጆች ይዛ እቃ የተሸከመች አንዲት እናትን ማገዝ ትልቅ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ትንንሽ ነገሮች ሁሉ በእኔ ዘንድ ትልቅ ቦታ ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ለተቸገሩት ያላችሁን ልብ ያሳያል፡፡ ለእነዚህ ጥቃቅን የፍቅር ማሳያዎች ታላቅ ዋጋ እከፍላችኋሁ፡፡

«መልካም ከመስራት አትታክቱ፡፡ ለወንጌል ፊታቸውን ላዞሩት እንኳን 'ጊዜው አጭር እንደሆነና ከምድሪቱ ኃጢያት የተነሳ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሊመጣ ስላለው መጥፎ ክስተቶችና ፍርድ በማስገንዘብ . . . ሰዎችን ኢየሱስን ታውቁታላችሁ?' ብሎ መጠየቅ እጅግ በጣም አስፈላጊው ነገር ነው፡፡ እነርሱ ተቀበሏችሁም አልተቀበሏችሁም ይህንን ነገር መናገር አስፈላጊ ነው፡፡

«አጠገባችሁ ያሉትን ሰዎች ስቃይ መጋራት ባትችሉ እንኳን በፀሎት መደገፍ ይህም በእኔ ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው፡፡ ከፍርሃት ሳይሆን ከፍቅር የተነሳ የሚደረጉ እንደነዚህ ዓይነት ትንንሽ ነገሮች ናቸው የሚያስፈልጉት፡፡ ሰዎቹ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለይታችሁ የምታደርጉት ነገር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

«ስለዚህ አሁን በዚህ በረከት ባርኬ ወደ አለም ልልካችሁ ነው፡፡ በመንገዳችሁ ሁሉ ላይ አይኖቻችሁን በደንብ በመክፈት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ እየተሰቃዩ ያሉትን በማየት የሌሎችን ተስፋና ህልም በማሳካት ሂዱ፡፡ በዙሪያችሁ ላሉና እርዳታ ፈልገው ለሚጮሁ ጆሮአችሁን ከፈትኩ፡፡ ምላሽ ለማግኘት በመፈለግ ሳይሆን ነገሮችን እንዲሁ በደስታ የምታደርጉበት ፀጋ በዚህ ምሽት አካፈልኳችሁ፡፡

«አሁን ወደፊት ሂዱ፡፡ ጎረቤቶቻችሁን እንደራሳችው ውደዱ»

### አለም ፍርክስክሱ ሲወጣ እናንተስ ትቆሙ ይሆን?/ ሜይ 11 ቀን 2015 ዓ.ም

### Will you stand when the world crumbles? / May 11, 2015

ክሴር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . የተወደዳችሁ የዩ-ቲዩብ ቤተሰቦች ጌታ ከገበያ ማዕከላት፣ ከኢንተርኔት መረቦች፣ ፊልሞችን ከማየትና ከሌሎችም የመዝናኛ ዓይነቶች እንድትርቁ የጠየቃችሁን ጉዳይ አንዳንዶቻችሁ ግራ እንደተጋባችሁ ነው የገለፃችሁት፡፡ ለእናንተ በምፀልይ ጊዜ ሁሉ ነገር ፍንትው ብሎ ታየኝ፡፡ በአሜሪካና በሌሎች ቦታዎች የምንገኝ ሁሉ በዳንኤል መፅሐፍ ምዕራፍ ሁለት ላይ የተገለፀው ጭኖቹ ብረት፥ እግሮቹ ግማሹ ብረት ግማሹም ሸክላ የሆነውና በምድር ሁሉ ላይ በመነሳት ምድርን የሚበላው ምስል ጉዳይ ሲፈፀም ልናይ ነው፡፡ የጀርመኑ ሂትለር እንዳደረገው እንደዛው ብዙዎች ግንዛቤው ሳይኖራቸውና ሳያውቁ ሊጠመዱ ነው፡፡

ግንዛቤው ሳይኖራቸው የሚጠመዱት ደግሞ ጊዜያቸውንና እሴቶቻቸውን በዚህ አለም ጉዳዮች ላይ ያደረጉ ሲሆኑ እነዚህም ገንዘብ፣ ገበያ ማዕከላት፣ ግብይቶች፣ ለተለያዩ ነገሮች መጓጓት፣ ክበረ በአላት፣የተለያዩ ግብዣዎች፣ ጊዜን የምናጠፋባቸው ሁኔታዎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ነገር ግን ጊዜያቸውን በቋሚነት ከጌታ ጋር የሚያደርጉና ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ዋጋ የሚሰጡ ሰዎች ስለሁኔታው በቅድሚያ በደንብ ስለሚያውቁ ፀንተው የሚቆሙት እነዚህ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ግን በዙሪያችን የሚንኮታኮቱትና በሚመጣው ኃይል እግር ሥር እንደ አቧራ ብናኝ የሚሆኑት ሁላችንም ነፃ ሰዎች እንደሆኑ የምናውቃቸው ሰዎች ናቸው፡፡

በአንድ ቀን አለም ይቀያየራል፡፡ ጊዜያቸውን በኢንተርኔት፣ በዜና፣ በቲውተር፣ በፌስ ቡክ፣ በዩቲብ፣ በስልክን በመሳሰሉት የመገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች ጊዜያቸውን የሚያጠፉ ሰዎች እነርሱ የሚያውቁት አለም ሲቆም በአንድ አፍታ አንዱ ከሌላው በመለየት ፍሬ አልባና ባዶ ይሆናሉ፡፡

በዚያን ወቅት እውነታችን እግዚአብሔር ብቻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት አሁን ካልኮተኮትነው በስተቀረ ባለስልጣኖች በጭፍን ወደ እሥራት ከሚመሩን እግዚአብሔራዊ ካልሆነው ከሚመጣው መንግስት እውነታ ውጪ ምንም እውነታ ሊኖረን አይችልም፡፡ ለገንዘብ ከኖራችሁ በገንዘብ ትወድቃላችሁ፡፡ ዋጋ ቢስ በሆነ መዝናናቶች፣ አለማዊ በሆነ መንገድ ኖራችሁ ከሆነ፣ እላይ በተጠቀሱት የመገናኛ መንገዶችና በከፍተኛ መጓጓት ኖራችሁ ከሆነ እናንተ እውነት ብላችሁ የያዛችሁት መንገድ ሲወሰድባችሁ እነዚህ የተወሰዱባችሁ ምቾቶቻችሁ እንዲመለሱላችሁና የደህንነት ስሜት እንዲሰማችሁ ለማድረግ የሚጠይቃችሁን መስዋዕት ሁሉ ትከፍላላችሁ፡፡

ነገር ግን በምን ዋጋ መጠን ነው ይህንን የምታደርጉት? ሰው አለምን ሁሉ ቢያተርፍና ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? በዚያን ሰዓት ብዙዎች ነፍሳቸውን ያጣሉ፡፡ ምቾቶቻቸው እንዲመለሱላቸው ለማድረግ ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ፡፡ መፅሐፍ ቅዱሳቸውንና የባንክ ደብተራቸውን ጎን ለጎን ያስቀምጣሉ፡፡ አይታያችሁም? ኢየሱስ ለእነዚህ ጊዜያቶች እያዘጋጀን ነው፡፡ በዚህም በእርሱ ላይ ፀንተን እንድንቆምና ነገሮችን ሳናውቅ ግራ በመጋባት እንዳንደነግጥ እያዘጋጀን ነው፡፡ ለዚህ ጊዜ ልባችንን አዘጋጅተናል፡፡ ጥንካሬያችንን ከእኛ ውጪ በሆነ በመገናኛ ብዙኃን ላይ ሳይሆን በውስጣችን በሚኖረው በእግዚአብሔር ላይ እንዲሆን ኮትኩተናል፡፡ የእኛ ጥንካሬ ሊሆን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው፡፡ የቀረው አለም በተፈጠረው ትርምስምስ ግራ ተጋብቶት እያለ እኛ ግን አይምሮን የሚያልፍ ሰላም ይኖረናል፡፡

እርሱ የመርከባችን መሪ በመሆን አቅጣጫን ያሳየናል፣ ይመራናል፡፡ ሞገዱ በኃይል ቢናወጥም የመርከቡ መሪ ክርስቶስ ከእኛ ጋር ስለሆነ ኢየሱስ በማዕበሉ ውስጥ እንደተኛ እኛም በሰላም እንተኛለን፡፡ ስለዚህም እኔ የምጠይቃችሁ ህይወታችሁን በመቀየር ጌታን እንዳታስቀኑት ነው፡፡ ይህንን እንድታደርጉ የጠየቃችሁ ለሥርጋችን ቀን ብቻ ሳይሆን ለሚያስፈልግና እውነተኛ ለሆነ ዓላማ ነው፡፡ ይህም ሌላው አለም በትርምስ ውስጥ ሲወድቅ እናንተ ፀንታችሁ እንድትቆሙ ነው፡፡ መልካም አድናቂዎች በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥሉ፡፡ እሴቶቻችሁንና በህይወት የምታደርጉት አትኩሮት ሁሉ በእርሱ ላይ አድርጉት፡፡ በዚህም አለም ሁሉ ሲበታተን እናንተ ግን እግዚአብሔር በገባላችሁ ቃል ላይ በመተማመን ትቆማላችሁ፡፡

## ለእኔ ማን እንደሆንሽ / እ.አ.አ ሜይ 31 ቀን 2015 ዓ.ም

## Who You Are To Me / May 31, 2015

“የኔ ፍቅር ምን ዓይነት እንደሆነ ማውራት እፈልጋለሁ፡፡ ማንም ሊረዳው በማይችል መልኩ እወድሻለሁ(ሙሽሪትን)፡፡ አየሽ በምድር ላይ ያለው ፍቅር የተሸረሸረ ወይም የደረቀ የኤሮስ ወይም የአጋፔ ፍቅር፤ የፍቅረኞች ወይም የወንድማማቾችና የእህትማማቾች ፍቅር ነው ያለው፡፡ እኔ ግን የሰጡሁሽ የማይጠፋ በወርቅ ማስቀመጫ እንደተሰራ ምርጥ እንቁ ነው፡፡ ባለፈው የማይሆን ምርጫ ስትመርጪ እንደ አጋር ላበረታሽ መጣሁ፡፡ የውስጥ ፍላጎትሽ ምን እነደሆነ ስለተረዳሁ ያንን ምርጫሽን አክብሬያለሁ፡፡ በአንቺ ላይ ከመፍረድ ይልቅ የአንቺ ወገን ሆኜ ላነሳሽና ተስፋን ልሰጥሽ ፤ እንዳውም ራስሽን እንዲታውቂ ላደርግሽ መጣሁ፡፡"

“አንድ ሰው የኃጢያት ልማድ ሲኖረው አንድ ነገር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመቀደስ ልምድ ሲኖረው ሌላ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ ራስን በመግዛት፣ በጥበብና በሙብሰል ከፍተኛ ደረጃ እንደደረሳችሁ አድርጋችሁ አታስመስሉ፡፡ ምን ሊሆን እንዳለ እኔ ቀድሜ አውቃለሁ፡፡ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት በሩን ሲከፍትና ልታመልጠው ስትል ሲይዛት እንኳን እኔ በአጠገቡ ነኝ፡፡ በየትኛው በኩል እንደምትፈተኑና ሊገጥማችሁ ያለውን እንቅፋት በግልፅ በማወቅ ስለ ደህንነታችሁ እጨነቃለሁ፡፡"

“ያሰብሽው ሳይሳካ ሲቀርና ስታዝኚ በጉንጮችሽ ላይ ያለውን እንባ እጠርጋለሁ፡፡ እንዴት መቀጠል እንዳለብሽ ግራ ሲገባሽ ከጎንሽ ቁጭ ብዬ አፅናናሻለሁ፡፡ በቀን ውስጥ የምታስቢውንን፣ ስሜቶችሽንና ለመሆን የምታልሚውን ሳልታክት ቀኑን ሙሉ በፍቅር እሰማለሁ፡፡ ይህንንም በመውሰድ በልብሽ ውስጥ ወዳስቀመጥኩት ፍፃሜ አትመዋለው፡፡“

“የህይወትሽ አካል ለመሆን ምንም እድል እንዲያመልጠኝ አልፈልግም፡፡ የእኔ ፍቅር ህይወትሽ የኔም ህይወት ነው፡፡ በእውነት አንድ ነን እናም ወደ ፍፃሜያችን ለመድረስ ሁለመናዬ አንቺን ለመርዳት ጀምሯል፡፡ በልብሽ የላቀ ሐሳብ አስቀምጫለሁ፡፡ ያየሽው ወርቃማው የሙዚቃ መሳሪያ እንኳን ሳይቀር! ገና በፊት ልብሽ ወደዚያ ሳያዘነብል ለአንቺ የፈጠርኩት ነው፡፡ ከዚያም በዘረመለመልሽ ውስጥ ያንን ፍላጎት አስቀመጥኩ፡፡ የዘረመለመልሽ አወቃቀር እንደዛ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ እናም የዚህ መከናወን የታቀደው በጊዜ መቆጠር ሳይጀመር በፊት ነው፡፡ ይህንን በሰው አዕምሮ ለመረዳት ይከብዳል፡፡"

“አንቺ ስወልድሽ ስምምነት ነበረን፡፡ የራሳችን ህልም ነበረን፡፡ እኔ ብቻዬን ወደ ፍፅምና የማደርሰው የራሳችን እቅድና ውጤት ነበረን፡፡ አ! ሰው ግን የራሱን መንገድ ቀየሰ፡፡ እውነታው ሰው በፊቱ በተቀመጡለት ዝግና ክፍት በሮች በጭፍን የሚጓዝ ነገር ግን በመንፈሴ ሥራ የሚመራ ነው፡፡ የተዘጉ በሮች እንኳን ህልሙን ለማሳደግ ጠቃሚ ናቸው፡፡ ሁለቱንም ክፍትና ዝግ በሮች ከፊቱ አስቀምጫለው፡፡

ክሌር ሰዎች ሁሉ ቢያምኑኝና ከሰወኛ አስተሳሰብ ወጥተው እኔ ያልኳቸውን ነገር ብቻ ቢያደረጉ ኖሮ! ፡፡ የእነርሱ ፍርኃት፣ ባዶነትና ማጣት የመጣው በራሳቸው መንገድ በጭፍን ስለተጓዙ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ ኩሩነታቸው ያመጣባቸው ጣጣ ነው፡፡ ምክንያቱም እነርሱ የሚያውቁትን ትተው እኔ በማሳያቸው መንገድ በጭፍን ለመሄድ የሚያውቁትን መተው ስለማይችሉ ነው፡፡"

(ክሌር)፡- ኢዚህጋ እየተናገረ ያለው ስለ ትህትና፣ ስለ መገዛት እና ስለ መታዘዝ በዘይቤያዊ አነጋጋር ነው፡፡ እኔ እንዳገኘሁት እርሱ እኔ በህይወት ያካበትኩትን ችሎታ አልጠየቀም፡፡ ነገር ግን ያደረገው ነገር የኔ የሆነውን በማስወገድ ፈቃዱን በራሱ ብቻ በእኔ ላይ እንዲፈፀም ነው፡፡

“ነገር ግን ብዙዎቹ ምላሹን ያውቁታል፡፡ ስለዚህም በላኩላቸው ጥበብ ፍሬ አያፈሩበትም፡፡ ነፍሶች የበለጠ ብልህ በሆኑ ቁጥር የተፈጠሩበትን እውነተኛ ዓላማ ለመሳት ዕድሉ ሰፊ ነው፡፡ የማሰብ ችሎታቸው የሚመረኮዘው በሰው አስተሳሰብ ላይ ነው፡፡ ጣራ ጥግ የደረሰው ፍልስፍናና አስተሳሰብ እንኳን እንዲሄዱበት በጠራኋቸው መንገድ ላይ የሞት ያህል እንቅፋት ነው፡፡ ህይወታቸውን የመቆጣጠር ህልማቸው ቅዠት ነው፡፡ ልክ መጨረሻ ላይ ሲደርሱ ግን ውስጣችንን ያረካል ያሉት ነገር ሁሉ ከንቱ ይሆንባቸዋል፡፡ ከዚያም ምንም የሚፅናኑበት ነገር ስለሚያጡ ባዶነት ወይም ጎዶሎነት ይሰማቸዋል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ይህ ሁሉ በራሳቸው መንገድ በመሄዳቸው ያፈሩት ፍሬ ነው፡፡

“ለእኔ ለመኖር ሲሉ ለራሳቸው የሚሞቱ ሴትና ወንድ ልጆች ማግኘት ፍፁም ያልተለመደ ነው፡፡ ለዚህ ነው እንደነዚህ ዓይነቶች በእኔ ዘንድ እንደ ኃብት የሚቆጠሩት፡፡ በማይመችና ክብካቤ በሌለው አለም ውስጥ እነዚህ ለእኔ መፅናኛዎቼ ናቸው፡፡ እነዚህንም ውበት የተሞላበት መከናወን የራሳቸው የሆነውን ህይወት ከውስጣቸው መጥጦ በማስወገድ በጭፍን ይመራቸዋል፡፡

"ስለዚህም የኔ ሙሽሮች የኔ ፍቅር ይግባችሁ፡፡ ከፍተኛ ዋጋ በመስጠት ተሸክሜ እየተከባከብኳችሁ ወደ ፍፃሜያችሁ አደርሳችኋለሁ፡፡ የራሳቸውን ጥበብ ትታችሁ የእኔን ልትከተሉ ስለወደዳችሁ የእናንተን ጉዳይ ለማሳመር ፈቅዳችሁልኛል፡፡ ስለዚህም እኔ ስፈጥራችሁ በእናንተ ልፈፅመው ያቀድኩትን እጅግ ልዩ በሆነው አደራረጌና በልዩ ቀለማቴ እንዲያሸበርቅ ለማድረግ ነፃ ስለሆንኩ ሁሉንም እንደሚገባው ሰርቼ እኔ ወዳየሁላቸው ፍፃሜ አስገባችኋለሁ፡፡

“ስለዚህ አንቺ ላይ እንዴት ኃይለኛ እሆንብሻለሁ? አየሽ አንቺ ድክ ድክ እያለች አባቷን እደምትከተል ልጅ ነሽ፡፡ አባቷ በመገኘቱ ደስተኛና ሃሴት የምታደርጊ፤ ከእርሱ ጋር ከመሆን ውጪ ሌላ ምንም የማትፈልጊና ለእርሱም ደስታ የምታመጪ ነሽ፡፡ ባንቺ እንዴት እንደምደሰትና እንደምዘምር፡፡ በእውነት አንቺ እንደ አይኔ ብሌን እና ከውድ እንቁ ይልቅ የምታበሪ ነሽ፡፡ የኔ ህይወት ለአንቺ ስለተሰጠ በትልቅ ጭንቀት እጠብቅሻለሁ፡፡ አ! እውነተኛ ማንነታቸውን አውቀው አፍቃሪ በሆነው አባታቸው እጅ ራሳቸውን አሳልፈው በሰጡት ነፍሴ እንዴት ሃሴት እንደምታደርግ፡፡

“ሁላችሁንም አሁን እባርካችኋለሁ፡፡ ለእኔ ፍላጎት ብላችሁ ራሳችሁን የተዋችሁና በአለም የሚገኘውን የማይጠወልግ መስሎ የሚታየውን የናቃችሁ የእኔ ውድ ሙሽሮች ናችሁ፡፡ አ! እንዴት ለእኔ ትልቅ ኃብት እንደሆናችሁ፡፡ አንድ ነገር ይቀራችኋል ያንንም ደግሞ እሰጣችኋለሁ፡፡ በእውነት ለእኔ ማን መሆናችሁን የሚያስገነዝበውን ፍቅሬን ፣ ራዕዬን፣ ሐሳቤን መቀበል የምትችሉበት ብቃትን፤ ይህም ለዘላለም በእናንተ ልብ ውስጥ እንዲኖርና ማንም ከእናንተ ድጋሚ እንዳይነጥቀው እባርካችኋለሁ፡፡

**እግዚአብሔር ስቃይን ለምን ይፈቅዳል? / ጁን 1 ቀን 2015 ዓ.ም**

**Why Does God Allow Suffering? / June 1. 2015**

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . «አመስጋኝ መሆን ለተሻሉና ለላቁ በረከቶች ከፋች በር ነው፡፡ በምስጋና የራስንም ሆነ የሌሎችን ሰንሰለት የሚያላላና የሚበጣጥስ ኃይል ይመጣል፡፡ መራራ መንፈስ በመንገድ ላይ ሲቆም እስራት ይሆናል፡፡ መራራውን መንፈስ ካስወገዳችሁ ግን ፈውስ ቦታውን ይይዛል፡፡

«ክሌር ብዙዎች አሉ መራራ መንፈስ በመንገዳቸው ላይ የቆመና በህይወታች እኔ እየሰራሁ ያለሁት፡፡ ምንም ሊረዱት የማይችሉት ነገሮች በነፍሳቸው ውስጥ ይከናወናሉ፡፡ ስለዚህም እኔን ይወቅሱኛል ደግሞም መራራ ይሆናሉ፡፡ እውነት ነው ነገሮች ውለው ሲያድሩ የሆነውን ነገር መከላከል እችላለሁ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ነገሮች ሁሉ የሚሆኑት ለምክንያት መሆኑ እውነት ነው፡፡ ነገሮች ከመፈጠራቸው በፊት መሆን ያለባቸው ሁሉ በምክንያት መሆኑም እውነት ነው፡፡ ይህ ምክንያት ግን የሰው ልጆች አይምሮ ሊረዳው የማይችለው ትልቅ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎች አሉ እነርሱ የህይወት ግብ ብለው ከግባቸው የደረሱ ነገር ግን መጨረሻቸው በሲኦል ውስጥ ሊሆን የሚችል፡፡ ነገር ግን በህይወታቸው ጣልቃ ለመግባት በመፍቀዴ ህይወታቸው ፍፁም የተለወጠ ይሆናል፡፡ እነርሱ ሊያዩት አይችሉም ስለዚህም መራራ ይሆናሉ፡፡»

ግን . . . መራር መሆናቸው ወደ ሲኦል አይወስዳቸውም?

«አንድ ሰው ጣልቃ ካልገባ ወደ ሲያል ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እኔ ይህንን አመለካከታቸውን እንዲቀይሩ ለማድረግ በመንገዳቸው ላይ ሰዎችን በማምጣት በሚታይ መልኩ ሰማይንና ምድርን አንቀሳቅሳለሁ፡፡ ነገር ግን ይህንን የማደርገው በዘመናቸው መጨረሻ ላይ አንድ እድል ሲቀራቸው ነው፡፡ ይህ ግን በቀድሞ ህይወታቸው ሳልሞክር ቀርቼ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ልባቸውን በጣም ስላደነደኑት ስህተታቸውን ለመረዳት የሚችሉት ከሞት ጋር ሲፋጠጡ ብቻ ነው፡፡

«የእኔ ውዶች እጅግ ብዙ ጊዜ በጣም የባሱ ነገሮች በመንገዶቻችሁ ላይ ነበሩ፡፡ እናም በእናንተ ፋንታ ሰይጣን ፊት ቆሜ ከለከልኩት፡፡ እናንተ በዛ ጊዜ ከእኔ ጋር እየተራመዳችሁ አልነበረም፡፡ ደግሞም አታውቁኝም ነበር፡፡ እንዳውም እኔን ለማወቅ እንኳን ምንም ፍላጎት የላችሁም ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ቢሆንም ግን እኔ ጠበኳችሁ፡፡ አያችሁ በእኔ ህግጋት ስር ስትሆኑ፣ ስትወዱኝና ስታገለግሉኝ በታላቅ ጥበቃ ውስጥ ትኖራላችሁ፡፡ ነገር ግን የጥበቃዬን አጥር ጥሳችሁ ወደ በረሃው ስትሄዱ እጄ እንዳይሰራ ትከለክሉኛላችሁ፡፡

"እንዲህም ቢሆን ግን ራሴን ለቀቅ በማድረግና ከተለመደው አሰራሬ ወጣ በማለት እጠብቃችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም ስለምወዳችሁና ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ ስለማታውቁ ነው፡፡ ከዓመት፣ ዓመት ከአሁን አሁን ከራስ ወዳድነትና ከአይነስውርነት መንገድ ትወጣላችው ብዬ ለመቅረብ እሞክራለሁ፡፡ እናንተ ግን ከዓመት ዓመት ችላ እያላችሁኝ በነፃነትና በደስታ የራሳችውን መንገድ መዝለል ጀመራችሁ፡፡

«ከዛ እድሜያችው መጨረሻ ላይ ስትደርሱና ስለነገሮች ማሰብ ስትጀምሩ፣ ወደኋላ ተመልሳችው ስለጥፋታችው በማሰብ፣ በምትሞቱ ጊዜ መጨረሻችሁ የት እንደሚሆን ማውጣት ማውረድ ትጀምራላችሁ፡፡ በዚህ ጊዜ እንኳን እኔ ያስጠነቀኳችሁን በመተው የራሳችሁን ምክንያት በመስጠት ሌላ ኃይማኖት በመምረጥ የኔ መንገድ ይህ ነው ትላላችሁ፡፡ ነገር ግን በሌሊቱ ዝምታ ወቅት ጣዕረ ሞት የሚመስል መጥቶ በእውነት ሲሳለቅባችሁ . . . ከዚያም መደነቅ ትጀምራላችሁ፡፡

«ስህተት የሆነውን መንገዳችውን ለመቀየር ብዙ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ ምክንያቱም የመረጣችሁት መንገድ የሚወስዳችሁ ለዘላለም እኔ ደግሜ ወደማላያችው ቦታ እንደሆነ ስለማውቅ ነው፡፡ ይህም ቦታ ስለ እናንተ በጣም የማዝንበት ቦታ፣ ድምፃችሁን ከሲኦል ውስጥ ሆናችሁ ስትጮሁ የምሰማበት ቦታ ነው፡፡ ነገር ግን እናንተ ልባችሁን ወደ እኔ እንድትመልሱ ካደረኩት ነገር ይልቅ ለዘላለም ከመረጣችሁት ምርጫ የተነሳ ምንም ማድረግ የማልችልበት ቦታ ነው፡፡

«የምታውቁኝ እናንተ ግን ይህ ጊዜ ልባችውን የምትፈትኑበትና የተሰወረ መራራነትን በውስጣችሁ የምትፈልጉበት፣ እንዳውም የተጠራቀመ መራራ በልባችሁ ውስጥ እንዳለ የምትፈትሹበት ጊዜ ነው፡፡ እኔን ይቅር የማትሉት ነገር ይኖራችሁ ይሆን? ይቅር ብያለሁ ብላችሁ ነገር ግን ሚዛናዊ ባልሆነ መንገድ ተመልከታችሁ ይቅር ያላላችሁኝ ቅሬታ በልባችሁ ውስጥ ይኖር ይሆን?»

ጌታ ሆይ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ አሁንም እቸገራለሁ፡፡ ከምቸገርበት ጉዳይ አንዱ .....የወላጅ ቤተሰቦቼ ጉዳይ ነው፡፡

«አውቃለሁ የእኔ ውድ፡፡ ቤተሰቦችሽ እንደዛ አይነት የማይረባ ውሳኔ በመወሰናቸው በጣም አዝናለሁ፡፡ እኔ በበኩሌ አልተጫንኳቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም በመጨረሻ የሚወስኑትን ውሳኔ አውቅ ስለነበር ነው፡፡ እናም ወደእዚህ አይነት ቤተሰብ ውስጥ ስለከተትኩሽ አዝናለሁ፡፡ ግን እደዚህ ልበልሽ እዚህ በምትመጪ ጊዜ ስለ እነርሱ ታመሰግኚኛለሽ፡፡»

ጌታ ሆይ አሁን እንኳን አይምሮዬ በትክክል በሚያስብ ጊዜ አመሰግንሃለሁ፡፡ አዎ አሁን እንኳን ስመለከተው በቤተሰብ በኩል የሰጠኸኝ ሁሉም ነገር መጥፎ አይደለም፡፡ ሆነም ቀረም በፍሊጋዬ አሸንፈህ አዳንከኝ፡፡ ስለዚህ ስለምን አማርራለሁ? እንደ አኗኗሬ ቢሆንማ ሲኦል ነበር የምገኘው፡፡

«ያልሽው ሁሉ ልክ ነው የእኔ ውድ፡፡ ነገር ግን መመልከት ያለብሽ አንቺ ከተገኘሽበት እጅግ ከከፋ አዘቅጥ ውስጥ በምን ያህል ፀጋ እንደወጣሽ ነው፡፡ ተመልከቺ እንዴት እጆቼን እንደያዝሽና በክብር ከእኔ ጋር እንደተነሳሽ፡፡ ይህ በእውነትም ልትደሰችበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡»

በጣም አስገራሚ ነው፡፡ ሙሉ የመሆን ስሜት ነው የሚሰማኝ፡፡ እናም ስለመረጥከልኝ ነገሮች ሁሉ ደስተኛ ነኝ፡፡

«ይህ ገና ጅማሬ ነው፡፡ ያለ ምክንያት አይደለም ከክብር ወደ ክብር ትሻገራላችሁ ያልኩት፡፡»

«የእኔ ልጆች በእኔ በኩል ሆናችው ብታዩት እንዴት የጨለማን መንግስት ድል እንደነሳችሁ ይታያችሁ ነበር፡፡ የሚደንቁ መሰናክሎችን፣ ሰይጣናዊ ሥራዎችን፣ ጠላቶችንና ኃያላትን ድል እንደነሳችሁ ብቻ ማየት ብትችሉ በጣም ትደነቁ ፣ትደሰቱና ትረኩ ነበር፡፡ ነገር ግን  እኔ የማየውን ማየት የምትችሉትና ምን ያህል ድል እንደነሳችሁ መገንዘብ የምትችሉት ከእኔ ጋር ከሆናችሁ ብቻ ነው ፡፡

«አሁንም እያንዳንዱን የልባችሁን ክፍል በመመርመር ራሳችሁን መፈተሽ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እኔ በፈቀድኩት ጉዳይ ላይ እስካሁን በውስጣችሁ መራርነት እንዳለ ፈትሹ፡፡ በህይወታችሁ እንዲሆን የፈቀድኩትን ነገር እጅግ ለመልካም እንደሆነ ታምናላችሁ? በዚህ ታምኑኛላችሁ? አሁን ማንነቴንና ተፈጥሮዬን አውቃችኋል፡፡ ለእናንተ ያለኝ ፍቅር በጭካኔ እንዳደርግ እንደማያስደርገኝ አውቃችኋል፡፡ አሁን ይህንን ሁሉ አውቃችኋል፡፡ ይህንን አሁን አምናችሁ በህይወታችሁ ለተፈፀመው ጥሩና መጥፎ ነገር ሁሉ ታመሰግኑኛላችሁ? ለእናንተ ያለኝን ፍቅር አሁን ስላወቃችሁና ስላመናችሁኝ በህይወታችሁ ስለተፈፀመው ስለ ጥሩውም ይሁን ስለ መጥፎው አሁን ታመሰግኑኛላችሁ?

«በዚህ ምሽት እያወራን እያለን ይህንን ፀጋ እያካፈልኳችሁ ነው፡፡ ደግሞም እያካፈልኳችሁ ያለሁት የዚህን ምድር ጥበብ ሳይሆን የበለጠውን ጥበብ ነው፡፡ ይህም የኔ ጥበብና ፀጋ፣ ስለሆነውና ስላልሆነው፤ ስለ ወሰድኩባችሁና ስለ ሰጠኋችሁ፤

ስለከለከልኳችሁና ስለፈቀድኩላችሁ፤ ጥሩና መጥፎ ስለሆነው ሁሉ ለማመስገን የሚያስችል ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉ በዓላማ መደረጉንና እጅግ ለመልካም ነገር መከናወኑን ታያላችሁ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ እናንተ ራሳችሁ በወሰዳችሁት ውሳኔ ምክንያት ወደ ሲዖል ልትገቡ ከነበረው ዕዳ ጋር በመስተካከል እንዳትገቡ ረድቷችኋል፡፡

«ይህንን ጉዳይ ከዚህ ቀደም ከክሌርጋ አውርቻለሁ፡፡ እጅግ ብዙ ነፍሶች በጣም ቆሻሻ በሆነ ቦታ ተወልደው ያለ እድሜያቸው እየሞቱ ነው፡፡ እነዚህ ነፍሶች ወደ ምድር ለመምጣትና በዚህ ሁኔታ ለመሰቃየት ውሳኔ ወስነው የመጡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዋጋ ተከፍሎላቸው ከዳኑት የሰው ልጆች መካከል ለመሆን ስለዳጉ ነው፡፡ እናንተ በዚህ ሰዓት ዋጋ ተከፍሎላቸው የዳኑ በመንግስተ ሰማያት አንፃር ምን ማለት እንደሆነ አይገባችሁም. . .፡፡»

ጌታ አንተ እኮ ጥሩ እንዲገባን የምታደርግ ተናጋሪ ነህ፡፡ ስለዚህም እነዚህ ነፍሳት እንዴት  በኤች.አይ.ቪ ወይም ተደፍረውና ተገድለው ለመሞት ከተመደበባቸው ሰዎች መካከል በመሆን ወስነው እንደሚወለዱ እንዲገባን ልትረዳን ትችላለህ፡፡ ጌታ እባክህ እንደሚገባን አድርገህ አስረዳን፡፡

«ክሌር የጠየቅሽው ትልቅ መግባባትን ነው፡፡ እሺ እሞክራለሁ፡፡ በምክንያታዊ አይምሮሽ ለራስሽ ልታስረጂ አትሞክሪ፡፡ የኔ ውድ ቀደም ብዬ እንደነገርኩሽ ያለሽ እውቀትና ክብር ከፊትሽ ይቆማል፡፡»

እሺ፣ ይቅርታ፡፡

«እያሰብሽ ያለሽውን አየዋለሁ ደግሞም እሰማዋለሁ፡፡ ትክክል ሆኖ ካላገኘሁት ይህንን ክፍል በቃ እሰርዘዋለሁ፡፡ በጣም ያሳፍራል! እና በእኔ ላይ ያለሽ አመኔታ የታል??? ወዴት ጣልሽው?»

ጌታ ሆይ አምኛለሁ አለማመኔን እርዳው፡፡

«የእኔ ውድ ክሌር ምንም ነገር ከእኔ አቅም በላይ አይደለም፡፡ ነገር ግን ብዙ ነገሮች ከእናንተ አቅም በላይ ናቸው፡፡ ምክንያቱም እኔ እንደማይ እናንተ ማየት አትችሉም፡፡ እናንተ አሁንም የምታዩት ባልጠራ መስታወት ነው፡፡»

ጌታ ሆይ ከዚህ በኋላ አትነግረንም ማለት ነው?

«እንደዚህ በማሰብሽ ራሱ መመታት አለብሽ»

ሁሌ የምገኝበትን ሥፍራ ስለምታውቅ እባክህ እንዳታደርገው!!

እባክህ ምን ያህል መጥፎ እደሆንኩ አትንገራቸው!

«በቸኮሌት ባር ውስጥ?»

«እሺ እስኪ አንድ ትንሽ ትል አስቢ፡፡ በመሬት ላይ በቀስታ እየሄደች እያለች አንድ ወፍ ከላይ መጥታ ትንሿን ትል ያዘቻት»

(ክሌር) እስካሁን ሴቷ ትልና  ቁራ ነበሩ በአይምሮዬ ውስጥ የነበሩት!

«እሺ አሁን ሴቷ ትል ያላትን ዕይታ አስቡ ፡፡ አሁን ደግሞ ቁራው ያለውን ዕይታ አስቡ. . . »

" ጭራሽ የሚነፃፀር አይደለም!

«ትክክል ነው፡፡ ቁራዋ መጥታ ትንሿን ትል ይዛት እስክትበር ድረስ የሚነፃፀር አይደለም፡፡ ነገር ግን ልክ ቁራዋ ይዛት ስትሄድ ትንሿም ትል ልክ እንደ ቁራው ማየት ትጀምራለች!»

(ክሌር) እሺ

(ኢየሱስ) «በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የመረዳታቸው የግዛት ልዩነት ነው. . .   »

(ክሌር) እያሰብኩ ነው፡፡

(ኢየሱስ) «እንዴ ጠየቅሺኝ አሁን ደግሞ መልሱን መስማት አትፈልጊም?»

(ክሌር)ጌታ ሆይ እንዴት እንደሆንኩ ታውቃለህ፡፡

(ኢየሱስ) «በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ቶማስ. . . አውቃለሁ»

(ክሌር) እሺ እንደዚህ ነው ደካማ ሙሽራህን የምትንከባከበው?

(ኢየሱስ) «እንደዛ ነው በተደጋጋሚ የሚያስተምርሽን አፍቃሪ የሆነውን ኢየሱስን የምትንከባከቢው?»

(ክሌር) አይ አይደለም፣ ይቅርታ፡፡

(ኢየሱስ) «እሺ ታዲያ ክሌር መልሱን ንገሪያቸዋ፡፡»

(ክሴር) ሴቷ ትል በመሬቱ ላይ እየሄደች እያለ በእያንዳንዱ እርምጃዋ ነገር ግን በተገደበ ሁኔታ ፍቅርህን ትለማመደዋለች፡፡ ነገር ግን በቁራው መንቁርት ስትያዝ ማየት የሚቻለውን ሁሉ በቅፅበት ማየት ትጀምራለች፡፡

«በትክክል! ነፍስ በመንግስተ ሰማያት ውስጥ ስትሆን የተበላሸውን ምድርንና ኃጢያት አትለማመደውም፡፡ ስለዚህም በዛ ያለውን ነገር ምንም ላታደንቀው ትችላለች፡፡ ነገር ግን ሙሉ በሙሉ በኃጢያተኛ ማንነት ውስጥ ሆነው ከዛ ውስጥ በመውጣት ወደ ላይ ሲወሰዱ በእኔ ምን ያህል እንደተወደዱ ወሰን በሌለው ቅፅበታዊ መረዳት ውስጥ ይሆናሉ፡፡ እናም በማንነቱና ለእነርሱ ባለኝ ፍቅር ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መንገድ ሐሴት ያደርጋሉ፡፡»

«እሺ ይህ የእኔ ሙከራ ነው ምን ታስቢያለሽ?

አይምሮ የሚያፈነዳ ነው??

«ምን ብያችሁ ነበር? እምም? እዚህ እስከትመጡ ድረስ አይገባችሁም አላልኩም?»

አይ ጌታ ሆይ ያስረዳኸው እጅግ በሚደንቅ ሁኔታ ነው፡፡ እኔን ስታናግረኝ ብዙ ጊዜ የማደርገው የአንተን ሐሳብ እወስድና በቃላት አስቀምጠዋለሁ፡፡ በዚህ ምሳሌ ግን እያንዳንዱ መግለጫ ሚስጥራዊ ሆኖብኛል፡፡ እስከመጨረሻው ድረስ ምንም ሊገባኝ አልቻለም፡፡ በኋላዬ ወድቄ ሊያነሱኝ በሚጠብቁኝ እጆችህ ላይ ለመውደቅ እየተዘጋጀሁ ነበር፡፡ ግን ይህንንም አላየሁም ፡፡ ስለዚህ እንዲሁ ማመን አለብኝ፡፡

«አንዳንድ ጊዜ በዚህ መልኩ ማውራት አለብኝ፡፡ ምክንያቱም የአመለካከት መስመሩና እኔ የማስረዳበት መንገድ ከእናንተ እውነታ ጋር ፍፁም የወጣ ነው፡፡ ለምሳሌ በመከራው ዘመን ስለሚከናወኑ ክስተቶች፤ እንዲሁም እንግዳ ስለሆኑ ፍጥረታት የሰጠሁሽ ማስጠንቀቂያዎች ወዘተ. . . ዓይነት ማለት ነው፡፡»

አዎ ያ ለእኔ በጣም ከባድ ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲገባን አደረግህ፡፡ ጌታ በጣም የምትደንቅ ነህ፡፡

«አውቃለሁ፡፡»

በትልቁ ሳቅ፡፡

«ስለዚህ በዚህ ምሽት የምድር ያልሆነውንና የላይኛውን ጥበብ በማካፈል ቀድሜ እባርካችኋለሁ፡፡ የኔ ጥበብና ፀጋ ስለፈቀድኩትና ስላልፈቀድኩት፣ ስለሰጠሁትና ስለከለከልኩት፤ ስለወሰድኩትና ስላልተካሁት ለማመስገን የሚያስችል ነው፡፡ ጥሩና መጥፎ ሁሉ ለዓላማ ሲውል ታያላችሁ፡፡

(ክሌር) ስለዚህ በጣም በትልቅ ችግር ውስጥ ያለፍን በተጨባጭ የአንተን ጥልቅ የሆነውን ፍቅርህን እንለማመዳለን፡፡

«አዎ የኔ ውድ አሁን እየተረዳሽው ነው! ብዙ ይቅር የተባለለት ብዙ ይወዳል፡፡ እናም የኔንም የፍቅር ብዛት ያያል፡፡ የጨለማን ጥልቀት የሚያውቅ ብርሃንን ያደንቃል፡፡ አሁን ደግሞ እንደገና ሁላችሁንም እባርካችኋለሁ፡፡ ይህ በጣም ጥልቅና ለመረዳት ትግል የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህም ጊዜ ወስዳችሁ ለመረዳት ሞክሩ፡፡ ነገር ግን በዚህ ምሽት ስትሰሙ እንዲገባችሁ የሚያስችል ፀጋን አካፍያችኋለሁ፡፡»

«በዚህ ምድር ባለው ህይወታችሁ ባጋጠማችሁ የበለጠ ኃዘንና ምሬት መጠን በመንግስተ ሰማያት የበለጠ ምስጋና አቅራቢዎች እንዲሁም በዘላለም ህይወት የበለጠ ሐሴትና ደስታ ይገጥማችኋል፡፡»

## እስተዳደሬን አልተቀበላችሁምና ሙሽራዬን መጥቼ ልወስድ ነው / ጁላይ 15 ቀን 2015 ዓ.ም
## You Have Rejected My Rule, I am coming to take My bride / July 15, 2015

(ክሌር)፡- ዛሬ ምሽት እያመለክሁ እያለ ከኢየሱስ ጋር የመቃብር ሥፍራ ላይ ነበርኩ፡፡ በእውነትም በትልቅ ኃዘን ላይ ነበርኩ፡፡ ይህም የሆነው በከፊል በእናንተ ፀሎት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ከኢየሱስ ጋር በመቃብር ስፍራ ነበርኩ፡፡ የተቀመጥኩት በቀኝ እጁ በኩል ሲሆን እርሱም እጁን በሰውነቱ ላይ በማነባበር በእርጋታ ተቀምጦ ነበር፡፡ እኔም አስተዳደሩ ተቀባይነት በማጣቱ ዝም ብዬ ሳለቅስ ነበር፡፡ ሰው ከመልካሙ አዳኛችን ይልቅ ኃጢያትንና የኃጢያትን ገዢነት መረጠ፡፡ አ! የሰው ልጅ እንዴት እንደዚህ ያላዋቂና አይነ ስውር ትሆናላችሁ?

ፊቱን በተመለከትኩ ጊዜ ሬይ ዶውኒግ የሚባለው ሰው የኢየሱስ ፎቶ ይህንን ይመስላል ብሎ ያቀረበውን ፎቶ ዓይነት መስሎ ታየኝ፡፡ ፊቱ ሰላምና ፀጥታ የሰፈነበት ነበር፡፡ነገር ግን እኔ እንዲህ ብዬ ማሰብ ጀመርኩ አ! እግዚአብሔር አንተን ያለመቀበላቸው እንዴት የሚያሳዝን ነው፡፡ ደግነትን፣ ፍቅርንና እውነትን፣ ፍትህን ሰጪና ለተጨቆኑት ጠባቂ የሆንከውን አንተን አልተቀበሉህም፡፡ አ! እንዴት አልተቀበሉህም? እንዴት እኛስ?

እኔም እንዲህ በማለት አሰብኩ 'ስንት ጊዜ ነው ከአንተ መንገድ ይልቅ የራሴን መንገድ ለመከተል የመረጥኩት? ማን እየነዳኝ እንደሆነ እንዳውቅ፣ እንድነቃና እንድመለስ ስንት ጊዜ ጠበከኝ ? እንድነቃ በማሰብ ትኩረት ባልሰጠኋቸው ትንንሽ ጉንተላዎችህ ስንት ጊዜ ነካኸኝ? በትንንሽ ነገሮች እንኳን የራሴን መንገድ ተከትዬ ስንት ጊዜ ሳልቀበልህ ቀረሁ? ሞኝ ሴት . .

'እናም አምላካችንን ላለመቀበል እስካሁን ድረስ ለሰው ልጆች የሚያንገዳግድ ጉዳይ ሆኗል፡፡ የሚያንገዳግድ፡፡'

ለሠላሳ ደቂቃ ያህል እነዚህን ነገሮች ሳወጣ ሳወርድ እያለሁ የጌታ እጅና መላ ሰውነት ከለር ሲመለስ ተመለከትኩ፡፡ በዚህ ጊዜ የጌታ ሁለንተና እንደወትሮው እንደተመለሰ ተመለከትኩ፡፡ እርሱም ተነስቶ ቁጭ አለና ጠንከር ባለ ውሳኔ እንዲህ አለ. . . "ሙሽራዬን መጥቼ እወስዳታለሁ ምክንያቱም በእርሷ ላይ ገዢ እንድሆን ስለምትፈልግ ነው፡፡"

(ክሌር) ተነስቶም ቆመና ሳመኝ፡፡

ኢየሱስ እንዲህ አለ . . . "አየሽ  ትውልዱ እንደማይፈልገኝ እስከሚያረጋግጥ ድረስ ብዙ ታግያለሁ፡፡ ስለዚህም የዚህን ውጤት መጨረሻውን እያስተካከልኩት ነው፡፡"

"በእውነት የምትፈልገኝን ሙሽራዬን ብቻ ለመውሰድ እመጣለሁ፡፡ ለህዝቤ ያኔ ቃል እንደገባሁት፣ በጌታ ስም የሚመጣ እርሱ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ አታዩኝም፡፡ ይህ ማለፉ የማይቀር ነው፡፡ ነገር ግን የሚታለፈው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ አስቸጋሪ መንገድ እንዲያልፉ እኔም አልፈልግልም ነበር፡፡"

"ህዝቤ እኔ በልብህ የተናገርኩህን መስማት እንቢ በማለት የራስህን ምርጫ መርጠሃል፡፡ ጊዜው ከመዘግየቱ በፊት ወደ እኔ ተመለስ ብዬ ድምፄን አሰምቼሃለሁ፣ ተናግሬያለሁ፣ ጮኬያለሁ። ነገር ግን የሚሰማኝ አልነበረም፡፡ ስለዚህም ለራስህ እቅድ ትቼሃለሁ፡፡

"ስለዚህ ማን ክፉ ማን መልካም እንደሆነ ታያለህ፡፡ ካሁን ወዲያ መልካሙን ክፉ ክፉውን መልካም አትልም፡፡ በአንፃሩ ግን ፊቴን ለማየት ትጓጓለህ፣ በሙሉ ልብህም እኔ እንድገዛህ ትመኛለህ፡፡"

"ዋናው ቁም ነገር ይኸው ነው፡፡ የኔ ህግ አንተን ለማስተዳደር በቂ አልነበረም፡፡ እና አሁን የራስህ ምርጫ ያመጣውን መከራ ትጋፈጣለህ፡፡"

"እኔ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም፡፡ እጆቼን አስረሃል ምን ማድረግ እችላለሁ? ስለዚህም እስከ መጨረሻው ውድቀት ድረስ ለራስህ እቅድና አስተዳደር አሳልፌ ሰጠሁህ፡፡ አዎን በትክክል ተብሏል እኔ በአባቴ ሥም መጣሁ አልተቀበላችሁኝም፣ በራሱ ሥም የሚመጣውን ግን ትቀበሉታላችሁ፡፡" ዮሐንስ 5፡43

"ትንሽ ቆየት ብሎ ግን የኔ ሙሽራ በዳመና ስመጣ ታይኛለሽ፡፡ በዚህም ጊዜ የምድር ወገኖች ሁሉ በእውነት ያዝናሉ፣ ጩኸታቸውም እስከ ሰማይ ድረስ ይሰማል፡፡ ከዚያም ህዝቤን አጠራለሁ፣ በመካከላቸውም ላስተዳድርና ልገዛ ተመልሼ እመጣለሁ፡፡ ነገር ግን እስከዚያው ድረስ ብዙ ትሰቃያላችሁ፡፡ ቢሆንም ግን እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ ምክንያቱም ለእናንተ ያለኝ ፍቅሬ አያረጅም፡፡ ኦ! ለዚህ ህዝብ ከልቤ እንዴት እጨነቃለሁ? ልንከባከብህ፣ በቁስልህ ላይ ዘይት ላፈስና በእግርህ ላይ ያማረ የሰንደል ጫማ ላጠልቅልህ እንዴት እመኝ ነበር?"

"ኦ! እንዴት እመኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ይፈፀማል ተብሎ የተነገረው ይህ የሚያመው ትንቢት በታሪክ ሊፈፀምና እናንተም በጌታ ሥም የሚመጣ የተባረከ ነው ብላችሁ እስከታውጁ ድረስ በምድር የተሞላው ቆሻሻ ሁሉ መጠረግ አለበት፡፡"

በእቅፌ ውስጥ አስገብቼ አድሳችኋለሁ፡፡ መንገዴን ተምራችሁ እንደገና ህዝቤ ትሆናላችሁ፡፡ ቃሌንና ፈቃዴን ለሚቀጥለው ትውልድ ታስተላልፋላችሁ፡፡ እስከዛው ድረስ ግን ህዝቤ በዚህ ምድር ላይ የሚያጠራ፣ የፍርድ ቀን፣ የጌታ ቀን መምጣቱ ስለሆነ ልብሳችሁን አውልቁና ማቅ ልበሱ፣ አመድ በራሳችሁ ላይ ነስንሱ፡፡"

ጌታ ይህንን እየተናገረ እያለ እንዲህ በማለት አሰብኩ . . .  ዋው! እየተናገርህ ያለኸው ስለ አሜሪካ ነው? ማለቴ ስለ አሜሪካና ስለ እስራኤል፡፡ ሁለቱ እጅግ የተጣመሩ በመሆናቸው፡፡

"እስራኤላውያን በዚህ አገርም በታማኝነት ይኖራሉ፡፡ ማየት ያለብሽ በቁጥር ብዛት በበላይነት ያሉትን ነው፡፡ ዶክተሮች፣ ዳኞች፣ ፖለቲከኞችና በመዝናኛ ኢንዱስትሪው ላይ የተሰማሩትን ነው፡፡ እርግጥ ነው ህዝቤ በሁሉም ፕሮፌሽንና

በእያንዳንዱ ተሰጥዎም ልቀዋል፡፡ እንዲሁም ነገሮችን በማበላሸትም ልቀው ተገኝተዋል፡፡ ማንም ህዝብ ቢሆን ከጥፋተኝነት ውጪ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጥፈተኝነቱ እንደ መሪዎች የሚሆን የለም፡፡ ብዙ አይሁዶች በስልጣን ላይ መሆናቸው በብዙሃኑ መገናኛ እንዳይታወቅና በትንሽ ሙቶኛ ብቻ እንዲታወቁ የተደረገው በጥንቃቄ ታስቦበት ነው፡፡ በእውነቱ ከሆነ ግን እነርሱ የሌሉበት የስልጣን እርከን የለም፡፡ በሁሉ ቦታ ላይ አሉ፡፡

"የኔ ፍቅር እኔ አሁን ሙሽራዬን ለመውሰድ እመጣለሁ፡፡ ይህችም ሙሽራ ልቧን ሳዳምጠው እኔን ለማግኘት በመጓጓት ልቧ የሚንሾካሾከው፣ ስለስቃዬ በእግሮቼ ስር ሆና የምታነባዋ፣ ውጤታማና ታብታም ብትሆንም እኔን ለመቀበል ታማኝ የሆነችዋ ናት፡፡ እኔ ደግሞ አሁን እጄን ወደ እርሷ በመዘርጋት የሁለታችን ዘላለማዊ ፍቅር ወደሚታወጅበት ወደ መሰዊያው እንቀርባለን፡፡

"የኔ ውዶች አይናችሁን ወደ ላይ አንስታችሁ ተመልከቱ፡፡ በቅርብ ተቃቅፈን ወደ መንግስተ ሰማይ ከተማ ከፍ እንላለን፡፡ በዛም ሽልማት ይጠብቃችኋል፡፡ በዚህ ለምትቀሩ ግን በርቱ እላለሁ፡፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ የጀግንነት ተግባራችሁን በሰዎች ፊት ሁሉ ፈፅሙ፡፡ እንዲሁም የምትሰበስቡት ምርት የበዛ ይሁን ፡፡ አልተዋችሁም፣ አልጥላችሁም፡፡ እንዳውም ለጦርነቱ አስታጥቃችኋለሁ፡፡ እናም ለኃያሉ ትዘርፋላችሁ፡፡

"ስመለስ የዘላለሙን ብድራታችሁን ትቀበላላችሁ፡፡"

## ቀላል የሥጋ ወደሙ አወሳሰድ ስርዓት/ ጁላይ 31 ቀን 2015 ዓ.ም

## A Simple Communion Service / July 31, 2015

ውድ ቤተሰቦች የጌታ ባርኮት በእኛ ላይ ነው፡፡ ዛሬ ላካፍላችሁ የምፈልገው በጣም ቀላል በሆነ መንገድ እንዴት ሥጋ ወደሙን መውሰድ እንደምትችሉ የሚያሳይ ንድፈ ሐሳብ ነው፡፡ እንዲሁም ይህንን አገልግሎት በተመለከተ ቪዲዮ ለመስራት አስቤያለሁ፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ እንዴት መወሰድ እንዳለብን በደረጃ አቀርባለሁ፡፡ በዚህ ውስጥ የተካተቱ ፀሎቶች ሁሉ የተወሰዱት ከመፅሐፍ ቅዱስ ከመዝሙረ ዳዊትና ከወንጌላት ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡ ለዚህም ሙሉ አገልግሎቱን የሚተነትን ፅሑፍ በፒዲኤፍ መልክ ስለሚኖር በቃላችሁ ማስታወስ አይጠበቅባችሁም፡፡

ሥጋ ወደሙን አገልግሎት ስታዘጋጁ በእውነት ከሆነ የዝግጅቱ ዓላማ ዳቦውንና ወይኑን ባርካችሁ በማስቀመጥ ስትፈልጉ እንድትወስዱት ነው፡፡ ይህንንም የባረካችሁትን ሥጋና ደም ለሳምንት ወይም ለጥቂት ቀናት ልታስቀምጡት ትችላላችሁ፡፡ ወይም በየቀኑ ስትወስዱ በዚያኑ ወቅት ልትባርኩት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ ያለጥርጥር ተመራጭ የሆነ አወሳሰድ ነው፡፡

ልናገር የምፈልገው አንድ ነገር ይህ አሁን እኔ የምናገረው የሥጋ ወደሙ አወሳሰድ መመሪያ የካቶሊክን፣ የኦርቶዶክስን ወይም በጳጳስ የሚተዳደርን የቤተ ክርስቲያን ስርዓትን ለመተካት አይደለም፡፡ ምናልባት እምነታችሁ በዚህ ውስጥ የሚካተት ከሆነ ማለቴ ነው፡፡ ይህ በቤት ውስጥ የሥጋ ወደሙ ለመውሰድ

የምንጠቀምበት አንዱና ቀላሉ የአወሳሰድ ዘዴ ነው፡፡ ወይም በትልቅ ስደት ውስጥ ሆነን ሌላ አማራጭ ከሌለን ልንጠቀምበት የምንችልበት ዘዴ ነው፡፡

ጌታ ይህንን ቃል ገብቷል፡፡ በልባችሁ አምናችሁ በአፋችሁ በእውነት ብትመሰክሩ ጌታ በልዩ ዓይነት መንገድ በሥጋ ወደሙ አገልግሎት ላይ በእርግጥ ይጎበኛችኋል፡፡ በምን አይነት መንገድ እንደሚገለጥ ይህ የጌታ የራሱ ምርጫ ነው፡፡ ነገር ግን የሥጋ ወደሙን መሰረታዊ ነገሮች ፍፁም በሆነ መልኩ በመቀደስ፣ በማከበርና ለእርሱም ክብር እየሰጠን ሊሆን ይገባል፡፡ ሥጋ ወደሙ ከወሰድን በኋላ የተረፈ ካለ እባካችሁ በቆሻሻ ውስጥ አትጣሉት፡፡ ደግሞም ለወፎች አትስጡት፡፡ በውሃ ካሟሟችሁት በኋላ በእግር የማይረገጥ ቦታ በክብር አስቀምጡት፡፡

ይህንን አገልግሎት ለመፈፀም ሰባት አጫጭር ክፍሎች አሉት፡፡ እናንተ በዚህ ላይ የፈለጋችሁትን ልትጨምሩም ሆነ ልትቀንሱ ትችላላችሁ፡፡ እኔ ያዘጋጀሁት በዚህ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡

1) አምልኮ፡- ይህ መዝሙር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ጌታን በማምለክ የምታሳልፉት ጊዜ ነው፡፡
2) ምስጋናና ፣ውዳሴ፡- ይህ ደግሞ ጌታን ስለማንነቱ የምናወድስበትና ስላደረገልን ነገር ሁሉ የምናመሰግንበት ጊዜ ነው፡፡
3) ንስሐ መግባት፡- ኃጢያታችንን በጌታ ፊት በማቅረብ የምንናዘዝበትና ንስሐ የምንገባበት ነው፡፡
4) ከመፅሐፍ ቅዱስ ቃሉን ማንበብ ፡- በዚህ ጊዜ የኔ ምርጫ ሬማ ቃል ከተቀደሱ መፅሐፎች ማንበብ ነው፡፡ ይህንንም የማደርገው ከመፅሐፍ ቅዱስ ወይም በርዕስ ከተዘጋጁ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመጠቀም ነው፡፡ እኔ የማደርገው መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ የቀኑን ቃል እንዲሰጠኝ እፀልና ለእርሱ አሳልፌ በመስጠት ዝም ብዬ አንድን የመፅሐፍ ቅዱስ ወይም ሌሎች የተቀደሱ መፅሐፍትን ገፅ እከፍታለሁ፡፡ ከዚያም ያንን የተቀበልኩትን ቃል ጮክ ብዬ አውጀዋለሁ፡፡ በልቤ ውስጥም አኖረዋለሁ፡፡ በቀን ውስጥም ብዙ ጊዜ ደጋግሜ እንደገና አውጀዋለሁ፡፡ ይህ እንግዲህ በቃሉ በኩል የማደርገው ነገር ነው፡፡
5) ዳቦውንና ወይኑን መባረክ፡-
6) ሥጋ ወደሙን መቀበል

ሥጋና ደሙን ከወሰድኩ በኋላ

7) በጌታ ውስጥ ማረፍ

እነዚህ እንግዲህ ለስጋ ወደሙ አገልግሎት እኔ ያወጣኋቸው ሰባት ደረጃዎች ናቸው፡፡ እንደተናገርኩት ይህ እኔ ያቀረብኩት የተግባር ዝርዝር ሊታከልበት የሚችልና እናንተ እንደፈለጋችሁ ልታደርጉት የምትችሉት ነው፡፡

<u>የሥርዓቱ አፈፃፀም</u>

<u>አምልኮ</u>

በመጀመሪያ ላደርግ የምፈልገው ነገር ማምለክ ነው፡፡ ስለዚህም እርሱን ለማምለክ አንድ ወይም ሁለት የአምልኮ መዝሙሮችን እከፍታለሁ፡፡ በዚህም በእርሱ መገኘት ውስጥ እርሱን ማምለክ፣ ማወደስና ማመስገን፡፡ከዚያም እጅግ ቀላል ፀሎት ማድረግ፡-

ፀሎት

ጌታ ሆይ እስካሁን ስላደረግህልኝና፣ ስለሰጠኸኝ ነገር ሁሉ፣ ስለ ጥበቃህ እንዲሁም ስለማትተወኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ በአንተ ላይና በወንድሞቼ ላይ ኃጢያት በመስራቴ ንስሐ እገባለሁ፡፡

በዚህ ጊዜ ትንሽ ቆም ብላችሁ በፀጥታ ሁኑና ልባችሁን መርምሩ፡፡ በዚህም ጌታን ቅር ያሰኛችሁት የሚመስላችሁ ነገር ካለ በፊቱ አቅርቡት፡፡ ኃጢያታችሁን ከመረመራችሁና በልባችሁ ያገኛችሁትን ለጌታ አቅርባችሁ ንስሐ ከገባችሁ በኋላ ይህንን ፀልዩ፡፡

ጌታ ሆይ በማይወድቀው ፍቅርህ ልክ ምህረት አድርግልኝ፡፡ ይቅር በለኝ፣ ከኃጢያቴም እጠበኝ፡፡ ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ፣ አድሰኝ፣ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ፡፡ በህይወት የሚያቆየኝንም የእሽታ መንፈስም ስጠኝ፡፡ (ከመዝሙር 51 የተወሰደ)

ቃሉን ማንበብ

አሁን ለማሰላሰል ቃሉ ያስፈልገናል፡፡ ለዚህም ቀላል ፀሎት ለመፀለይ እወዳለሁ፡፡ "ቃለህ ለእግሬ መብራት ነው፤ በመንገድህ ምራኝ፡፡"

የመፅሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃል (Bible promise book) ወይም ከመሳሰሉት መፅሐፍ አንዱን ገፅ ዝም ብዬ በመክፈት የመጣልኝን የሬማ ቃል በማድረግ እወስደዋለሁ፡፡ ይህም መፅሐፍ በርዕስ የተሰበሰበ ጥቅስ ያለው መፅሐፍ ነው፡፡ ወይም ደግሞ ከመፅሐፍ ቅዱስ የሬማ ቃል በመውሰድ ቃሉን ማሰላሰል ትችላላችሁ፡፡ ደጋግማችሁ ጮክ ብላችሁ በሉት፡፡ ለምሳሌ ይህንን ቃል ቀኑን ሙሉ ለማወጅ አስታውሱ፡፡ "እነሆ መንፈሴን በእናንተ ላይ አፈሳለሁ፣ ቃሌም በእናንተ ዘንድ እንዲታወቅ አደርጋለሁ፡፡" ይህንን ቃል ወስዳችሁ ዝም ብላችሁ አሰላስሉት፣ በልባችሁና በአይምሯችሁ ውስጥ አስቀምጡት፡፡ ከዚህም ባለፈ ደግሞ በካርድ ላይ ፅፋችሁ ጌታ ቃል የገባላችሁን ቀን ለማስታወስ በግልፅ የሚታይ ቦታ አስቀምጡት፡፡

የባርኮት ቃል

ቃሉን ካሰላሰላችሁ በኋላ የጌታን ቅድስና እንዲህ በማለት አውጁ፡- ጌታ አንተ ቅዱስ ነህ፣ ታላቅና ኃይል የተሞላህ ነህ፡፡ መንግስተ ሰማያት ክብርህን ያውጃሉ! እናም "ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።

በአጠገባችሁ ያስቀመጣችሁትን ዳቦና ወይን አሁን ትባርኩታላችሁ፡፡ ጌታ የእናንተን ድርሻ እንድትወጡ ይፈልጋል፡፡ ይህ እኔ የማቀርብላችሁ መመሪያ ምንም ለማለት ካልቻላችሁ ሊረዳችሁ የሚችል ቀላል አባባል ነው፡፡

ከመሞትህ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ከደቀመዛሙርትህ ጋር ዕራት ስትበሉ ዳቦውን ከጠረጴዛው ላይ ወደ አብ በማንሳት ምስጋናን አቀረብህ፣ (ምስጋናን ለጌታ ማቅረብ)፡፡ ዳቦውን ቆርሰህ ለደቀመዛሙርቶችህ በመስጠት "ሁላችሁም ከዚህ ወስዱና ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሰጠው ሰውነቴ ነው፡፡" አልክ (ዳቦውን ቆርሳችሁ አስቀምጡት)፡፡

ቀጥሎም ብርጭቆን በማንሳት እንዲህ በሉ "እንደገናም የወይኑን ብርጭቆ ወደ አብ በማንሳት ምስጋናን አቀረብህ (ምስጋና ለጌታ አቅርቡ)፡፡ ደቀመዛሙርትህንም እንዲህ አልካቸው፡፡ ሁላችሁም ከዚህ ወስዳችሁ ጠጡ፣ ይህ ለአዲሱና ለዘላለም ኪዳን፣ ስለ እናንተና ስለ ሁሉም የኃጢያት ይቅርታ የሚፈሰው ደሜ ነው፡፡ ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" አልክ፡፡ (ብርጭቆውን አስቀምጡት)፡፡

*<u>ሥጋ ወደሙን መውሰድ</u>*

*ሥጋ ወደሙን* ከመውሰዳችሁ በፊት ይህንን ፀሎት ፀልዩ፡፡ . . . *ጌታ በእኔ ጣራ ሥር ልትመጣ የማይገባኝ ሰው ነኝ፡፡ ነገር ግን አንድ ቃል ተናገር እኔም እፈወሳለሁ፡፡* ይህንን ከፀለያችሁ በኋላ *ሥጋና ደሙን* ውሰዱ፡፡

*ሥጋና ደሞን* ከተቀበላችሁ በኋላ እንዲህ ብላችሁ አጭር ፀሎት ፀልዩ፡፡ "*ጌታ መጥተህ በክብር እስክትወስደን ድረስ ሥጋና ደምህ ለአንተ ብቻ እንድኖር ብርታት ይስጠኝ፡፡*"

*ሥጋና ደሙን* ከወሰዳችሁ በኋላ ከጌታ ጋር የቆይታ ጊዜ ይኑራችሁ፡፡ *ሥጋና ደሙን* ከወሰዳችሁ በኋላ ጌታን መስማትና ማየት የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊ አይኖቻችሁና ጆሮቻችሁ ከተለመደው ጊዜ ይልቅ የተከፈቱ ቢሆን አይድነቃችሁ፡፡ ምክንያቱም ይህ *ሥጋና ደሙን* ስትወስዱ በተደጋጋሚ ሊያጋጥማችሁ የሚችል ክስተት ነው፡፡

ከዚያም *ሥጋና ደሙን* የተቀበላችሁባቸውን ዕቃዎች በክብር አፅዱ፡፡ በዕቃው ላይ ትንሽ ፍርፋሪ እንኳን ብታገኙ በውሃ አሟምታችሁ በእግር ሊረገጥ የማይችል የአትክልት *ሥፍራ* አፍሱት፡፡

ከባረካችሁት ላይ የቀረ ዳቦና ወይን ካለና ለሌላ ጊዜ ለመጠቀም ከፈለጋችሁ ጌታ የገባውን ቃል አስታውሱ፡፡ እርሱ *ሥጋና ደሙን* ስንካፈል በጣም በልዩ መንገድ እንደሚገናኘን ተናግሮናል፡፡ ስለዚህም የቀረውን ዳቦና ወይን በተቀደሰ አቀማመጥ አስቀምጡት፡፡ በተለየ ዕቃና በከበረ *ሥፍራ* አስቀምጡት፡፡ ይህንንም የተቀመጠውን *ሥጋና ደም* ስትወስዱ የባርኮቱን ፀሎት እንደገና ሳትፀልዩ የሰራችሁትን ኃጢያት በመናዘዝና *ጌታ በእኔ ጣራ ሥር ልትመጣ አይገባኝም . . .* ከሚለው ፀሎት በመጀመር ልትወስዱ ትችላላችሁ፡፡

በእውነቱ ከሆነ በቃ ይኸው ነው፡፡ በጣም ቀለል ያለ፣ ነገር ግን ደግሞ ከጌታ ጋር እጅግ ሊያቀራርብ የሚያስችል የ*ሥጋ ወደሙ* አወሳሰድ ስርዓት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ እጅግ ቀላል ንድፍ ነው፡፡ እናንተ በዚህ ላይ እንደፈለጋችሁ ልትጨምሩ ወይም ልትቀንሱ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ስለ *ሥጋ ወደሙ* አወሳሰድ ትንሽ የጠፋባችሁ ነገር ካለ በማለት ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በመውሰድ፣ እኛ በተለያዩ *ሥፍራዎች ሥጋ ወደሙ* ስንወስድ ካየነው፣ እንዲሁም በአንደኛው ክፍለ ዘመን ኢጋማሽ ላይ በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የተፃፈውን በማገናዘብ ነው ያዘጋጀሁት፡፡ ይህ ግን ከተለመደው ወጣ ያለና አጭር ስርዓት ነው፡፡

በዚህ ስርዓት ጊዜ ለሌሎች ሰዎች መፀለይ ወይም ምልጃ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡ ወይም ከሌላው ሁሉ ለይታችሁ ስርዓቱን ለብቻው መፈፀም ትችላላችሁ፡፡ ይህ የራሳችሁ ምርጫ ነው፡፡ ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡፡ ይህንን አጭር የ*ሥጋ ወደሙ* አወሳሰድ ተቀብላችሁ፣ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሳችሁን ጨምራችሁበት በደስታ እንድትጠቀሙበት ፀሎቴ ነው፡፡ ጌታም እንደጠየቃችሁ የራሳችሁ አድርጉት፡፡

በሁሉም ነገር በራሳችን ህሊና መመራት አለብን ብዬ አምናለሁ፡፡ እኛ መሆን ያለብን በጌታ በእግዚአብሔር ተፅዕኖ ሥር እንጂ በማንም ሰው ተፅዕኖ ውስጥ መውደቅ የለብንም፡፡

ጌታ ሁልጊዜ ይባርካችሁ ደግሞም ይምራችሁ ፡፡

## የመጨረሻው መጨረሻ ከፋች ክስተት/ ዲሴምበር 6 ቀን 2015 ዓ.ም

## Turning key event / December 6, 2015

ኢየሱስ እንዲህ ይላል . . . በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሞስሊሞች መስኪድ ሲፈርስ በጉልበታችሁ ተበርከኩ፡፡ ያ የመጨረሻው መጀመሪያ ክስተት ነው፡፡"

"የኔ ውድ ወደ ሩጫው መጨረሻ እየደረስሽ ነው፡፡ ቀጥ ብለሽ ፊት ለፊትሽን ብቻ በትኩረት ተመልከቺ፡፡ ጊዜው እያለቀና መሆን ያለባቸው ለመሆን እየፈጠኑ ነው፡፡ ስለዚህም ጠላት ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት እየቀረበ ነው፡፡ ታስታውሻለሽ ባለፈው ስለ ነገርኩሽ ከፋች ክስተት? በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሞስሊሞች መስኪድ መውደም?"

"አዎን ጌታ አስታውሳለሁ፡፡"

"ያንን ባየሽ ጊዜ፣ በጉልበትሽ ተንበርከኪ፡፡ ያን ጊዜ የፈተናው ጅማሬና እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች አይተውት የማያውቁትና በህልማቸው እንኳን ይሆናል ብለው ያልገመቱት ይሆናል፡፡ መስኪዱ እንዲፈርስ እቅዱን ያወጡት እንኳን ያስከተለውን ውጤት ሲመለከቱ በድንጋጤ ይዋጣሉ፡፡ ክሌር አትፍሪ በቅድሚያ ነገሬሻለሁና አትፍሪ፡፡ ተበርከኪና መዳንሽ እንደቀረበ አውቀሽ አመስግኚ፡፡

"ክስተቱ ከተፈፀመ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ችግሩ ሳይጎላ ቢቆይም ወዲያው እጅግ እየከፋ ይመጣል፡፡ አገሮች ሁሉ ሲፈራርሱ በዓይኖቻችሁ ፊት ትመለከታላችሁ፡፡ እናም አይኖች ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ያርፋሉ፡፡ ለመዘጋጀት ምንም ጊዜ የለም፡፡ ምንም ጊዜ፡፡ ስለዚህም በፀሎት ብቻ ቆዩ፡፡ ወደ ውጪ አትውጡ፤ ቤታችሁን አትልቀቁ፡፡ በጉልበታችሁ ወድቃችሁ ፀልዩ፡፡ መለኮታዊ የምህረት ፀሎት/The divine Mercy prayer/ መፀለይ ያለበት በመንፈሴ በተደገፈ ፀሎት ነው፡፡

"የመጨረሻው የምህረት ጠብታ ከተሰጠው የተስፋ ዋንጫ ውስጥ ይለቀቃል፡፡ አዎን የመጨረሻው ጠብታ፡፡ ያን ጊዜ ወደ እኔ የሚመለሱ እንደሚድኑ ሁሉ አንዳንዶች ደግሞ በእሳቱ ውስጥ ያልፋሉ፡፡

"ነገር ግን እናንተ ብርቅዬ ሙሽራዎቼ፣ እናንተና ቤተሰባችሁ ይህም እውነተኛ ቤተሰባችሁ በእናንተ ጥላ ሥር ይሆናሉ፡፡ ሁላችሁም ጥንቃቄ ይደረግላችኋል፡፡ መፍራት ምንም አይጠቅምም፡፡ የሚጠቅመው መፀለይና መታመን ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ አምንሃለሁ፣ ኢየሱስ አምንሃለሁ በማለት አሁንም አሁንም እየደጋገማችሁ ፀልዩ፡፡ "ለመሃፀን ፍሬዎቻችሁ እኔ ጥንቃቄ አደርጋለሁ፡፡ ኃጢያታቸውን እያመኑና ንስሐ እየገቡ አንድ በአንድ ወደ እኔ ይመለሳሉ፡፡ ክሌር በዚህ ምድር እስካለሽ ድረስ የምትችይውን አድርጊ፡፡ በኢየሩሳሌም ያለው መስኪድ በወደመ ጊዜ በጉለበቶችሽ ተንበርከኪ፡፡

"ክሌር ለእኔ ያዘጋጀሻቸው ስጦታዎች አሉ?"

ጌታ አዝናለሁ፡፡ እኔ በጣም ገብጋባ ሆኛለሁ፡፡

"ደህና ለእኔ ስትዪ አድርጊው፡፡ የምግብና የተፈጥሮ ፍላጎትሽን የበለጠ በመቆጣጠር የምትገልጫቸውን እነዚህን ትንንሽ የፍቅር ምልክቶችን ማየት እፈልጋለሁ። እባክሽ ክሌር ትንሽ ትሞክሪያለሽ? እኔ ፀጋውን እሰጥሻለሁ፡፡"

እሺ ጌታ እሞክራለሁ፡፡ ለመሞከር የምችልብትን ፀጋ አገኛለሁ?

"አዎ ይሰጥሻል፡፡ አገልግሎትሽን ከሁሉ በፊት አስቀድሚ ፡፡ ሌላውን ሁሉ ወደጎን አድርጊው፡፡

"ለእናንተም ለሙሽሮቼ የምለው ይህንኑ ነው፡፡ ስለ እኔ የምትሰጡት ምስክርነት ለእኔ እንደ ትንንሽ የሥርግ ስጦታ አድርጋችሁ አቅርቡልኝ፡፡ ስለ እምነታችሁ ንቀትንና ውርደትን ችላችሁ የኖራችሁ አሁን በቅርብ ጊዜ፣ በጣም በቅርብ ጊዜ ደስታን ትጎናፀፋላችሁ፡፡ ህይወታቸውን ሙሉ መርከቡን ሲሰሩ ንቀት እንደደረሰባቸው እንደ ኖህና ቤተሰቡ እናንተም ይህ ቢደርስባችሁ አሁን ግን ነፃ የምትወጡበት ጊዜ ደርሷል፡፡ በጥፋት ውኃ ዘመን የመርከቡን በር ዘግቼ  የታላቁ ምንጮች ተነድለው ውኃው ምድሪቱን ሲያጥለቀልቅ በግድግዳው እያለፈ ይሰማ የነበረው የፌዝ ሳቅ ትንሽም ሳይቆይ በጩኸት ተተክቶ ነበር፡፡

"በዚያን ጊዜ ታዲያ ኖህና ቤተሰቡ በጣም በጥልቅ ሐዘን ላይ ነበሩ፡፡ ነገር ግን እነርሱ የድርሻቸውን እንደተወጡና የጠፉትን ለማዳን ሰው ሊያደርግ የሚችለውን ጥረት ሁሉ እንዳደረጉ ስነግራቸው ከመረዳት በላይ የሆነ ሰላምን አገኙ፡፡ በእውነቱ ከሆነ እኔ ውጪ የቀሩት ሰዎች ወደ መርከቢቱ እንዲገቡ ፈቃዴ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም የእነሱ ህይወት በኃጢያትና በኔፍሊሞች እጅግ ተመርዞ ስለነበረ ነው፡፡

"ታዲያ ያን ጊዜ ብዙ ምህረት ተደርጎ ነበር፡፡ የኔ ተፈጥሮ ከሰው ሊወዳደርና የሰው ልጅ ሊረዳውና ሊገባው ከሚችለው በላይ ስሜቴ አግባብነት ባለው መልኩ ቶሎ የሚነካ ነው፡፡ የእናንተ የባህል ችግር ደግሞ አስተሳሰባችሁን የተዛባ ማድረጉ ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህም ቢሆን በኖህ ዘመን ከነበሩት ከኔፍሊም ወንዶችና ሴቶች ጋር ሲወዳደር ገና የእነሱን ያህል ድርጊታችሁ አስከፊ አልሆነም፡፡ ነገር ግን እንደዚያ ሊሆን እያኮበኮበ ነው፡፡

"እግዚአብሔርን መፍራት የለም፡፡ ይህንን ስል በእውነት እግዚአብሔርን መፍራት የለም ማለቴ ነው፡፡ ነገር ግን ወደፊት ይህ መሆኑ አይቀርም፡፡ እኔ ግን እያወራሁ ያለሁት ሰዎች ከፍራቻና መጥፎ ነገር ይደርስብናል ብለው ከመስጋት የሚመጣውን እግዚአብሔርን መፍራት አይደለም፡፡ እኔ እያወራሁ ያለሁት በፍፁም ጥልቅ በሆነ ፍቅር ላይ የተመሰረተውን እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ እግዚአብሔርን መፍራት ይገባል፡፡ ይህም እኔ እንደ ሰው ኃጢያትን እንደማላፀድቅ ወይም ከኃጢያት ጋር እንደማልተባበር ፣ እንዲሁም እኔ ስለ ፅድቅ ያለኝ ሐሳብና የሰው ልጅ ስለ ፅድቅ ያለው ሐሳብ የተለየ መሆኑን በመረዳት በእውቀት ላይ የተመሰረተ እግዚአብሔርን መፍራት ይገባል ማለቴ ነው፡፡

"ያ ወጣት ትልቅ ፀጋ የተሰጠው፣ ህዝቤ የኔን መምጣት ተገንዝቦና ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ ለማድረግ ነው፡፡ ክሌር ወጣቱ ምን እንደተማረ ስታጠኚ ስለ ፅድቅ ምንነት እየገባሽ ይመጣል፡፡ እናም የሰው ልጅ እንዴት እንደተበላሸ ይገባሻል፡፡ ይህም

እናንተ ስለ ኃጢያታችሁ ዕዳ መክፈል እንደማትችሉ፣ ስለዚህም እኔ ለእናንተ ኃጢያት በመስቀል ላይ መሞት እንደነበረብኝና እናንተ እዳችሁን መክፈል በፍፁም እንደማትችሉ ነው፡፡ በፍፁም መክፈል አትችሉም ነበር፡፡

"የኔ ውድ አሁን ግን ከእኔ ጋር ልትሆኚ እንደምትፈልጊ ልብሽን አይቻለሁ፡፡ ለዚህም ለዘላለም ከእኔ አጠገብ እንድትሆኚ እንደገና መልሼ እራሴን ለሞት አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡

"የኔ ሙሽሮች ይህ እናንተንም የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ነው አንድ ኃጢያት ስትሰሩ፣ በጣም ትንሿን ኃጢያት እንኳን ስትሰሩ በአባቴ ፊት እያለቀስኩ የምማልደው፡፡ ደግሞ ከሁሉም በጣም የሚጎዳው እያወቃችሁ ሳትታዘዙ ስትቀሩ ነው፡፡ እመኑኝ ሙሽሮቼ እኔ የምጠይቃችሁ ለእናንተ እጅግ መልካም የሆነውን ብቻ ነው፡፡ ታምኑኛላችሁ?

"አሁን ወደ እኔ ቅረቡ ምክንያቱም የምንሰራው ሥራ አለ፡፡ ነፍሳት ነፃ እንዳወጣቸው ወደ እኔ እየጮሁ ነው፡፡ የእውነትና የፍቅር አምባሳደሮቼ በመሆን ለጩኸታቸው መልስ ስጡልኝ፡፡ ይህንን ለማድረግ ጥረት ስታደርጉ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ስታገኙ እርዱ እንጂ ምን ላድርግ ብላችሁ አትጨነቁ፡፡ በዚህም ኃሳብ ላይ ልባችሁን አሳርፉ፡፡ እኔ ማድረግ ያለባችሁን እንድታደርጉ ልባችሁን አፈጥናለሁ፡፡ እኔ እመጣለሁ!!! ቶሎ እመጣለሁ፡፡ ደግሞ የኔን መምጣት እያሰባችሁ ልባችሁን በዚህ ተስፋ ላይ አሳርፉ፡፡"

## ለመነጠቅ ዝግጁ ናችሁ? / ኦክቶበር 5 ቀን 2015 ዓ.ም

## Are You Ready for The Rapture? / Octobere 5, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች ፡- ጌታዬ ልትናገረን በልብህ ውስጥ ያለው ምንድነው?

ኢየሱስም *"መንግስተ ሰማያት"* በማለት ጀመረ፡፡

ክሌርም ... *መንግስተ ሰማያት?* በማለት ጠየቀች፡፡

ጌታም እንዲህ በማለት ቀጠለ . . . *"ያዘጋጀሁላችሁን ባያችሁ ጊዜ ፊታችሁ ላይ የሚታየውን ስሜት ለማየት በጣም ጓጉቻለሁ፡፡ ለሙሽሮቼ አንድም በጅምላ የተዘጋጀ ስጦታ የለም፡፡ ለእያንዳንዱ የተዘጋጀው በሙሽሮቼ ልዩነት መሰረት በእጅ ምርጥ ተደርጎ ነው፡፡*

*"ክሌር በታሪክ ውስጥ ለዚህ ጊዜ እጅግ ጓጉቻለሁ፡፡ ለእኔ ብለው ልባቸውን ላሳዩኝ ምርጦቼን የምሸልምበትን ቀን በሙሉ ልቤ ሆኜ ስጠባበቀው ቆይቻለሁ፡፡ እውነት ነው ቀድመው ለሄዱት በሰማይ ሽልማት አለ፡፡ ነገር ግን ከአካላቶቻችሁ ጋር በክብር ስትገናኙ ደግሞ እጅግ በጣም ለየት ያለ ነገር ይኖራል፡፡ ይህንንም ታዩታላችሁ፡፡*

*"በከበረ አካል በምትገለጡ ጊዜ ይህንን ክስተት ተያይዘው የሚመጡ የተወሰኑ ነገሮች፣ የተወሰኑ ስሜቶችና ጣፋጭ ሁኔታዎች ስላሉ በኔ ፊት ሁላችሁም ሙሉ ሆናችሁ ለማየት እጅግ ጓጉቻለሁ፡፡ ስለዚህም ይህንን ቀን በትልቅ ጉጉት እየጠበኩት ነው፡፡አዎን ትክክል ነው አንቺ እንደምታስቢው በብዙ የሚቆጠሩትን የጠፉትን ነፍሳት መከራ መቀነስ ለእኔ መጽናናት ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ከእናንተ መነጠቅ በኋላ ትልቁ መንፈሳዊ መነቃቃት ምድርን ያጥለቀልቃታል፡፡ ይህ መንፈሳዊ መነቃቃት በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንዶች ስለእኔ በመሞታቸው ይደሰታሉ፡፡"*

“የእናንተ መሄድ እኔ እኔ እንደሆንኩ፣ ተግተው ለሚፈልጉኝ ሽላሚ ስለመሆኔ የማይካድ ሃቅኛ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡"

“ሳይነጠቁ ለቀሩትም እኔ ከእነርሱ በፊት የሄድኩት ለእነርሱም ቦታ ላዘጋጅ እንደሆነ ማረጋገጫ ይሆናቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የሚጠብቃቸው ሞት ቢሆንም እስከ መጨረሻው ከአካላቸው በመለየታቸውና የእንባው ጊዜ በማለፉ ይጽናናሉ፡፡ ይህም ለብዙዎች የመሄጃ ጊዜያቸው እስኪደርስ ድረስ በህይወት እንዲቆዩ ይረዳቸዋል፡፡ በሞት ለሚቀጧቸውም እኔ እውነተኛ ስለመሆኔ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ ብዙ ገዳዮችም ስለ እኔ ማንነት የእምነት ሞገድ ባጥለቀለቃቸው ጊዜ የእነዚያን ፈለግ ይከተላሉ፡፡”

“አሁን ደግሞ መሰረታዊ ወደሆነው ልምምዶቻችሁ እንሂድ፡፡ ከእናንተ መካከል አሁንም በኃጥያት ውስጥ እየኖሩ የንጥቀቱ ተካፋይ እንደሚሆኑ ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡ ሙሽሮቼና ወደፊት ሙሽሮቼ ልትሆኑ የምትችሉ ሁሉ ራሳችሁን ከኃጥያት መለየት አለባችሁ፡፡ ብዙዎቻችሁ ከኃጥያት የተነሳ ሙሽራ ለመሆን አልተዘጋጃችሁም፡፡”

ክሌር ፡- ጌታ ምህረትህስ?

“ምህረቴ ለማያውቁት ወይም እያንዳንዱ ሙከራቸው ለሚከሽፍባቸው ደካሞች ብቻ ነው፡፡ እኔ እያልኩ ያለሁት አለም እንደሚያስበው ለምታስቡትና አለም በሚስማማባቸውን ባህሪያት የሚስማሙና በስህተትም እኔ ከእነርሱ ጋር የምስማማ ለሚመስላቸው ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ከእነርሱ ጋር አልስማማም፡፡ ስለዚህ እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ፡፡”

“<u>እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ። ዳሩ ግን። እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።</u>" 1ኛ ጴጥሮስ 1፡14-14

“አብረው እየኖሩ እያሉ አሁንም ያንን ሰው ለማግባት የማይፈልጉ የተወሰኑ ሰዎች አሉ፡፡ በዚህም ዝሙት እየፈጸማችሁ ነው፡፡ ምኞት ከቅድስና ቅድሚያ ተሰጥቶታል፡፡ ከቅድስና ውጪ የመነጠቅን እድል ልታገኙ ይቅርና ነፍሳችሁ በገሃነም ላይ ተንጠልጥላለች፡፡ የተወደዳችሁ ይህ የሚገባ ነገር ነው? ትክክለኛውን ነገር ካለማድረጋችሁ የተነሳ የገሃነም እሳት ውስጥ እራሳችሁንን ማግኘት ትፈልጋላችሁ እንዴ?”

“ባህርያችሁ አማኝ ካልሆኑት ጋር የሚያስወግዛችሁ ከሆነ የመጽሀፍ ቅዱስ እውቀታችሁና ኃይማኖታዊ ስርዓታችሁ ምን ይጠቅማችኋል? አንዳንዶቻችሁ እስከዚህ ብቻ እኄዳለሁ  ከዚህ ግን አላልፍም እያላችሁ በማሰብ በእሳት ትጫወታላችሁ፡፡ ገና በመጀመሪያው መሳሳም ኃጥያት እንደሰራችሁ አታውቁምን? እርግጥ ነው በቅድስና አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላም ተባባሉ፡፡ ነገር ግን መስመሩን ሳትዘሉ ፍላጎትን ማርካት በእኔ መፅሐፍ ዕይታ መስመር መዝለል ነው፡፡ ኃሳቦቻችሁንና እይታዎቻችሁን እህታዊና ወንድማዊ እንዲሆን አድርጉ፡፡የእሳት ነበልባሉን እያባባሳችሁ ኃጥያት የሌለባችሁ አይምሰላችሁ፡፡ መለወጣችሁን ለነገ አታቆዩት፡፡ ምክንያቱም ነገ የእናንተ ለመሆኑ ማረጋገጫ የላችሁም፡፡”

“የምወደውን ለምንድነው በኃይል ቃል የምናገረው? ምክንያቱም ስለምወዳችሁ፣እራሳችሁን ባለመጠበቃችሁና ባለመጠንቀቃችሁ የምታጧቸውን ነገሮች በሙሉ እንድታጡ ስለማልፈልግ ነው፡፡ ይህን ያህል መንገድ መጥታችኋል ሁሉንም እንዳታጡት፡፡ ኃጢያት ሊያመጣ የሚችለውን መንገዶች በሙሉ ራቁ፡፡ ራሳችሁን መቆጣጠር የማትችሉበት ደረጃ እስክትደርሱ ድረስ አትጠብቁ፡፡ ነገሮችን ሁሉ ንፁህና በሮች ሁሉ ዝግ አድርጉ፡፡”

“አትስረቁ፡፡ እናንተ የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት ብላችሁ ልክ ያልሆኑ አቋራጭ መንገዶችን አትጠቀሙ፡ በእርግጥም ጥቃቅን ነገሮች ናቸው የወይኑን ፍሬ የሚያበላሹት፡፡ ጠላታችሁ ደካማ ጎናችሁን ለማግኘት ሁሌም የእናንተን እንቅስቃሴ ይከታተላልና እናንተም በተጠንቀቅ ጠብቁ፡፡”

“አትዋሹ፣ የሐሰተኛ ምሳሌም አትሁኑ፡፡ የሰዎችን ንግግር ለእናንተ አጀንዳ እንዲመች አድርጋችሁ አታጣሙ፡፡በውሸት የሚመሰክሩትን እፀየፋልሁ፡፡ ስለዚህም እንዲጠሩ በተደጋጋሚ በሰይጣን እንዲፈተኑና እንዲጠሩ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁ፡፡"

“አገልጋዮችን አትበድሉ፡፡ሚስቶቻችሁን ወይም ባሎቻችሁን እንደራሳችሁ ሥጋ ተንከባከቡ፡፡ እርስ በራሳችሁ በቅንነትና ከልብ በሆነ ፍቅር ተዋደዱ፡፡ የበላይ ሆኖ ልቆ የመገኘት፣ የመጀነን፣ የንቀት ባህርያትን ተዉ፡፡ እራሳችሁን ዝቅ ብታደርጉ እኔ አነሳችኋለሁ፡፡ ሚስቶች በማይነገሩት ነገሮች እንኳን የባሎቻችሁን ፍላጎት አሟሉ፡፡ ባሎች ደግሞ ሚስቶቻችሁ ያለባቸውን ሸክም በግልፅ ሳይናገሩ ነገር ግን ለእናንተ የገቡትን ቃል ስለሚፈፅሙ ደግና ገር እንዲሁም ይቅርባይ ሁኑላቸው፡፡”

“ተገቢ ላልሆኑ ባህሪያት ከሚያስከትሉ ሙዚቃ፣ ፊልሞችና መዝናናቶች ራሳችሁን አታጋልጡ፡፡ ኃጥያትን ማየት ኃጥያት እንደመፈጸም ነውና፡፡ ሌላው ቢቀር እንኳን ኃጥያቱን እያፀደቃችሁ እና እያበረታታችሁ ነው፡፡ አይኖቻችሁ ፣ልባችሁና አእምሮዋችሁ ለእነዚህ ነገሮች በፍፁም ባይጋለጡ መልካም ነው፡፡”

በቃሉ እንደተፃፈው <u>“እዘምራለሁ ፥ ንጽሕ መንገዱንም አስተውላለሁ ፥ ወደ እኔ መቼ ትመጣለህ? በቤቴ መካከል በልቤ ቅንነት እሄዳለሁ፡፡ በዓይኔ ፊት ክፉን ነገር አላኖርሁም ፤ ሕግ ተላላፊዎችን ጠላሁ፡፡ ጠማማ ልብም አልተጠጋኝም ፤ ክፉ ከእኔ በራቀ ጊዜ አላወቅሁም፡፡ ባልንጀራውን በቀስታ የሚያማን እርሱን አሳደድሁ፤ በዓይኑ ተዕቢተኛ የሆነውና ልቡ የሚሳሳው ከእኔ ጋር አይተባበርም፡፡ ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ፤ ዓይኖቹ በምድር ምእመናን ላይ ናቸው ፤ በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል፡፡ ትዕቢትን የሚያደርግ በቤቴ መካከል አይኖርም፤ ዓመፅን የሚናገር በዓይኔ ፊት አይቀናም፡፡”</u> መዝሙረ ዳዊት 101፡2-7

“እነዚህን ነገሮች ብታደርጉ እንዴት ደስተኛ እንደምትሆኑ አሁን አውቃችኋል፡፡ ለዚህ መልዕክት ተቃውሞ እንዳታሳዩ እገስፃችኋለሁ፡፡ ኃሃጥያት ውስጥ ከሆናችሁ ከዚያ ውጡ፡፡ መንፈሴ በተለያዩ ማስጠንቀቂያዎች እናንተን ጎብኝቷችኋል፡፡ አሁን ነገሮችን የምታደባልቁበት ወይም ሰነፍ የምትሆኑበት ጊዜ አይደለም፡፡”

“ማንም በዚህች ምድር ላይ ሌላ ቀን እንደሚኖረው የተረጋገጠ አይደለም፡፡ነገ የመጨረሻችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ህይወታችሁን አሁኑኑ አስተካክሉ ለሌላ ቀን አታስተላልፉ፡፡”

“ጌታ የሚወዳቸውን ይቀጣል፡፡ ያልኩትን ነገር በማጣመም ራሳችሁን በፍርድ ብርድ ልብስ እንዳትጠቀልሉት፡፡ በኃጥያት ውስጥ ከሆናችሁ ራሳችሁ በደምብ ታውቁታላችሁ፡፡”

“የቀራችሁት ውዶቼ- መልካሙን ገድል የተጋደላችሁ፣ ራሳችሁን ከኃጢያት መንገድ የጠበቃችሁ፣ ዝሙት ላለመፈፀም በብቸኝነት የተሰቃያችሁ፣ ብዙ ዋጋ የከፈላችሁ ሁሉ በመንግስተ ሰማያት ሽልማታችሁ እንዲሁ ትልቅ ነው፡፡"

"ለመንግስት ያልዋሻችሁና በውሸት ያልመሰከራችሁ ለእናንተ ጥሩ ሰርታችኋል እላለሁ፡፡ ትልቅ ምድራዊ ጥቅማ ጥቅሞች ቀርተውባችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ነፍሳችሁን አጥታችሁ አለምን ሁሉ ብታተርፉ ምን ይጠቅማችኋል? በዚህ ምክንያት ደህይታችሁ ቢሆንም ትክክለኛውን ነገር መርጣችኋል፡፡"

“ከአለም ብክለቶች እራሳችሁን ንጹሕ አድርጋችሁ ለጠበቃችሁ ሁሉ ጥሩ አድርጋችኋል እላለሁ፡፡ በህሊናችሁ ውስጥ ያስቀመጥኩትን መመሪያች በትክክል ተከትላችኋል፡፡ በእናንተ ልብ ውስጥ ደስተኛ ነኝ፡፡ በዚህም መፅናናትን አግኝቻለሁ፡፡”

“እናንተ በኃሜት፣በአሉባልታ ወሬና በክፉ ሰዎች የተጠቃችሁ ሆኖም ግን ከልባችሁ ለእነርሱ የፀለያችሁ የእኔን የእሾህ አክሊል መስላችኋል ፡፡ በመነጠቅ ጊዜ እናንተን በደንብ እለያችኋለሁ፡፡”

“አሁን በደረቴ መካከል ተማምናችሁ በመኖር ከማያልቀው ፍቅሬ ወስዳችሁ ለዚህ ለወደቀና ለተራቆተ አለም ፍቅሬን አካፍሉ፡፡ ፍቅራችሁ በእርግጥ ያስፈልጋል፡፡ እናም ከምርጡ ወይን ልመግባችሁ ደስተኛ ነኝ፡፡”

“አሁን ሁላችሁንም እባርካችኋለሁ፡፡ ደግሞም እንዲህ እላችኋለሁ፡፡ በህይወታችሁ ውስጥ ለመነጠቅ የሚከለክሏችሁን ማንኛውንም ነገሮች ሊወቅሳችሁ የእኔ መንፈስ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ትኩረት ስጡ፡፡ ይህንን ድምጽ በደምብ አድምጡት እንጂ አትሽፋፍኑት፡፡ የምወዳቸውን አርማለሁና በጥንቃቄ አድምጡት፡፡ ፡፡”

## መልካም ዛፍ መጥፎ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም / ኦክቶበር 7 ቀን 2015 ዓ.ም

## A good tree cannot bear bad fruit / October 7, 2015

የተወደዳችሁ የዩትዩብ ቤተሰቦችና ኸርትድዌለርስ ጌታ ከእኛ ጋር ነው ፡፡

ዛሬ አንድ ነገር ለእናንተ ለመንገር ፈልጌያለሁ፡፡ ዛሬ ምሽት በአምልኮ ነበር የጀመርኩት፡፡ በዚህም አምልኮ ጊዜ ምናልባት ወደ አንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ወደ አምልኮ እገባና ከዚያ ደግሞ እንቅልፌ በደንብ ይመጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጌታ ይህንን የሚያደርገው በእርሱ ለማረፍ እንድንችል ብሎ ነው። ለእርሱ ስንታዘዝና ስንገዛ በአይምሮአችንና በልባችን ላይ ብዙ ማስተካከያዎችን ያደርጋል።

ስለዚህ ፣ እናንተ በጸሎት ጊዜ ወይም በአምልኮ ጊዜ እንቅልፍ ያስቸገራችሁ ሰዎች ፣ ምናልባት ጌታ ለጥቂት ጊዜ በእሱ ውስጥ እንድታርፉ ፈልጎ ሊሆን ይችላል ፡፡ ያ ብዙውን ጊዜ የሚቆየው ለሃያ ደቂቃዎች ገደማ ነው፡፡ ከዚያም ስትነቁ አይምሮዋችሁ በጣም ንቁ ይሆናል፡፡ እናንተም እንደገና ታድሳችሁ ትነሳላችሁ፡፡ ይህ አንዱ ሲሆን ሌላው ትኩረቴን የሳበው ደግሞ የሚከተለው ነው፡፡

ትንሽ የሆድ ህመም ተሰምቶኝ ቢሆንም ግን እራት በልቼ ነበር፡፡ እናም ስሜቴ ትክክል አልነበረምና ጥቂት አይስክሬም ለመብላት ከባድ ጉንተላ ተሰማኝ። እኔም እንዲህ በማለት አሰብኩ 'ጌታ አንተን ከማዳመጤ በፊት አይስክሬሙን መብላት አልፈልግም። ቢያንስ አንድ ነገር እራሴን ለመከልከል እፈልጋለሁ፡፡' ነገር ግን እርሱ እንዳደርገው ሲገፋፋኝ ተሰማኝ። ስለዚህ ጥቂት አይስክሬም በልቼ የሆዴ ህመም ሙሉ በሙሉ ተወኝ፡፡ ወደ ኮምፒዩተሬ ተመልሼ ከእርሱ ጋር መነጋገር ስጀምር ጌታን እንዲህ አልኩት ‘ኢየሱስ እኔ ለራሴ ሸክም ነኝ ፡፡ ይህ ሰውነት ጨካኝ ነው! እናም እስካሁን ልቆጣጠረው አልቻልኩም፡፡’

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ጀመረ . . . “የኔ ፍቅር ከሰውነትሽ ባለፈ እንሂድ፡፡ ምክንያቱም በነፍሶች ላይ የምንሠራው ሥራ አለ፡፡ ሰውነትሽ አንቺን ያገልግል። ማድረግ ያለብሽን አድርጊ፡፡ ነገር ግን ለእኔ ስትዪ ወደ ነፍሳቱ እንሂድ።”

ከሌር:- አዎ ጌታ እኔም በእርግጥ የምፈልገውም ይህንን ነው ፡፡

“አንቺን የሚያፅናናሽ ከሆነ ልንገርሽ ይህንን ጨካኝ ሰውነት በምድር ላይ ሆነሽ ልትገዢው አትችይም። ስለዚህ ተይው ፡፡ በቃ ተይውና በነፍሶች ላይ አተኩሪ፡፡”

ከሌር:- ጌታ እኔም ማድረግ የምፈልገው ይህንን ነው ፡፡ ነገር ግን ራስን መካድና መፆም እናም ይህ ሁሉ ነገር ችግር አለብኝ፡፡

“ይህንን በመብላትሽ ወይም ያንን ባለመብላትሽ ከጨለማው አለም የሚሰነዘርብሽን የጥፋተኝነት ስሜት መስማት አያስፈልግሽም። ይህ በጥፋተኝነት ስሜት ሽፋን ወደራስሽ እንድትመለሺ ለማድረግ የሚፈጥሩት ማታለያ ነው፡፡ ለመጨመር የምፈልገው ነገር ብዙዎች፣ እጅግ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ ይታለላሉ። ከእነዚህ መካከል አንዷ አትሁኚ።“

“ሙሽሮቼ በማንኛውም ጊዜ ትኩረታችሁ ሌሎችን ከመንከባከብ ላይ አንስታችሁ ወደ ራሳችሁ ድክመቶች እና ውድቀቶች ስትቀይሩት ስለ ሌሎች እንዳታስቡ የሚያደርግ ከሳሽ አጋንንት ወደ እናንተ እንደተላከ መጠራጠር አለባችሁ፡፡ ከዚህ ሌላ ግን የተለይ ሁኔታ የሚፈጠረው ሰዎችን ዝቅ አድርጋችሁ ለማየት እንዳትችሉ ብዬ እኔው እራሴ ስህተቶቻችሁን እንድታዩ ሳደርጋችሁ ብቻ ነው። ቀን ከሌሊት ለማስወገድ መሥራት ያለባችሁ ይህንን አንድ ጨካኝ ነገር ነው፡፡

“አንቺ የእኔ ፍቅር በእኔ መገኘት ዘና የምትይውና እኔ መሆኔን መጠራጠር የምታቆሚው መቼ ነው?” (ከሌር:- ጌታ ይህንን ያለው መንፈስን ለመለየት ሁልጊዜ ስለማጣራ ነው) በየምሽቶቹ ሁሉ መጥቼ እንደማናግርሽ ትጠራጠሪያለሽ፡፡ ከሌር መቼ ነው የምታምኚኝ?”

ከሌር:- በመንግስተ ሰማያት መንፈሳዊ ነገሮችን በግልፅ ማየት ስለምችል ከአንተ ጋር በመንግስተ ሰማያት ስሆን ?፡፡

"ነገር ግን እኮ በጎቼ ድምፄን ይለዩታል ... እናም አንቺም ድምፄን ታውቂዋለሽ ፡፡ የሌሎች ትችት ይሆን እንዲህ እንድትጠራጠሪ ያደረገሽ?"

ከሌር:- ጌታ ለምን ትጠይቀኛለህ? ከአንተ የተደበቀ ምንም ነገር የለም። በእውነት ግን ሰይጣን በጭራሽ እንደማይተኛ አውቃለሁ፡፡ እናም ሌሎችን ለመምራት ስለጠራኸኝ እነሱን ለማሳሳት አልፈልግም ፡፡

“የእኔ ፍቅር ለዚያም ነው ሕዝቅኤልን ወደ ህይወትሽ የላኩት፡፡ እናም ካሮልን ጭምር፡፡ ራስሽን ዝቅ እስካደረግሽ ድረስ እኔ እንደምጠብቅሽ ትረጃለሽ ደግሞም ታውቂያለሽ፡፡ መታለልን መፍራት ያለብሽ እራስሽን ከፍ ከፍ በማድረግ በሌሎች ላይ መፍረድ ስትጀምሪ ነው፡፡”

ከሌር:- እኔ ያንን ፍፁም እጠላለሁ፡፡ ደግሞም የዛ ተካፋይ መሆን አልፈልግም፡፡ ስለዚህም ያንን በጭራሽ ላለማድረግ እየሞከርኩ ነው ፡፡

“ነገር ግን ሁልጊዜ በዚያ መንገድ ትፈተኛለሽ፡፡ ምክንያቱም ያ አገልጋዮቼን ለመጣል ፈጣኑ መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ አጋንንቶች በሚገባ ያውቁታል፡፡ አየሽ በሌሎች ላይ ለመፍረድ ራስሽን ስትፈቅጅለት ኃጢአትን ትሠሪያለሽ።” በቃሉ እንደተፃፈው:-

“እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ፣ በምትፈርዱበትም ዓይነት ፍርድ ይፈረድባችኋል፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል፡፡ በዓይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳትመለከት፣ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ለምን ታያለህ?” (የማቴዎስ ወንጌል 7: 1-2)

ከሌር፦ ግን ጌታ ስለእምነት በምንነጋገርበት ጊዜ መንፈስን መመርመርና በቅዱሳት መጻሕፍት መሰረት መመዘን አለብን አይደል?

“መንፈስን መለየት አንድን ወንድምን ወይም እህትን ከመተቸት በጣም የተለየ ጉዳይ ነው ፡፡ አዎ ሁልጊዜም ከቃሌ ጋር መመዘን አለበት፡፡ ነገር ግን ደግሞ ቃሌን በአዲስ መልኩ ለመረዳት ፈቃደኛና ክፍት ሆነሽ መገኘት አለብሽ፡፡ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስካሁን ማንም ያላገኛቸው ብዙ መገኘት ያለባቸው ግኝቶች አሉ፡፡ በመንፈሴ በመመራት ቃሌ ስለተገለጠላቸውና ነጥቦቹን ማገናኘት የቻሉ ሰዎች ደህንነት በማይሰማቸው ሰዎች ይፈተናሉ ደግሞም ይወገዛሉ። እነዚህ ሰዎች ደህንነትና ሁሌም ትክክል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ለማድረግ ብለው ሌሎችን ወደራሳቸው ትምህርት ለማስገባት ይጥራሉ።”

“እነዚህ ሰዎች እንዳይታለሉ እጅግ ስለሚፈሩ ተገቢውን የመንፈሴን እንቅስቃሴ ያወግዛሉ። ምክንያቱም ለእነሱ እንግዳ ስለሆነና የእነሱን ክልል አደጋ ላይ ይጥላል ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ እንዲሁም ቅናትም በውስጡ አለበት፡፡ ብዙዎች በውስጣቸው በሚስጥር መገለጥን እንዳልሰጠኋቸው ያስባሉ፡፡ ይህ እውነት ሊሆን አይችልም። ይህ ነው እንግዲህ በሌሎች ላይ ለመፍረድ መሠረት የሆናቸው፡፡ እነዚህ ታዲያ በምድር ላይ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ከፍተኛ ጉዳትን የሚያደርሱ ናቸው፡፡

"ለዚህ ነው መንፈስን መለየት ፍፁም አስፈላጊ የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጋር መዋጋት አትፈልጉምና ነው፡፡ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ: - “አሁንም የምላችሁ እነዚህን ሰዎች ተዉአቸው፤ አትንኳቸው፣ ሐሳባቸው ወይም አድራጎታቸው ከሰው ከሆነ ይጠፋልና፡፡" ሐዋ 5፡38

“ለምሳሌ ያህል ስለ ሥላሴ ትክክለኛ መግለጫ አልሰጠሁም፡፡ ሆኖም ግን በጥልቀት ስትመለከቱ በቃሉ ውስጥ አለ፡፡ እናም ሐዋርያቶቼ በመንፈሴ ተመርተው ግንኙነቶቹን በመረዳት ጤናማ የሆነ የክርስትና አስተምሮ ሊመሰርቱ ችለዋል፡፡ ነገር ግን ያንን ባለማመናችሁ ወደ ገሃነም አትገቡም። ስለዚህ ሕግን የበላይ አድራጊዎች አትሁኑብኝ!

“አንዳንድ ሰዎች ምንም ደህንነት የማይሰማቸው ስለሆኑ በዙሪያቸው ያለውን ነገር ሁሉ እነርሱ በመደቡት ምድብ ለመመደብ ዘወትር ይሞክራሉ ፡፡ እኔ እያወራሁ ያለሁት እንደ ግብረ ሰዶማዊነት ያሉትን ብልሹ ሥነ ምግባሮችን አይደለም። ይህ ምንም ማመቻመቻ የማያስፈልገውና ኃጥያት መሆኑ ግልፅ የሆነ ነገር ነው።“

“እኔ እየተናገርኩ ያለሁት ሁሉንም ሰውና ሁሉንም ነገር በመጭመቅ እናንተ ያሰባችሁትን ቅርፅ ለማስያዝ ስለምትሞክሩት ነው። ይህንንም የምታደርጉት የራሳችሁን አመለካከት በመውሰድ፣ ከባድና ፈጣን ትምህርት በማድረግ የእናንተን ሃሳብ የማይጋሩትን ሌሎችን ለማውገዝ ለመጠቀም ነው።

"ፈሪሳውያኑ ያደረጉት ይህንን ነው ። ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ፣ ከዚህም የበሉ ደግሞ በሰሩት ጥፋት ለፍርድ ይቀርባሉ።"

(ክሌር)፦ ጌታ ታዲያ ካለው መፅሐፍ ቅዱስ አዲስ መገለጦች ሲመጡ ካለፈው ትርጓሜ አንፃር እንዴት ነው የምንመዝነው?

"መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ የተነባበረ ነው። ትንቢት፣ ታሪክ ፣ ልባዊ ምክር ፣ ጥበባዊ ምሪት ፣ ሰወኛ ጉዳዮች ፣ ሁሉንም የህይወት ዘርፎች ያካተተ፣ ጤናን ሁሉ ያካተተ ነው። እንዲሁም ለእናንተ ብቻ የሚሆን የተቀባ የጊዜው ቃል ወይም የቃሉ መገለጥ ያለበት ነው። አንድ ንጉሥ ወደ ጦርነት ከመግባቱ በፊት ነቢያቶችን ወይም ካህኑን በመጥራት የጦርነቱ ውጤቱ ምን እንደሚሆን ለማወቅ እኔን ምክር ይጠይቁ ነበር። ይህ እንግዲህ የቃሉ መገለጥ ሲሆን ከእኔ የሚለያችሁን መሸፈኛ ከገለጥኩ ጊዜ ጀምሮ ለሁሉም አማኝ የተሰጠ ነው።

"ስለዚህም ሰዎች በመንፈሴ አማካኝነት ከዚህ በፊት ለማንም ተገልጦ ያልነበረ አዲስ አመለካከትን ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ የኔ ሥራ ነው። ነገር ግን የምትኖሩት በአሳች በበዛበት ጊዜ በመሆኑ ውሸታም መናፍስቶች እምነትን እያጣመሙ ይገኛሉ።

"አንዳንድ ነገሮች መቼም ትክክል ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልፅ አድርጌላችኋለሁ"

(ክሌር)፦ ጌታ ታዲያ አንድ አዲስ የትርጉም መገለጥ በመንፈስ ቅዱስ የተመራና ከነበረው መፅሐፍ ቅዱስ የተገኘ መሆኑን ወይም የብርሃን መንፈስን ተመስለው ያመጡት የአጋንንቶች ትምህርት መሆኑን እንዴት መለየት እንችላለን?

ልክ በዚህ ጊዜ ይህንን ጥቅስ አስታወስኩ። "በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች እምነትን ክደው አታላይ መናፍስትንና የአጋንንትን ትምህርት እንደሚከተሉ መንፈስ በግልጥ ይናገራል። እንዲህ ያለው ትምህርት የሚመጣው ህሊናቸው በጋለ ብረት የተጠበሰ ያህል ከደነዘዘባቸው ግብዝ ውሸተኞች ነው። (1ኛ ጢሞቲዎስ 4፡ 1-2)

(ክሌር)፦ ጌታ ሆይ አስተማሪዎች ለአማካይ ሰው ጥሩ ሆነው ሊታዩ እና ሊሰሙ ይችላሉ። ግን እነርሱ ቅን እና በእውነት ከአንተ ጋር ናቸው?

በተጨማሪም "እንደእነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለውጡ፣ ሐሰተኞች፣ ሐዋርያትና አታላይ ሠራተኞች ናቸው። ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም። ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መላዕክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል። እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች የፅድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን የሚያስገርም አይደለም። ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።" (2ኛ ቆሮ 11:13 13)

"ክሌር ጥያቄሽን ራስሽ መለስሽው። 'መጨረሻቸው ለድርጊታቸው የሚገባቸው ይሆናል።' በፍሬዎቻቸው ታውቋቸዋላችሁ። ይህ ቀላልና ግልፅ የሆነ ነው። ፍሬውን ቅመሱት ... መራራ ነው? የተበላሸ ነው? በጥላቻ፣ በትችት ፣ በክስና በቁጣ የተሞላ ነው? ወይንስ ጣፋጭ ነው? ግጭትን የሚጠላ? ገር ፣ ደግ እና ሰላማዊ እንዲሁም ሁልጊዜ የፅድቅ ፍሬ በበለጠ ለማፍራት ከእኔ ጋር ጥልቅ ወደሆነ ግንኙነት የሚመራ ነው? ። ዘወትር ከኃጢያት መቆጠብ፣ ንስሐ መግባትና አዲስ ሕይወት ለመኖር ውሳኔ ያለው ነው?። እነዚህ ፍሬዎች ሁሉ የተማራችሁት ትምህርት ከእኔ መሆኑን የሚያስረዱ ግልፅ ማስረጃዎች ናቸው ።"

"ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬን ማፍራት አይችልም ። ፍሬውን ቅመሱ ። የኔ ፍቅር አንቺ ከእኔ ጋር ነበርሽ። ረዘም ላለ በቂ ጊዜ በእኔ መመሪያ ሥር በመሆን ሳስተምርሽ ቆይተሻል። እነዚህን ሁሉ ማወቅ ስላለብሽ ለምን ትጠይቂያለሽ?"

ክሌር፡- እምም... ምክንያቱም ሌሎችን ከሰበኩ በኋላ እኔ ራሴ እንዳልጣል ...

“ክሌር ፍርሃትሽን ወደዚያ ጣዪ ። እየኖርሽ ያለሽው እኔ የመደብኩልሽን ሕይወት ነው ፡፡ የኔ ማረጋገጫና በረከት አለሽ - ከዚህ የበለጠ ምን ትፈልጊያለሽ?

ክሌር፡- ምንም ጌታ ፣ በፍፁም ምንም አልፈልግም፡፡

“ሙሽሮቼ እውነትን ከሐሰት ለመለየት በጣም አቅልዬላችኋለሁ፡፡ ፍሬውን ቅመሱት ፡፡ ምክንያታዊ ከሆነው አይምሮአችሁ ጋር አትከራከሩ ወይም ለማስረዳት አትሞክሩ፡፡ ሁል ጊዜ አንድ ነጥብ ታጣላችሁና ማለቂያ የሌላቸው ጥያቄዎችን፣ቅራኔዎችንና የተሳሳቱ መደምደሚያዎችን ያስነሳሉ። ነገር ግን አንድ ነገር ምንጩ እውነተኛ መሆኑን ይገልጣል ይህም ፍሬው ነው። ጥሩ ዛፍ መጥፎ ፍሬ ማፍራት አይችልም።

“እነዚህን ቃላት አጥብቃችሁ ያዙ ምክንያቱም ወደ እውነት ሁሉ ይመሯችኋልና ነው።"

## ኑና ወደ ዕረፍቴ ግቡ / ኦክቶበር 19 ቀን 2015 ዓ.ም/

## Enter Into My Rest / October 19, 2015

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . ኸርት ድዎለርስ ጌታ ይባርካችሁ፡፡ የዛሬውን የፀሎት ጊዜ በጌታ አስደሳች መገኘት ነው ጀመርነው፡፡ ወደ እርሱ ዕረፍት ስለመግባት የሚደንቅ ትምህርት ሰጥቶናል፡፡ እጅግ ቆንጆ የሆነ ትምህርት ነው፡፡

እያመለኩት በነበርኩበት ጊዜ ጌታ ይዞኝ በአምልኮ መዝሙሮች ስንወዛወዝ ተመለከትኩኝ፡፡ ከዚያም የሚገርም ሰላም ውስጥ ገባሁ፡፡ ይህም ከከባድ መንቀዥቀዥ ወጥቼ ፍፁም ወደሆነ መረጋጋት የገባሁ ነው የመሰለኝ፡፡ የነበርኩበትም ቦታ ያለሁበትን መረጋጋት በትክክል የሚገልፅ ነበር፡፡ የቆምኩት የሚያንፀባርቅ መስታወት የሚመስል የማይንቀሳቀስ ኃይቅ አጠገብ ይመስለኛል፡፡ አለመንቀሳቀሱ እጅግ ያምራል፡፡ በልቤ ውስጥ የገባው ይህ የሰላም ስሜት ነበር፡፡ በእርሱ ትክክለኛ ዕረፍት ውስጥ ነበርኩኝ፡፡

ጌታ ሆይ የወሰድከኝ ቦታ እንደመስታወት የሚያንፀባርቅ ኃይቅ ያለበት፣ የማይንቀሳቀስና የተረጋጋ በጣም የሚያምርና ሰላማዊ የሆነ ቦታ ነው፣ አመሰግንሃለሁ፡፡ የሚገርም ነው የተለየ ስሜት ተሰማኝ፡፡

ኢየሱስም . . . “ይህ ዕረፍት ይባላል፣ ወደ ዕረፍት መግባት፡፡ ይህ ቦታ ሙሉ ለሙሉ ራስን አሳልፎ የሚሰጥበት ቦታ ነው፡፡ ትኩረታችሁን ሁሉ በእኔ ላይ ታደርጉና እናንተ ደግሞ ትደበዝዛላችሁ፡፡ የኔ ፍቅር እዚህ ቦታ መገኘት እጅግ ውብ ሲሆን ለመታደሳችሁም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡”

(ክሌር) ኢየሱስ ለእኔ ጣፋጭ፣ ሩህሩህና ቀና ነህ፡፡ ለአንተ የምገባ አይመስለኝም፡፡

ኢየሱስም "አይ! አይደለም የእኔ ውድ፡፡ ስለራስሽ ምንም ነገር መወሰን የለብሽም፡፡ እንዳውም ራስሽን በፍቅር ወደተሞሉት እጆቼ ውስጥ አድርገሽ ራስሽን እርሺው፡፡ ትክክለኛው ዕረፍት ይህ ነው፡፡”

(ክሌር) በእርግጥም እንደዛ ለማድረግ የምታስችልበት መንገድ አለህ!

(ኢየሱስ)“ይህ የእኔ ፍፁም ደስታ ነው፡፡”

(ክሌር) ጌታ ዛሬ ስለምን መነጋገር ትፈልጋለህ?

(ኢየሱስ) “ስለእዚህ ብቻ”

“ሙሽሮቼ አንዳንዶቻችሁ ወደ እረፍቴ ለመግባት በጣም እየሞከራችሁ ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ ለመግባት እየገፋችሁ፣ እየገፋችሁ ነው፡፡ እንዲህ ልበላችሁ እያደረጋችሁ ያላችሁትን ማድረግ ያለባችሁ በተቃራኒው ነው፡፡

“እኔን ለመገናኘት የምታደርጉትን ሙከራ እንደማከብር እየጠበቃችሁ ልባችን አንድ ወደሚሆንበት ሚስጥራዊ ወደሆነው ቦታ ኑ ፡፡ በአለም ብዙዎች ስኬትን ለማግኘት በኃይል ይታገላሉ፡፡ በእኔ መንፈሳዊ አለም ግን ራስን አሳልፎ መስጠት እንጂ የማግኘት ጉዳይ አይደለም፡፡ አለም ቅድስናን ለማግኘት ይሞክራል እናንተ ግን ለቅድስና ራሳችሁን አሳልፋችሁ መስጠት ነው ያለባችሁ፡፡ እናንተ መታገል ስታቆሙ እርሱ ይቆጣጠራችኋል፡፡”

“ይህንን እንዴት ነው የምናደርገው ብላችሁ ጠይቃችሁ? በአምልኮ ወደ እኔ ኑ፡፡ ከዚያም መዝሙሩ ከውስጣችሁ እንድትወጡ ያደርጋችኋል፡፡ ሁሉም ባይሆኑም ብዙዎቹ መዝሙሮች መጀመሪያ በመንግስተ ሰማይ እንደተጻፉ ለመሆኑ ታውቃላችሁ? የሙዚቃውን መሳሪያ እንኳን የሚመርጡት መዝሙሩን የሚያዘጋጁት ዘማሪ መላዕክት እንደሆኑስ? መሳሪያዎቹ በሰማይ ካሉት ድምጾች መካከል ናቸው፡፡ ከዛ እሩቅ ከሆነው ቦታ መጥተው እናንተን ከፍ ከፍ በማድረግ እሩቅ ወደሆነው ቤታችሁ ከእነርሱ ጋር ይውስዷችኋል፡፡ ይህን ያህል ቀላል ነው፡፡

“በእውነት የተቀቡት ዘማሪዎች የመዚቃቸው ምንጭና ከቅባቱ ጋር ያላቸው ትብብር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ በአግባቡ ያውቁታል፡፡ሁሉም ነገር ከቅባቱ ጋር የተጣበቀ እንደሆነ ያውቃሉ፡፡ እነዚህን ጣዕመ ዜማዎችና ቃላቶች ወደተጎዳና ከቆሻሻው አንስቶ ወደ ከፍታ ሊያወጣውና ሊለውጠው ወደሚፈልገው አለም እንዲደርስ የሚያደርግ የሚፈስ ጥልቅ የሆነ ወንዝ በውስጣቸው አለ፡፡

"ዘማሪያን የኔ ምርጦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሙሽሮቼ እኔን እንዲቀበሉ ስለሚያዘጋጁቸው ነው፡፡ አዎ ክሌር ምን እንደምታስቢ አውቃለሁ፡፡"

(ክሌር) ግን እኔ እኮ ምንም አላልኩም!!

(ኢየሱስ) ግን እኮ ተናግረሻል! በመንግስተ ሰማይ ኃሳብሽ በተለይም ባጉረመረምሽና ባልተረዳሽ ጊዜ እጅግ ከፍ ብሎ እንደሚሰማ አታውቂም? ፡፡ አሁን የሆነው እንደዚህ ነው፡፡

(ክሌር) እሺ ጌታ አንተ አምላክ ስለሆንክ ከሌሎች የበለጠ ምርጥ ሊኖርህ አይገባም፡፡ ዘማሪያን ያልሆኑትስ ሌሎቹ?

(ኢየሱስ) “ሁላችሁም ምርጦቼ ናችሁ፡፡ የተናገርኩትን እንደገና ግልፅ ላድርገው፡፡ . . . አየሽ የሰው ማንነቴ የማወቅ ፍላጎትሽን ለማርካት እንዴት እንደሚፈልግ?”

“ምርጡ ስጦታዬ መዝሙር ነው፡፡ ምክንያቱም ሙሽራዬን ከእርሷ እውቅና ውጪ ወደ ልቤ ውስጥ ስለሚያስገባት ነው፡፡ ከራስዋ ጥልቅ ይሰማታል፡፡ ነፍሷ ማለትም አብረን የምንኖርበት ቦታ ከሰማይ የሚላከውን የተቀባ መዝሙር ሲሰማ በደስታ ይዘላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ድምፆች ከትውልድ ቦታዋና በፍቅር ከተሞላው ልቤ የመጡ ስለሆኑ ነው፡፡

(ክሌር) ጌታ ለአሁኑ እንደምንም አመለጥክ!!

(ኢየሱስ) “ከጎበዞቹ ተምሬ ነው ክሌር!”

(ክሌር) ድንቅ!

(ኢየሱስ) “እሺ ትንሽ ተዝናንተናል አሁን ደግሞ እንቀጥል፡፡ እውነት ነው የኔ ውድ ፡፡ ሙዚቃ ነፍስን የሚያጓጓና ቀጥታ ወደ እጄ እንድትመጣ የሚጋብዛት መስህብ አለው፡፡

(ክሌር) "ዘ ሚሽን" በሚለው ፊልም ላይ ቄሱ ዋሽንት እየተጫወተ ጠላት የሆኑትን የአገሩን ተወላጆች ለማወቅ ፍላጎት ፈጥሮባቸው ወደ እሱ እንደጠራቸው ተዕይንት እንደ ማለት ነው? ያ ፊልም መጥፎው ቦታ ላይ እስከሚደርስ ድረስ የሰማይ ተምሳሌት ሆኖልኝ ነበር፡፡

(ኢየሱስ) ያ መዝሙር በመንግስተ ሰማይ ተጽፎ ለአቀናባሪው ተሰጥቶ እንደነበር ታውቂ ነበር?

(ክሌር) አቀናባሪው ግን በአለም አይደል እንዴ?

(ኢየሱስ) “ምንም ይሁን፡፡ መሰረቱ ከየት እንደሆነ ሳያውቁ የእኔን መዝሙሮች እሰጣቸዋለሁ፡፡ ዋናው ኃሳብ መዝሙሩ ለሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡”

(ክሌር) ግን እኮ ........

ኢየሱስም . . . “ሰይጣንም ሙዚቃዎችን ይሰጣል ማለትሽ ነው? አዎ በደምብ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን የእርሱ ሙዚቃዎች ከብጥብጥና ከኃጥያት ስለሚመነጩ ለሌላ ብጥብጥና ኃጥያት ይጋብዛሉ፡፡ ሙዚቃውን ሊሰሙ ከሚችሉ ነፍሶች ጋር ለመነጋገር ስፈልግ በአለም ላሉት ሙዚቀኞች የሚያነሳሳውን ሙዚቃ እሰጣቸዋለሁ፡፡ ባለፈው አትክልት ቤት ስትገቢ በመደነቅ ያስቆመሽ ሙዚቃ ዓይነት ማለት ነው፡፡ ፍቅር የማይዳከም ርዕስ ነው፡፡ እናም በትንሹ ቢስተካከል ትርጉሙ ከአለማዊነት ወደ ቅዱስነት ተቀይሮ ለሙሽራዬ ሊሆን ይችላል፡፡"

(ክሌር) በእርግጥም ልቤን የሚያላውሱ ጥቂት ሙዚቃዎች አጋጥመውኛል፡፡ ለምሳሌ 'ሌት ኢት ቢ ሚ' የሚለው ኢቨርሊይ ብራዘርስ በ 50ሳዎቹ ወይም 60ሳዎቹ የተጫወቱትን ዘፈን ብንወስድ ግጥሙም እንዲህ ይላል፡፡ አንተን ያገኘሁበትን ቀን ባረኳት ከአንተ ጋር መቆየት እፈልጋለሁ፡፡ እናም እኔ እንድሆን እለምንሃለሁ፡፡ መንግስተ ሰማያትን ከእኔ አትውሰድብኝ፡፡ እናም አሁንና ለዘላለም አንተ የምትጣበቀው ከአንድ ሰው ጋር ቢሆን እኔ ያንን ሰው ልሁን፡፡ ከአንተ ጋር በተገናኘሁ ቁጥር ፍቅርን ፤ የተሟላ ፍቅርን አገኛለሁ፡፡ ያላንተ ፍቅር ህይወት ምን ትርጉም አላት? ግጥሙ ይህ ነው፡፡ ጣዕመ ዜማው ደግሞ የሚያምር እና ከዚህ አለም ውጪ የሆነ ነው፡፡

(ኢየሱስ) "ያንን መዝሙር ለእኔ ስትዘምሪልኝ እንዴት ደስ ይለኛል መሰለሽ፡፡ ነገር ግን እናንተ ኃጥያትን በመስራት ስለተጠመዳችሁ ልቤ ሲመታ አትሰሙትም፡፡ ጊዜያችሁን ለእኔ በመዘመር ስትጠቀሙ ከልቤ ደስ ይለኛል፡፡ በሁለቱም አቅጣጫ እንደሚሰራ ታውቂያለሽ? ለእኔ ስትዘምሩልኝ እኔ ወደ እናንተ እቀርባለሁ እናንተም ወደ እኔ ትቀርባላችሁ፡፡ ስለዚህ እንሳሳባለን፡፡ ይህ በመንግስተ ሰማይ ስትመጡ በአግባቡ የምትረዱት ሚስጥር ይሆናል፡፡

“የዚህ ትምህርት ዋናው ኃሳብ ነገሮችን ሁሉ በመተውና ራስን በመልቀቅ ወደ ዕረፍቴ ስለመግባት ነው ፡፡ ዛሬ ድምጼን ከሰማችሁ ልባችሁን እንደ አመፀኞቹ አታደንድኑ፡፡"

“ሰምተው ያስመረሩት እነማን ነበሩ? በሙሴ ተመርተው ከግብጽ የወጡ ሁሉ አይደሉምን? አርባ ዓመትም የተቆጣባቸው እነማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ የወደቀ ፥ ኃጢአትን ያደረጉ እነርሱ አይደሉምን? ካልታዘዙትም በቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን፡፡

“እናም በተጓዳኝ ህዝቦቼን ከሃይማኖት በረሃና ከሰው ሰራሽ ህጎች እንዲወጡ እያደረኩ ነው፡፡ አንዳንዶች በዚህ ትምህርት ላይ ልባቸውን እያደነደኑ ነው፡፡ ይህም ደህንነታቸውንና ለመቆጣጠር ያላቸውን ስሜት ስጋት ላይ ጥሎታል፡፡ እናም በእውነቱ ከሆነ የሚመራው መንፈስ እንደ ኤልዛቤል መንፈስ(እባብ) የአመፃ መንፈስ ሲሆን ይህም መንፈስ የምልካቸውን ነብያቶች ሁሉ የሚቃወም መንፈስ ነው፡፡

"ስለዚህ ይህንን ክፉ መንፈስ የሚሰሙና ከእኔ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዲፈጥሩ የጠራኋቸውን ጥሪ በመቃወም ልባቸውን የሚያደነድኑ ፍሬ በማይገኝበት ደረቅ የህግ መፅሐፍትና የእምነት በረሃ ምክንያት ይጠወልጋሉ፡፡ ሁልጊዜ ይፈልጋሉ፣ ሁልጊዜ ይማራሉ ነገር ግን ወደ እውነት ሊመጡ አይችሉም፡፡ ልክ ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት እነዚህ ደግሞ እውነትን ይቃወማሉ።

<u>“ነገር ግን ክፉ ሰዎችና አታላዮች ፥ እያሳቱና እየሳቱ ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ፡፡ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር ፥ ከማን እንደተማርህው ታውቃለህና ፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን ፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል፡፡ የእግዚአብሔር ሰው ፍጽምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡</u>”(2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3፡13-17)

“ሙሽራዬ ወደጌታዋ ደስታ ስትገባ ወደ ዕረፍቴ ትገባለች፡፡ እናም ለምን ትገባለች? ምክንያቱም ስላመነች ነው፡፡”

"ያለ እምነት እኔን ደስ ማሰኘት አይቻልም፡፡ ወደ እኔ የሚመጣ እኔ እኔ እንደሆንኩና ለሚፈልጉኝ ዋጋ እንደምሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል።" (ወደ ዕብራውያን 11፡6)

"የአምልኮት መልክ አላቸው ነገር ግን አነቃቂ ከሆነው ክብርና በመገኘቴ ከሚመነጨው መታደስ የሚመጣውን ኃይሌን ግን ከደዋል፡፡"

“ይህ ቃል ከእኔ ጋር የጠለቀ ህብረት ማድረግ የተገባላችሁ የፍቅሬ መልክት ነው፡፡ በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እናም ሌላውን አይከተሉም፡፡ ስለዚህ ዛሬ ድምጼን ብትሰሙ ልባችሁን አታደንድኑ፡፡ ለእኔ ተገዙ፡፡ ጥረታችሁን ትታችሁ ወደ እኔ የፍቅር እጆች ኑ፡፡ እናም ወደ ዕረፍቴ ግቡ፡፡

"ይህንን መልዕክት ወደ ልባችሁ ላደረጋችሁ ሁሉ የድሮውን ትታችሁ አዲስ የሆነውን የፍቅሬን ወይን እንድትይዙ በአዲስ ቅባት እነበኛችኋለሁ፡፡ የልቤ ውዶች ወደ እኔ ኑ፡፡ ወደዚህ ኑና በእጄ ውስጥ ዕረፉ፡፡"

**ጊዜው አጭር ቢሆንም የተዘጋጃችሁ ግን አንዳንዶች ናችሁ / ኦክቶበር 28 ቀን 2015 ዓ.ም/**

**Time is short, some of you are ready / October 28, 2015**

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . " የኔ ውዶች ጊዜው በጣም አጭር ነው ፡፡ በቅርቡ ልወስዳችሁ እመጣለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቻችሁ አሁንም ዝግጁ አይደላችሁም፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ደግሜ ደግሜ ነግሬያችኋለሁ፡፡ በተለይም ኪወሲብ ስነ-ምግባር ጉድለት ራሳችሁን ጠብቁ፡፡ ነፍሳችሁን ወደ ገሃነም የሚያስገባ ኃጢያት መሆኑን ተረድታችኋል? ከኃጢያት መለየት አለባችሁ፡፡ በአለም የተማራችሁት የተሳሳተና ለገሃነም እሳት የሚያመቻች ትምህርት ነው፡፡ ይህንን በቀላሉ የምል ይመስላችኋል? አይደለም፡፡

"ህሊናችሁ ስርዓት ይዞ እንዲያድግ አልተደረገም፡፡ ከባል ወይም ከሚስት ውጪ የሚደረግ የወሲብ ግንኙነት ኃጥያት ነው፡፡ እናም የተወሰናችሁት አሁንም ይህንን ኃጥያት እየሰራችሁ ነው፡፡ እባካችሁ ይህንን ባህርይ ትታችሁ አካሄዳችሁን በቁም ነገር ከእኔ ጋር አድርጉ፡፡ ለሌላ ቀን አታስተላልፉት፡፡ በእውነት የምትወዱኝ ከሆነ ትታዘዙኛላችሁ፡፡ አሁኑኑ ከኃጥያት ተለዩ፡፡

"አዎን በቅርቡ ልመጣ ነው፡፡ አንዳንዶቻችሁ ተዘጋጅታችኋል፡፡ በእውነቱ ከሆነ አንዳንዶች ደግሞ ከሚገባው በላይ ዝግጁ ሆናችሁ ሌሎችንም በትክክል መሄድ እንዲችሉ እየቀረፃችኋቸው ትገኛላችሁ፡፡ ለእናንተ ጥሩ አድርጋችኋል እላለሁ፡፡ ብዙ ቢያስከፍላችሁም በቅድስና ጠንክራችሁ ስለተገነባችሁ ሌሎችም በምሳሌነታችሁ እየተከተሏችሁ ነው፡፡"

"ከእኔ ጋር ወደ ቤት እስክወስዳችሁ ድረስ ምንም ስለማያስተማምን አሁንም ንቁ ሆናችሁ ተጠባበቁ፡፡ የሰጠኋችሁን ለሌሎች እየሰጣችሁ ሌሎችንም በመምራት ቀጥሉ፡፡ እነርሱም የምታደርጉትን እየተመለከቱ እየተከተሏችሁ ነው፡፡ በዚህም ለመንግስቱ ፍሬን እያበዛችሁ ነው፡፡ እኔም በቅርብ ጊዜ 'ጥሩ ሰርታችኋል፡፡ ወደ ጌታችሁ ደስታ ግቡ' እላችኋለሁ፡፡

"ከእናንተ መካከለ አንዳንዶቻችሁ በመጨረሻው ከገንዘብና ከሰው ፍቅር  ነፃ ወጥታችኋል፡፡ አለምን በመናቅ እያደጋችሁ ነው፡፡ እኔም ለመንግስተ ሰማያት እያዘጋጀኋችሁ ነው፡፡ ባህሪያችሁ ላይ ያለው ለውጥ የማይታይ እንዳይመስላችሁ፡፡ ለውጡ እየታየ ነው፡፡ በተለይም በዘመዶቻችሁ ለውጡ ግልፅ ሆኖ እየታየ ስለሆነ 'ምናልባት በህይወታችን እግዚአብሔር አለ የሚሉት ልክ ሊሆን ይችላል' በማለት እያደነቁ ነው፡፡ አዎ ብርሃናችሁ እያበራ ሰዎችን ሁሉ ወደ እኔ እየሳበ ነው፡፡

"ጥሩ አድርጋችኋል፡፡ በጥሩ ውሳኔያችሁ ፀንታችሁ ቁሙ፡፡ ወደ ኋላ ለመመለስ ለራሳችሁ ፈቃድ አትስጡ፡፡ የቀረው ትንሽ ጊዜ ስለሆነ ጥሩውን በመያዝ የልባችሁን የአትክልት ሥፍራ አረሙን በመንቀል ቀጥሉ፡፡ በእኔ መንግስት ውስጥ የሚጠብቃችሁ ትልቅ ሽልማት አለ፡፡

"አንዳንዶቻችሁ በአልጋችሁ ላይ ታማችሁ ተኝታችሁ እያለ ለእኔና ለሰው ልጅ ያላችሁ ፍቅር እያቃጠላችሁ ነው፡፡ እንዲህም በመሆኑ ነፍሳትን በማዳን ስራ ላይ የተሻለ ሚና ባለመጫወታችሁ በየቀኑ ኃዘን ላይ ናችሁ፡፡ ከመፀለይ የበለጠ የተሻለ ሚና ግን የለም፡፡ በመሪው ዋና ሥፍራ ላይ ስለሆናችሁ አለምን በሙሉ ከጥግ እስከ ጥግ ድረስ በፀሎታችሁ መድረስ

ትችላላችሁ፡፡ አንዱ ጥግ ላይ በወንጌል ሥራ ላይ ብትሰማሩ ግን ዋናው ቦታ የሆናችሁትን ያህል ተፅእኖ ማምጣት አትችሉም፡፡ ከዚህ የበለጠ የላቀ ቦታ አለን? ከማላጅነት የበለጠ ቦታ በፍፁም የለም፡፡ ምክንያቱም ፀሎታችሁ የታሪክን አካሄድ ይቀርፃልና፡፡”

“ለእናንተ እንዲህ እላለሁ፡፡ በሰማይ ያለው ሽልማታችሁ ከምታስቡት በላይ ነው፡፡ ራስን ባለመውደድ ለእኔና ለፈቃዴ ያላችሁ ታማኝነት ጓደኛዬና ሙሽራዬ እንድትሆኑ አድርጓችኋል፡፡ ጠላት ታማችኋልና ምንም ጥቅም የላችሁም ብሎ እንዲደብቃችሁ አትፍቀዱለት፡፡ ከመወለዳችሁ በፊት ይህ በሽታ የሚፈጠርበትን ጊዜ እንደማውቅ እንዲሁም በሚያስፈልገው ክፍት ቦታ ላይ ከእኔ ጋር ቆማችሁ ለእነዚህ ነፍሳት እንደምትማልዱ ገና ዱሮ እንደማውቅ ተረዱ፡፡ በሰው ልጆች ብትጠሉና ዝቅ ተደርጋችሁ ብትታዩም በእኔ ዘንድ ግን ክብር አላችሁ፡፡

“ለአገልጋዮቼ በሙሉ እንዲህ እላለሁ ለሚመጣው እሳት እጃችሁን ለሥራ አዘጋጁ፡፡ አዎ በህዝቤ ላይ የመንፈስ ቅዱስን እሳት አዘንባለሁ፡፡ እናም ለአለም ሁሉ ምስክር ይሆናሉ፡፡ እሳቱን ተቀበሉና ሙቁት፡፡ ነበልባሉንም እያራገባችሁ አቀጣጥሉትና ብርሃናችሁ ይውጣ፡፡ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚታይ የክብሬ ነጸብራቅ በእናንተ ላይ ይሁን፡፡

“ጠላት ነበልባሉን ሊያጠፋ በተስፋ መቁረጥ ሊያጠቃችሁ ቢሞክርም ለአለም በሙሉ የክብሬ ነጸብራቅ መሆናችሁን ቀጥሉ፡፡ ትንሽነታችሁ ጥንካሬያችሁ ነው፡፡ ትንሽነታችሁ የተጎዱትን፣ የተፈናቀሉትንና የሚያስፈልጋቸውን ወደ እናንተ ይስባል፡፡ ዝቅ አድርገው የሚመለከቷቸውን ሃብታምና ታዋቂ ሰዎችን አብሮነት ባይፈልጉትም ራስ ወዳድ ያልሆኑትንና እኔን ብቻ የሚገልፁትን ሰዎች ህብረት ግን ይፈልጋሉ፡፡

“ይህ አገልግሎት ለአካሌ የሚያስፈልግ ነው፡፡ ሆኖም ግን እጅግ ብዙዎች ራሳቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን ቀዳሚ አድርገው ቢቆጥሩም እነርሱ ግን የመጨረሻ ናቸው፡፡ ኃይሌ ፍፁም የሚሆነው በድካማችሁ ስለሆነ ትንሽነታችሁን አትናቁ፡፡

በዕለቱ ማብቂያ ሁላችሁም ነፍሳችሁ እረፍት ወደምታገኝበት ወደ እጆቼ ኑ፡፡ ለእናንተ ቅባትን የማካፍልባት ያችን ሰዓት ለሁልጊዜ እየተጠባበቅሁ ነው፡፡ በቀን ውስጥ አብረን የምንሆንበት ጊዜ ስለሌለ ይህ እንዲሆን በጉጉት እየተጠባበቅሁ ነው፡፡ ወደ እኔ ኑ!!!!

## ኢየሱስ "ኑ ወደ እኔ" እያለ ይጣራል / ማርች 14 ቀን 2016 ዓ.ም
## Why temptations & hope for you who are lost / March 14, 2016

ኢየሱስ እንዲህ ይላል . . . “አሁን የምናገረው ለጠፋችሁት ነው፡፡ ጠላቶቻችሁን በመፍራት መኖር የለባችሁም፡፡ ህይወታችሁን ለእኔ ብትሰጡኝ እኔ እጠብቃችኋለሁ፡፡ እናንተን የሚጠብቁ መላዕክቶችን እመድባለሁ፡፡ ለእኔ ጊዜ ከሰጣችሁኝ በየቀኑ እያገኘኋችሁ እመራችኋለሁ፡፡ በመንገዳችሁ ሁሉ እጠብቃችኋለሁ፡፡ ያልተጠበቁ እቅዶችን በእናንተ ላይ አደርጋለሁ፡፡ መልካም የሆኑ፣ ያልተጠበቁና እናንተ እንዳላችሁ የማታውቋቸውን ስጦታዎችን፣ አስደናቂ ነገሮችንና ጥሪዎችን አደርጋለሁ፡፡ እነዚህም ነገሮች የማያልቅ የደስታና የሙላት ምንጮች ይሆኑላችኋል፡፡ ጠላት ተስፋ እንድትቆርጡና በቁጣ የተሞላ አኗኗር እንድትኖሩ ለማድረግ እነዚህን ነገሮች ከልክሏችሁ ነበር፡፡

“ይህ የአኗኗር ዘዴ ምንም ያህል አስፈላጊ መስሎ ቢታያችሁም ባዶና ዘላለማዊ የሆነ ሽልማት የሌለው ነው፡፡ እንዳውም የባሰ ቁጣን፣ ህመምን፣ መራራነትንና ሞትን ያስከትላል፡፡ ዋና የህይወት ጉዳይ የሆነውን የፍቅር ፍላጎታችሁን በምንም መልኩ አያሟላም፡፡

“ስለእናንተ ሁሉንም ነገር ባውቅም አሁንም እወዳችኋለሁ፡፡ ደግሞም  ከእኔ ጋር በመንግስተ ሰማይ እንድትኖሩ አሁንም እፈልጋለሁ፡፡ ህይወታችሁ ምን ያህል ጨለማና ከፉ እንደሆነባችሁ አውቃለሁ፡፡ነገር ግን በእኔ ውስጥ መኖሪያ እንደምታገኙ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ ከእኔ ጋር መኖር፣ በየቀኑ አዳዲስ እድሎች የሚገኙበት፣ እያንዳንዱ ወር በእድገት የተሞላና እያንዳንዱ ዓመት ደግሞ የበለጠ ደስታን የሚያመነጭበት ህይወት ነው፡፡

“ይህ የሚሆነው ግን ህይወታችሁን ሙሉ የተከተላችሁትን ከፉ መንገድ ትታችሁ ለዚህ ኑሮ ጀርባችሁን በመስጠት ወደ እኔ መጥታችሁ ህይወታችሁን ስትሰጡኝ ነው፡፡ እጃችሁን ይዤ በድል ጎዳና እመራችኋለሁ፡፡ ሁሌ ሲያሸንፋችሁ የነበረውን ነገር አሁን ታሸንፉታላችሁ፡፡ በፊተኛው ኑሯችሁ ዕለት በዕለት ተስፋ የሚያስቆርጣችሁን፣ እስራት፣ጭቆናና ጨለማ የሞላው ህይወታችሁ በትርጉምና በዓላማ ይሞላል፡፡

“ልጆቼ የመጣሁት ልታደጋችሁ ነው፡፡ የመጣሁት የኖራችሁበትን የእስራት ቀንበር ለመስበር ነው፡፡ የመጣሁት ቁጥር በሌለው መመታት የቆሰለውን ልባችሁን ልፈውስ ነው፡፡ መጠላትና መናቅ እንዴት እንደሚሰማ አውቃለሁ፡፡ ለሞት የሚያደርስ መደብደብንም አውቃለሁ፡፡ ጥሩ በምታስቡላቸው ሰዎች ፊታችሁን መረገጥንም አይቼዋለሁ፡፡ ከልክ ያለፉ እነዚህን መከራዎች ሁሉ ያሸነፍኩት በፍቅር ነው፡፡ በፍቅር እንድታሸንፉ የፍቅርን ኃይል አስታጥቃችኋለሁ፡፡

“ያለፈውን ምሬትንና ነቀፋን አስወግጄ ካባን እደርብላችኋለሁ፣ ለጣታችሁም ቀለበት አደርግላችኋለሁ፡፡ እኔ የመጣሁት ስትወለዱ ጀምሮ የተሰረቀባችሁን ህይወታችሁን ልመልስ ነው፡፡ መሆን እንችላለን ብላችሁ ወደማታውቁት ማንነት እመልሳችኋለሁ፡፡ ነፃ አወጣችኋለሁ!! ደግሞም ጥበቃ አድርጌላችሁ ከእኔ ጋር ወደ መንግስተ ሰማያት እወስዳችኋለሁ፡፡

“እናንተ ማድረግ የሚጠበቅባችሁ ወደ እኔ የፍቅር እጆች ዘራችሁ 'እሺ ጌታዬ ዛሬ ባለሁበት ሁኔታ ህይወቴን እሰጥሃለሁ፡፡ ዛሬ ነፍሴን ለአንተ አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡ እስከዛሬ ለኖርኩት የከፋት ኑሮ ይቅር በለኝ፡፡ ሌሎችንም የበደልኩትን ይቅር በለኝ፡፡ እኔንም የበደሉኝን ይቅር እንድላቸው እርዳኝ፡፡ ኢየሱስ ወደ ልቤ ግባና ይህንን ግራ የተጋባ ህይወቴን ተቆጣጠር፡፡ ለአንተ አሳልፌ እሰጥሃለሁ፡፡'"ማለት ብቻ ነው፡፡

“ልጆቼ ይህንን ከልባችሁ በሉ፡፡ ከዚያም አቅፌ ክብር ወዳለው ወደ አዲሱ የወደፊት ኑሮአችሁ እወስዳችኋለሁ፡፡ እኔ ይህንን ቃል እገባላችኋለሁ እናንተ ህይወታችሁን ስጡኝና የእኔን ተስፋ እሰጣችኋለሁ፡፡በልባችሁ ያለውን እውርነትና ስለታሙን ምሬት አስወግዳለሁ፡፡ እነዚህን ቁስሎች ፈውሼ ከጠላቶቻችሁ በላይ አቆማችኋለሁ፡፡ የድሮዎቹን ሰይጣኖች ታሸንፉና ታስወግዷቸዋላችሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ የእነሱ ሸብር አያስደነግጣችሁም፡፡

“ኑ እጄን ያዙ፡፡ ኑ አሁን የእኔ ናችሁ፡፡ ኑ አንድ ላይ በመያያዝ ካለፈው እስራት ወጥተን የክብር ብርሃን ወደሚያበራው አዲስ ቀን እንሂድ . . . ኑ፡፡”

## ያሳለፋችሁት ህይወት አልባከነም/ ማርች 23 ቀን 2016 ዓ.ም

## Your Lives Have Not Been Wasted/ March 23, 2016

ክሌር ፡- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጣፋጭ የሆነው ሰላሙና ጥበቡ ከእናንተ ጋር ይሁን።

ጌታ ዛሬ ከሰይጣን በመቅደም ራሳችንን ከጠላት ውሸቶች እንዴት መጠበቅ እንዳለብን የሚያስችለንን አንድ መልዕክት ሰጥቶኛል። ይህም የሚገኘው በመልእክቱ ማብቂያ አካባቢ ነው።

ወደ ፀሎት በገባሁበት በዛው ቅጽበት ጌታና እኔ ለስለስ ባለ ብርሃን ባለው የዳንስ ሥፍራ ላይ ነበርን። ብቻችንን ሆነን "የሚያምር" በሚለው የካሪ ጃብ የአምልኮ መዝሙር እየተወዛወዝን ነበር፡፡ ይህ መዝሙር አምልኮአዊ በሆነ የቅርብ ግንኙነት እጅግ ድንቅ ነው። እኔም የሠርግ ቀሚሴን ለብሼ ነበር፡፡ ጣፋጭ ካቆምኩ ጀምሮ ለሁለተኛ ጊዜ ከጌታ ውብ ከሆነው ልቡ ጋር ተገናኘሁ፡፡ ጣፋጭ የተውኩት ሙሉ ለሙሉ መፆም ስለማልችል ለጌታ እንደ ስጦታ ለመስጠት አስቤ ነው፡፡ የነበረው ሁኔታ ከማመሩ የተነሳ አስደመመኝ። ወደ ፀሎት ስገባና ማምለክ ስጀምር ወደእሱ እንደሳበኝ ተሰማኝ። ጣፋጭ፣ ሃይለኛና የተቀባ ነበር።

አይን ለአይን ስንተያይ ከመሬት በመንሳፈፍ መንግስተ ሰማያዊ ወደሆነው ማንነቱ እንደመግባት ያህል ይሰማኛል። የሚገርምና ደስ የሚል ስሜት ነበር። እግዚአብሔር ለእኔ ባለው ፍቅር መንፈሴ በመማረኩ የደስታ እምባዎች በጉንጮቼ ላይ ይወርዱ ነበር።

ከጌታ ጋር ሆኜ ስወዛወዝ የነበረኝ ስሜት እኔና ህዝቅኤል እንደምንደንሰው አይነት ሐምሳያ ነበረው፡፡ እናም ለእራሴ እንዲህ አልኩ "ይህንን ስሜት የማውቀው ስሜት ነው፡፡ በዚን ጊዜ የነበረኝ ስሜት ልክ ባሌ ንፁህ በሆነ ልቡ ሲያቅፈኝ የሚሰማኝ አይነት ስሜት ነበር የሚሰማኝ ።"

ኢየሱስም እንዲህ በማለት መለሰልኝ " አዎ ልክ እሱ እንደሚወድሽ እኔም እወድሻለሁ፡፡"

ክሌር ፡- እናም ይህንን በደንብ አሰላሰልኩት ፡፡ ባለቤቴ በጣም መልካምና አፍቃሪ ወንድ ነው። እናም እሱ የሚወደኝን ያህል ማንም በንፁህ ልብ ወዶኝ አያውቅም። እንዳውም ከሚገባኝ በላይ ይወደኛል ማለት እችላለሁ (እንደዚህ የሚባል ነገር ካለ ማለት ነው)። ያለማቋረጥ ይንከባከባኛል፣ ከእኔ ጋር አብሮኝ ለመሆን ይፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ስንፀልይ ወይንም አብረን ራት ስንበላ አብረን እንደምንሆነው አይነት ማለቴ ነው። እርሱ ያለው ጥልቅ የሆነ አክብሮት እንጂ ምንም አይነት ወሲባዊ ፍላጐት ያለበት አይደለም። ይህ በነፍሳችን ውስጥ እርስ በርስ የሚሰማንን አስደናቂ ፍቅር ምስጋናና እውቅና የመስጫ መንገድ ነው፡፡

እናም ዛሬ ማታ ከጌታ ጋር የተሰማኝ ይህ ንፁህ ፍቅር ነው። ጌታም እንዲህ ብሎ አረጋገጠልኝ " አዎ ህዝቅኤል እንደሚያፈቅርሽ እኔም አፈቅርሻለሁ፡፡ እኔ በእርሱ ውስጥ እኖራለሁ ይህ ይሰማሻል?"

"አዎ እኔ በህዝቅኤል ውስጥ መገኘቴ ነው እንዲያፈቅርሽ የሚያደርገው። በተመሳሳይ መልኩ ለእሱም የዚህ አይነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርገው የእኔ በውስጥሽ መገኘት ነው። ጋብቻ እንዲሆን የምፈልገው እንደዚህ ነበር። ለዚህም ነው ትክክለኛውን ሰው ማግባት ያለባችሁ፡፡ ምክንያቱም እድሜ እየጨመረ ሲሄድ የወሲብ ፍላጐት ይቀንስና በአንፃሩ ልብ

የሚማርክና የተቀደሰ ፍቅር እየጨመረ ይሄዳል። ይህም የሆነው በመጨረሻዎቹ አድሜዎቻችሁ ላይ ስትሆኑ የፍቅርን ምርጥ የሆኑትን ወርድና ስፋቶች (dimensions) እንድታጣጥሙ በማስፈለጉ ነው፡፡"

ከሌር ፦ ጌታ ሆይ ሌሊቱን ሙሉ እንደዚህ ማሳለፍ እችላለሁ፡፡

ጌታም "እኔም እችላለሁ" ብሎ መለሰልኝ "ዛሬ ማታ እንግዲህ ለአንቺ ያለኝን ፍቅር በትንሹ እንኳን ቢሆን መመልከት ችለሻል፡፡ አይደል?"

ከሌር፦ አዎ ጌታ በድጋሜ እየተሰማኝ ነው።

ኢየሱስም ቀጠለ ፦ "ጊዜያችን በጣም ቅርብ ነው፣ የኔ ውድ እጅግ ቅርብ። እናም እያንዳንዱን ቃል የገባሁልሽን እፈፅማለሁ። ከአንቺ የሚጠበቀው አሁንም እጅሽን በማረሻው ላይ በማድረግ ዘርችን ለማግኘት ማረስ መቀጠል ነው። ከዚህም በኋላ የአዝመራ ጊዜ ይመጣል። ለጊዜው ግን በእርሻው ማሳ ላይ እየሰራሽ ቀጥዪ። እናም ተጨማሪ አሳዎችን እያጠመድሽ ነው፡፡ እመኚኝ በዚህ ቻናል የተነሳ ብዙ አስደናቂ ነፍሳትን ማጥመድ ተችሏል። ቢሆንም ግን አንቺ ከሄድሽ በኋላ ካለው ብዛት ጋር ሲወዳደር አይገናኝም። በዚን ጊዜ ከፍታው ላይ ይደርስና ይፈነዳል።

"ምንም ያህል ተቃውሞዎች ቢሰነዘሩብሽም ትክክለኛው መንገድ ላይ መሆንሽን ላረጋግጥልሽ እፈልጋለሁ።"

ከሌር ፦ ጌታ ዛሬ በሃሳብህ ውስጥ ያለው ምንድነው?

"እንግዲህ መናገር የምፈልገው እየመጣ ስላለው የነፍሳት አዝመራ ወቅት ነው። በዚህ ቻናል ላይ ላሉት ሙሽሮቼ ሁሉ አንድ ነገር ላረጋግጥላቸው እፈልጋለሁ። ይህም በምድር የዘሩት ዘር ሁሉ በጣም ብዙ አጭደው ይሰበስባሉ፡፡ የቅድስና ህይወታችሁ በሚያውቋችሁ ሰዎች ላይ ያለውን ውጤት ለመናገር ያህል በጣም ትደነግጣላችሁ ብላችሁ ይበቃል። ኢየሱስ 'በእኔ አሳዛኝና ትንሽ ህይወት ይህንን ሁሉ ሠራህ?" ትላላችሁ።"

"ስቃይ፣ ጭንቀትና እንግልት፣ እንዲሁም ተስፋ መቁረጥ እየቀጠለ በመሄዱ ምክንያት ውይይቶች ይቀጣጠላሉ። በዚህም ለውይይት የተዘጋጁን ነፍሳት ሊያበራ እየጠበቀ ያለ ትልቅ ቅባት አለ፡፡ ዘይትን ለማምረት የሚጠቅሙ እርሻዎችን አስቢያቸው። ገበሬዎቹ ለመኖር የሚያበቃቸውን ያህል ዘር ለማብቀል እጅግ ከባድ ጊዜ ገጥሟቸው ነበር። እናም አንድ ቀን ጥቁር ፈሳሽ ነገር ከመሬት ውስጥ ፈለቀ። በመጀመሪያ ዝም ብሎ የማይረባ ነገር ይመስል ነበር፡፡ ነገር ግን ምርመራ ሲካሄድ እንደ ንፁህ ጥቁር ወርቅ የሚታይ ሆነ፡፡

"ህዝቅኤል በህልሙ በተራራው ላይ ስላየው ርስት ታስታውሻለሽ ? "

ከሌር፦ ከአፈሩ በታች የከበረ ድንጋዩች የነበሩበትና አንድ ነገር ስንፈልግ አፈሩን በመጥረግ ዋጋ ያለው እንቁ ማውጣት ብቻ የሚያስፈልገውን ማለትህ ነው?

"አዎን እሱኛው ህልም፡፡ በዛን ጊዜ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አታውቂም ነበር። አሁን ግን ታውቃላችሁ። በዛ ተራራ ላይ የተሰቃያችሁትና ያጋጠማችሁ ነገር ሁሉ ለእኔ ስጦታ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ፍሬ እያፈራ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ህይወታቸውን ለእኔ አሳልፈው ሰጥተው አሁን ባዶ መስሎ ቢታያቸውም በትልቁ መከር ጊዜ ማበባቸውን ያውቃሉ።

"ለዚህ ነው ውጤቶችን እንዳትመለከቺና ለእኔ ብቻ ታማኝ በመሆን እንድትሰሪ በልብሽ ስታውቂ የሰጠሁሽን ሥራዎች እንድትሰሪያቸው ያስተማርኩሽ፡፡ በዚህ አለም ላይ ውጤትንና ሽልማትን የሚፈልጉ ሰዎች በቀላሉ ተስፋ ይቆርጣሉ። ነገር ግን እኔን በማስደሰትና የእኔን ፈቃድ በመፈፀም የሚገኘውን ሽልማት የሚፈልጉ ግን ከህይወታቸው የተነሳ የተነቃቁ ነፍሳት አዝመራ ሲሰበሰብ ሽልማታቸው ይበዛል፡፡ የሰማዕታት ደም የቤተ ክርስቲያን ዘር ነው አልተባለምን?

" ብዙዎች በጣም ብዙዎች በመልካሙ እምነታቸው ምክንያት ሰማዕታት ሆነዋል፡፡ መሥዋዕቶቻቸው ምን ውጤት እንዳስገኘ አላዩም ፡፡ ሁላችሁንም ልነግራችሁ የምፈልገው ምንም እንኳን የተሰበሰበ መከርን ባታዩም ህይወታችሁ በከንቱ አላለፈም ፡፡ ይህንን በመጨረሻው ታዩታላችሁ፡፡ በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ተራ የሆኑ፣ እውቅና ያልተሰጣቸውና የሚጸልዩ የቤት  እመቤቶች እና ወንዶች ጸሎቶቻቸው ምን እንዳከናወኑ እና በመንግሥተ ሰማይ የምሰጣቸውን ሥፍራ ሲመለከቱ በደስታ አብረው ይሆናሉ። በሰጠኋቸው ነገሮች የታመኑ እነዚያ ፍፁም 'ከዚህ ዓለም ውጪ' የሆነ እድገትን ያገኛሉ ፡፡ አዎ  ለእኔ በሥራ የደከሙ ሁሉ አንድ ላይ በመሆን ደስታቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡

"ይህንን ምድር ለቃችሁ የምትሄዱበት ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ አንዳችሁም ሕይወቴ ዋጋ ቢስ ነበር በሚል ተስፋ እንድትቆርጥ አልፈልግም ፡፡ ታላቅ ወንጌላዊ ወይም ታዋቂ ፓስተር ስላልሆናችሁ ብቻ በፍሬ የተሞላ የአትክልት ቦታ የላችሁም ማለት አይደለም ፡፡ እንዲገባችሁ የሚያስፈልገው ነገር ትልቅ መከር ለሚያፈሩ ሰዎች ዋነኛው የእናንተ ፀሎት እንደሆነ ነው፡፡

"ቢሊ ግራሃም ያዘጋጀው አይነት መነቃቃት ያለበት ጉባኤ ስትሳተፉ እና አንድ ወጣት ወደ መድረኩ በመሄድ እኔን ሲቀበል ስትመለከቱ ፣ ወጣቱን ወደ መንግስቴ ያመጣው የእናቱ ፀሎት እንጂ ቢሊ ግራሃም አለመሆኑን እወቁ። ቢሊ ግራሃምም ቢሆን ቅብዓቱን ያገኘው በሌሎች ጸሎት አማካኝነት ነው። እናም እርሱ የተቀባው መረቡን ለመዘርጋት ነው።  ነገር ግን በትክክለኛው ጊዜ ወደ መረቡ እንዲገቡ የሚያደርጋቸው በታላቁ ውቅያኖስ ውስጥ ያለው ሞገድ ይህም የተደረጉ ፀሎቶችና ምልጃዎች ናቸው።  በዚህ ምድር ላይ ግን ይህ በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክለኛ ግንዛቤ የለም፡፡ ነገር ግን በመንግሥቴ ውስጥ በቀላሉ ይታወቃል።

"ለዚህ ነው መንግስተ ሰማይን ሊጎበኙ የመጡ ሰዎች ብዙ ተራ ሰዎች ታላላቅ የሥልጣን ቦታ ላይ ሲያይዋቸው የሚደነቁት ፡፡ የሙሽሮቼን ልብ ስመለከት የእኔን ልብ ወደሚመስል ሲቀየር ተመልክቻለሁ፡፡ ቁስላቸውን፣ መናቃቸውን፣ የደረሰባቸውን ተቃውሞና ይቅርታ አድራጊ መሆናቸውንና በዚህም ልባቸው  እጅግ የኔን እንደመሰለ ተመልክቻለሁ። ብዙዎች የሚፈልጉት ንግስትን ነው፡፡ እኔ የምፈልገው ግን አገልጋይን ነው፡፡ እኔ ንጉሥ ብሆንም የመጣሁት ግን እንደ አገልጋይ ሆኜ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙሽራዬቱ  ሙሽራውን መምሰል ያለባት።

"ዝና እና ተፅዕኖ አድራጊነት ወደ መንግስተ ሰማይ ያስገቡናል ብላችሁ አታስቡ። በጭራሽ እነዚህ  ሁሉ ከማንነታችሁ ይነሱና በእናንተ ላይ የሚቀረው ለሚያስፈልጋቸው ያደረጋችሁት ደግነት እና ፀሎቶች ናቸው፡፡ ለእኔ ካላችሁ ፍቅር የተነሳ የምታደርጓቸው መስዋቶች ሁሉ እንደ እኩለ ቀን ፀሐይ ያበራሉ፡፡ በእናንተ ላይ ከሚያርፈው ትልቅ ክብር የተነሳ በምድር የሚኖር አንድ ሰው ሊያያችሁ የሚችለው በታላቅ ችግር ነው። ይህ ምንም እውቅና ለሌላቸውና የውስጥ ፍላጎታቸው ፍቅር ብቻ ለሆነ የምሰጠው ልዩ ሽልማት ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች የምነግራችሁ እናንተን ለማበረታታት እና ለማጠንከር ነው፡፡ እንደነገርኳችሁ በመጪዎቹ ጊዜያት በእናንተ ላይ፣ በእምነታችሁ ላይና በእኔ ላይ ባላችሁ እምነትና ተስፋ ምክንያት ብዙ ጥቃት ይደርስባችኋል፡፡

“ይህንን መልዕክት ሁልጊዜ አስታወሱ ደግሞም ቅርብ ሥፍራ አስቀምጡት። ምክንያቱም ወደእኔ ከመምጣታችሁ በፊት ተስፋ እንድትቆርጥ ሊያደርጓችሁ የሚሞክሩ እሳት የያዙ የጠላት ቀስቶችን ለመከላከል ስለሚረዳችሁ ነው፡፡ ብዙዎቻችሁ ደካሞች ስለሆናችሁ ይህ የማፅናኛ መልዕክት ያስፈልጋችኋል፡፡ ይህንን አጥብቃችሁ ያዙና ፈታኝ ሁኔታ ሲያጋጥማችሁ አንብቡት። በዚህ ቻናል ላይ ያላችሁና ለበርካታ አስርት አመታት ፍላጎቴን በማስፈፀም ተግባር ላይ ያላችሁ አላችሁ። ጠላት ግን ይህ እንዳልሆነ አሳምኗችኋል፡፡ እናም አሁን እድሜያችሁ እየገፋ ሲሄድ ህይወታችሁን ተመልሳችሁ ስትመለከቱት ፍሬ አልባ መስሏችኋል። ነገር ግን በጣም ተሳስታችኋል! ምንም እንኳን በአገልግሎት ውስጥ ብትደናቀፉም፣ በጎ ፈቃዳችሁና ለእኔ ያላችሁ ታማኝነት በሺዎች የሚቆጠሩ ነፍሳትን አስገኝቶላችኋል። አዎ በሺ የሚቆጠሩ ነፍሳት፡፡ ይህንን ወደፊት አይታችሁ እጅግ ደስ ይላችኋል።

“ለማጠቃለል ምንም ነገር እንዲያስፈራራችሁ ወይም ተስፋ እንዲያስቆርጣችሁ ወይም ህይወታችሁ እንዲነቀፍ አትፍቀዱ ፡፡ በሙሉ ልባችሁ የምትወዱኝ ከሆነ የደረሰባችሁን መከራ ሁሉ መንግስቴን በነፍሳት ለመሙላት ተጠቅሜበታለሁ ፡፡ ስለዚህም በውድቀቶቻችሁ እንኳን ተደሰቱ። እነዚህ ነገሮች ለእኔ ምን እንዳከናወኑ እስከምታዩ ድረስ ጠብቁ!”

## የክስተቶች ቅደም ተከተል / ኤፕሪል 8 ቀን 2016 ዓ.ም

## Jesus Speaks on Order of Events / April 8, 2016

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች . . .ኸርት ዱዌለርስ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ብርታትና ጥበብ ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡

ዛሬ ማታ አንድ መልዕክት ትኩረቴን ስቦት ነበር፡፡ ይህም ስለ አስተሮይድ የተነገረ አንድ ትንቢት ሰምቼ ነው፡፡ ነገር ግን ጌታ ስለዚህ ጉዳይ ዘርዘር ባለ መልኩ የተናገረኝ ነገር አልነበረም፡፡ እንዲሁም በቅርብ ሊፈፀሙ ያሉ ነገሮችን መቼ እንደሚሆኑ ጊዜውን አልነገረኝም ነበር፡፡ ስለዚህም ባልተገባ መልኩ ትንሽ ግራ ተጋብቼ ነበር፡፡

እናም ወደ ጌታ ቀርቤ እንዲህ አልኩት፡፡ ጌታ ሆይ ስለዚህ ጉዳይ እንዴት እንደማደርግ አላውቅም፣ ግራ ገብቶኛል፡፡ይህ መልዕክት እኛ ለማወቅ በመጓጓት ፈልገነው የሰማነው ጉዳይ ሳይሆን መልዕክቱ እኛ እንድንሰማው የተደረገ ነው፡፡ ደግሞም አንተ ልታስተላልፍ የፈለከውን መልዕክት ሁሉንም በአንድ ሰው በኩል ሳይሆን በተለያዩ ነቢያቶችህ በኩል እንደምታስተላልፍ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም ምን ማሰብ እንዳለብኝ አላውቅም፡፡

ጌታም ለዚህ ነገር ቶሎ ነው መልስ የሰጠኝ፡፡ እንዲህ በማለት "ይህንን ነገር ላብራራልሽ ትፈልጊያለሽ? ይህ ለማውራት የማልፈልገው ርዕስ ቢሆንም ህዝቤ ግን ግራ ተጋብቶት ማየት አልፈልግም፡፡"

"እርግጥ ነው ኮሜት ፖርት ሪኮን ይመታል፡፡ በዚህም አደጋ ሚሊዮኖች ይገደላሉ፡፡ ለዚህም ልቤ በጥልቅ ኃዘን ውስጥ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ከንጥቀት በፊት ነው፡፡"

(ክሌር) ከንጥቀት በፊት?

(ኢየሱስ) "አዎን ያንን ህልም ለምን የላኩብሽ ይመስልሻል?"

(ከሌር)- ጌታ የሚናገረው ከዓመት በፊት አንድ ሰው ያየውን ህልም ነው፡፡ ይህንን ህልምና ሌሎችንም ጌታ የገለጠልኝን መልዕክቶች ለማገናዘብና ለማቀናበር ተስኖኝ ስለነበር ነው ጌታ ቅደም ተከተሉን እስኪነግረኝ እየጠበኩ ያለሁት፡፡

የህልሙ ይዘት ይህንን ይመስላል፡፡ እኔ ከቤተሰቤ ጋር በሰሜን ካሊፎርኒያ እቤታችን ውስጥ ነበርን፡፡ በጊዜውም በጣም ጭንቀት ላይ ነበርን፡፡ በጣም ብዙ የሚያስፈሩና ብዙ  የአደጋ ጊዜዎችን አገራችን (አሜሪካ) አሳልፋለች፡፡ እናም እነዚህን ጊዚያቶችን ተቋቁመን አሳልፈናል፡፡ ነገር ግን አሁን እየተከሰተ ያለው ነገር አንድ ነገር ከምስራቅ አቅጣጫ ወደ እኛ እየመጣ ያለ ሲሆን ይህም ከአቅማችን በላይ በመሆኑ በህይወት ለመኖር የማንችልበት ደረጃ ላይ ስለደረሰን በህይወት ለመኖር የቀረን ጊዜ በጣም ጥቂት ሴኮንዶች ብቻ ነበሩ፡፡

ባለቤቴንና ሁለት ታዳጊ ህፃናቶቹን አየኋቸውና ኢየሱስ ወደ እርሱ ለመሄድ ዝግጁ እንዲያደርገን እንፀልይ አልኳቸው፡፡ ሁላችንም አንገቶቻችንን ዝቅ አደረግንና እኔ መፀለይ ጀመርኩ፣ "ኢየሱስ እባክህ ከአንተን ጋር እንድንገናኝ ዝግጁ አድርገን"፡፡ በዚህም ጊዜ ትልቅ የፍንዳታ ኃይል በእኛ ውስጥ ተፈጠረ፡፡ በዚያው ቅፅበት ሁላችንም ማብራት ጀመርን፡፡ በዚያ ወቅት በሰውነታችን ላይ ምን የተለየ ሁኔታ እንዳለ እንኳን ለማየት አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ሁላችንም እንደ ብርሃን የሚያበራ ነጭ ኮከብ መስለን ነበር!!!

እስቲ ፀሐይን ለመመልከት ሞክሩ፡፡ ልክ እንደዛ አብርተን ነበር፡፡ አዎ አውቃለሁ ያ የሆነው በውስጣችን ካለው ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሳ ነው፡፡ ፍፁም የቀየረን ከሙታን የተነሳው የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በኛ ውስጥ ስለፈነዳ ነው፡፡

ይህም ፍንዳታ ትልቅ የመብረቅ ድምፅን በመፍጠር በመካከላችንም ሰማያዊ ብልጭታን ሲፈጥር ተመለከትኩ፡፡ በዚህ ቅፅበትም ሁላችንም በብርሃን ፍጥነት ወደ ሰማይ እንደ ሮኬት ተተኮስን፡፡

እኛ ብርሃን ነበርን በብርሃንም ፍጥነት እየተጓዝን ነበር፡፡ በዚህ ሂደት አይኔን ለመክፈት ባልችልም፣ አይኔን ብከፍት ግን እራሴን በገነት እንደማገኘው እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ በቅፅበታዊ ሁኔታ ኢየሱስ ተመስገን በማለት ጮሁኩ፡፡ እርሱን ማመስገን ማቆም አልቻልኩም፡፡ ከእንቅልፌ ስነቃ በጣም በትልቅ ደስታ፣ በሰላምና በትልቅ የመደነቅ ስሜት ነበር፡፡

(ከሌር)  እና ይህንን ህልም ያሳየኸኝ እንዲገባኝ ነበር?

(ኢየሱስ) "በትክክል ነገሩ እንዲገባሽ ለማድረግ ነበር፡፡ አየሽ ፖርቶ ሪኮ ላይ የሚወረወረው ኮሜት ምድርን ከዛቢያዋ ይወርውራታል፡፡ እንደ ሰከረ ሰውም ያደርጋታል፡፡ ሞኞች ሆይ ልጆቻችሁ ከዚህ ክስተት የሚያመልጡ ይመስላችኋል? ይህ ኮሜት ምድርን ከመታት በኋላ ምድር በጣም ለመኖርያ እጅግ የተለየች ትሆናለች፡፡ ነገር ግን እናንተ ይህንን ለማየት እዚህ አትገኙም/የሚነጠቁት/፡፡ ህልሙን እንደነገረቻችሁ ሴት ተለወጣችሁ ከምድር ትወሰዳላችሁ፡፡ ከዚህ ግዙፍና አስቀያሚ ክስተት በፊት ህዝቅኤል በህልሙ እንዳየው እናንተም ድንገት አወጣችኋለሁ፡፡"

(ከሌር) ህዝቅኤል በፈረንጆች አቆጣጠር ዲሴምበር 6 ቀን 2015 ዓ.ም ያየው ህልም ይህ ነው፡፡ በመኪና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እየሄድን ነበር፡፡ በቅፅበት በጣም ከባድ ንፋስ ከበስተጀርባችን ከምስራቅ አቅጣጫ የሚመጣ ንፋስ ይነፍስ ጀመረ፡፡ እኔም ምን እንደሆነ ለማየት ወደ ኋላ ዞሬ ብዬ ስመለከት በሰማይ ላይ ጥቁር ዳመና እየተከባለለና እየተሽከረከረ አየሁ፡፡ በመጀመሪያ ግራጫና ዳመናማ ሲሆን በኋላ ግን ጥቁርና ጨለማ እንዲሁም የሚያጉረመርም ማዕበል በመሆን እያደገ አየሩን ሁሉ ተቆጣጠረው፡፡ ድምፁ እጅግ ከፍ ያለና የሚያስጠላ እንዲሁም በራሱ ህይወት ያለው ይመስል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ

ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡ ጨለማው በመንገዱ ላይ የሚገኘውን ሁሉ እየጠራረገ ይሄድ ነበር፡፡ ነገር ግን ከእኛ በላይና ከፊታችን የሚገኘው ሰማይ ንፁህና ፀሐያማ ቀን ይመስል ነበር፡፡

ዳመናው መናጥና መሽከርከር በመቀጠል እንግዳ የሆነ ቅርፅን ፈጠረ፡፡ቅርፁም በደንብ ሲለይ የመቅዘፊያ ቅርስ ሆኖ ወጣ፡፡ በደመናው የሚታየው ምስል እኛን ለመውሰድ እንደሚጣደፍ በጣም በትልቅ ፍጥነት እየተጓዘ ነበር፡፡ ይህ በፍጥነት የሚጓዘው ነገር በደረሰባቸው ጊዜ በጨለማ ውስጥ ስለሚከታቸው ከበስተኋላችን ጩኸት ይሰማ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ እኛም ከሌሎች ብዙ ሌሎች መኪናዎች ጋር ከዚህ ነገር ለማምለጥ ፍጥነታችንን እጅግ በመጨመር ለማምለጥ እየሞከርን ነበር፡፡ በቅፅበት ከሰሜን ምስራቅ ነጭ ፈረስ በአየሩ ላይ እየጋለበ ታየን፡፡ እኔም ግልፅ በሆነ ሁኔታ ስመለከት ከኋላው ሰረገላና ሌሎች በዛ ያሉ ፈረሶችና ፈረሰኞች አየሁ፡፡ እየቀረበ ሲሄድ ኢየሱስ ነጭ ልብስ ለብሶና በራሱ ላይ ዘውድ ጭኖ በሰረገላው ላይ ተቀምጦ በግልፅ ይታያል፡፡ ኢየሱስ ዳመናውንና መቅዘፍያውን በመቅደም ከኋላችን ሆነ፡፡ እርሱም እጁን እያውለበለበልን ልክ በጎችን እንደሚጠብቅ በቡድን በቡድን በማድረግ ወደፊት ወሰደን፡፡ ከኋላችን ከጌታ ሠራዊት ጀርባ ጨለማው እየወሰዳቸው ስለሆነ አሁንም የሚሰቀጥጥ ጩኸትና ድምፅ ይሰማ ነበር፡፡

ጌታና የእርሱ ሠራዊት ከዚህ አስደንጋጭና አውዳሚ ሁኔታ በመካከላችን በመግባት ከለላ ወይም ሽፋን ሆኑን፡፡ በጣም በፍጥነትም እየተጓዝን ከአስደንጋጩ ነገር እየራቅን ሄድን፡፡ እኔ በዛ ጊዜ የሚመስለኝ በዓየር ላይ ነን ወይም ደግሞ ወደ ላይ ወደ ዓየር ልንወሰድ ነው፡፡ ህልሙ እዚህ ላይ ያበቃል፡፡"

ኢየሱስም . . . "ደህና አሁን አንዳንድ ዝርዝር ሐሳብ አግኝተሻል፡፡ አሁን ተረጋጋሽ?"

ክሌርም እንዲህ አለች . . . ስለዚህ የክስተቶቹ ቅደም ተከተል በኢየሩሳሌም የሚገኘው የሙስሊሞች መስኪድ መውደም፣ የ3ኛው የዓለም ጦርነት፣ የሰላም ስምምነት/በእስራኤልና በክርስቶስ ተቃዋሚው መካከል/ መደረግ፣ የኮሜት መውደቅ ከዚያም መነጠቅ ነው?

(ኢየሱስ) "የሰላሙ ስምምነት ከቤተ ክርስቲያን መነጠቅ በፊት አይከናወንም፡፡ የሰላም ስምምነቱን ለማድረግ ጊዜ የለም ያ የሚከናወነው ከንጥቀት በኋላ ነው፡፡ ጦርነቱ ምድርን ለኮሜት ዝግጁ እንድትሆን ያደርጋታል፡፡ የማያሚ መመታትና የኮሜት መውደቅ በአንድ ቀን የሚከናወን ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ጨለማውና ንፋሱ ሲከሰት እናንተ በዚህ የላችሁም /የሚነጠቁትን ይመለከታል/፡፡ በዚያም ክስተት የምድር ስርዓት ይለወጣል፡፡ ይህም ለውጥ በፊዚካል፣ በኤሌክትሪክ ማግኔቲክ፣ በአየር ንብረትና በቅርፅ ጭምር ነው፡፡ ክሌር ይህንን ያመጣው ሰው ነው፡፡ እኔ ይህቺ ፕላኔት ምድርን እንድትመታ አላደረኩም፡፡ ይህ የሚፈፀመው ያላዋቂ ሰዎች ኢጋንንትን በመስማት ህሊናቸውን ለክብርና ለስግብግብ ዓላማ በማዋላቸው ነው፡፡ ይህም በምድር ከሚኖሩት ሰዎች ሦስት አራተኛው ቢጠፉ ምድሪቱ ለመኖሪያ የተመቸች ትሆናለች ብለው በማሰብ ነው (ይህም በኒውክላር ጦርነቱ ነው)፡፡ ነገር ግን ገሃነምን በሰው ስትሞላ ምድር እንደምትለጠጥና በምድር ሥር ያሉ ከተሞቻቸው የእነሱ መቀበሪያ እንደሚሆኑ ያላቸው እውቀት በጣም ትቂት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም ይህች ኮሜት መሬትን ትጭርና ዝም ብላ ትጓዛለች፡፡"

(ክሌር) ዝም ብላ ትጓዛለች?

(ኢየሱስ) "በትክክል፣ ይህ ክስተት መፈንከት ስለሚያስከትል በውጪኛው ጠፍር ጉዞ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ በዚህም አያበቃም፡፡ የተፈጠረው ፍንከት በጣም ትልቅ ነው፡፡ ይህም ሁለት ማይልስ ዲያሜትር(የከብ ኢጋማሽ ስፋት) ያለው ነው፡፡ በተጨማሪም እንዲገባሽ የሚያስፈልገው የምድር ፍርስራሽና ጋዞች አብረው ከምድር ጋር እንደሚጓዙ ነው፡፡ ይህ ነው የከፋና የባሰ ጥፋት የሚያደርሰው፡፡

"ይህ ፍርሃትን ለማምጣት የተነገረ አይደለም፡፡ የኔ ውድ እውነታው ይህ ነው፡፡ይህም ሰው አግባብ በሌለው መንገድ ምድርን ለመነካካት ባደረገው ነገር የመጣ ውጤት ነው፡፡ እንዲሁም የአውሮፓ የኒኩላር ጥናት ድርጅት/CERN/ በዚህ ሥራ ላይ እጁ አለበት ፡፡

"ጠላትም በሚፈጠረው በዚህ ክስተት በመፈንጠዝ ላይ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ክስተት ብዙ ሰዎች ህይወታቸው ስለሚያልፍና ገሃነም በፍጥነት በሰው ስለሚሞላ ነው፡፡ ይህም ክስተት የሃጉራት የመሬት ይዞታ ይለውጣል፣ ግዙፍ የመሬት እንቅስቃሴዎችን ወይም መንሸራተትን፣ የመሬት ርዕደቶችንና አጥፊ ሱናሜዎችን ይፈጥራል፡፡

(ክሌር) ጌታ ለዚህ ክስተት እንዴት ነው የምንዘጋጀው?

(ኢየሱስ) "እምነታችሁን በእኔ ላይ ጣሉ፣ ኃጢያታችሁን ተናዘዙ፣ ጠላታችሁን ይቅር በሉ፣ ደግሞም በየቀኑ በንስሐ ህይወት ቆዩ፡፡ የምህረት እጆቻችሁን በዙሪያችሁ ላሉና ለተቸገሩ ሁሉ አድርጉ፣ በየትኛውም ጊዜ ጎረቤቶቻችሁን ለመርዳት ወደኋላ አትበሉ፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ለምህረት ፀልዩ፡፡"

"በምድር ላይ የሠራችሁት ትክክለኛ ሥራ ለመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ሰዎችን ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ሥራቸውን ለማውገዝ፣ ወይም የሰው ልጅ በምድር በኖረበት ዘመን ሥራውን ለመመዘን ትክክለኛው መለኪያ እናንተ ናችሁ፡፡ አዎን የህይወት መፅሐፍ ይከፈታል፣ መዝገባትም ይቀርባሉ፡፡ ምንም እንኳን ለነፍሳችሁ ሙሉ መስዋዕት ብከፍልም በህይወት ዘመናችሁ የፈፀማችሁት መልካም ሥራ ከሰራችሁት ኃጢያት ጋር ሚዛን ላይ ይቀርባል፡፡

"ይህ ሁለተኛው ፍርድ ሲሆን ይህም የፍርድ የተዘጋጀው ለሙሽራዬ ሳይሆን በመሬት ውስጥ ለሚገኙና እኔን ተቀብለው ለእኔ ላልኖሩት ሙታኖች ነው፡፡ ይህ የፍርድ ጊዜ ለብዙዎች እጅግ ትልቅ ሐዘን የሚፈጥር ነው፡፡ እነዚህም ፍርድ የሚጠብቃቸው ነፍሳት ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ማስጠንቀቂያዬን በመንፈሳቸው ያደመጡ ነገር ግን ያልተስተካከሉ ወይም የፍርዱን ማስጠንቀቂያ በህሊናቸው ቢረዱም ትክክለኛ የሆነውን ላለማድረግ በህሊናቸው እንዳይወቀሱ ህሊናቸውን የዘጉ ናቸው፡፡

"በምድር የምትኖሩና እኔን ያልተቀበላችሁ ወደ ልባችሁ እንድገባ ፍቀዱልኝ፡፡ ለመሆኑ አንድ ቀን በሰማይና በምድር ፊት ለፍርድ እንደምትቆሙ አታውቁም? በህይወት ዘመናችሁ ሁሉ ህሊናችሁ በውስጣችሁ አንድ ነገር እንደሚያስፈልጋችሁ ወይም አንድ ነገር እንደጎደላችሁ ሲወቅሳችሁ እንደነበረ አታውቁም? እኔን ችላ ማለትና የምለውን ያለመስማት የሚያስከትለውን ነገር አታውቁም? እኔ ሁልጊዜ ልባችሁን ሳንኳኳ፣ ሳንኳኳ ነበር፡፡ ነገር ግን እናንተ ልባችሁን አልከፍት አላችሁኝ፡፡ አሁን ግን በዓለም ላይ /በምድሪቱ ላይ/ ሊመጣ ያለውን አስደንጋጭና ትልቅ ስቃይ ልትቀበሉ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ብዙዎቻችሁ አሁንም ግትር በመሆን እኔን ችላ በማለት ልባችሁን ጥርቅም አድርጋችኋል፡፡

"በዚህ ሁኔታ ሆናችሁ ከሞታችሁ እኔን የተቀበሉ ዘመዶቻችሁን ከአሁን ወዲያ በፍፁም አታይዋቸውም፡፡ በሐዘናችሁ ጊዜ እንዲያጫውቷችሁና እንዲያዝናኗችሁ የሰጧኋችሁን የምትወዷቸውን ለማዳ እንስሳቶቻችሁን ከአሁን ወዲያ አታዮአቸውም፡፡ የልጅ ልጆቻችሁን ከአሁን ወዲያ አታይዋቸውም፡፡ መኖርያችሁም ለዘላለም ሰይጣንና መላዕክቱ በሚኖሩበት በእሳት ባህር ውስጥ ይሆናል፡፡ በእሳቱ ውስጥም የምትጣሉት ለአንድ ሰዓት፣ ለአንድ ቀን፣ ለአንድ ሳምንት ወይም ለዓመታት አይደለም፣ ነገር ግን ለዘላለም ነው፡፡ እንግዲህ ምርጫው የእናንተ ነው፡፡ ከእኔ ጋር ያላችሁን ግንኙነት የተስተካከለ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፡፡ እኔ እንደምወዳችሁ ባለቤቶቻችሁ ወይም ልጆቻችሁ ወይም ቤተሰቦቻችሁ በተደጋጋሚ ነግረዋችኋል፡፡ ነገር ግን አሁንም እንዳቋሸሻችሁኝና እንደገፋችሁኝ ነው፡፡

"ስለዚህም በችግራችሁ ጊዜ ልደርስላችሁ አልችልም፡፡ ምክንያቱም በምድር የሚከሰተው ነገር ሲገለጥ በሚሆነው ነገር ስለምትደነግጡ በድን ትሆናላችሁ፡፡ ነገሩ ሲፈፀም የሚቀራችሁ ጊዜ እጅግ ጥቂት በመሆኑ ለሁሉም ነገር የዘገያችሁ ትሆናላችሁ፡፡ለማምለጥ ብትፈልጉም እንኳን ማምለጥ አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ነገሩ ሁሉ በጣም በፍጥነት ስለሚሆን አይምሯችሁ በብዙ ነገር ስለሚያዝ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ እንኳን መወሰን ያቅታችኋል፡፡ ስለዚህም በዛ ወቅት ንስሐ ልትገቡም ሆነ እኔን ለመቀበል ጊዜ አይኖራችሁም፡፡ በተቃራኒው ወዲያው ለዘላለም ወደምትሰቃዩበት ወደ ገሃነም በአጋንንት ተጎትታችሁ ትወሰዳላችሁ፡፡ ይህም ሥፍራ ስጋችሁ በትል እየተበላና እንደገናም እየተተካ ባለማቋረጥ በትሎች የሚበላበት፣ እንዲሁም ሥጋችሁ ባለማቋረጥ በእሳት የሚቃጠልበትና የተቃጠለው እየዳነ እንደገና ለእሳት ስቃይ ለዘላለም የሚዳረግበት ሥፍራ ነው፡፡

"ስለዚህም ይህንን የመጨረሻ ጥሪዬን ለእናንተ አቀርባለሁ፡፡ በእውነት በጣም እወዳችኋለሁ፡፡ በህይወታችሁ የሆነው መልካም ነገር ሁሉ ከልቤ በመነጨ ለጋስነት የተደረገ ነው፡፡በሰዎች ላይ የፈጸማችሁትን በደል ሁሉ ይቅር እላችኋለሁ፡፡ ከእናንተ የሚጠበቀው ስህተታችሁንና ያደረጋችሁትን ጥፋት አውቃችሁ ንስሐ ለመግባት ፀጋ እንድትቀበሉ እኔን መጠየቅ ብቻ ነው፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ በህይወት ዘመናችሁ በፈፀማችሁት ክፉ ድርጊት ከክፉው ሽልማት አግኝታችሁበታል፡፡ ከድሆች ሰርቃችኋል፣ ንፁሃንን ገድላችኋል፣ ጥፋተኛ ያልሆኑትን አስራችኋል፣ በአጠቃላይ ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጥቅም ስትሉ ማንኛውንም ነገር አድርጋችኋል፡፡ ቢሆንም ለዚህ ሁሉ ላደረጋችሁት ሥራ እኔ ለመስቀል ሞት እራሴን መስዋዕት አድርጌ አቅርቤያለሁ፡፡ አሁን እኔ የምጠራችሁ ንስሐ እንድትገቡ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ በአለም ሁሉ ላይ በቅርብ ሊመጣ ያለው መቅሰፍት ሲገለጥ ንስሐ ለመግባት ጊዜ የላችሁም፡፡ አንዳንዶቻችሁማ ይህ መቅሰፍት እንዲመጣ በእቅዱ ውስጥ ተሳትፋችኋል፡፡"

"እናም አሁን የምጠይቃችሁ እኔ እየሰማኋችሁ ስለሆነ ለእኔ እንዲህ ብላችሁ ተናገሩ፡፡ "ኢየሱስ እኔ ኃጢያተኛ እንደሆንኩ አውቃለሁ፡፡ እስካሁን የሠራሁትን ለመጋፈጥ አልቻልኩም ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን የቀረኝ ጊዜ ጥቂት እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ስለዚህም ይቅር በለኝ፣ ምህረትን አድርግልኝና በመንግስትህ ተቀበለኝ፡፡ አንተ ለእኔ ኃጢያት እንደሞትክ አምናለሁ፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ከኃጢያት መንገዴ ተመልሻለሁ፡፡ በአንተ እርዳታ ለአንተ ለመኖር ወስኛለሁ አሜን፡፡"

## ለመንገዳችሁ ተዘጋጁ / ኤፕሪል 19 ቀን 2016 ዓ. ም

## Get Ready For Your Journey/ April 19, 2016

ክሌር እንዲህ በማለት ጀመረች. . . በልቡ የምትኖሩ ሁላችሁ ኢየሱስ እየመጣ ስለሆነ ሙሽራው እንድትዘጋጅ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም እያዘጋጀን ነው ።

ያለፈው ሳምንት ጌታን ሳላየው ነበር ሳምንቱ ያለፈው፡፡ ይህም የሆነው ጌታን ፍፁም ለማያውቁ ነፍሳት ለማዘን እንድችል ውስጤን ሊሞላኝ ስለፈለገ ነበር፡፡ ዛሬ ግን ስላየሁት ከእኔ ጋር አይደለም የሚለውን ፍርሃቴን ለመተው የሚያስችል አዲስ ፀጋ ሰጥቶኛል፡፡ በዚህም ሰላም አግኝቻለሁ፡፡ እናም እሱን ለማድመጥ ሰዓቱ ላይ ስደርስ በፍጥነት . . . " አለሁ" አለኝ፡፡

(ክሌር) ጌታ ከአንተ ጋር ለመሆን እንኳን እየሞከርኩኝ አልነበረም፡፡ እንዳውም ምላሽ ባትሰጠኝ እንኳን  አንተን ለማምለክ ልቤ ወስኖ ነበር፡፡ እናም አንተን በመናፈቁ የሚሰማኝን ውጋት ቀንሶልኛል፡፡”

(ኢየሱስ) “እውነት ነው አብሬሽ እንዳለሁ ታውቂያለሽ፡፡ እናም ምንም ምላሽ ሳትጠብቂ እኔን በማምለክሽ ደስታን እያገኘሽ ነው፡፡ እናም ይህ በደንብ ሰርቷል፡፡ ሙሽራዬ በዚህ ቦታ ለብዙ ጊዜ ባልተውሽም ይህ ለእኔ ምርጡ የፍቅርሽ ስጦታ ይሆነኛል፡፡”

(ክሌር) ስለ ሁኔታው ሙሉ ሰላም አለኝ ደግሞም ደስተኛ ነኝ፡፡ እዚህ እንደሆንክ በእምነት አውቃለሁ ይህም በቂዬ ነው፡፡ ስለዚህም ፀጋ አመሰግንሃለሁ፡፡”

(ኢየሱስ) “የኔ ውድ ምንም አይደለም”

(ክሌር) ዛሬ ለህዝብህ የምትለው ምንድነው?

(ኢየሱስ) “ዛሬ በልቤ ያለው ስለ ዝግጅት ነው፡፡ እኔን ለመገናኘት በእኔ ዕይታ ወይም በእኔ መስተዋት ፊት ልባቸውን በማየትና ትክክል ያልሆነውን ነገር በይቅርታ በማስተካከል ዝግጅት እንዲደርጉ ነው፡፡

“እነዚህን ሁሉ ዓመታት ህዝቦቼ ከሁሉት መንገዶች አንዱን መርጠው ሲሄዱ ኖረዋል፡፡ይህም በቋሚነት ጥፋተኛነት ሲሰማቸው ወይም በቋሚነት ትክክለኛነት ሲሰማቸው ይህም በእኔ ላይ ምንም ስህተት የለም በሚል አመለካከት፡፡ አሁን ግን የምጠይቃችሁ የበለጠ ቅንነት በተሞላበት ዕይታ፣ ምንም ሳይሸፋፈንና ግልጽ በሆነ መንገድ ራሳችሁን በጥልቀት እንድታዩት ነው፡፡ ልጆቼ የግል ቅድስና የሚጠብቅባችሁን ነገር አልተረዳችሁትም፡፡ ከምህረቴ የተነሳ ብዙ ነገሮች ታልፈዋል፡፡ ወጣቱ ናትናኤል በአድማጮቹ ፊት ኃጢያቱ ሲጋለጥ እንደደነገጠ እናንተም ኃጢያታችሁ ሲገለጥ ከምትደነግጡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጊዜን በማሳለፍ እስካሁን በውስጣችሁ ያለውን ጨለማ እንዲያሳያችሁ ጠይቁት፡፡”

“ኃጥያታችሁ ምን እንደሆነ መረዳት ስትጀምሩ ጥግ ድረስ እንድትሄዱ አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም እኔ ሁሉንም አውቃለሁ፡፡ ከእናንተ የምፈልገው እንድትናዘዙ፣ ይቅርታ እንድትጠይቁ፣ ለወደፊትም ያንን ኃጢያት ደግማችሁ እንዳትሰሩት መወሰንና ለዚህም የሚረዳችሁን ፀጋ እንደትቀበሉ መፀለይ ነው፡፡ ብትወድቁና ፍጽም ባትሆኑም ጥፋታችሁን በመናዘዛችሁ ብቻ ይቅር

እላችኋለሁ፡፡ እናም ስህተታችሁን እስከመጨረሻው እስከትተዉ ድረስ የሚረዳችሁን ፀጋ መስጠቴን እቀጥላለሁ፡፡ ፍጽም መሆን የለባችሁም ነገር ግን ፍፁም ለመሆን በመፈለግ ንስሐ መግባት አለባችሁ፡፡”

“የዚህ ትምህርት ዋናው ኃሳብ እኔን ለማየት ማድረግ ስላለባችሁ ዝግጅት ነው፡፡ ወደ ሰማይ እስከትሄዱ ድረስ ብዙ ነገር ይወገዳል ደግሞም ይቅር ይባላል፡፡ ነገር ግን ቅር ያሰኟችሁን ይቅር ማለት ደግሞ ግዴታ ነው፡፡ ይቅር ባለማለታችሁ የተነሳ የሚጠብቃችሁን አጋጣሚ እንዲበላሽባችሁ አልፈልግም፡፡”

“አንድ ልትረዱት የሚያስፈልገው ነገር ማንም ምንም ቢያደርጋችሁና ቢጎዳችሁ ከእኔ ፈቃድ አግኝቶ ነው፡፡ የክፉ ፀሐፊ አይደለሁም፡፡ ነገር ግን ሌሎችን መውደድና ለእራሳችሁ መሞት እንድትችሉ በማለት ፈተና እንዲሆን እፈቅዳለሁ፡፡ በስተመጨረሻም እኔ ስለፈቀድኩ እኔን መውቀስ ትችላላችሁ፡፡ ስለዚህ ይቅርታ ስታደርጉ ያንን ሰው፣ ራሳችሁንና እኔን ይቅር ማለታችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ስለዚህም እነዚህን ሶስት አካላት በመጨመር በልባችሁ ምሬት ሥር እንዲሰድና እንዲበክላችሁ የፈቀዳችሁትን እንዳስወግድ ጠይቁኝ፡፡ በእርግጠኝነት በእያንዳንዳችሁ ውስጥ ሥር የሰደደ ምሬት አለ፡፡ ይህንን ለማወቅ መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ የእናንተ ድርሻ ነው፡፡ እንዲሁም ሁኔታውን በመቃወም ብትፀልዩና እንዲነሳላችሁ ብትጠይቁ እኔ አስወግደዋለሁ፡፡

“ይህ ልምምድ ብዙ ጊዜ ሊወስድባችሁና ከዘለአለማዊ ህይወት ሊያስቀራችሁ አይገባም፡፡ ብዙዎቻችሁ ይቅር ባለማለታችሁ ልትዘገዩ ትችላላችሁ፡፡ ልባችሁ ውስጥ ምሬት ካለ ከቆሻሻዎች ሁሉ እጅግ የሚያስጠላውና የሙሽራ ልብሳችሁ ፊት ለፊት በገሃድ የሚታይ እድፍ ነው፡፡ ስለዚህ ማስወገዳችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ አብርዱት ማለቴ ከባድ ወደሆነ ንዴት ውስጥ እንዲከታችሁ አትፍቀዱለት፡፡ ይህንን ንዴትና ይቅር አለማለት በእኔ ስም ገስፃችሁ ፍፁም ግንኙነት እንዳይኖራችሁ ተቃወሙት፡፡ ታማኝ በመሆን እንዲነሳላችሁ እውነተኛ ሙከራ ለማድረግ ከወሰናችሁ እኔም ሙሉ ለሙሉ እንደማስወግድላችሁ ታማኝ ነኝ፡፡”

“ንስሐ ልትገቡበት የሚገባው ሌላው ግድፈታችሁ ራስ ወዳድነት ነው፡፡ ለሌሎች ማድረግ እየቻላችሁ ያላደረጋችሁበትን ጊዜዎች እስኪ ተመልከቱ፡፡ ስላልፈለጋችሁ ወይም ነገሩ ስላልተሰማችሁ ብቻ አላደረጋችሁም፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ከራሳችሁ ውጪ በማሰባችሁና እናንተ ታማችሁ እንኳን ለሌሎች ቸርነትን በመፈለጋችሁ ስንት ጊዜ በሽታን እንደፈወስኩ ታውቃላችሁ? በዚህ ሁኔታ ትልቅ ለውጥ አለ፡፡

“ሰይጣን ነገሮች ከመሆናቸው በፊት ያውቃል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ፈተና እንደሚመጣ ወይም ከተቸገረ ሰው ጋር እንደምትገጣጠሙ በቅድሚያ ያውቃል፡፡ ስለዚህም አጋንንትን በመላክ እናንተን አበሳጭተውና ኃሳባችሁን ሰርቀው መልካም ሥራ እንዳታደርጉ ያደርጋል፡፡ ይህ በጣም የተለመደ ነገር ነው፡፡ ብዙ ነገሮች ሊያበሳጯቹህ ሲሞክሩ ለምን ይህ ሁሉ ጥፋት ሆነ? የሚረዳ ሰው አለ? እንድንገናኝ የታሰበ ሰው አለ? አንድ ሊከሰት ያለ ሁኔታ አለ?ብላችሁ አስቡ፡፡”

“እንዲገባችሁ የሚያስፈልገው ነገር አጋንንቶች ያላቸው ኃይል የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም በህይወታችሁ ሊመጣ ያለውን ወሳኝ የሆነ ነገርን በማየት እናንተን ለመረበሽ አጋጣሚዎችን ይጠብቃሉ ፡፡ በህይወታችሁ ሊመጣ ያለው ነገር በጣም ወሳኝ ከሆነ በቅድሚያ ስለሚያውቁ(ደግሞ ብዙ ጊዜ ያውቃሉ፣ ምክንያቱም አንዳቸው ለአንዳቸው እንዲህና እንዲህ ሊሆን ነው ወይም ደግሞ እከሌና እከሌ እየሄዱ ነው በማለት መልዕክት ይለዋወጣሉ) ሁኔታዎችን በማጥናት ለአንድ ለሚያስፈልገው ነፍስ እርዳታ ልታደርጉ እንደሆነ ያገናዝባሉ፡፡ ስለዚህም የእናንተን ሐሳብ ለመስረቅና ቀጠሮውን

እንድትሰርዙ ለማድረግ ይሞክራሉ፡፡ ወይንም እኔ ለምልከው ሰው ምንም እርዳታ ለማድረግ እንዳትችሉ አድርገው ያዳክሟችኋል፡፡ በነገራችን ላይ የምልከው ሰው ለኔ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሰው ነው፡፡ “

“ሌላው ራስ ወዳድነት ላይ ትኩረት ልትሰጡት የሚገባው ነገር እኔ ብቻ ነኝ አስፈላጊ፣ ለሌሎች ጊዜ የለኝም የሚለውን አመለካከት ነው፡፡ ይህም ለእናንተ ብዬ የምሰራውን ነገር ለማቆም ያህል አስፈላጊ አይደላችሁም የሚል አመለካከትን በውስጡ የያዘ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በጣም የምጠላው ነገር ነው፡፡ አሁን ደግሞ የክፉ ሁሉ መሰረት ወደሆነው ወደ ኩራት እንመልከት፡፡ ራስ ወዳድነት ወደ ኩራትና ራስን ፃድቅ ወደ ማድረግ ይመራል፡፡ ህሊናችሁ መጥፎ ስሜት ተሰምቶት ችላ ያላችሁበትን ጊዜያት አስቡ፡፡ እነዚህ የተደበቁ ኃጥያቶችን ለማሳየት ጥሩ አመላካቾች ናቸው፡፡”

“የኔ ቆንጆ ሙሽራ እነዚህን ነገሮች የምናግርሽ መጥፎ ስሜት እንዲሰማሽ ሳይሆን በእኔ ፊት ስትቆሚ ንፁህ ሆነሽ እንድትቀርቢ ብዬ ነው፡፡ ኃጥያት ቆሻሻ ሲሆን ያልተናዘዛችሁት ኃጥያት ደግሞ በቆሻሻ ውስጥ ሆኖ መቆየት ማለት ነው፡፡ የተናዘዙት ኃጥያት ግን ይቅር ተብሏል ደግሞም ተሰርዟል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በኋላም የለም፡፡ የሙሽሮቼ ኃጥያቶች በሙሉ እንዲሰረዙላቸው እፈልጋለሁ፡፡"

“የእኔን መንገድ ሳይሆን የእናንተን መንገድ እንድትከተሉ የሚያደርጓችሁ የራስ ፈቃድ ፤ የራስ ወዳድነት ምኞትና ቅናትን መናዘዝ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ እርግጠኛ ካልሆናችሁ በኋላ ከመፀፀት መጠንቀቅ ይሻላል፡፡ ደብቃችሁት እኔ ከማወጣው እናንተው ብታውቁት በጣም የተሻለ ነው፡፡ አ ይህ እጅግ የተሻለ ነው፡፡

“የራሳችሁን ባህሪይ ስትመረምሩ ማየት ያለባችሁ ዝርዝር ጉዳዮች ፍርሃት፤ኩራት፤ቅናት፤ በሰው ላይ መፍረድ፤ ብስጭት/ንዴት፤ ስንፍና፣ ስስት(ንፉግነት)፤ ሆዳምነትና መስገብገብ ናቸው፡፡

"ልክ እንዳልሆናችሁ በመንፈሳችሁ እያወቃችሁ ነገር ግን ሁልጊዜ የምታደርጓቸው ነገሮች ላይ በደንብ ትኩረት ልትሰጡበት የሚገባችሁ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህርያት በህይወታችሁ ውስጥ መዘበራረቅን የሚያመጡና ደግሞም ዝሙት ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ከእኔ ይልቅ በማስቀደማችሁ ነው፡፡ ደግሞም እነዚህ ነገሮች ያለምንም ጥርጥር የሰርግ ልብሳችሁን የሚያጨማድዱ ናቸው፡፡”

“ቅድም እንዳልኩት ይህን የምለው እናንተን አቅም ለማሳጣት ወይም ለመውቀስ አይደለም፡፡ነገር ግን ያለምንም የቆሻሻ ጠብታ፣ መጨማደድና እንከን ከእኔ ጋር እንድትገናኙ ለማዘጋጀት ነው፡፡"

“ጠብታ ራሳችሁን እንዲበክል የፈቀዳችሁለት ነገር፤ መናገር ያልነበረባችሁና መከልከል ሲኖርባችሁ ያስተናገዳችሁት ስሜት ነው፡፡”

“እንከን ደግሞ የውስጥ መንፈሳችሁ መበከልን የሚያሳይ ነው፡፡ መታየት የሚጀምረውም ከውስጥ ልክ ያልሆነ ነገር ሲኖር ነው፡፡ ይህም የምታደርጉትን ሁሉ የሚበክል ዝንባሌ ወይም አመለካከት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ራስን በመውደድ የሚደረግ በቀል፡፡"

“መጨማደድ የሚፈጠረው ደግሞ ቋሚ የሆነ ኃጢያትና የተዘበራረቀ ባህርይ ሲኖር ነው፡፡ ለምሳሌ ከባድ የብድር እዳ ውስጥ ስለገባችሁ በእሁድ ቀን ሥራ የምትሰሩ ከሆነ የመጨማደድ ምልክት ነው፡፡ ንፉግነታችሁ ለመግዛት እንድትፈልጉና

በብድር እንድትገዙ ያደርጋችኋል፡፡ ስለዚህም እዳችሁን ለመክፈል ስትሉ በሳምንት አንድ ቀን አርፋችሁ ከእኔ ጋር በመሆን መታደስ የሚገባችሁን ጊዜ በመተው ብድሩን ለመክፈል እንድትሰሩ ይጋብዛችኋል፡፡"

"አንዳንዶቻችሁ ያገኛችሁት ሥራ እሁድ ብቻ እንድትሰሩ የሚያስገድዳችሁ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ በህጋዊ መልኩ እያወገዝኳችሁ አይደለም፡፡ በሰንበት እህልን አለቀምኩምን? በሰንበት ህመምን አልፈውስኩምን? ነገር ግን እያንዳንዱን ደቂቃ የምትፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚገፋፋ የስግብግብነት ዝንባሌ በልባችሁ ውስጥ አለ፡፡"

"ለእኔ የተባለው ቀን በአስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያዝ ሌላ ቀንን ለእኔ የሚሰጥ የልብ ዝንባሌ ደግሞ አለ፡፡"

“ከሳምንቱ ውስጥ የተቀደሰው ቀን የቱ ነው የሚል ጭቅጭቅ ውስጥ እንዳትገቡ እመኘላችኋለሁ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ መመሪያ አልሰጣችሁም፡፡ ምክንያቱም የኃይማኖተኝነት መንፈስ ውስጥ ስለሚከታችሁ ነው፡፡ እኔ የምፈልገው ልባችሁን ነው እንጂ ለህግ ተገዥነታችሁንና የከንፈር አገልግሎታችሁን አይደለም፡፡ አዎ አሁን ድንጋዮች በአየር ላይ ሲበሩ ይሰማኛል፡፡ ይህ የልብ ባህርይ ከእኔ ጋር ለሚኖራችሁ የግል ህብረት ገዳይ እንደሚሆን አውቃለሁ፡፡ እናንተ አታደርጉትም፡፡ ፀሐፍትና ፈሪሳውያን ናቸው ልባቸውን ለእኔ የከለከሉኝ፡፡ ምክንያቱም እነሱ እንደሚመቻቸው የሰንበት ህጋቸውን ስላላከበርኩላቸው ነው፡፡"

“ከሚያስጨንቃቸው ነገር ውስጥ አንዱና ዋነኛው ምን እንደነበር ታውቃላችሁ? ከመስዋዕት ሽያጭና ሳንቲም ከመለወጥ የሚያገኙትን ገንዘብ እንዳያገኙ የማደርጋቸው መስሏቸው ነው፡፡ እውነት ነው በቤተመቅደሶች ውስጥ በፈፀሟቸው ተግባራት ብዙ ገንዘብ አካብተዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህን የተከለከሉ ተግባራትን ከማድረግ የሚያገኙትን ገንዘብ ማጣት ነው ያሳሰባቸው፡፡ ይህ መጨማደድ ነው፡፡ ተጨማሪና የተሻለን የማካበት ልማድ አእምሮዋቸውን እንዲጣመም በማድረግ ፍላጎታቸውን ከመጠን በላይ አሳድጎታል፡፡

“አንዳንዶቻችሁ በተለይ ወጣቶች ከፍርሃት የተነሳ ለእዚህ ነገር ተቃውሞ ታሳያላችሁ፡፡ የእኔ ውዶች እባካችሁ እናንተን የሚያወግዝ አይደለም፡፡ ይህን የምለው ስለ እግዚአብሔር ቅድስና እንድትረዱና ጥልቀቱ ምን ያህል እንደሆነ እንድታውቁ ነው፡፡ ብዙዎቻችሁ ትክክለኛ ህሊናን አላዳበራችሁም፡፡ ቃሉን በመማር በተቀደሰ ቤት ውስጥ አላደጋችሁም፡፡ ስለዚህ ወደ መሰረቱ ወስጃችሁ አንዳንድ ያልተማራችኋችሁ ነገሮች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ እንድታውቁ እፈልጋለሁ፡፡

“እኔ ግን የህግ አምላክ አይደለሁም፡፡ በይቅርታ የተሞላሁ የምረዳና ይቅር ባይ አምላክ ነኝ፡፡ እኔ የምፈልገው ልባችሁን ነው፡፡ የምፈልገው እንድትወዱኝ፣ እንድታምኑኝ ወደ እኔ እንድትመጡና ድክመታችሁን፣ ኃጥያታችሁን፣ መተማመኛ ያጣችሁበትንና ፍርሃቶቻችሁን ለእኔ እንድትነግሩኝ ነው፡፡ እነዚህን ነገሮች መቋቋም እንድትችሉ ልረዳችሁ እፈልጋለሁ፡፡

“መቀየር የማትችሉትና እኔን እንዳያስከፋኝ የምትፈሩት ነገር ካለ ለእኔ ንገሩኝ፡፡ እኔ እረዳችኋለሁ፡፡ ምናልባት በእናንተ በኩል የምታደርጉት ነገር ስህተትም ላይሆንም ይችላል፡፡ ምናልባት ስለራሳችሁ መጥፎ እንድታስቡ የሚያደርጋችሁ ከውሸት አባት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

አዎ! ማውገዝ እርሱ የሚወደው መሳሪያው ነው፡፡ ለምን ብላችሁ ከጠየቃችሁ ምክንያቱም እናንተ መጥፎና ዋጋ የሌላችሁ ናችሁ ብሎ ቢያሳምናችሁ፣ እንዲሁም እኔ ኃይለኛና ፈራጅ እንደሆንኩ ካሳመናችሁ ወደ እጆቼ ለመምጣት እምነት እንዳይኖራችሁና እኔን እንድትርቁኝ ስለሚያደርጋችሁ ነው፡፡

"ስለዚህ ለዚህ መልዕክት ተቃውሞ አታሳዩ። እንዳውም ማጣራት ያለባችሁ ዝርዝር ነገሮች አድርጋችሁ ውሰዱት። መንገድ ልትሄዱ ስለሆነ ነገሮቻችሁን ማዘጋጀት አለባችሁ። ስለዚህም በዝርዝሩ መሰረት መስራት ያለባችሁን ሥሩ። እናም ለመጋፈጥ የምትፈሯቸውን ነገሮች እኔ እረዳችኋለሁ። ትክክል የሆኑትንና ያልሆኑትን ነገሮች ለመለየት የመጽሐፍ ቅዱስ የተስፋ ቃሎች መፅሐፍ በመጠቀም /Bible promises book/ አመሳክሩ። ከእኔ የተላኩ ምልክቶችን ለማየት አካባቢያችሁን ተመልከቱ። ለምሳሌ የምትዘምር ወፍ ፤ ምግባችሁ ላይ ወይም መሬት ላይ የወደቀ ቅጠል ላይ ልብ ቅርጽ የመሳሰሉትን። እንዲሁም በሱቅ ውስጥ የሚሰማ የፍቅር ሙዚቃ ፤ መንፈሳችሁን የሚያጥለቀልቅ ድንገት የሚሰማ የእርካታ ስሜት። እነዚህ ሁሉ ነገሮች እናንተን የማበረታታበትና ከእናንተ ጋር መሆኔን የማሳይበት መንገዶች ብቻ ሳይሆኑ እናንተ ወይም ሙከራዎቻችሁ እንዳስደሰቱኝ የማጸድቅበት መንገዶች ናቸው።"

"ጠቅለል ባለ መልኩ እያልኳችሁ ያለሁት እኔን ለመገናኘት በንሰሐ ውስጥ ቆዩ ነው። ልክ ለአንድ ትልቅ ዝግጅት ገላችሁን እንደምትታጠቡት ራሳችሁን በእኔ ፍቅርና ይቅር ባይነት እጠቡ። ምንም ነገርን ለመናዘዝ አትፍሩ። ይህንን አስታውሱ ስታደርጉትም እዛው ነበርኩ። ስለዚህም ንሰሐ በገባችሁት ነገር ላይ ይቅር እላችኋለሁ። ይህንንም አብረን እናድርገው።

በሁሉ ነገሬ የእናንተ ነኝ። በድካማችሁም ቢሆን አልተዋችሁም። እጅግ እወዳችኋለሁ ስለዚህ አትፍሩ።

## የቅድስና ጣፋጭ መዓዛና የጠላት ማዘናጋት / ሜይ 24 ቀን 2016 ዓ.ም
## Sweet Aroma of Holiness / May 24, 2016

(ክሌር)፡- በልቡ የምትኖሩ ሁላችሁ መልካም የሆነውና የተረጋጋው የጌታ መገኘት ከእኛ ጋር ይሁን። በአምልኮ ረዘም ያለ ጊዜ ካሳለፍኩኝ በኋላ መፅሐፍ ቅዱስ በማንበብና በመፀለይ የሥጋ ወደሙን አገልግሎት መስጠት እንዳለብኝ ተሰማኝ። ግን ጌታ ከልክሎኝ እንደዚህ አለኝ . . .

ክሌር አሁን የምፈልገው አንቺን ማቀፍ ብቻ ነው። ለብዙ ቀናት በእጆቼ አቅፌሽ መወዛወዝና ከውስጥሽ የሚመነጨውን የፍቅርሽን ጣፋጭ መአዛ ማጣጣምና ከአንቺ ጋር እንደዛ መቆየት ነው።

(ክሌር) ሲያሞጋግሰኝ እንደተለመደው መጠራጠር ስጀምር ይህንን በማወቅ እንደዚህ ብሎ መለሰልኝ . . .

(ኢየሱስ) "እባክሽ እምነት በማጣት አታቁስይኝ። ላቅፍሽና አብረን ስንሆን ከነፍስሽ የሚመጣውን ጣፋጭነት መተንፈስ ነው የምፈልገው።"

(ክሌር) ዙሪያዬን በአንድ ነገር እንደተጠቀለልኩ ያህል የሚነግረኝን ሁሉ እሰማ ነበር። 'ግን እኮ ኢየሱስ ከሌሎቹ መጥፎ ልማዶቼ በተጨማሪ አሁንም እናደዳለሁ።'

(ኢየሱስ) "ችግር የለውም ይህ ልብሽ አይደለም። ክሌር አስደስተሽኛል። ደግሞም ታስደስችኛለሽም።"

(ክሌር) ራሴን የማየው በጭራሽ እንደዚህ ስላልሆነ ማልቀስ ጀመርኩ።

(ኢየሱስ) "ነፍስሽ ውስጥ ጣፋጭነት እንዳለ የምነግርሽ ለዛ ነው፡፡ አዎ ይህንን መንገር ያለብኝ ከፍተኛ ጥላቻ በመጣ ጊዜ እዛ ላይ እንዳታተኩሪና ልብሽ የጎበጠ እንዳልሆነ እንድታዩ ነው፡፡

"ልጆቼ ብዙዎቻችሁ ለእኔ አስደሳች ናችሁ፡፡ ከእናንተ የቅድስና ጣፋጭ መዓዛ ይንቆረቆራል፡፡"

(ክሌር) ይህንን ከተናገረ በኋላ አብረን እየተወዛወዝን እያለ እንደዚያ የሚመስል ነገር አየሁ፡፡ የሚመስለው ከጭንቅላቴ ላይ የሚመነጭ መዓዛ ነው፡፡ በወቅቱም ኢየሱስ ጉንጬን ያሳረፈው በዛ ቦታ ላይ ነበር፡፡

(ኢየሱስ) "አዎ ያለማቋረጥ ራሱን ለእኔ አሳልፎ የሚሰጥ ነፍስ መዓዛ አለው፡፡ ይህም ለእኔ ጣፋጭና አፅናኝ ነው፡፡"

"በውስጣቸው ያለ የጥላቻ መርዝ ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ብዙዎችን ለመጠጋት አልቻልኩም፡፡ ህዝቦቼ እባካችሁ የጥላቻ መጥፎ ጠረን ከሐሳባችሁ እንዳይመነጭ አድርጉ፡፡ አዎ የአይምሮአችሁ እንቅስቃሴ ይህንን መዓዛ ያመነጫል፡፡ ጣፋጭ መዓዛ ሲሆን በደምብ በተያዘ የአትክልት ቦታ ውስጥ የምሄድ ይመስለኛል፡፡ የሚያውክ ጠረን ሲሆን ግን የሞተና የበሰበሰ ሥጋ ጠረን ያሸተትኩ ይመስለኛል፡፡ ምን ያህል አስቀያሚ እንደሆነ ልትረዱት አትችሉም፡፡"

(ክሌር) ኢየሱስ ዛሬ ለሙሽሮችህ ምን ማለት ትፈልጋለህ?

"ልላቸው የምፈልገው ነገር የሰጠኋችሁን ስጦታዎች ጠብቁ ነው፡፡ ቅባቶቻችሁን ጠብቁ ፣ ህልሞቻችሁንና ራዕዮቻችሁን ጠብቁ፡፡ እናም የአብሮነታችንን ተወዳጅ ጊዜዎች ጠብቁ፡፡ ጠብቁ ጠብቁ፡፡ ጠላት መጥቶ ወደ አለማመን ጎትቶ እንዲያስገባችሁ አትፍቀዱ፡፡

"ጠላት እናንተን በማበሳጨት፣ በምሬት ፣ በቅሬታና በሞኛዊ ፍርሃት ሊሰርቅ ያንዣብባል፡፡ እነዚህን ስሜቶች ሊሰሟችሁ ሲጀምሩ ጠላት እየሰረቃችሁ መሆኑን ተረዱ፡፡ በዚህም ጣፋጭነታችሁን፣ ከእኔ ጋር መገኘታችሁንና የምሰጣችሁን ሙላት ለመስረቅ እየፈለገ ነው፡፡"

(ክሌር) ታውቃላችሁ! ይህ የሚናገረው ነገር በጣም የሚገርም ነው፡፡ ወደ ሰማይ የተነጠቀው ወጣቱ ናታን እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ 'ጌታ ቅን የሆኑትን ሰዎች ይለያል፡፡ ቅን የሆኑትን ሰዎች የሚለያቸውም በሽታ ነው፡፡ ሁሉም ወንዶች የተቀደሰ ልብሳቸውን ለብሰው ነበር፡፡ ነገር ግን ጥሩ መዓዛ እንዳላቸው ያሸተታቸውን ብቻ ነበር ጥበቃ ሊደረግ ባለው ሽለቆ እንዲገቡ የፈቀደላቸው፡፡ ይህ በጣም አስገራሚ እንደሆነ አሰብኩ፡፡ ምክንያቱም አሁንም እንደገና እየተናገረ ያለው ስለመዓዛ ነው፡፡

(ኢየሱስ) "ቀናችሁን ከመጀመራችሁ በፊት ወይንም አንድ ሥራን ልትጨርሱ ስትሉና ለመፀለይ ስትፈልጉ እናንተን ለማድከም ቁጣን ማነሳሳት ይወዳል፡፡ በጆሮዋችሁ ውሸትን ሹክ ማለት ይወዳል፡፡እንዲሁም  በቁጣ ወይም በፍርሃት እናንተን በማጠፍ ለቀኑ ያሰባችሁትን እንዳታደርጉ ለማድከም እነዚህን ማታለያዎች እንድትፈጽሙ ያደርጋል፡፡ ብልህ ስለሆነ የቱን ነገራችሁን እንደሚነካ ያውቃል፡፡ ምክንያቱም የእርሱ ሰራተኞች ማለትም አጋንንቶች ሁልጊዜ በትኩረት እየተከታተሉ ማስታወሻን ይይዛሉ፡፡"

(ክሌር) ኢየሱስ ይህንን ማንሳቱ በጣም የሚገርም ነው፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ያሳለፍኩባቸው ቀናት ነበሩኝ፡፡ በብስጭት ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ በተከታታይ ሁለት ቀናት በዚህ መልክ ተበላሽተውብኛል፡፡ የሚገርም ነው፡፡ እዚህጋ ጌታ በትክክል እኔን እየተናገረኝ ነው፡፡ የበለጠ ትኩረቴን ይሻሉ ያላልኩዋቸው ነገሮች ባላሰብኩት ሁኔታ ከፀሎትና ከመልእክቴ

አርቀውኛል፡፡ ከዚያም ተጨማሪ ጥፋትን መቻል እስከሚያቅተኝ ድረስ በየቀኑ ተስፋ እየቆረጥኩ መጣሁ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሌላ አቅርቦት ያስፈልገኝ ነበር፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው ንዴቴ ምንም እስከማይቀርልኝ ደረስ አደከሞኝ ነበር ፡፡

እናንተ እንዴት እንደሆናችሁ ባላውቅም እኔ ግን ስበሳጭ ጉልበቴ በሙሉ ይሟጠጣል፡፡ ወደፊት መሄዴ ቀርቶ ቀኑን ሙሉ እያነከስኩ እውላለሁ፡፡ ከዛም ትዕግስት በማጣቴና በሰው በመፍረዴ ደግሞ የጥፋተኝነት ስሜትን አስተናግዳለሁ፡፡

(ኢየሱስ) “የእኔ ውድ አሁን የገለፅሽው እንዴት ሰይጣን በትክክል እንደሚሰርቅ፣ እንደሚገድልና እንደሚያጠፋ ነው፡፡ አለመግባባትን ይፈጥርና ከዚያም ንዴትን ፣ መገለልን ፣ በሌሎች መፍረድን ፣የጥፋተኝነት ስሜትን፣ እናም በመጨረሻም ያለውዴታችሁ ነገሮችን እንድታደርጉ ያደርጋል፡፡ በዚህም በቀረው ቀናችሁ ሰላምን በማሳጣት በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ሥራ ለመስራት እንዳትችሉ ያደርጋል፡፡"

ኢየሱስም "ውዶቼ ጠላት በተላላኪዎቹ አማካኝነት እንዴት እንደሚሰራ እወቁ፡፡ በዚህም እወቀት ገና በእንጭጩ ቅጩት፡፡ ‘ኢየሱስ ከክፉ ሁሉ ጠብቀኝ በማለት ወደ እኔ ጩኹ!’ እኔም ልረዳችሁ እመጣለሁ፡፡ ይህን ለማድረግ ራስን መግዛትና ስነ ስርዓት ማድረግ ይጠይቃል፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በጠላት ሁን ተብለው በመታቀድ የሚደረጉ ሲሆን ይህም ሁለት ነገሮች ለመሸርሸርና ነው፡፡ እነዚህም የተወጠኑት እናንተን ለማድከምና ጊዜ ለማሳጣት ነው፡፡ በምንም አይነት ሁኔታ አንድን ነገር መጨረስ እንዳለባችሁ ቢሰማችሁም የሚያቋርጥና ሃሳብ የሚሰርቅ ነገር ሲመጣ ጭንቀትና ቅሬታ ውስጥ ትገባላችሁ፡፡ ሲደክማችሁ ደግሞ በትክክል ማሰብ ያቅታችኋል፡፡ ፍርሃት ህመምና የማያልቅ ማቋረጦች ከፈቀዳችሁላቸው እናንተንም ያዳክማሉ፡፡ከዛም የባሱ ስህተቶችን ትፈጥሩና ንሰሐ መግባት ይኖርባችኋል፡፡ ስለዚህም ብዙ ጊዜያችሁን ችግሩን ለማስተካከል ታጠፋላችሁ ማለት ነው፡፡ይህ ደግሞ ከግባችሁ ወደኋላ እንድትርቁ ያደርጋችኋል፡፡

"ልጆቼ ተጠንቀቁ፡፡ ጠላታችሁ በጣም ብልህ ስለሆነ ተጠንቀቁ፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜም በትዕግስት ፣ ሁሌም ይቅር በማለት ፣ በሌሎች ባለመፍረድ በፍቅሬ ኑሩ፡፡ እናም መልካም ባህርይ እንዲኖራችሁ ፈተናዎችን የምፈቅድ እኔ እንደሆንኩ እወቁ፡፡ እነዚህን ነገሮች እየተቆጣጠርኩ መሆኑን የምትረዱበት ዕይታ በፊት ለፊታችሁ ብታስቀምጡ ቀናችሁ ሳይሰርቅባችሁ ሰላማችሁን እመልስላችኋለሁ፡፡

"አሁን በትዕግስት፣ በጥንካሬና ራስን በመግዛት እባርካችኋለሁ፡፡ አደራ የሰጠኋችሁን መልካም ነገሮች ጠብቁ፡፡ ማንም ከእናንተ እንዲሰርቀው አትፍቀዱ፡፡ እናም እባካችሁ አስታውሱ ..... በቅርቡ እመጣለሁ፡፡"

## የሙሽሮቼ ንጥቀት ለሁሉም የሚታይ ይሆናል / ሜይ 28 ቀን 2016 ዓ. ም

## The Rapture Event Will Be Visible / May 28, 2016

ክሌር፡- ለመነጠቅ የምንጠባበቀው ትልቁ ተስፋችን እርሱን ተጠንቅቀን እንደንጠብቀው ያድርገን፡፡

አሁን ስለ መነጠቅ የተዘጋጀውን አጭር ፊልም በቦብ ባርበርስን ቻናል አይቼ መጨረሴ ነው፡፡ በእርግጥ ፊልሙ በደንብ ተደርጎ ነው የተሰራው፡፡ ያንን በአዕምሮዬና በልቤ ይዤ ነበር ጌታን ለመስማት የመጣሁት፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ... "እስካሁን ምንም አላየሽም፡፡ ለመሆኑ እነዛ የተተኮሱት አንፀባራቂ ስራዎች አስደነቁሽ? እኔ ያቀድኩትን ሙሉ ሥራውን እስከታዪ ድረስ ጠብቂ፡፡ ያ ማንም የፊልም አዘጋጅ ከሚያስበው በላይ የሚሆነው ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ለማለት የምፈልገው ነገር የተሰራው ፊልም በጣም ጥሩ ሙከራ ነው፡፡ በእርግጥም ስለ ንጥቀት የማታውቂውን ትንሽ ብልጭ እንዲልልሽ አድርጓል፡፡ ዳዊት ታማኝ አገልጋዬ ነው፡፡"

ጌታ የተናገረው ፊልሙን ስለሰራው ስለ ዴቪድ ኤ.ር ዋይት /David A.R. White/ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሰው እግዚአብሔር አልሞተም የሚለውን አጭር ፊልም የሰራ ሰው ነው፡፡

"ቢሆንም እኔ ለሙሽራዬ ያዘጋጀሁት አይን ያላየው ጆሮ ያልሰማውና በማንም ልብ ውስጥ ያልታሰበ ነው፡፡ መግለፅ ከሚቻለው በላይ የከበረና ልብ ከሚችለው በላይ ቆንጆ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ቀናቶች መዋዠቅና ችግር የበዛባቸው ናቸው፡፡ ለአንዳንዶቻችሁ መጠበቅ ፍፁም የማትችሉት ሆኖባችኋል፡፡ ነገር ግን የኔ ፀጋ እንድትችሉ ያደርጋችኋል፡፡ ያ በጣም ቆንጆና ምስጋና የሚገባው ነገር ጠላት በዓለም ቆሻሻ ተሸፍኖ እንዳይታይ አድርጎታል፡፡ ነገር ግን ለጥቂቶች ለአጭር ጊዜ  ሽፋኑ ተነስቶ የሚያያችሁን ታዩታላችሁ፡፡"

"እንደዚህ ዓይነት ነገር ሆኖ አያውቅም፡፡ ወደፊትም አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሰማይ ስትውርደ ካልሆነ በቀር አይሆንም፡፡ ይህ ክስተት መቼም ጊዜ ቢሆን የማንረሳው ክስተት ነው፡፡ የኔ ሙሽራ ወደ ሰማያት ተወስዳ! ተለውጣ ማየት እንዴት እንደምጓጓ!፡፡ ሊሆን ያለው ነገር አይን ያላየውና በሰው ልብ ውስጥ ያልታሰበ ነገር ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ብዙ በክብር የተሞላን ነገር አይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ሊሆን ያለው ነገር ከታየው ሁሉ የሚልቅ ነው፡፡

"የኔ ሙሽሮች እኔ ለእናንተ ያዘጋጀሁት ነገር ካልታየ በስተቀር በፍፁም የሚታመን ነገር አይደለም፡፡ ይህ ሆኖ እንኳን ሁኔታው ለጠላት ጥቅም እንዲውል ተደርጎ ተጣሞ ይቀርባል፡፡ እንዲህ ቢሆንም ግን አንዳንዶች የሆነውን ነገር በፍፁም በማመን ራሳቸውን ለእኔ አሳልፈው ይሰጣሉ፡፡ በተለይም የንጥቀት ተካፋይ የሆኑት ዘመዶቻቸው፡፡ ዘመዶቻችሁን ስለዚህ ነገር ስላዘጋጃችዋቸው ይህ የትንቢቱ መፈፀም መሆኑን ሊክዱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ይህ ክስተት በውስጣቸው በመቀረፁ ቀሪ ዘመናቸውን ሁሉ ይዟቸው ይጓዛል፡፡

"ስለዚህም ከዚህ በኋላ እኔ እውነት እንደሆንኩና መጥቼም እንደምገዛ ጥርጣሬ አይኖራቸውም፡፡  በአሁኑ ጊዜ ሁሉም በዓለም ጉዳይ ስለተጠመዱ ማንም ይህንን ሊቀበል የሚችል የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ክስተት ነገሮችን ሁሉ ቀይራል፡፡ ልባቸው እጅግ የደነደነ ብቻ በወቅቱ ምን እንደተከሰተ ጥያቄ ይፈጥርባቸውና ዓለም የምትሰጠውን ትንታኔ ለመስማት በመፈለግ በዛ ይተኩታል፡፡"

"ለዚህ ነው ይህንን ክስተት ሁሉም ህብረተሰብ እንዲያየው የሚደረገው፡፡ የምድር ወገን ሁሉ ያን ጊዜ ያዝናል፡፡ በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል፡፡ የምድር ወገኖች ሁሉ ያለቅሳሉ፡፡ የሰው ልጅም በሰማይ ደመና ሆኖ በኃይልና በታላቅ ክብር ሲመጣ ያዩታል(ማቴዎስ 24፡30)፡፡"

"ይህ አሁን የምናገረው ቀጥታ የሚመለከተው የእስራኤልን ወገን ነው። እነሱ አዳኛቸውን ገድለዋል ስለዚህም ይህ እነርሱ የሚሰበሩበት ጊዜ ነው። ከአሁን ወዲያ ህዝቤን የሰው ኩራት አይገዛውም፣ ህዝቤ የመጨረሻውን ትህትና ይላበሳል። ከእነርሱ ትልቅ የሆነው ራሱን እጅግ ኃጢያተኛ አድርጎ ይመለከታል። የፃህፍትና የፈሪሳውያን ትምህርት የኔን እውነተኛ ማንነት እንዲያውቁ አላዘጋጃቸውም። በሰው የሚደረገው የፅድቅ ሥራ ይፍረከረካል። እናም ሴተኛ አዳሪዎች ከእነርሱ ቀድመው መንግስተ ሰማያትን ይወርሳሉ።"

"ነገር ግን ይህንን የምለው ላሳፍራቸው አይደለም። እኔ ለህዝቤ ያለኝ ፍቅር ትልቅ ነው። እነርሱ እኔ የህጉ ዋና ቁንጮ ወይም ልብ እንደሆንኩና ነቢያት የተናገሩትን ለመፈፀም እንደመጣሁ ወደፊት ገብቷቸው ለማየት እጓጓለሁ። እኔ ለእነርሱ ከአዳኛቸው በላይ ነኝ። እኔ በሥጋ የመጣሁ ህያው አምላካቸው ነኝ። እናም በምድር በኖርኩት ህይወት የእምነታቸውን ምንነትና እንዴት መኖር እንደሚጠበቅባቸው አሳይቻቸዋለሁ።"

"ከአሁን ወዲያ ማንም ሰው በራሱ ሥራና በምድራዊ እሴት ፍርድ ሊሰጥበት አይገባም። የምድር ባለጠጋዎች ሁሉ እስካሁን ዋጋ ባልተሰጠው ክቡር ደሜ ሥር ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ አለባቸው። ሽባው፣ አንካሳውና ደካማው ስለምፈወሳቸው በእኔ ልዩ ሥፍራ አላቸው። ህጉ ንፁህ አይደሉም ብሎ የደነገገባቸውን እነዚህን በደሜ ታጥበው ለዘላለም ይነፃሉ።"

"በምድር ትልቅ የሚባሉት ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ በዝቅታቸው ደስ ይላቸዋል። እንዲሁም በምድር የሚገኙ ድሆች ደግሞ ወደ ትክክለኛው የህይወት እሴት በመመለስ ከፍ ብለው ይታያሉ። ሁሉም በደሜ ስለተገዛ ከዚህ ወዲያ ማንም ሰው ይሄኛው ከዛኛው ይሻላል ብሎ ሊፈርጅ አይችልም።"

"ክሌር የኔ ልጅ የህግ ዋናው ነገር ፍቅር እንደሆነ ታውቂያለሽ? በእኔ ልብ ውስጥ ሥፍራ ለማግኘት ምንም "መንገድ" የለም። የኔን ደም አስቀድማችሁ ተቀብላችሁ በደም ሥራችሁ ውስጥ እየተዘዋወረ ነው። ስለዚህም እናንተ ውድ ከመሆናችሁ የተነሳ ዋጋ ሊተመንላችሁ አይችልም። እና ደግሞ የመንግሰተ ሰማያት ገንዘብ ፍቅር ነው። ፍቅር ለመንግስተ ሰማያት እጅግ ዋጋ የሚሰጠው ባህርይ ነው። ስለዚህም በፍቅር የሚመላለሱ በአባቴ ደረት ውስጥ የሚገኙ ዋጋ የማይተመንላቸው ናቸው። እነዚህ የዚህን ዓለም ጉዞና ፈተና ጨርሰው ወደ ተፈጠሩበት ንፅህና የተመለሱ ናቸው።"

"ይህ ታላቅ ሚስጥር ነው። በሥጋ የተገለጠና ወደ አብ ያረገ፣ በሰማይ መላዕክት የታየና የከበረ፣ በወደቁት ገሃነም የተፈራ ነው። ሰዎች ራሳቸውን አሳልፈው ለእኔ ሲሰጡ የኔ ህይወት፣ ሞትና ትንሳዔ ተደጋገሞ እንደቀረበ ዓይነት ነው። በእውነትም ፍፁም አደርጋቸዋለሁ። እነሱ መላዕክቶች ሊኖራቸው የማይችለውን ፍፅምና አላቸው። እነርሱ ማንም ፍጥረት ሊደርስበት የማይችለውን አንድነትና ህብረት ከእኔ ጋር ይሰማቸዋል። አዎን ይህ እኔ ራሴን ለፍጥረቴ የሰጠሁት ታላቅ ሚስጥር ነው። አዎ እኔ ወደ ምድር ተጥዬ ለመታጨድ የደረሰ ብዙ የበሰሉ ፍሬዎችን ያፈራሁ የስንዴ ቅንጣት ነኝ።

"በፍፅምና ተፈጥሮ የነበረው ፍጥረት የራሱን መንገድ ጨርሶ ወደ እኔ ተመልሷል። ነገር ግን አሁን ራሱን ለሞት አሳልፎ ለእኔ ለሚሰጠው ለእያንዳንዱ ክብር ይሆናል። ኦ! ስንቶች በዚህ ሚስጥራዊ ሞት ተጣብቀዋል? ለእያንዳንዳችሁ ራሴን አሳልፌ የሰጠሁት በግል በእናንተ ውስጥ ለመኖር መሆኑን፣ እንዲሁም እናንተም በሞትና በትንሳኤ የክርስቶስ አካል መሆናችሁን በእውነተኛው መንገድ ልትረዱ የምትችሉት በመንግስተ ሰማይ ብቻ ነው።"

"ይህ እንዲገባችሁ አሁን እራሳችሁን አታስጨንቁ፡፡ በቅርብ ጊዜ እንደ ውኃ ጥርት ብሎ ይታያችኋል፡፡ አሁን ግን ጊዜው ህዝቤን መረጋገጫ ያደረጉትን የዚህን ምድር ክፉ ኃይላት መቋቋም ነው፡፡ አሁን ግን ጊዜው ገና የፈተናና የመፈተኛ ወቅት ሲሆን በዚህም የኔ ክብር በአሸናፊዎች ላይ የሚፈነጥቅበት ወቅት ነው፡፡ አውቃለሁ ከእናንተ ማንኛችሁም አሸናፊዎች ነን ብላችሁ አታስቡም፡፡ ነገር ግን ታምኑኛላችሁ? አሸናፊዎች ናችሁ፡፡ አውቃለሁ ለራሳችሁ ትንሽ ግምት እንደምትሰጡት፡፡ ይህ ደግሞ ትክክልና እንዳትወድቁ የሚጠብቃችሁ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን በሌላው አንፃር ራስን ከሚገባው በላይ ማሳነስ ነው፡፡"

"ቢሆንም ስለ መዳናችሁ ሲባል እንዲህ ዓይነቱን ነገር በጣም አተኩሮ መመርመር ቢቀር ይሻላል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ምድር እስካላችሁ ድረስ ለኩራት፣ ለቅናትና ከሌላው እበልጣለሁ ብሎ ለመገኘት የተጋለጣችሁ ናችሁ፡፡ እናንተ ከእነዚህ የምታመልጡት ራሳችሁን ትንሽ አድርጋችሁ ስትቆጥሩ ነው፡፡ እናም በትንሽነታችሁና ምንም ባለመቻላችሁ በእውነት ከልባችሁ ደስታ የሚሰማችሁ ከሆነ ጦርነቱ በድል እንደተጠናቀቀ ማሰብ ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ያልኩበት ምክንያት ለሌሎች ምንም መስላችሁ ብትታዩም፣ በዚህ ነገር ለመውደቅ እናንተም የተጋለጣችሁ በመሆናችሁ ከውድቀት እንድትጠበቁ የእናንተ ውበት ያለው በእኔ ውስጥ ስለሆነ ነው፡፡"

"እናም ሙሽሮቼ በዚህ ሐሳብ ላይ ልታርፉ ትችላላችሁ? ሁሉንም እንደነበረ ወደ አብ ለመመለስና ቁንጅናችሁ እንደተጠበቀ ለማድረግ፣ እንዲሁም በጦርነቱ የቆሰላችሁት ቁስል ታይቶ እንደማይታወቅ ዕንቁ እንዲያበራ ለማድረግ በሚደረገው ራዕይ ላይ ልታርፉ ትችላላችሁ? አዎ ! ይህንን ቃል በልባችሁ ያዙት፡፡ በየቀኑ ራሳችሁን አዘጋጁ፣ ደግሞም በዚህ ሥራ ላይ አብሮ ሰራተኞች መሆናችንን እወቁ፡፡ እናም ወደ ፍፅምና እያመጣኋችሁ እንደሆነ ተገንዘቡ፡፡

"የጌታ እጅ ያልተዳሰሰውን የእናንተን ማንነት ለማስተካከል ሲንቀሳቀስ ከብዙ አንዱን ፍጥረቱን መንካቱ ስለሆነ ልታደርጉ የምትችሉት ጥቂት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን በመገንዘብ በዚህ ሐሳብ ላይ እረፉ፡፡ እናንተ ምንም ልታደርጉ አትችሉም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን አጋጣሚ በመውደድ፣ በእያንዳንዱ ውድቀት ንስሐ እየገባችሁ ተከተሉኝ፡፡ እንዴት እንደማነሳሳችሁና እንደምመራችሁ አውቃለሁ፡፡ ለአንድ ደቂቃ እንኳን አትፍሩ፣ ይህ የኔ ስራ ነው፡፡ ደግሞም በሚገባ እሰራዋለሁ፡፡"

"በእናንተ ውስጥ በተትረፈረፈው መገኘቴ የምትሮጡትን ሩጫ በአሸናፊነት እንድትጨርሱ የበቃ ይሁን፡፡ እኔም ይህንን እከታተላለሁ፡፡"

## እግዚአብሔርን መፍራት የቅድስና መንገድ / ሰብቴምበር 9 ቀን 2016 ዓ.ም
## The Journey of Holiness / September 9, 2016

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ንግግሩን ጀመረ . . . "ክሌር እኔ ማድረግ የያስኩት አስፈላጊውን ነገር ብቻ ነው፡፡ ይህም ሁላችሁንም ወደ አዲስ የተቀደሰ ህይወት ማምጣት ነው፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው፡፡ የአምላክነቴን ሚና በቁም ነገር ነው የምወስደው፡፡ አንዲት ነፍስ ለመቀደስ ያለማቋረጥ ስትጮህ ይህንን ቃል ተቀብዬ ደስታ ወደ ተሞላ ርስቷ እንድትገባ የሚያስፈልገውን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡

“በእውነትም የደስታ ርስት ነው፡፡ ቦታው ከንፁህ ህሊና የሆነ፣ ከጥረትና ከብክለት ነፃ የሆነ የዕረፍት ቦታ ነው፡፡ እንዲሁም ይህ ቦታ ያለምንም ማጉረምረም በመስቀሉ ሥራ የተሰጣቸውን ስጦታ የያዘ ቦታ ነው፡፡ የተቀደሰ ነፍስን ከመያዝ የሚበልጥ ውብና የሚደንቅ ነገር የለም፡፡

“ነገር ግን ይህ ጉዞ በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ብዙዎች ግማሽ መንገድ ላይ ይቆማሉ፡፡ እኔ ግን ሙሉውን መንገድ አብራችሁኝ እንድትሄዱ እየጠራኋችሁ ነው፡፡ በዚህ አለም ላይ እኔን ከማግኘት የበለጠ ነገር ምንም የለም፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ንፁህ፣ የተቀደሰና ከኃጥያት የነፃ ህሊና መኖር ነው፡፡”

“ቅድስናን የመረጠ ነፍስ ከእኔ ጋር ከመጣበቅ በቀር ከሌላ ጋር መጣበቅ አይችልም፡፡ እርግጥ ነው ባልንጀራውን መውደድ ይገባዋል፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን ምርጫው አመለካከቱና ፍላጎቱ እኔ በህይወቱ እየሰራሁ ካለሁት ጋር መግባባት አለበት፡፡

(ክሌር) ኢየሱስ ረጅም መንገድ እንደሚቀረኝ ተረድቻለሁ፡፡

(ኢየሱስ) "ይህ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን ማሰብ ያለብሽ መንገዱን መምረጥሽን ነው፡፡ ደግሞም በመንገዱ ላይ ለመቆየት ወስነሻል፡፡ ይህ ደግሞ ለእኔ እጅግ አስፈላጊው ጉዳይ ነው፡፡ ብዙ ነፍሳት ከእኔ ጋር ከመቆየት ይልቅ የአለም አጀንዳ እየጎተታቸው በመንገዱ መጀመሪያ ላይ ጉዟቸውን ያቋርጣሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በጨቅላ እድሜያቸው የትኞቹ እጅግ አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸውን ስላልተማሩ ነው፡፡ እንዳውም በተቃራኒው ተወዳጅ ለመሆን፣ በተትረፈረፈ ህይወት ለመኖር ፣ በስልጣንና በልበ ሙሉነት እንዲሁም በውበት ፉክክር በየአቅጣጫው እየተጎተቱ ይገኛሉ፡፡ ልጆች ገና በአፍላ እድሜያቸው ለእነዚህ እሴቶች ከፍ ያለ ዋጋ የመስጠት ባህሪያትን ከወላጆቻቸው በመረዳት እየተቀረፁ ያድጋሉ፡፡ ወላጆችም እነርሱ ትልቅ ዋጋ የሰጧቸው እነዚህ እሴቶች ሳይሳኩላቸው ሲቀሩ ልጆቻቸው እንዲያሳኩላቸው በዚህ መንገድ ይመሯቸዋል፡፡

"በዚህም ምክንያት እኔን ብሎ ሁሉንም ነገር ለመተው የተዘጋጀ ነፍስ ሲገኝ ያልተለመደ ስጦታ ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ግን የሚያስከፍላቸው ዋጋ ምን እንደሆነ አያውቁም፡፡ ስለዚህም ቃላቸውን እቀበልና ወደ ተራራው በቀስታ እመራቸዋለሁ፡፡ አንዳንዴም ተራራውን የማወጣቸው ተሸክሜ ነው፡፡ ነገር ግን ማጣሪያ የሚካሄድባቸው መጋጠሚያ ቦታዎች አሉ፡፡ ይህም የሚጠበቅባቸው ነገር እነሱ ለመስጠት ፍቃደኛ ከሆኑት ሲበልጥና ፈተናዎቹ አማላይ ሲሆኑ ማለት ነው፡፡ መተው ያለባቸውን ብልጭልጭ ነገር ወይም ሐሳብ ሳይተዉ ሲቀሩ ተራራውን መውጣት እንዲቀጥሉ ለማድረግ በሌላ መንገድ አባብላቸዋለሁ፡፡ ይህንንም የማደርገው በጣም ስለምወዳቸው፣ የሚፈልጉትን ስለማውቅና በህይወታቸው መጨረሻ ያንን እንዲያገኙ ስለምፈልግ ነው፡፡ ስለዚህ ከተቃውሞ ባለፈ ተራራውን መውጣት እንዲቀጥሉ የሚያስችሉ ነገሮችን አዘጋጃለሁ፡፡ ጉዞው ምንም ቀላል ባይሆንም በስተመጨረሻው ግን ወሮታ ያለው ነው፡፡ እናም በጉዞው ማለቂያ ላይ የተከፈለው መስዋዕትነት አንዱም አይቆጫቸውም፡፡

“ስለዚህ አሁን እናንተ የወንድማማች ፍቅር የሆነውን ተራራ እየወጣን በመንገዱ ላይ እኔን ማመንና ለእኔ እጅ መስጠትን እየተማራችሁ ነው፡፡ በቋሚነት ለእኔ ያላችሁን እምነትና መተማመን እያሰፋችሁ ነው፡፡ ክሌር የምትመኚውን አውቃለሁ፡፡ ፈቃደኛ ባትሆኚም እጅ እንደምትሰጪም አውቃለሁ፡፡

“የሰው ልጅ ተፈጥሮ በህይወት የላቀ ስፍራን ለመያዝ በሚሞክሩ ሊገለፅ በማይችሉ፣ ተቆጥሮ በማያልቁ፣ የሚጋጩ ስሜቶችና ሃሳቦች የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን እኔ ስቆጣጠራችሁ ሁሉንም መልክ አስይዝና ለነፍሳችሁ ጥቅም እንዲሆኑ አደርጋለሁ፡፡

“በጉዟቸው መጀመሪያ ላይ ገሃድ ያልወጡ እጅግ ብዙ ስጦታዎች ለነፍሳት አካፍያለሁ፡፡ ነገር ግን በውስጣቸው ስላለው አስደናቂ ነገር አያውቁም፡፡ ሆኖም ይህንን የምገልፅላቸውና መሳሪያቸውን እንዲያነሱ የማነቃቃቸው እኔ ነኝ፡፡ ይህን ከማድረጌ በፊት ግን መሰረታዊ የግብረገብና የስነምግባር መዋቅራቸውን ማለትም ለእኔና ለሌሎች ያላቸውን ፍቅር ማዳበር አለብኝ፡፡

“ይህም ጥንካሬን የሚፈትን በመሆኑ በበረዶና በእሳት ውስጥ ብዙ ጊዜ ማለፍን የሚጠይቅ ሂደት ነው፡፡ ሆኖም በጉዞው ወቅት በየመጋጠሚያው ሲደርሱ "እሺ" የሚሉ ነፍሳት ጉዞው በሚያልቅ ጊዜ እኔን በመምሰላቸው በጨለማውና በግራጫው አለም ላይ ተስፋን፣ መነሳሳትንና የመንግስተ ሰማያትን ራዕይ በማምጣት እንደ አልማዝ ያበራሉ፡፡

“ይህ ግዙፍና ሰፊ ሐሳብ ነው፡፡  ጉዞውን  ሊረዱ የሚችሉት በእውነት የተመረቁት ብቻ ናቸው፡፡ በመካከሉ ስትሆኑ ከተወሰነ ርቀት በላይ ከፊታችሁ ያለውን ማየት አትችሉም፡፡ በመጨረሻው ግን የእኔን አመለካከትና ለአለም የምታበሩትን ድንቅ የሆነውን ብርሃን ታያላችሁ፡፡

“እናም ይህ ብርሃን ደግሞ መቼም አይደበዝዝም፡፡ እውነትን ለሚፈልጉት ሁሉ እንደ ወደብ መብራትነት ያገለግላል፡፡ እኔም የምጠራችሁ እንደዚህ እንድትሆኑ ነው፡፡ ከእኔ ጋር ሥትሰሩ በሥራ የምታገኙት ውጤት ዋነኛ አይደለም፡፡ ዋናው አስፈላጊው ነገር ባህርያችሁ እንጂ የሰራችሁት ሥራ አይደለም፡፡ ይህም ለራሳችሁ ስትሞቱ  ያለው ማንነታችሁ ነው፡፡

“ስለዚህ የኔ ውዶች ይህንን ለመረዳት እንደሚከብዳችሁ አውቃለሁ፡፡ ቃል ልገባላችሁ የምችለው ነገር ቢኖር በጉዞው ማለቂያ ላይ ከፍ ያለ ደስታና ሙላትን እንደምታገኙ ነው፡፡ ለዚህም ቃሌን ሰጥቻችኋለሁ፡፡ ከእኔ ጋር ከሞታችሁ ከእኔ ጋር ለዘላለማዊ ህይወት ትነሳላችሁ፡፡"

### ለእናንተ ያቀድኩት አስደናቂ ነገሮች አለኝ / ኦክቶበር 19 ቀን 2017 ዓ.ም

### Ask Me for Supernatural Gifts / October 19, 2017

ኢየሱስ እንደዚህ በማለት ጀመረ.... "የምላችሁን ብትቀበሉ እኔ ለእናንተ ያቀድኩት አስደናቂ ነገሮች አለኝ፡፡ ህዝቤ እኔ በፈውስ፣ ሰዎችን ነፃ በማውጣትና ለደካሞችና ለቆሰሉት አዲስ ህይወትን ለማምጣት ወደሚያስችል ወደ መንፈሴ ሙላት ላመጣችሁ እፈልጋለሁ፡፡

"እኔ ላካፍላችሁ የምፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አለ፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያ አሮጌ ልማዳችሁን፣ አሮጌ አስተሳሰባችሁን እንድትተዉ እፈልጋለሁ፡፡ እያነፃኋችሁና ወደ አዲስ ከፍታ እየወሰድኳችሁ እንደሆነ በማወቅ ወደ ፆም ህይወት ግቡ፡፡ አዎ አንዳንድ ጊዜ ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ከእኔ የሚሰጠው ምላሽ እጅግ ሰፊ ነው፡፡

"እንደማነፃችሁና ለትልቅ ነገር እንደማዘጋጃችሁ በማወቅ ወደ ፆም ግቡ፡፡ አዎ አንዳንድ ጊዜ ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ምላሹ ከምትረዱት በላይ ነው፡፡ ደግሞም ራሳችሁን በትንሹ መካድ አቅቷችሁ በህይወታችሁ ፍፃሜ ወቅት የጠበቃችሁት ባለመሆኑና መስራት እየቻላችሁ ባመለጣችሁ መልካም ሥራ እንደምትሸማቀቁ ቃል እገባለሁ፡፡

"እኔ  ወደ አዲስ የአምልኮና መጋረጃ ወደሌለበት ከፍታ ልወስዳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን እናንተ ወደእዛ ከፍታ ለመድረስ ዝግጁ መሆንና የመንፈስ ቅዱስ መገኘት በሙላት ወዳለበት፣ አሁን እናንተ "እውነታ" ብላችሁ የምትሉት እውነት እንደሆነ ወደማይትቆጥሩበት ከፍታ ልወስዳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይህም እውነታ እንደሚታየው ዓለም የሚጨበጥና ፍፁም እውነት ነው፡፡ ይልቁንም የኔን እውነታ ጠልቃችሁ ስትገቡበት የቁሳዊው ዓለም ነገር ሁሉ ለእናንተ ጣፋጭ መሆኑ ይቀራል፡፡

"ብዙዎቻችሁ ሰዎችን ለመፈወስ ህልም አላችሁ፡፡ እናም የፈውስ ፀጋን ስትመኙ ነበራችሁ፡፡ ይህንን ፀጋ ለመቀበል ጊዜውና ወቅቱ አሁን ነው፡፡  ይህም እኔ የምላችሁን መመሪያ ብትቀበሉና አሁን ደስታ የሚሰጣችሁን ነገር ለሚበልጠው መልካም ነገር መስዋዕት ብትከፍሉ በመጨረሻው ቅር አትሰኙም፡፡ ብዙዎች ይህንን መንገድ ጀምረው በመጨረሻው ራሳቸውን በመግዛት ጉሮሯቸውን መዝጋት አቅቷቸውና ያላቸውን ንብረት በመውደድ ቃል ከገቡለት መንገድ ፈቀቅ ብለው ወደኋላ ተመልሰዋል፡፡

ክሌር፡- ጌታ እኔ ይህንን ለማድረግ የሚያስችለኝ የአንተ ፀጋ ብቻ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ምክንያቱም እኔ ከእነዚህ አንዱ ነኝ፡፡

"አዎ ይህንን አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን ክሌር መታመን ያስፈልግሻል፡፡ ወደ መንፈሳዊ ህይወት በጥልቀት ለመግባት ፍላጎት እንደሰጠሁሽ ሁሉ ራስሽንም ለመግዛት ፍላጎት እንዲኖርሽ ማድረግ እችላለሁ፡፡ውዴ እባክሽ ወደኋላ አትመለሺ፣ ወደኋላ አትመለሺ፡፡ የልብሴን ጫፍ በመያዝ ሥጋን ለመግደል፣ ራስን ባዶ ለማድረግና የተወደደውን ህይወት ለመሞላት የሚያስችለውን ፀጋ ለምኚ፡፡"

ክሌር፡- ግን ጌታ እኔ በጣም ደካማ ነኝ፡፡ ደግሞም ከብዙ ነገሮች ጋር ተጣብቄያለሁ፡፡

"አዎ በጣም ደካማ ነሽ፡፡ እኔም ስለዚህ ነው ቀን በቀን ራስሽን በመካድና በእውነት ለውጥ ማምጣትሽን እኔ ምልክት እስክሰጥሽ ድረስ በእምነት ወደ እኔ እውነታ እንድትገቢ የምፈልገው፡፡ ነገር ግን ከአሁን ወዲያ እንደቀደመው ጊዜ አንቺ እንደፈለግሽው ማድረግ አትችይም፡፡ ምክንያቱም ብዙ ነፍሳትና ሁኔታዎች ወደሚደነቅ ሥፍራ ይስቡሻል፡፡ ራስሽን መካድ ከፈለግሽ መስቀልሽን ይዘሽ ተከተይኝ፡፡

"ክሌር ያንን ያህል ከባድ አላደረኩብሽም፡፡ የፐሮቲን መጠጦችሽን አልከለከልኩሽም፡፡ ወደፊትም አላደርገውም፡፡ ምክንያቱም ይህ ወደፊት እንድትቀጥዪ ከሚያደርጉሽ ነገሮች አንዱ ስለሆነ ነው፡፡ ነገር ግን ወደፊት ላስቀጥልሽ የምችለው እኔ ብቻ ብሆን አይሻልም ነበር? ያንን አስቢ የኔ ውድ፡፡ ደግሞም ይህንን አስታውሺ፣ በእኔ ፈቃድ ሁሉን ብትጠይቂ ለአንቺ አደርገዋለሁ፡፡ ይህ የጊዜ፣ የትዕግስትና ከእቅዴ ጋር የመጣበቅ ጉዳይ ነው፡፡ ነገሮች ለአንቺ አስቸጋሪ በሆኑብሽ ጊዜ ያንጊዜ ነው ለመበርታት ወደ እኔ መቅረብ የሚያስፈልግሽ፡፡

"ነገሮች ለእናንተ አስቸጋሪ በመሰሉ ጊዜ፣ ያን ጊዜ ነው ለመበርታትና ነገሮችን ለማጠናቀቅ ወደ እኔ መቅረብ የሚያስፈልጋችሁ፡፡ በራሳችሁ መሥራት የምትችሉት እጅግ ጥቂት ነገር ነው፡፡ ይህ በመደጋገም ብዙ ጊዜ አላጋጠማችሁም?"

ክሌር፡- አዎ ጌታ እኔ አጋጥሞኛል፡፡

"ደህና ይህንን ማወቅሽ ለአንቺ ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ለብቻሽ እንዳልተውኩሽና ስትወድቂ እንዳነሳሁሽ ታውቂያለሽ፡፡ በተጨማሪም የመውጫ መንገድ እንዳዘጋጀሁልሽ ትረጃለሽ፡፡ እኔ ታማኝ ነኝ፡፡ እስካሁን ይህንን አልተረዳሽም?"

ክሌር፡- አዎ ጌታ አንተ ታማኝ ነህ፡፡

"ኸርትዱዌለርስ ይህ ለእኔ ጥሩ ምስክርነት ይሆናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ ምንም የማይቻል ነገር የለም፡፡ ትንሹን ነገራችሁን ስትተዉ ቃል ከገባሁላችሁ ትንሹን ስትፀልዩ በሚከናውን ጊዜ ለምሳሌ አካል ጉዳተኛ ከተሽከርካሪ ጋሪው ላይ ብድግ ሲል ያላቸውን ክብር ትጥላላችሁ፡፡

"ህዝቤ የአንተ ፈቃድ ከሆነ እኔ በውስጥህ እሳትን ላከማች መጥቻለሁ፡፡ ይህ የአንተ ፍላጎት ከሆነ በእያንዳንዱ ቀን ለእኔና ለሌሎች መኖር መጀመር አለብህ፡፡ ወደ አምልኮ ህይወት ግባ፡፡ እናም ለእኔ ያለህን ፍቅር በመሰዊያው ላይ በመሆን በቃላት ግለጥልኝ፣ ደግሞም ጠይቀኝ፡፡ እንዲሁም ታላቁን ስጦታ መጠየቅህን አታቋርጥ፡፡ ቢያንስ ለረዥም ጊዜ የጠየቁኝን፣ የተዋረደና በፍቅር የተሞላ ልብ ያላቸውን አለመቀበል አልችልም፡፡

"ባጠቃላይ እኔ እነዚህን ስጦታዎች ለእናንተ ለመስጠት እፈልጋለሁ፡፡ ነገር ግን እናንተ ደግሞ ከቀደመው፣ ከአሮጌውና ከአረጀው ጋራ የተጣበቀ ነገራችሁን በማንፃትና ንፁህ በማድረግ ለእነዚህ ስጦታዎች ቦታ ማስለቀቅ አለባችሁ፡፡"

## የእግዚአብሔርን የጦር መሳሪያ በፀሎት መልበስ - በካሮል ጄኒንግዝ / ኖቬምበር 21 ቀን 2017 ዓ.ም

## The Armor of God--A Prayer by Carol Jennings / November 21, 2017

ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የጦር መሳሪያ አሁን እንድታለብሰኝ እጠይቅሃለሁ፡፡

### የመዳን ራስ ቁርን አልብሰኝ

ጆሮዎቼን ከጠላት ውሸትና ማንሾካሾክ እንዲጠበቁ በጆሮ መሸፈኛው በደንብ ሸፍናቸው። ንግግሬ የአንተን ቃልና የአንተን የድምፅ ለዛ እንዲያወጡ አንደበቴ በፍቅር እንዲጠበቅ ሸፍነው። አለምን ስመለከት አንተ ያፈሰስከውን ደም እንዳስብ አይኖቼን በምህረትና በርህራሔ ጋርዳቸው፡፡ የመዳን ራስ ቁሩ አልብሰኝ። በኃጢያት ምክንያት የመዳን ራስ ቁሩ ተሸንቁሮ አይምሮዬን በሚወረወረውን ፍላፃ፣ ሐሳብ፣ ባለፉና በማይፈለጉ ክፉ ሐሳቦች እንዳይጠቃ ጠብቀኝ ፡፡ የአንተ አይምዕሮ በእኔ ውስጥ ይሁን፣አንድን ነገር ሳስብ፣ ስወስንና ሳደርግ በአንተ ዕይታ እንጂ በእኔ እንዳይሆን፣ ይህም ከአንተ ጋር አንድና አንድ እስኪሆን ድረስ እንዲሆን እለምንሃለሁ፡፡

**ደግሞም ይህንን አውጃለሁ**

እኔ የአንተ ነኝ፣ አንተም የእኔ ነህ፣ እኛ አንድ ነን፡፡በሙሉ ልቤ፣ በሙሉ ሐሳቤ፣ በሙሉ ፈቃዴ ይህንን ቃል እገባለሁ፡፡ ከአሁን ወዲያ ምንም ኃጢያትና ሊጋንንት ከአንተ ሊለየኝ፣ በመካከላችን ሊገባ ወይም በልቤና በአይምሮዬ በማሰብ እንኳን አንድ እርምጃ ከአንተ ሊነጥለኝ አይችልም፡፡

**የፅድቅ ጥሩርን አልብሰኝ**

ልቤን፣ መንፈሴን፣ ነፍሴን፣ አይምሮዬን፣ ፈቃዴንና የአትክልት ሥፍራዬን ሁሉ አንፃቸው። እነዚህንም የነፁትን ሁሉ ሰብስበህ በአንተ ቅድስና ውስጥ ጠብቃቸው። የጠላት የጦር መሳሪያዎች ሁሉ በአንተ የፅድቅ ጡሩር ነጥረው ይመለሱ። ጠላቶቼ ያመጡት ቆሻሻ ከላዬ ላይ ይከባለል፣ በእኔ ላይ ምንም የሚቀር፣ ምንም የሚጣበቅ ነገር አይኑር። በኃጢያት ምክንያት የፅድቅ ጥሩር እንዳይሰነጣጠቅና በዚህም ሊጋንንት አንተ የምትኖርበትን ሥፍራ ዘልቀው ለመግባት እንዳይችሉ ፀጋህን ስጠኝ፡፡

**የእውነት ቀበቶን አስታጥቀኝ**

ጠላቶቼ በብልሃት ባቀነባበሩት ውሸትና ማታለል ሌባ ወደ አንድ ቤት መግባት እንደሚችል፣ አንተ ወደ ምትኖርበት ወደ ውስጤ ለመግባት እንዳይችሉ፣ ዝግና የማይከፈት እንዲሆን የእውነትን ቀበቶ በዙሪያ አስታጥቀኝ። እውነትን ሁልጊዜ ግለጥልኝ። ደግሞም እውነትን እንዳላጣምም፣ ችላ እንዳልል፣ ወይም እንዳልክድ እርዳኝ። ሁልጊዜ እውነትን እንድፈልግና እንድናገር እርዳኝ፡፡

**የወንጌልን የሰላም ጫማ አጫማኝ**

እግሮቼን በወንጌል ሰላም አጫማቸው። የአይኖቼ ትኩረት አንተን ብቻ በማድረግ እያንዳንዱ እርምጃዬ በሰላም ውኃ ውስጥ ይራመዱ። ይህም የሰላም ውኃ በእያንዳንዱ የቀን እርምጃዬና ከሰው ጋር ባለኝ ግንኙነት ከውስጤ እየፈሰሰ በአካባቢዬ የሚገኙትን ሰዎች ልብ፣ አይምሮና ዝንባሌ ይንካ። አይምሮን በሚያልፈው ሰላምህ ጠብቀኝ፡፡

**ሰይፍና ጋሻህን አስታጥቀኝ**

የመንፈስ ቅዱስን ሰይፍ በእጄ እይዛለሁ፣ ከእጅህ የእምነትን ጋሻ እወስዳለሁ። እነዚህን የጦር መሳሪያዎች በአንተ ጥበብ፣ ኃይልና ስልጣን እንዴት እንደምጠቀምባቸው አስተምረኝ። አንተ እንድዋጋ ከላከኝ ጦርነት ወደኋላ እንዳልመለስ አስተምረኝ። ይህንን ማድረግ የምችለው በአንተ ኃይልና ስልጣን ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም በምንም ዓይነት መንገድ ለትዕቢት ቦታ እንዳልሰጥ እርዳኝ፡፡

**በትህትናን መሸፈኛ ሸፍነኝ /The Cloak of Humility/**

እኔንና የጦር መሳሪያህን ሁሉ በትህትና መሸፈኛ ሸፍነን። ጭንቅላቴን፣ አንገቴንና ሁለመናዬን በትህትና መሸፈኛ ውስጥ ደብቀኝ/ folds and hood/። ሌሎች አንተ በእኔ ውስጥ ሆነህ ስታፀባርቅ እንጂ እኔን በፍፁም እንዳያዩ እፀልያለሁ፡፡

ለብዙ ወራቶች ኢየሱስ እነዚህን የጦር መሳሪያዎች እንዲህ ሲያለብሰኝ አየሁ፡፡ እናም ስለ እያንዳንዱ የጦር ትጥቅ ምን ሊያሳውቀኝ እንደፈለገ የተሰማኝን ስፀልይ ቆየሁ፡፡ ይህንንም የጦር መሳሪያ ለመልበስ የምጠየቀው ከአምልኮ በኋላ፣ ኃጢያቴን ከተናዘዝኩና ንስሐ ከገባሁ በኋላ እንዲሁም ከነፃሁና ሥጋ ወደሙ ከእርሱ ጋር ከወሰድኩ በኋላ ሲሆን ነገር ግን ጠላትን ለማሰር /Binding Prayer/ ከሚደረግ ፀሎት በፊት ነው፡፡

አንድ ቀን ጠዋት መንፈስ ቅዱስ  ይህንን ሁሉ እንድፅፈው አነሳሳኝ፡፡ እኔን እንደረዳኝ እናንተንም እንዲረዳችሁና እንዲባርካችሁ እፀልያለሁ፡፡

## ብዙዎቻችሁ ስለንጥቀቱ ጊዜና ስለ ማስጠንቀቂያው እየተጨነቃችሁ ነው / ኤፕሪል 4 ቀን 2019 ዓ.ም/

## Clare Has Not Abandoned You & New Onslaught of Demons / April 4 , 2019

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጀመረ . . . “ብዙዎቻችሁ ስለ ንጥቀቱና ስለ ጊዜው ተጨንቻችኋል፡፡ ነገር ግን ብዙ ጊዜ እንደመከርኳችሁ በየቀኑ የተቻላችሁን ያህል ለእኔ ኑሩ፡፡ ለሰራችሁት ኃጥያት ንሰሐ ግቡ፡፡”

(ክሌር) ይህም ማለት ማድረግ ያልነበረባችሁ ነገር ግን ያደረጋችኋቸው ነገሮች፣ እንዲሁም  ማድረግ እያለባችሁ ያላደረጋችኋቸው ነገሮች ማለት ነው፡፡

(ኢየሱስ)“አካባቢያች ሁ ካሉት ሰዎች ጋር በተለይም ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ሰላም ፍጠሩ፡፡ ከሁሉም በበለጠ ወደ እናንተ ስመጣ ማየት የምፈልገው ነገር ራስ ወዳድ ያልሆነ አኗኗር ነው፡እንዲሁም በሰማይ ያለውን የአባታችሁን ጉዳይ በትልቅ ፍቅር እየፈጸማችሁ ላያችሁ እፈልጋለሁ፡፡"

“ይህ ማለት ለአንዳንዶቻችሁ ለቤተሰባችሁ ሰርቶ ማቅረብና ወደ ቅድስና እንዲደርሱ ማሳደግ ሊሆን ይችላል፡፡ ለሌሎቻችሁ ደግሞ ተቸገርናል ለሚሏችሁ ሰዎች በጎ አድራጎት ማድረግና ሲፈልጓችሁ አብሮ መሆን ሊሆን ይችላል፡፡ በቅድሚያ ግን ችግሩን መለየትና እነሱን መርዳታችሁ የኔ ፈቃድ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል፡፡ የኔ ውዶቼ በአካባቢያችሁ በብቸኝነት፣ በህመምና በሙተው የሚሰቃዩ በጣም ብዙዎች አሉ፡፡”

“በቀናችሁ ማብቂያ ላይ የምትማሩት ብዙ ትምህርት አለ፡፡ አንዳንዶቹ ትምህርቶች ጤነኛና ጠንካራ በሆናችሁ ጊዜ ሌሎችን ለመርዳት ያላችሁን ታማኝነት እንዲሁም አዛውንትንና ቤት የሌላቸውን መንከባከብን ያካትታል፡፡ የምታጭዱት ያንኑ የዘራችሁትን ነው፡፡ በተለይ ደግሞ መጥፎና ቅር የሚያሰኙ ከሆኑ እናንተ የምትሰጧቸው ጊዜ የበለጠ ክብር ይኖረዋል፡፡ ከአንዳንዶቹ ጋር ያለሁት በጣም በቅርበት ነው፡፡ እናም ያለኋቸው ሃብት እኔ ብቻ ስለሆንኩ ያውቁኛል፡፡ በህይወት ያጋጠማቸው ምንም አይነት አለመሳካት ቢሆንም ድሆች ሁሌም ከእናንተ ጋር ናቸው፡፡ እናም እነሱን ለማገልገል ፀጋዬ ከእናንተ ጋር ይሆናል፡፡”

“በፖለቲካ ግራ መጋባት ውስጥ ስትሆኑ በአካባቢያችሁ እየተጎዱ ላሉት ሰዎች ስሜት አልባ ያደርጋችኋል፡፡ በእርግጥም በምንም ነገር ውስጥ መወሳሰብ እንዲሁ ተመሳሳይ ውጤት አለው፡፡ ክሌር ስለእዚህ ነገር በደምብ ታውቃለች፡፡ ማለትም

በጣም ትኩረት ትሰጣለች ወይም እስከነጭራሹ አታተኩርም፡፡ እናም  ከሰዎች ጋር ጊዜን ለማሳለፍ ስትጠብቅ እራስዋን ታገኘዋለች፡፡

(ክሌር) ጌታ ይህ በጣም እውነት ነው፡ ሌሎችን በቦታው መርዳት ሳልችል ስቀር ይከፋኛል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ችግሮች ሁሌ እንደሚኖሩ፣ ለመዘመርና ለመልዕክቶች ያለኝን ጊዜ በአግባቡ ካልጠበኩ እንደሚበታተን አስተምረኸኛል፡፡ እናም በቀኑ መጨረሻ እንዳልተሳካልኝ እየተሰማኝ ያልቃል፡፡

(ኢየሱስ) " የእኔ ውድ ለማገልገልም ሆነ አገልግሎትን ለመተው ጊዜ አለ፡፡ ጠላት የመነሳሳት ስሜትሽን የሚጎዳውን የጥፋተኝነትና የውድቀት ስሜት እንዲሰማሽ ማድረግ ያውቅበታል፡፡"

(ክሌር)  እናም ደግሞ ከመንገዴ ያስወጣኛል፡፡

(ኢየሱስ) "እውነት ነው ሁሉንም ነገር ማድረግ አትችይም፡፡"

## ለመነጠቅ የመጨረሻ የማጣሪያ ፈተናዎች/ ኤፕሪል 30 ቀን 2019 ዓ.ም/

## Final Exams for the Rapture in Progress / April 30, 2019

የተወደዳችሁ ኸርት ድዌለርስ ሁላችሁንም ጌታ ይባርካችሁ። ይህ ጊዜ የሚገርም ጊዜ ነው። ጌታ የመጨረሻ የማጣሪያ ፈተና መድረሱን በቅድሚያ ስላስጠነቀቀን ላመሰግነው እወዳለሁ። የፈተና ወረቀቶችን ውጤት እንኳን እየለየህ ለመነጠቅ ማን ብቁ እንደሚሆን እየተመለከትክ ነው። እናም ይህንን መልዕክት የሚሰሙ ጆሮዎች ዳባ ልበስ እንዳይሉና ይልቁንስ ፈቃደኛ ያልሆነችው ሙሽራ ወደ አጠገብህ በመሮጥ ፈተናውን እንድታልፍ እፀልያለሁ፡፡ አሜን፡፡

ሁላችሁም እንደምታውቁት ከአቅማችን በላይ የሆኑ ብዙ አስደናቂ እክሎች ገጥመውን ነበር። ከዚህም የተነሳ ብዙዎቻችን በብዙ ድካምና ፍርሃት ውስጥ እንገኛለን። ጌታም ስለዚህ ጉዳይ አሁን ይናገረናል።

ባለፉት ሁለት ወይንም ሶስት ቀናት ህዝቅኤል በከፍተኛ ህመም ውስጥ ነበር። ካሮልም የሆኑ ነገሮች እየገጠማት ነበር። በዚህ ጊዜ ወደ ጌታ ልብ በመቅረብ ሙሽሪት ትኩረት እየሰጠች አለመሆኑን ተገንዝበናል። እርሷ ትኩረት እየሰጠች አይደለችም። ነገር ግን በአንፃሩ ይህ ለእርሷ እጅግ ከባድ ወቅት ነው፡፡

እኔ በዚህ ወቅት የእግዚአብሔር አብን ምስል እየሳልኩ ነው፡፡ እንዲሁም ጌታ ለሰዎች እንዲደርስ የፈለገውን መዝሙርም እየሰራሁ ነበር፡፡ በተጨማሪም ብዙ ግዜዬን ከእርሱ ጋር በመሆን እያሳለፍኩ ነበር። ሆኖም ግን ጌታ በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምንም የተናገረኝ ነገር አልነበረም፡፡ እንዳውም ያተኮረው በማፅናናቱ ላይ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ከነበረው ሁኔታ የተገለልኩ መሰለኝ። ስለዚህም "ጌታ ሆይ እባክህ እኔ ከአንተ ተለየሁህ እንዴ ? እነሱ እንደሚሰማቸው እኔን ለምን አልተሰማኝም? ብዬ ጠየኩት፡፡

ሙዚቃውን እንድሰራ የጌታ ፈቃድ ቢሆንም ይህን ያህል ጊዜ በማጥፋቴ ፀፀት ተሰምቶኛል። እናም እርሱን ችላ ብዬው እንዳይሆን በደንብ እርግጠኛ መሆን ነበረብኝ።

ስለዚህም ጌታን እንዲህ አልኩት፡፡ "ኢየሱስ እባክህ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ ንገረኝ።"

ኢየሱስም "እዚሁ አለሁኝ የእኔ ፍቅር። ጠጋ ብለሽ ያዥኝ። በጌታ ራት ወቅት ያነቡብሻቸው ክፍሎች ዕይታሽን በደንብ ግልፅ ሊያደርጉልሽ ይገባል።"

(ክሌር) : - ጌታ ያነበብኳቸው ክፍሎች ድንጋጤን ፈጥረውብኛል። በጣም ሃሳብ ውስጥ ከተውኛል። ኸርት ድዌለርስ ምላሽ ባለመስጠት ችላ አሉህ እንዴ?

ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ "ክሌር ብዙዎቹ በአለም ነገር ተጠምደዋል። ልክ አንቺ አንድ ሥራ ላይ ጊዜሽን መስዋዕት ስታደርጊ እንደምትሆኚው ዓይነት ማለት ነው። በዚያን ጊዜ ትኩረትሽን ወደእኔ ለመመለስ ያስቸግራል። ግን ታማኝ ስለሆንሽ ልወቅስሽ አልፈልግም።"

(ክሌር):- ጌታ ህዝቅኤል ኸርት ድዌለርስ ስለደከሙና ሃሳባቸው በሌሎች ነገሮች ስለተያዘ ምላሽ እየሰጡህ እንዳልሆነ ነግሮኛል። እባክህ ንገረኝ ይህ እውነት ነው?

ኢየሱስም "ግማሽ በግማሽ ትክክል ነው ልንል እንችላለን።"

(ክሌር) :- ታድያ ከህዝቅኤል የተቀበልኩት አመፃን የሚያመለክተው ንባብስ ?

"ምክንያቱም አብዛኛዎቹ "በተለመደው መልኩ" ወደ ቤተክርስቲያን እየሄዱ ነው። ቤተክርስቲያንም በፊታቸው እየፈራረሰች ትሄዳለች። ብዙዎቹ ደግሞ በፊታቸው ምን እየተከናወነ እንደሆነ ምንም ግንዛቤው የላቸውም። ቤተክርስቲያንም ከዚህ በኋላ "ቤተክርስቲያን" ሆና ለብዙ ጊዜ አትቀጥልም። በስደት ወይም በመጥፎ ድርጊት አሉባልታ የተነሳ የበለጠ እየተንኮታኮተች ትሄዳለች። ከንጥቀት በኋላ ደግሞ እንደተለመደው ዓይነት "ቤተክርስቲያን" አይኖርም፡፡ እስከ ጭራሹም አይኖርም ። በእሳት ውስጥ የነበሩ ወደ ቤታቸው ሲወሰዱ ያልቆረጡት ልጆቼ ግን "ለምን? ለምን እኔ አልተወሰድኩም የሚሉትን ከባባድ ጥያቄዎች እየጠየቁ እዚሁ እንዲቆዩ ይደረጋሉ።

"እንግዲህ ይህ ለምን እንደሆነ እኔ ልነግራችሁ ነው። ይሄ መልዕክት በጣም አስፈላጊ ነው።

"ለመሆኑ መንገድ ላይ ያሉትን ድሃ ቤተሰቦችና ሰዎችን ለመርዳት ሰዓታችሁንና ገንዘባችሁን የሰጣችሁት የመጨረሻው ጊዜ መቼ ነበር? ሌሊቱን በሙሉ በፀሎት ያሳለፋችሁትስ? በሳምንት ውስጥ ለብዙ ቀናት በቀን ለሁለት ሰዓት በፀሎት ያሳለፋችሁት የመጨረሻ ቀንስ? ህሊናችሁን ለመመርመር ጊዜ ሰጥታችሁ እናንተ ያሰራጫችሁትን አሉባልታ እና ሃሜት ህሊናችሁ ውስጥ ያገኛችሁት መቼ ነው?

"መርምራችሁ እናንተ ውስጥ ራስ ወዳድነት እንዳለ የተረዳችሁትስ መቼ ይሆን? እንዳውስ እነዚህን ነገሮችስ ትመረምራላችሁ? ምንም ጥፋት ሳይገኝበት ሃሜት የደረሰበትን ሰው የተከራከራችሁለትስ መቼ ነው? ከእናንተ በታች ነው ብላችሁ ያሰባችሁትን ሰው በንቀት ስሜት የተመለከታችሁትስ? በአንድ ሥራ ተጠምዳችሁ ቢሆንም እንኳን አንድ ሰው ትኩረት እንድትሰጡት በመፈለጉ ሥራውን አቁማችሁ ሰዓታችሁን የሰዋችሁት መቼ ነበር?"

“ነፍሳችሁን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በማድረግ ውስጣችሁን በመፈተሽ ማድረግ ያለባችሁን ነገር ግን ያላደረጋችሁት፤ እንዲሁም ማድረግ ያልነበረባችሁ ነገር ግን ያደረጋችሁት ነገር አግኝታችሁ በመፀፀት ንስሐ የገባችሁት መቼ ነበር?

"በዚህ ዓይነት ምርመራ የነፍሳችሁ ሁኔታ በአግባቡ ብትመለከቱ “ለምን ሳልነጠቅ ቀረሁ” ለሚለው ጥያቄያችሁ በፍጥነት ምላሽ ታገኛላችሁ።

"ነገሮችንስ ስታደርጉ የምታደርጉት ለታይታ ወይም ለሙገሳ ብላችሁ ነው? ወይንስ እኔ እንድታደርጉልኝ የጠየኳችሁን ነገር ምንም የሰው ዕይታ ውስጥ ባይገባም እየሰራችሁ ነው? በመንግስተ ሰማያት የትንንሽ ነገሮች ድምር ዋጋ እንዳለው ይህንን ቃል እገባላችኋለሁ። እኔ ሰው የማያየውን አያለሁ። በተለይም ሁኔታው ለእናንተ ሳይመች በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች የራሳችሁን ምቾት በመተው ስለምታደርጓቸው ነገሮች ሁሉ እኔ በልዩ ሁኔታ እመለከተዋለሁ። ይህ መስዋዕት ነው፡፡

“በራስ ወዳድነት የተነሳ አንድ ሥራን ለመጨረስ እየሰራችሁ ነው? ወይንስ እሱን ትታችሁ ለተጎዱ እርዳታን እየሰጣችሁ ነው?

"ይህንን ስናገር ክሌር ምን እያልኩ እንደሆነ በደንብ ትረዳለች፡፡ ምክንያቱም በትዕግስትና በበጎ አድራጎት ዙርያ እያለማመድኳት ስለነበር ነው። አብዛኛውን ጊዜያት እርሷ መልእክቶችን በማዘጋጀት፣ ስዕል በመሳልና መዝሙሮችን በማዘጋጀት ወይንም በራሷ ጉዳይ ላይ ተጠምዳ ስለምትገኝ ህዝቅኤልን ለእርዳታ አነሳሳዋለሁ ።

“አዎ የኔ ፍቅር ይህንን አደርግ የነበረው ሆን ብዬ ነበር።

"ስልኩን ከማንሳትሽ በፊትና ካነሳሽው በኋላ ፣ እንዲሁም እርዳታውን ስታደርጊና ከዛም ተመልሰሽ ስትመጪ ያለሽን ዝንባሌ እመለከተዋለሁ። እናም አብዛኛውን ጊዜ በጥሩ ትወጪዋለሽ። ይህም ያደረግሽው ነገር ለእኔ የሚያስፈልገኝን ክብካቤ ማድረግሽ እንደሆነ ስለተረዳሽ ነው። ስራሽም በማቋረጡ ተበሳጭተሽ ሳይሆን ጣፋጭና በጎ አድራጊ ለመሆን ባለሽ ቆራጥነት ነበር።

"እነዚያ ለንጥቀት ዝግጁ መሆንሽን የማረጋግጥበት ፈተናዎች ናቸው።

"ውዶቼ ይህንን ለሁላችሁም የማደርገው ይሆናል። የሙሽራዬ ክብካቤ በምፈልግበት ሰዓት ሁሉ ከጎኔ እንደምትሆን ለማረጋገጥ በተደጋጋሚ የምፈትንበት ይሆናል። አሁን እንዳለሁት ሆኜ ወይንም በሌላ ሰው ተመስዬም ብመጣ ማለት ነው። ሙሽራዬ በእኔ ጉዳይ ላይ ብቻ ሆና መመልከት እፈልጋለሁ። እናም በጭንቅ ውስጥ ያሉ ነፍሳት ካሉ እኔም አብሬያቸው በዚያው ነኝ። ሁላችሁም ከልባችሁ በመነጨ ቸርነት፣ እንግዳ ተቀባይነትና እንከን በሌለበት የልብ ደስታ እንድትመልሱላቸው እፈልጋለሁ። ይህ ነው ለእኔ ትልቅ ምቾት የሚሰጠኝ።

"አዎ ሁላችሁም ከእኔ የተቀበላችሁትን ሥራ እየሰራችሁ በመሆኑ በእያንዳንዳችሁ ደስተኛ ነኝ። ሆኖም ግን የልባችሁን ዝንባሌና ቅድሚያ የምትሰጡት ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ እፈልጋለሁ። ከእኔ እንኳን የተቀበላችሁትን አንድ የምትወዱትን ሥራ በመተው ለአንድ ለተጠማ ልጅ ውሃ ትሰጣላችሁ?

"እነዚህ የዘመን ማጠቃለያ የፈተና ውጤት ወረቀቶች ማለት ትችላላችሁ። ይህንንም ፈተና በምድር ላይ በሚገኘው የወንድማማቾች ፍቅር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የተማራችሁት ትምህርት በደንብ እንደገባችሁ ለማረጋጋጥ የሚሰጥ የመጨረሻው

ፈተና ልትሉት ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ነው በትክክል በእናንተ ላይ እያደረኩ ያለሁት። በጣም በትኩረት ስትሰሩት የነበረውን ሥራ በመተው አንድ የሚፍጨረጨር ሰውን ትረዳላችሁ? እንዲሁም ቀብር ወይንም ሰርግን ትሳተፋላችሁ?

"ፀሎታችሁስ ምን ያህል በጥልቀት ነው?"

ጌታ ሆይ ይህንን በተመለከት እኔ አሁን መጥፎ ደረጃ ላይ ነኝ፡፡

"ጥሩ ሌላው ቢቀር እንኳን ይህንን ተረድተሻል ደግሞም ለመቀየር ትፈልጊያለሽ

(ክሌር)፦ ውዶች፣ እኔ አሁን የእግዚአብሔር አብን ምስል ሰርቼ ልጨርስ ተቃርቤያለሁ፡፡ እናም እንዴት አድካሚ እየሆነ እንደመጣ ለመንገር ይከብደኛል። ይህም የሆነበት ምክንያት ስህተት ሰርቼ ያንን ማስተካከል ስለነበረብኝ ነው፡፡ ስህተቱን ለማረም ደግሞ ከሥር መሰረቱ በማጥፋት እንደገና እንደ አዲስ መጀመር ነበረብኝ። ያውም የተሳሳትኩት ደግሞ አይኑን ነው!

እናም ኮምፒውተሬ ሲቃጠል ኢሜል ለመላክ እንኳን የሚከብዱ ችግሮችን ይዞብኝ መቷል እንኳንስ የመቅጃ ፕሮግራሜን ሊያስነሳው ይቅርና።

ኢየሱስም እንዲህ በማለት ቀጠለ፦ "ክሌር እነዚህ የማጠቃለያ ፈተናዎች ናቸው። እያንዳንዱ ሰው ያልተለመደ ዓይነት የሃሳብ መበታተንና ችግሮች እየገጠመው ነው። ምክንያቱም የልቤን ሐሳብ ማን እንደሚያውቅና ማን ተግባርያዊ እንደሚያደርገው እያየሁበት ነው። የልቤን ሐሳብ አውቀው የሚያደርጉት እነርሱ የሚነጠቁ ይሆናሉ፡፡ ሌሎቹ ግን እስካሁን በያዙት ሥራ በመደናገጥ ውስጥ ተደብቀው ትተዋቸው የሚሄዱትን ሰዎችና ሁኔታዎችን ትቶ ለመሄድ የፀፀት ባቡርን ተሸክመው ያሉ ናቸው፡፡ የተወደዳችሁ ለእናንተ ግን የቀረው ጊዜ በጣም ጥቂት ነው። ስለዚህም ንሰሃ ግቡና ለውጥን አድርጉ። ከእናንተ ፍላጎት በላይ የእኔን የልብ ፍላጎት ፈፅሙ።

"ይህ ድርጊት ከኩራት ትምህርት ጋር የተሳሰረ ነው። አዎ ኩራት እንዲህ ይላል "እኔ አሁን እየሰራሁ ያለሁት ሥራ እግዚአብሔር የሰጠኝ ሥራ ስለሆነ ይህንን ትቼ የአንተን ጉዳይ ያውም ራስህ ልትፈፅመው የሚገባህን ነገር ለማገዝ ብዬ የያዝኩትን ትቼ ልመጣ አልችልም፡፡" ይህ በሌላ አነጋገር "እግዚአብሔር የሚፈልገው ነገር ከአንተ ችግርና ጭንቀት ይበልጣል" እያላችሁ ነው።

"ለእናንተ ይህ አይሆንም እላችኋለሁ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ እኔ የምፈልገው ጉዳይ አይበልጥም። ትኩረት የሚስቡ ነገሮችን በመተው በሙሉ ልባችሁ ምላሽ የምትሰጡበት ጊዜ አለ። ቸርነትና የመንፈሴ ሹክሹክታ ይህንን ለመለየት እንድትችሉ ይረዳችኋል።

(ክሌር)፦ ጌታ ሆይ በዚህ እኔ ተጠያቂ የሆንኩ ይመስለኛል።

ኢየሱስም መለሰ ፦ "የሚረዳሽ አጥተሽ ስለምታውቂ ሌሎችን ከማትረጂበት ጊዜ የበለጠ የምትረጂበት ጊዜ ይበልጣል። እኔ የምናገረው ከእናንተ መካከል ራሳቸውን በመውደዳቸው የተነሳ ሌሎችን ያለመርዳትን ልምድ ያደረጉትን ነው። እኔ እያወራሁ ያለሁት ችግራቸው ተስፋ በማስቆረጥ እናንተን ስለሚፈልጉት ችግረኞች ነው። እነሱን ወደ እናንተ የላኳቸው ልፈትናችሁ ነው። እኔ ለእናንተ ያለኝን ፍቅር በሌሎች ላይ ስታፈሱት በተግባር ማየት እፈልጋለሁ።

“በእኔ ለመሞላት የሚያስፈልጋችሁን ጊዜ ከእኔ ጋር ስለማታሳልፉ ልባችሁ ቀዝቃዛና ምላሽ የማይሰጥ ሆኗል። የሌላችሁን ልትሰጡ ስለማትችሉ በአጠገባቸው ዝም ብላችሁ ታልፋላችሁ። ወይንም ለሌሎች ታስተላልፏቸዋላችሁ። ልጆቼ የመንግስተ ሰማያት መለኪያ ከእናንተ መለኪያ እጅግ ይለያል። ህመም እስኪሰማችሁ ድረስ ማፍቀርን መማር አለባችሁ።

(ክሌር):- አሁን ዕረፍት ለመውሰድ መነሳት ነበረብኝ። ከድካሜ የተነሳ ኮምፒውተሩ ላይ ልተኛ ነው። በመታጠቢያ ቤት ቆይታዬ ለሙሽራዬ የፍቅር ደብዳቤዎች ቁጥር 1 የሚለውን መጽሐፍ ለመክፈት ውስጤ አነሳሳኝና ይህንን ምዕራፍ አገኘሁ።

1 በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ።2 ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ። 3 ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።4 ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤5 የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤6 ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤7 ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።8 ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።9 ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ 10 ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል። 11 ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አስብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ። 12 ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ። 13 እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።(1ኛ ቆሮንቶስ 13:1-13)

ከዚያም በኋላ ያለው ክፍል የሚናገረው ሰው ሁሉ የሚመኘውንና ጎልቶ የሚታይ ክርስቲያን ያደርገናል ብለን የምናስባቸውን ስጦታዎች ነው፡፡

ነገር ግን ትንቢት ቢሆን የሚቀር ነው፡፡ ልሳንም መናገር ገደብ አለው፡፡ እውቀትም ቢሆን ኃላፊ ነው፡፡ ምክንያቱም የምናውቀውና የምንተነብየው ከፊሉን ነው፡፡ፍፁሙ የሆነው በመጣ ጊዜ ግን ከፊሉ ይሻራል፡፡ አሁን የምናየው በመስታወት እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፡፡ በኋላ ግን ፊት ለፊት እንተያያለን፡፡ አሁን የማውቀው በከፊል ነው፡፡ በኋላ ግን እኔ እንደምታወቅ ያህል በሙላት አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሦስቱ እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ፀንተው ይኖራሉ፡፡ ከሁሉ የሚበልጠው ግን ፍቅር ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ በማለት ቀጠለ:- "ለንጥቀት የምትዘጋጁት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመፅሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም እየተጋጫችሁ፣ የመሪነትና የአስተማሪነት ቦታን ለማግኘት በመሻኮት፣ ኮንፈረንሶችን በማዘጋጀትና በፕሮግራሙ ላይ የእናንተን ያህል ማድረግ ያልቻሉትን በክፋት እየፈረዳችሁባቸው ንግግር በማድረግ ከሆነ፣ በንጥቀት ጊዜ ትልቅ ሐዘን ይገጥማችኋል። በአለም ዕይታ ምንም ያልነበሩ ሲነጠቁ እናንተ ግን ፍቅርን፣ ርህራሄን፣ ይቅር ባይነትንና የተዋረደ ነፍስ ማክበርን እንድትማሩ በምድር ትቀራላችሁ። ምክንያቱም የተዋረዱ ነፍሳት የተገዙት በእኔ ደም በመሆኑ ደግሞም በውስጣቸው ስለምኖር ነው።

(ክሌር):- ውዶች በኮንፍረንስ ላይ ንግግር ለማድረግ እየሄድኩ እያለሁ ሽባዎችንና ድሆችን በንቀት መልክ በአጠገባቸው ባልፍ በንጥቀት ዕለት ምን ዓይነት ሽልማት የሚጠብቀኝ ይመስላችኋል? ጌታ ቀራጮችና ኃጢያተኞች፣ ራሳቸውን ፃድቅ አድርገው ከሚመለከቱት ይልቅ ወደ መንግስተ ሰማያት በመግባት ይቀድሟቸዋል ብሎ የለም ?

በሌላ አንፃር ደግሞ አንድ ድሃ የሆነ ሰው ወደ ኮንፈረንሱ እየሄደ እያለ በመንገዱ ላይ አንድ የተጨነቀ ሰው አግኝቶ ኮንፈረንሱ ላይ ዘግይቶ ቢደርስ ጥሩ መቀመጫ እንደማያገኝ እያወቀ ቆም ብሎ ለሰውዬው በርገርና የሚጠጣ ቢገዛለት ይህስ ሰው ሽልማቱ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

እኛ ነገሩን ገለባብጠነዋል፡፡ እናም ጌታ የቤተክርስቲያን ህንፃዎችን ገልብጦ ውስጡን ባዶ ለማድረግ ሥራውን ጀምሯል። ምክንያቱም እርሱ የሚፈልገው ከእያንዳንዳችን ጋር ንፁህ የሆነና የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረን ነው። እርሱ የሚፈልገው ጥርት ብሎ የሚሰማውን ስብከት እንድንሰማና በዚህም የሰንበትን ህግ ፈፅመናል ብለን እንድንረካ አይደለም፡፡

እኔና ህዝቅኤል ላለፉት ብዙ ሳምንታት ትላንትናን ጨምሮ በተደጋጋሚ ሲደርሱን የነበሩ ንባቦች እነዚህ ነበሩ፡፡

(ህዝቄኤል 2፡1-4) 1 "እርሱም እንዲህ አለኝ “የሰው ልጅ ሆይ ተነስና በእግርህ ቁም እኔም እናገርሃለሁ አለኝ፡፡ 2 በተናገረኝም ጊዜ መንፈስ ገባብኝ በእግሬም አቆመኝ፣ የሚናገረኝንም ሰማሁ፡፡ እርሱም እንዲህ አለኝ 3 የሰው ልጅ ሆይ፥ በእኔ ላይ ወደ ዐመፁ ወደ ዓመፀኞች ሰዎች ወደ እስራኤል ልጆች እልክሃለሁ። እነርሱና አባቶቻቸው እስከ ዛሬ ድረስ ዐመፁብኝ። 4 እነርሱ ፊታቸው የተጨማተረ ልባቸውም የደነደነ ልጆች ናቸው። እኔ ወደ እነርሱ እልክሃለሁ፤ አንተም። ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በላቸው።"

ትኩረቴን የሳበው ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ ያለው የመዝሙር ክፍል ነው።

(መዝሙር 123፡1-4) 1 በሰማይ የምትኖር ሆይ፥ ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ። 2 እነሆ፥ የባሪያዎች ዓይኖች ወደ ጌታቸው እጅ እንደ ሆኑ፥ የባሪያይቱም ዓይን ወደ እመቤትዋ እጅ እንደ ሆነ፥ እንዲሁ እስኪምረን ድረስ ዓይናችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ነው። 3 ማረን፥ አቤቱ፥ ማረን፤ ንቀትን እጅግ ጠግበናልና፤ 4 የባለጠጎች ስድብና የትዕቢተኞችን ንቀት ነፍሳችን እጅግ ጠገበች።

(ክሌር):- ይህ በጣም አስደሳች ነው። ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚናገረው ለልቤ ነው። ድሆችና ታማኞች ትኩረታቸው በጌታ ፊት ላይ፣ በፍላጎቶቹ ላይና ምን እያደረገ እንደሆነ ነው፡፡ ሃብታሞቹ ግን በካባድ ንቀት ተሞልተዋል።

እናም ይህንን መጠየቅ አለብኝ። ለመሆኑ ስንቶች ናቸው የንጥቀትን ቀን በእውነት እየተጠባበቁ ያሉ? ምን ያህሉስ ናቸው በአለም ጉዳይ ተወጥረው "የምገዛው ቤት አለ፣ የምንከባከበው ትዳር አለ፣ አዲስ የገዛሁትን መኪና መውሰድ አለብኝ፣ ምንም ነገር ተፈጥሮ ለማያውቅና ለዚህ ለማይረባ ትንቢት ጊዜ የለኝም፡፡" ብለው የሚናገሩ?

ስንቶቻችን ነን እነሱ ለተናገሩት ንግግር እና ዝንባሌ ፀጥ ባለ የፀሎት ጊዚያችን ምላሽ የምንሰጠው? ወይንም በልባችን "እውነቱን ነው፣ ምንም አልተፈጠረም" ብለን የምናስበው?

(ክሌር):- እናም በጌታ ራት ጊዜ ያነበብነው የመጨረሻው ክፍል የደቀመዛሙርቱን እግር ማጠብ የሚለው ክፍል ሲሆን እኛም ዝቅ ብለን ሌሎችን መርዳትና መታዘዝ እንዳለብን ምሳሌ እንዲሆነን ተብሎ ነው። በአጭሩ ንባቦቹ በሙሉ ጌታ ከተናገረኝ ጋር አንድ ነበሩ። በዚህ ሰዓት ወደጌታ ዞር ብዬ ጌታ የምትጨምረው ነገር አለ ብዬ ጠየኩት።

ጌታም እንዲህ አለ :- "እነሆ የአገልጋዮቹ አይኖቻቸው የጌታቸውን እጅ እንደሚመለከቱ፣ ፣ እንዲሁም የሰራተኛዋ አይን የእመቤትዋን እጅ እንደሚመለከት እንዲሁም የእኛ አይኖች ወደ ጌታ አምላካችን ይመለከታሉ።"

"በእውነቱ ከሆነ ከእናንተ የምፈልገው ይህንን ነው። በምንም ሰዓት ላይ አይናችሁን በእኔ ላይና እኔ በማደረገው ነገር ላይ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በአሁኑ ሰዓት መቅሰፍትን የሚከለክል በቂ ፀሎት እየተደረገ አይደለም። የኔ ውዶች ከእናንተ ብዙ ፀሎትን እፈልጋለሁ። ጥልቀት ያላቸውና የበለጠ ትኩረት ያላቸው ፀሎቶችን እፈልጋለሁ። እንዲሁም እያንዳንዱ ለእኔ የምትከፍሉት መስዋዕት ከመንግስተ ሰማያት የተትረፈረፈ ቅባቶችን ያዘንብላችኋል፡፡ ይህም ቅባት ለእናንተ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ፍላጎት የሚተርፍ ነው፡፡።

“ጊዜው እየሮጠ ነው። አሁን ያለነው ገና በአደጋው ክልል ውስጥ ብንሆንም ብዙዎቻችሁ በፆምና በፀሎት በጣም ደክማችኋል። ለእናንተ ይህንን እላለሁ ለእኔ የከፈላችሁት መስዋዕት አንዱም ዋጋ ቢስ አይሆንም። በጣም ሲደክማችሁ ራሳችሁን በሃይል አትግፉት። እንዳውም እረፍት አድርጉና አገግሙ። ከዛም እኔ እንደገና አስነሳችኋለሁ፡፡ በተለይም ሥጋ ወደሙን ከወሰዳችሁ በኋላ ጥረታችሁን እንደገና ትቀጥላላችሁ።

"ራሳችሁን የማትበገሩና የማትሞቱ አድርጋችሁ በማሰብ አትሳሳቱ። እናንተም ብትሆኑ ማረፍ አለባችሁ።

"በዚህ የዕረፍት ጊዜያችሁ ግን እኔን ፈልጉኝ። ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል በሬማ ቃል ወይንም ከኸርት ዱዌለርስ ድረገፅ ሬማ (Heartdwellers.org) ፈልጉኝ። ትኩረታችሁን በእኔ ላይ አድርጉ። ምንም እንኳን ትንሽ ዕረፍት ለነገሮች ያላችሁን ትክክለኛ ዕይታ ቢያስተካክልም ብዙ በመዝናናት ጊዜያችሁን አታባክኑ።

"ከምንም በላይ እየተፈጠሩ ያሉ እነዚህ ሁኔታዎች ከሸፈው የሰዎች ልብ ወደ እኔ እንዲመለስ ከልባችሁ ፀልዩ። ሙሽሮቼ እንኳን ለእኔ ለቅሶና ጭንቀቴ ስሜት አልሰጣቸውም፡፡ እኔን ቅር ያሰኘኝ ይህ ነው፡፡ ጌታቸው እጅግ በሚፈልጋቸው በዚህ ወቅት እነርሱ አይኖቻቸውን ከጌታቸው እጅ ላይ አንስተዋል፡፡

"ውዶቼ እባካችሁ ትኩረታችሁን፣ ፀሎታችሁን እና ፍቅራችሁን እፈልጋለሁ። ፍቅራችሁንም ለታናናሾች የሚያስገልጋቸውን በማሟላት ወይም የምግብ ፍላጎታችሁን በመግታት ብታሳዩኝ! ምንም ነገረ ለእኔ ብላችሁ የምታደርጉትን ነገር ለሙሽራችሁ ያላችሁን ፍቅር መግለጫ በማድረግ የሰርግ ቀን ስጦታ አድርጌ እቆጥረዋለሁ። ይህንንም ደግሞ እጅግ የማደንቀው ይሆናል፡፡

"ስለዚህ የተወደዳችሁ ይህንን እጠይቃችኋለሁ። ራሳችሁን ትሁት አድርጉ። ልምዶቻችሁንና ዝንባሌዎቻችሁን መርምሩ። ስህተት ለሆኑ ሥራዎቻችሁ ሁሉ በመላዕክቶቹ ፊት ንስሃ ግቡ። ለሌሎች ስትሉ ከመንገዳችሁ ወጥታችሁ በጎ አድርጉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ፍላጎቴን ለመፈፀም ትችሉ ዘንድ ልባችሁን አለዝባችሁ ዕይታችሁን በእጄ ላይ አድርጉ፡፡

"እያንዳንዱን ያሳለፋችሁት ደቂቃ ቅድሚያውን ለእኔ በመስጠት ከእኔ ጋር አንድ በመሆን ተጉዛችኋልና በንጥቀት ጊዜ ትወሰዳላችሁ። ይህም የእኔ ምርጥ ውዶች ያደርጋችኋል። እናም በሰርግ ድግሴ ላይ ሥፍራን አዘጋጅላችኋለሁ። እነዚህን ነገሮች አድርጉና 'የኔ ታማኝና መልካም አገልጋይ ጥሩ አድርገሃልና ወደ ጌታህ ደስታ ግባ' የሚለውን ትሰማላችሁ።"